# የስኬታማ አገልግሎት መርሆዎች

Principles of Effective Ministry

ከበደ በከሬ

# የስኬታማ አገልግሎት መርሆዎች

**Principles of Effective Ministry**

## ከበደ በከሬ


አሳታሚ፡- ጌጃ ቃለ ሕይወት ሥነጽሑፍ አገልግሎት
ፖ.ሣ.ቁ.698 ፤ስልክ 76 33 28/ 76 98 30
E-mail hiwotlit@ethio.net.et

መጋቢት 1997 ዓ/ም

© Kebede Bekere, 2005

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::
All Rights Reserved.
Published by Heywet Literature
P.o.Box 698
E-mail hiwotlit@ethio.net.et
Addis Ababa, Ethiuopia

የኮምፒውተር ለቀማ:- ዘውዲቱ በቀለ

## ምሥጋና

ከሁሉም በማስቀደም ይህን መጽሐፍ እንድጽፍ ለረዳኝ ለጌታ ለእግዚአብሔር ክብር ምሥጋና ይድረሰው:: የሁልጊዜ ድጋፋቸው ሳልተለየኝ ለቤተሰቦቼ ልባዊ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ:: እንዲሁም ውድ ጊዜያቸውንና እውቀታቸውን በመስጠት የዚህን መጽሐፍ ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየትና እርማት ለሰጡኝ ለወንድም ኤርምያስ አበበ፣ ለወ/ሮ ኃይሉ ቸርነት፣ ለፓስተር ስለሺ ከበደ፣ ለአቶ ግርማ፣ ለአቶ በድሩ ሁሴን፣ ለፓስተር ቀልቤሳ ሙለታ፣ለወ/ሮ ውድነህ እንዳይላሉ የእግዚአብሔር በረከት ይብዛላቸው እላለሁ::

# ማውጫ


ገጽ

መግቢያ 4

## ክፍል አንድ፡ የአገልግሎት ጥሪና ዝግጅት

1. የአገልግሎት ጥሪ ምን እንደሆነ ማወቅ.....6
2. የአገልግሎት ጥሪ ዓይነቶችን ማወቅ.....10
3. የአገልግሎት ጥሪ እንዴት እንደሚመጣ መገንዘብ.....16
4. ለአገልግሎት ምን ዓይነት ሰው እንደሚጠራ ማወቅ.....22
5. እግዚአብሔር ሰዎችን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚጠራ ማወቅ.....28
6. የጥሪ መለያ ምልክቶችን አጥርቶ መለየት.....32
7. ለአገልግሎት መዘጋጀት.....51

## ክፍል ሁለት፡ የአገልጋይ ሕይወት እና አገልግሎት

8. ለአገልግሎት መሾም.....60
9. የአገልግሎት ስጦታን መለየት.....64
10. የአገልጋይ ሕይወትና አገልግሎት ምሳሌዎችን በማወቅ መከተል...68
11. በአገልግሎት ጊዜ ቅድሚያ ለምን እንደሚሰጥ ማወቅና ማድረግ.....80
12. የአገልጋይ መልካም ባህርያትን መከታተልና መኖር.....96
13. የአገልጋይ ተግዳሮቶችን ማወቅና በጸጋው መጋፈጥ.....108
14. የአገልጋይን ብድራት ትኩር ብሎ መመልከት.....115

# መግቢያ

እግዚአብሔር ሰዎችን ጠርቶ ለአገልግሎት እንደሚያሰማራቸው የታወቀ ነው። ይሁን እንጂ ማን በእርግጥ እንደተጠራና ማን እንዳልተጠራ ለይቶ ማወቅ የሚቻል ቢሆንም የማወቁ ሂደት በጣም አስቸጋሪ ነው። አንዳንድ ጊዜ እንኳን የሌሎች ሰዎችን የአገልግሎት ጥሪ ማወቅ ቀርቶ የራሳችንም ቢሆን "በእርግጥ እግዚአብሔር አገልጋይ እንድሆን ጠርቶኛል ወይስ...?" የሚለውን ጥያቄ መመለስ ከባድ ይሆናል። የአገልግሎት ጥሪ ከእግዚአብሔር መሆኑን ማረጋገጥ እጅግ ከባድ እንደሆነ እኔም በሕይወቴ አይቻለሁ። ገና ማንም ሰው ለመሆን የሚመኘውን ለመሆን ዕድል እያለኝ አንድም ነገር ሳልሞክር የጠራኝ እግዚአብሔር ነው ወይስ ሌላ ነገር? ያልኩበት ወቅት ነበር። ጥሪው በእርግጥ ከእግዚአብሔር መሆኑን ለማወቅ እጅግ ፈታኝ ጊዜያትን አሳልፌአለሁ። ይህ የእኔ ብቻ ሳይሆን የብዙዎች ልምምድ እንደሆነ አስባለሁ። የአገልግሎት ጥሪ ሲወራ እንጂ በሕይወት ሲተገበር በቀላሉ መለየት ያስቸግራል።

ጥሪው ከእግዚአብሔር መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ ተጠርቻለሁ ማለት ብቻ በቂ አለመሆኑ ይከተላል። እግዚአብሔር ምን እንድሠራ? የት እንዳገለግለው ጠራኝ? የሚሉት ጥያቄዎች ደግሞ ምላሽ ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር እንደጠራኝ ደግሞ እንዴት ለሌሎች ሰዎች በተለይም ለቤተክርስቲያን መሪዎች መናገር እችላለሁ? ባያምኑኝስ ምን አደርጋለሁ? የሚሉና ሌሎች ጥያቄዎችም ጥሪን ውስብስብ ያደርጉታል። እነዚህን ጥያቄዎች በተመለከተ ትክክለኛ መልስ የምናገኘው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነው። ከእኛ በፊት የነበሩ ሰዎች እንዴት ተጠሩ? ጥሪን እንዴት አስተናገዱ? የሚሉትን ነጥቦች መመልከቱ መልካም ነው። የተጻፈው ለትምህርታችን ነውና ከእነርሱ ሕይወት ለራሳችን የምንማራቸው መሠረታዊ አሳቦች አሉ። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በተለየ ሁኔታ ቢጠራም መሠረታዊ አካሔዶቹ ተመሳሳይ ናቸው።

አገልግሎት በጥሪ ይጀምር እንጂ ሂደቱ ረጅም ነው። አንድ ሰው ጥሪው ከእግዚአብሔር መሆኑን ካረጋገጠ በኋላ ወደተጠራበት የአገልግሎት መስክ ከመሠማራቱ በፊት መዘጋጀት አለበት። ለውትድርና መመልመል ማለት ወታደር መሆን ማለት አይደለም። ምልመላ ወደ ሥልጠና መግቢያ በር ነው። ወታደር መሆን በአስቸጋሪ ሥልጣና ውስጥ ማለፍን ግድ ይላል። አንዳንድ ምልምሎች ወደ ውትድርና ሳይደርሱ በሥልጠናው ወቅት ይሰናበታሉ። የጸኑ ደግሞ ወታደር ይሆናሉ። በተመሳሳይ መልኩ ዝግጅት ከአገልግሎት ይቀድማል። በጥሪ ደስ የተሰኙ ሰዎች ሥልጠና መኖሩን ሲሰሙ ወይም የሥልጠናው ጊዜ ሲራዘምባቸው ተስፋ ቆርጠው ጥሪውን እምቢ ይላሉ። ሌሎች ደግሞ ሥልጠናውን አቋርጠው ቶሎ በአቋራጭ ወደ አገልግሎት ይገባሉ። የመጀመሪያው ስህተት አለመታዘዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ያለበቂ ዝግጅት መሰማራት ስለሆነ የአገልግሎቱ ስኬታማነት ያጠራጥራል። አገልጋይ ከተጠራ በኋላ የሚያደርገው ዝግጅት ወይም ሥልጠና ምንድነው? ዝግጅቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስድበታል?

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የአገልግሎት ጥሪ ኖሮት ጥሪውን ካረጋገጠ በኋላ የሚቀጥለው ምዕራፍ በአገልግሎት መሰማራት ነው። የተጠራና የተዘጋጀ አገልጋይ ወደ አገልግሎት መስክ ይገባል። ወደ አገልግሎት ለመግባት መጠራትና መዘጋጀት ብቻ በቂ ናቸው ወይስ ሹመት ያስፈልጋል? አንድ ሰው ሳይሾም በሙሉ ጊዜ አገልግሎት ማገልገል አይችልምን? ሹመት ምን ጥቅም አለው?

አገልጋይ በአገልግሎት ላይ ከተሰማራ በኋላ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ደረጃውን የጠበቀ መንፈሳዊ ሕይወትና መልካም ባህርያት ሊኖሩት ይገባል። ለመሆኑ እነዚህ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊኖራቸው የሚገቡ መልካም ባህርያት ምንድናቸው? አገልጋይ እግዚአብሔርን ቢያገለግልም ሕይወቱና አገልግሎቱ ከተግዳሮት የነጻ አይደለም። ብዙውን ጊዜ ምዕምናን በሚቸገሩበት ተመሳሳይ ችግር አገልጋይም ሲቸገር ይታያል። አገልጋይን የሚገዳደሩ ወይም የሚፈታተኑ ተግዳሮቶች ወይም ፈተናዎች ምንድናቸው? አገልጋይስ እንዴት አድርጎ እነዚህን ተግዳሮቶች መቋቋም ወይም ማሸነፍ ይችላል?

አገልጋይ እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ የተጠራበትን አገልግሎት እንደሚገባ ቢያገለግል ብድራቱ ምንድነው? አገልጋይ ብድራቱን የት ያገኛል? ጥሩ ደመወዝ የአገልጋይ ብድራት ሊሆን አይችልምን? የአገልጋይን ፍሬያማነት ገምግሞ ብድራቱን የሚተምንለትስ ማንነው?

ይህ መጽሐፍ በክፍል አንድ ውስጥ በአገልጋይ ጥሪና ዝግጅት ዙሪያ የሚነሱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ሚዛናዊ ምላሽ ለመስጠት ይሞክራል። ይዘቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሆኖ የሀገራችንን የአገልጋዮች የጥሪ ሁኔታና ዝግጅት የሚዳስስ ስለሆነ ያለንበትን ሁኔታ ይበልጥ ለመረዳት እና መፍትሔ ለሚሹ ጉዳዮችም ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ያግዛል።

በክፍል ሁለት ከአገልግሎት ጅማሬ ጀምሮ በአገልጋይ ሕይወት እና አገልግሎት ዙሪያ የሚነሱትን ከላይ የተጠቀሱትን እና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በማንሳት ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ሚዛናዊ ምላሽ ይሰጣል።

በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ ለሚያነቡት ሁሉ እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያለውን ዕቅድ እንዲመለከቱ፣ እንደሚያደርግና ለጌታ ኢየሱስ ጥሪ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጡ እንደሚያግዛቸው እምነቴ ነው። እንደዚሁም በሀገራችን ያለውን የአገልጋይ ሕይወትንና አገልግሎት በማጉላት አገልጋዮችም ሆኑ የሚያስማሩአቸው መሪዎች ራሳቸውን እንዲያዩ ይረዳል። በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች በአገልጋይ ሕይወትና አገልግሎት ዙሪያ ለሚሰጡ ኮርሶች የማስተማሪያ መጽሐፍ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በመጨረሻም ይህን መጽሐፍ ለምታነቡት ሁሉ እግዚአብሔርን በትክክል ለማገልገልና ለበረከት ይሁንላችሁ እላለሁ! አሜን!

ከበደ በከሬ

1997 ዓ.ም

# ክፍል አንድ: የአገልግሎት ጥሪና ዝግጅት

## 1

## የአገልግሎት ጥሪ ምን እንደሆነ ማወቅ

እግዚአብሔር ሰዎችን ለሥራው የሚጠራ አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል አምላክ ሆኖ ሳለ በዚህ ምድር የሚሠራውን ተግባር ከሰዎች ጋር ሆኖ መሥራትን ይፈልጋል። ይህ የሚያስደንቅ የእግዚአብሔር አሠራር ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ከእርሱ ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች እንዲሆኑ ይሻል። ለዓላማው ስኬታማነት ሰዎችን ይጠራና ያሰማራቸዋል። እግዚአብሔር የሚጠራና የሚያሰማራ የማንኙነትም አምላክ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ጠርቶ ሲያሰማራ ለሥራው እንዲበቁም ያደርጋቸዋል።

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የአገልግሎት ጥሪ ሳያገኝ ለአገልግሎት መውጣት ያለፈቃድ ወይም ሳይቀጠር በሰው ድርጅት ውስጥ ገብቶ ሥራ እንደ መሥራት ያህል ነው። አንድ ሰው ለአገልግሎት ከመውጣቱ በፊት ከእግዚአብሔር ዘንድ ግልጽ የሆነ ጥሪ ሊኖረው ይገባል። ስለዚህ ጥሪው እስኪመጣ ድረስ በትዕግስት መጠበቅ እንጂ ያለጥሪ አገልጋይ መሆን የማታ ማታ ያዋርዳል። አንድ ሰው ጥሪ ካልመጣለት የወንጌል አገልጋይ ከሚሆን በሚችለው መንገድ ሌላ ሥራ ፈልጎ ቢሠራና ኑሮውን ቢመራ የተሻለ ነው።

ስለአገልግሎት ጥሪ በዝርዝር ከማየታችን በፊት ጥሪ ምን እንደሆነ መተርጎሙ አስፈላጊ ነው። ጥሪ የሚለው ቃል ጠራ ከሚለው ግስ የመጣ ሲሆን መጋበዝን ያመለክታል። በዚህ መልክ የአገልግሎት ጥሪ የሚለው አሳብ ለእግዚአብሔር መለየት ወይም መቀደስ ማለት ነው። ይህ መለየት በተለየ ሁኔታ የእግዚአብሔርን አሳብ ለማከናወን መጋበዝ ነው።

አንድ ሰው ለግብዣ ከተጠራ ወይም ከተጋበዘ የመሄድም ሆነ ያለመሄድ መብቱ የተጠበቀ ነው። ሆኖም የጠሪው ዓላማ የተጠራው ሰው በግብዣው ላይ ጥሪውን አክብሮ እንዲገኝለት ነው። የተጠራው ሰው ያለበቂ ምክንያት ከቀረ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት ሊበላሽ ይችላል። የተጠራው ሰው አዎንታዊ ምላሽ የማይሰጥ ከሆነ ጠሪውን ያሳዝናል።

በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ጥሪ እንደ መጋበዝ ነው። እያንዳንዱን ሰው "ና ከእኔ ጋር ሆነህ..." የሚል ዓይነት ጥሪ ማቅረብ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች የእርሱን ሥራ እንዲሠሩ ይጋብዛቸዋል። በእግዚአብሔር ለአገልግሎት መጠራት ከእርሱ ጋር ሆኖ የእርሱን ሥራ ለመሥራት ነው። የተጠሩ ሰዎች ለቀረበላቸው የአገልግሎት ጥሪ የራሳቸውን ምላሽ መስጠት ይችላሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የአገልግሎት ጥሪ እንደ ትዕዛዝም ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ሲጠራ መጋበዝ ብቻ ሳይሆን ያዛቸዋል። ይህ ደግሞ ሰዎች የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣላቸው በጎ ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው ያሳስባል። የእግዚአብሔር ለሥራው መጋበዝ ከትዕዛዙ ስለሚቀድም ብዙዎች በፍቅር ግብዣው ተሸንፈው ለአገልግሎት ይወጣሉ። እንዲህ ማድረግ ካልቻሉ ግን

እግዚአብሔር ሰዎችን ለሥራው እንደሚፈልጋቸው በመግለጽ ወደ ዓላማው የሚመራበት ሁኔታ ይኖራል።

ለአገልግሎት መጠራት ማለት ለእግዚአብሔር ሥራ መለየት ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን በምንመለከትበት ጊዜ ለእግዚአብሔር ሥራ ብቻ የተለዩ ሥፍራዎች፣ ዕቃዎችና ሰዎች ነበሩ። እነዚህ ለእግዚአብሔር የተቀደሱ ነገሮች ይባላሉ። ይህ ማለት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ካልሆነ በስተቀር ሰዎች ለሌላ ተግባር ሊጠቀሙባቸው እንዲጠቀሙባቸው አይፈቀድም ነበር።

እግዚአብሔር እስራኤልን የራሱ ሕዝብ አድርጎ ጠርቷል። በአጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ሁሉም በእግዚአብሔር ተጠርተዋል ማለት ይቻላል። ሆኖም ከተጠሩት ውስጥ አንዳንዶቹን ለተለየ አገልግሎት ደግሞ እግዚአብሔር ሲለያቸው እንመለከታለን። ለምሳሌ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩበት ወቅት እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት የመገናኛ ድንኳን ያስፈልጋቸው ነበር። የመገናኛ ድንኳን ብቻ ሳይሆን በውስጡም የተቀመጡ ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ እንዲሠሩ እግዚአብሔር ፈልጎ ነበር። ይህን ሥራ ለመሥራት ከእስራኤል ሕዝብ የተመረጡ ሰዎች ጥቂቶች ናቸው። ለዚህ ሥራ በቀደሚትነት የተጠራው ባስልኤል የሚባል ሰው ነበር። "*ከይሁዳ ነገድ...ባስልኤልን በስሙ ጠርቼዋለሁ። በሥራ ሁሉ ብልሃት በጥበብም በማስተዋልም በእውቀትም የእግዚአብሔርን መንፈስ ሞላሁበት...ሥራውን ሁሉ ይሠራ ዘንድ*" (ዘጸ31:2-6)። ባስልኤል ሲጠራ እግዚአብሔር ለጠራበት ተግባር የሚያስፈልገውን እውቀትና ጥበብ ሰጠው። በዚህ በተሰጠው እውቀትና ጥበብ ተጠቅሞ እግዚአብሔር እንደሚፈልገው አድርጎ ሠራው።

በአዲስ ኪዳንም እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ሰዎችን ወደ መንግሥቱ ጠርቷል (1ጴጥ2:9)። እነዚህ የተጠሩት ሰዎች ሁሉ በመንግሥቱ ውስጥ የራሳቸው የሆነ የአገልግሎት ድርሻ አላቸው። እንደ ክርስቶስ የአካሉ ብልቶች ተግባሮቻቸውን በሚገባ እንዲያከናውኑ ለእያንዳንዳቸው የተለያዩ መንፈሳዊ ስጦታዎች ተሰጥተቸዋል (ሮሜ.12:4-6)።

እግዚአብሔር ለሰዎች የሚያቀርበው የመጀመሪያው ጥሪ የድነት ጥሪ ነው (ማቴ11:28)። ይህም ጥሪ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን የማዳን ወንጌል ሰምተው በክርስቶስ አምነው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ የሚጋብዝ ነው። ጌታን ያላመኑ ሰዎች ሁሉ ይህን ጥሪ ተጠርተዋል። ሁለተኛው ጥሪ ግን የአገልግሎት ጥሪ ነው። በወንጌል አምነው ዳግመኛ ለተወለዱ እና የእግዚአብሔር የልጅነት መብትን ላገኙ የሚመጣ ለወንጌል አገልጋይነት ራስን ሙሉ በሙሉ መስጠትን የሚጠይቅ ጥሪ ነው።

በአንድ በኩል በጌታ ያመኑ ሁሉ ለእግዚአብሔር ተጠርተው የወጡ ሰዎች ናቸው። በዚህም የእግዚአብሔርን ዓላማ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ይፈጽማሉ። ሆኖም እግዚአብሔር አንዳንዶችን ከሌሎች በተለየ ሁኔታ በመገናኘት ለተለየ ተግባር ይጠራቸዋል። ይህ የአገልግሎት ጥሪ ከዚህ አጠቃላይ ከሆነው( ለእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ መገዛት) የተለየ ነው። ስለሆነም ይህ ጽሑፍ የሚያተኩርበትም

የጥሪ ዓይነት የተለየ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት በራሱ በእግዚአብሔር በማያሻማ ሁኔታ ተለይቶ ለዚያ ሥራ የሚያስፈልገውን እውቀት፣ ችሎታና ጥበብ በማግኘት ለአገልግሎት መውጣት በሚመለከተው የጥሪ ዓይነት ላይ ነው። ለምሳሌ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ጳውሎስን ለወንጌል ሚስዮናዊነት እንደለያቸው እንመለከታለን። ከሌሎች ምዕመናን ጋር ሆነው ሲያገለግሉ እግዚአብሔር እነርሱን በተለየ ሁኔታ ለወንጌል ተልዕኮ መረጣቸው። *"እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ"* (የሐዋ13:2)።

እንግዲህ እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ መንግሥቱ ይጠራና የተጠሩት ሁሉ ከእርሱ ዘንድ በተሰጣቸው ስጦታ የራሳቸውን ድርሻ ለተጠሩበት አካል እንዲያበረክቱ ያደርጋል (1ቆሮ.12)። ከእነዚህ ከተጠሩት ውስጥ ደግሞ ሕዝቡን ወደ እግዚአብሔርሙላት ለመምራት እና ሌሎች ገና ወደ መንግሥቱ ሊመጡ ያሉትን ደግሞ ለማምጣት ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ሰዎችን በልዩ ሁኔታ ተገናኝቶአቸው በልዩ ኃይል ሞልቶአቸው ያስነሳቸዋል። እነዚህ ሕዝቡን ለማገልገል በእግዚአብሔር የሚጠሩ ሰዎች አስቀድሞ እንደ ማንኛውም ምዕመን ወደ ድነት የተጠሩ ሰዎች ናቸው። ለድነት ሳይጠሩ ለአገልግሎት መጠራት አይታሰብም። እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰዎችን ወደ ድነት ይጠራቸዋል። ከዚያ በኋላ ወደ አገልግሎት ይጠራቸዋል። ስለዚህ ለአገልግሎት የሚጠሩ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸውና ጌታቸው አድርገው ተቀብለው ከእግዚአብሔር ጋር የታረቁ ሰዎች ናቸው። በጌታ ኢየሱስን አምነው ያልዳኑ ሰዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት አይጠሩም።

የአገልግሎት ጥሪ በመስፈርት ሳይሆን በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ ይከናወናል። ይህ ማለት እግዚአብሔር ሰው የእርሱ አገልጋይ ለመሆን ስለተመኘ ብቻ ለአገልግሎት አይጠራም። በምድራዊ አሰራር የአንድ ድርጅት ሠራተኛ መሆን በምኞት ብቻ አይሆንም። ይህን የፈለገ ሰው ከመፈለግና ከመመኘት አልፎ ድርጅቱ የሚፈልገውን መስፈርት በማሟላት ለሥራ ፈላጊዎች ማስታወቂያ ሲወጣ መወዳደር ይኖርበታል። አሠሪው ለመቅጠር ከፈለገና መስፈርቱን ካሟላ ሰውየው ይቀጠራል። ለእግዚአብሔር ሥራ ግን ሠራተኛ የሚኮነው በዚህ መንገድ አይደለም።

እግዚአብሔር አንዳንድ ምዕመናንን ጠርቶ ለአገልግሎት የሚያሰማራቸው በምን መስፈርት እንደሆነ ማወቅ አስቸጋሪ ነው። መስፈርቶቹን በእርግጥ የሚያውቀው እርሱ ብቻ ነው። አንድ ግልጽ የሆነው መስፈርት ሰዎቹ ጌታን ያወቁና የእርሱ እውነተኛ ተከታዮች መሆናቸው ነው። ስለዚህ የአገልግሎት ጥሪ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ነው። የወንጌል አገልግሎት ዋና ሥራ አስኪያጅ እግዚአብሔር ስለሆነ ሠራተኞችን የሚቀጥረው እርሱ ራሱ ነው። ቤተክርስቲያን ቀጣሪ ሳትሆን ሥራ አስፈጻሚ ናት። እግዚአብሔር የላካቸውን አገልጋዮች ታሰማራለች። ታዲያ እነዚህን እግዚአብሔር የላካቸውን ሰዎች እንዴት ታውቃቸዋለች? ይህን አሳብ ወደፊት እናነሳዋለን።

በጥሪና በምርጫ መካከል ጥቂት ልዩነት እንዳለም መረዳት አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ሲጠራ በራሱ መስፈርት ላይ ተመርኩዞ ነው። አንድ ሰው የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ ሆኖ ለመጠራት ማሟላት የሚጠበቅበት መስፈርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጻፈም። ነገር ግን አገልጋይ እንዴት መመላለስ እንደሚገባው የሚያሳዩ ትምህርቶች አሉ። ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት እግዚአብሔር ራሱ ሰዎችን ይጠራና ይልካቸዋል። በዚህ ሂደት የመጀመሪያውን እርምጃ የሚወስደው እግዚአብሔር ነው። ከዚያም ስለጥሪው የሚያውቀው የተጠራው ሰው ነው። ቤተክርስቲያን ከዚያ በኋላ ትሰማለች። እነዚህ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ የተባሉ ሰዎች የወንጌል አስተማሪ፣ ወንጌላዊ፣ መጋቢ ... የሚባሉት ናቸው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉት ምዕመናን አንዳንድ የአገልግሎት ጸጋ ያላቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በተጠቀሰው መስፈርት መሰረት ይመረጣሉ። ለምሳሌ ሽማግሌዎች እና ዲያቆናት ከእግዚአብሔር የሆነ ልዩ ጥሪ ሳይኖራቸው በቤተክርስቲያን ምዕመናን ተመርጠው ያገለግላሉ። ሕይወታቸው ግን ከአገልግሎታቸው ጋር የሚጣጣም ስለመሆኑ መስፈርቱን ማሟላት አለባቸው። እነዚህ ሰዎች የግድ የእግዚአብሔርን ጥሪ ማወቅ አለብን ብለው ግትር መሆን አይጠበቅባቸውም። አገልግሎቱ የዕድሜ ልክ ሳይሆን የትርፍ ጊዜ ስለሆነ ጌታ በሰጣቸው ጸጋ እርሱን ያገለግላሉ። በዚህ መልክ ለሙሉጊዜ የወንጌል አገልጋይነት መጠራትና በቤተክርስቲያን ተመርጦ አንዳንድ አገልግሎቶችን ማገልገል የተለያዩ ናቸው። ሁለቱም እግዚአብሔርን ቢያገለግሉም ከጥሪና ከሚጠይቀው መስዋዕትነት አኳያ ሲታይ ልዩነት አላቸው።

ለሙሉ ጊዜ አገልጋይነት የሚጠሩ ሰዎች እንዴት ይጠራሉ? እግዚአብሔር በተዓምራዊ መንገድ ይጠራቸዋል? ወይስ ሰዎች ተራ ነው ብለው በሚያስቡት መንገድ ይጠራቸዋል? ይህን በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን?

---

## ጥያቄዎች

1. የድነት ጥሪና የአገልግሎት ጥሪ ተመሳሳይነትና ልዩነት ምንድነው?
2. ምዕመናን ሁሉ የእግዚአብሔር ካህናት ናቸው (1ጴጥ2:9) የሚለው አሳብና እግዚአብሔር የተወሰኑ ሰዎችን ለአገልግሎት ይጠራል (ኤፌ4:11) የሚለው አሳብ እንዴት ይጣጣማል?
3. በእግዚአብሔር መጠራትና በቤተክርስቲያን ምዕመናን ለአገልግሎት መመረጥ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
4. አንድ ሰው በእግዚአብሔር ለአገልግሎት ለመጠራት ምን ምን መስፈርቶችን ማሟላት ይጠበቅበታል? ለምን?
5. በአንተ ሕይወት የተፈጸመው ጥሪ የትኛው ነው?

# 2

## የአገልግሎት ጥሪ ዓይነቶችን ማወቅ

እግዚአብሔር ሰዎችን በተለያየ ዓይነት ወይም ሁኔታ ይጠራል። የእግዚአብሔር አሰራር የማይወሰን ስለሆነ እግዚአብሔር ሰዎችን በዚህ ወይም በዚያ ብቻ ይጠራል ብሎ መደምደም መንፈሳዊ ልጅነት ነው። ሆኖም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር አገልጋዮች አጠራር አኳያ ሲታይ ጉልህ ሆነው የሚታዩ የአጠራር ዓ ይነቶች አሉ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጥሪ በአመጣጥ ሁኔታው በሁለት ዓ ይነት ተከፍሏል። የመጀመሪያው ድንገተኛ ጥሪ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አዘጋሚ ጥሪ ነው። እያንዳንዱ አሳብ ምን እንደሆነ በዝርዝር እንደሚከተለው ይገለጻል።

### ድንገተኛ ጥሪ

ድንገተኛ ጥሪ የሚባለው ሰዎች እግዚአብሔርን ስለማገልገል ምንም አሳብ ሳይኖራቸው ሳይታሰብ የሚመጣ ጥሪ ነው። ሰዎቹ በራሳቸው ሥራ ላይ ተሰማርተው ባሉበት ሁኔታ እግዚአብሔር ድንገት ተገልጦላቸው ለራሱ ሥራ እንደሚፈልጋቸው የሚጠራቸው ጥሪ ነው። በዚህ ሁኔታ የሚጠሩ ሰዎች እነርሱም ሆኑ ሌሎች ሰዎች ለአገልግሎት እንደሚወጡ አስቀድሞ መተንበይ አይችሉም። እነዚህን ሰዎች የሚያውቃቸው ጠሪው እግዚአብሔር ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ የሚጠሩ ሰዎች ጥሪያቸውን እንደ ተዓምር ይቆጥራሉ፤ ምክንያቱም በእነርሱም ሆነ በሰዎች ግምት ይሆናል ተብሎ ያልታሰበ ነገር በመሆኑ ነው። እነዚህን ሰዎች ዱሮ የሚያውቁአቸው ሰዎች ዛሬ እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ሲያዩአቸው በመደነቅ ይሞላሉ።

በድንገተኛ ጥሪ ውስጥ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መዘጋጀት ቢኖርም ሰዎች ለዚህ ዓላማ እንደሚዘጋጁ ሳያውቁ ይፋዊ የሆነ ጥሪ ይመጣላቸዋል። እግዚአብሔር እነርሱ ባላስተዋሉት ሁኔታ ሊጠራቸው ላሰበበት አገልግሎት ያዘጋጃቸዋል። እነርሱ የዕለት ተዕለት ሥራዎቻቸውን እየሠሩ እንደሆኑ ቢያውቁም እግዚአብሔር ለዓላማው ያዘጋጃቸዋል። ሰዎቹ ይህን የሚያስታውሉት እግዚአብሔር ለሚፈልጋቸው አገልግሎት ከጠራቸው በኋላ ነው። ያሳለፉትን ሕይወት ወደ ኋላ ሲመለከቱት "ለካስ እግዚአብሔር በዚያ ሁኔታ ውስጥ ሲያሳልፈኝ ለዚህ አገልግሎት እያዘጋጀኝ ነበር!" በማለት ይናገራሉ።

ከእግዚአብሔር ቃል ለዚህ ዓይነት ጥሪ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች አሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። ኤልሳዕ አንዱ ነው። ኤልሳዕ ገበሬ ነበር። የእግዚአብሔር ጥሪ የደረሰው እርሱ በግብርና ሥራው ላይ በነበረበት ጊዜ ነበር። ኤልሳዕ አንድ ቀን በእግዚአብሔር መንፈስ ተሞልቶ ድንቅና ተዓምራት የሚሠራ የእግዚአብሔር ነቢይ እንደሚሆን ምንም አያውቅም ነበር። እርሱ ባያውቅም እግዚአብሔር ግን ስለእርሱ አስቀድሞ ያወጣው ዕቅድ ነበር። ኤልሳዕ ጥሪው ሲደርሰው

ድንገተኛ ቢሆንም እግዚአብሔር ግን አስቀድሞ እንደጠራው ለሌላ የእግዚአብሔር ሰው ገልጦለት ነበር። ኤልሳዕ እርሻ እያረሰ ነበር ጥሪው የመጣለት። ቤተሰቡም ኤልሳዕ የተለመደ የዘወትር ሥራውን እንደሚሠራ ያውቁ ነበር። ኤልሳዕም ሆኑ ቤተሰቡ አንድ ቀን ሥራውን ትቶ ነቢይ እንደሚሆን ገምተው አያውቁም ነበር። ጥሪው እንደ ደረሰው ወዲያውኑ ሁኔታዎች ተለወጡ። ኤልሳዕ ሥራውን ትቶ፣ ቤተሰቡን ተሰናብቶ እግዚአብሔር ወደ ጠራው አገልግሎት ገባ።

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ሲጠራ የሚጠሩ ሰዎች እንደሚጠሩ ሳያውቁ ስለጥሪያቸው ለሌሎች ሰዎች ሊገልጥ ይችላል። እነዚህ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ጥሪ ለተጠሪዎች እንደሚመጣ የሚገለጽላቸው ሰዎች የእግዚአብሔር ሰዎች ሆነው እነዚያን የተጠሩ ሰዎችን በመቀባት ለአገልግሎት የሚለዩ ናቸው። እግዚአብሔር ለእነርሱ የገለጸው በእግዚአብሔር ስም እንዲያሰማሩአቸው ነው። እግዚአብሔር የኤልሳዕን መጠራት ለኤልያስ ገለጠው። ኤልያስም ወደ ኤልሳዕ ሄዶ ቀባውና ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለየው።

የዳዊት ለእግዚአብሔር ሕዝብ መሪነት መጠራትም ድንገተኛ ነበር። የእግዚአብሔር ነቢይና ካህን የነበረው ሳሙኤል፣ የዳዊት ቤተሰብ እና ዳዊትም እግዚአብሔር እርሱን እንደሚጠራው አላወቁም ነበር። ዳዊት የተለመደ ሥራውን ከሚሠራበት ከእረኝነት ተግባሩ ላይ ድንገት ተጠርቶ ሲመጣ እግዚአብሔር እርሱን ለመሪነት እንዲቀባው ነቢዩን አዘዘው። ዳዊት ተጠርቶ እንደመጣ እግዚአብሔር ሳሙኤልን *"ይህ ነውና ተነሥተህ ቀባው አለ። ሳሙኤልም የዘይቱን ቀንድ ወስዶ በወንድሞቹ መካከል ቀባው"* (1ሳሙ16:12-13)። ይህ ለዳዊት አስገራሚ፣ ያልተጠበቀና በድንገት የተከናወነ ክስተት ነበር።

ለዳዊት የእግዚአብሔር ጥሪ ሳይታሰብ መጣና ተቀባ። ከዚያም በኋላ ዳዊት ተራ ሰው መሆኑ ቀረ። ከተቀባ በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል ወረደበት (1ሳሙ16:13)።

እግዚአብሔር ዳዊትን በድንገት ከእረኝነት ላይ ቢጠራውም እረኛ በነበረበት ወቅት ዳዊትን ሊጠራው ላሰበው ሥራ ያዘጋጀው ነበር። ይህን ዳዊት አያውቅም። ዳዊት ይህ የተገነዘበው እግዚአብሔር ከጠራው በኋላ ነው። ዳዊት የእስራኤልን ሕዝብ የተገዳደረና ልባቸውን ያቀለጠውን የታወቀ ጀግና ጠላት ለመግጠም በመጣ ጊዜ ንጉሡና ሌሎችም ሰዎች ዳዊት የውጊያ ልምድ እንደሌለው በመቁጠር ሲናገሩ ዳዊት ግን እርሱ እረኛ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር ሲያለማምደው እንደ ነበር ገለጸላቸው።

> *እኔ ባሪያህ የአባቴን በጎች ስጠብቅ አንበሳና ድብ ይመጣ ነበር፤ ከመንጋውም ጠቦት ይወስድ ነበር። በኋላውም እከተለውና እመታው ነበር፣ ከአፉም አስጥለው ነበር፣ በተነሣብኝም ጊዜ ጉሮሮውን ይዤ እመታውና እገድለው ነበር* (1ሳሙ17:34-35)።

ድንገተኛ ጥሪ ለሚጠራው ሰው እንጂ ለእግዚአብሔር ድንገተኛ አለመሆኑን ከዚህ አሳብ መረዳት ይቻላል። እግዚአብሔር ሰዎችን

ከመጥራቱ በፊት ሊመጣላቸው ላለው ጥሪ ያዘጋጃቸዋል። ከተጠሩም በኋላ ለተልዕኮአቸው ያዘጋጃቸዋል። ለአገልግሎት መዘጋጀትን በተመለከተ ወደፊት በስፋት እንመለከታለን።

አሞጽም ስለራሱ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ እንደነበር እና ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ እንዳልሆነ ይናገራል። *"እኔ ላም ጠባቂና ወርካ ለቃሚ ነኝ እንጂ ነቢይ ወይም የነቢይ ልጅ አይደለሁም፤ እግዚአብሔርም በጎቹን ከመከተል ወሰደኝ፤ እግዚአብሔርም፦ ሂድ ለሕዝቤም ለእስራኤል ትንቢት ተናገር አለኝ"* (አሞ7:14-15)። ይህ ማለት አሞጽ ትንቢት ከመናገሩ በፊት ስለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚያውቀው ነገር አለመኖሩን ያመለክታል። አሞጽ ተራ ሰው እንጂ የነቢይነት ማዕረግ የነበረው ሰው አልነበረም እግዚአብሔር ግን ያልተጠበቀውን ሰው አስነስቶ ለዐመጹ ሰዎች የእግዚአብሔርን መልዕክት እንዲያደርስ አደረገው። ከዘሩም ወይም ከቤተሰቡ በትምህርት ወይም በውርስ ያገኘው አገልግሎት ሳይሆን እግዚአብሔር እንዲሁ ጠርቶ የላከው ሰው ነበር።

ጳውሎስ ለአገልግሎት የተጠራው ከጌታ ኢየሱስ ጋር ተገናኝቶ ሕይወቱ በተለወጠበት ወቅት ነበር። መለወጡና ጥሪው አንድ ላይ ነበር። ጳውሎስ በዛሬው ቋንቋ *ጴንጤ እሆናለሁ* ብሎ በሕልሙም አስቦ አያውቅም። ነገር ግን አንድ ቀን ጌታ ኢየሱስ ተገናኘውና የሕይወቱን አቅጣጫ ለወጠው። በዚያው ዕለት ለእርሱ የተመረጠ ዕቃ እንደሚሆን እግዚአብሔር *"ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ የተመረጠ ዕቃ ነውና"* (ሐዋ.9:15) የተባለውን መልዕክት ነገረው። በዚህ ወቅት የጳውሎስን ጥሪ የሚያውቁት እርሱና ሐናንያ ብቻ ነበሩ። ይህ ቅጽበታዊ የሆነ ጥሪ ነበር።

እግዚአብሔር ከጊዜ በኋላ ጳውሎስና ባርናባስ እርሱ ለጠራቸው አገልግሎት እንዲለዩት በመንፈስ ቅዱስ በኩል ለቤተክርስቲያን ተናገረ። በግል የነበረው ጥሪው ይፋዊ ከመሆኑም ባሻገር እግዚአብሔር በግሉ የገለጠለትን ጥሪ አረጋገጠለት። *"እነዚህ ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ"* (የሐዋ13:1-3)። ጳውሎስ አስቀድሞ በግሉ ጥሪ ቢደርሰውም ጥሪው በቤተክርስቲያን ደረጃ ታውቆ ለአገልግሎት አልተሰማራም። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እርሱና ባርናባስ እግዚአብሔር አስቀድሞ ለጠራቸው አገልግሎት ተለይተው እንዲወጡ ተናገረ። ይህ ጥሪ ድንገተኛ ወይም ሳይታሰብ የሚመጣ ቢሆንም ለአገልግሎት መሰማራት ወዲያው እንደማይሆን ያመለክታል። ከጥሪ በኋላ መቆየት የሚለውን አሳብ <ዝግጅት> በሚለው ርዕስ ሥር እንመለከታለን።

## አዝጋሚ ጥሪ

ይህ ጥሪ ቀስ እያለ እየተገለጠ የሚመጣ ጥሪ ነው። በዚህ ሁኔታ የሚጠሩ ሰዎች እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ በፈቃደኝነት እግዚአብሔርን ያገለግላሉ። በቤተክርሰቲያን ውስጥ ጉድ ጉድ ሲሉ ይታያሉ። እግዚአብሔርን ማገልገል ደስ ይላቸዋል። የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ምን እንደሆነ ጥቂት እውቀትና ልምምድ አላቸው። በተለይ

በእግዚአብሔር ተጠርተው ከሚያገለግሉ አገልጋዮች ጋር በመሆን ጥቃቅን የሆኑ ሥራዎችን በአብዛኛው የጉልበት ሥራዎችን ይሠራሉ።

በዚሁ ሁኔታ እግዚአብሔርን እያገለገሉ እያሉ በአገልግሎታቸው ፍሬ እየታየ ሲሄድ የቤተክርስቲያን መሪዎች ለሆነ አገልግሎት ሰው ሲፈልጉ "እገሌ" ቢሆንስ በማለት ይጠቁማሉ። ምናልባት ይህ ሰው የመሪዎቹን ዓይን ከሞላ ለሚፈለገው አገልግሎት ይመረጣል። ከዚያም በአገልግሎት ላይ ይሠማራና ፍሬ እያሳየ ከመጣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር አለ በማለት ለአገልግሎቱ ይሾማል።

ይህ መንገድ ለአሠራር ምቹ ቢመስልም አደገኛነት አለው። በዚህ ሁኔታ የሚጠሩ ሰዎች በአብዛኛው በቤተክርስቲያን መስፈርቶች በመሆኑ የእግዚአብሔር አሳብ በዚህ ውስጥ በሙላት መገኘቱን ሁልጊዜ ማረጋገጥ አይቻልም። በተጨማሪም ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን ጠጋ በማለት፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች ወዳጆች በመሆንና እነርሱን በማገልገል የሚፈልጉትን የአገልግሎት ሥፍራ ለመያዝ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። በቤተክርስቲያን ውስጥ በቋሚ የሙሉ ጊዜ አገልጋይነት እስኪሾሙ ድረስ ጾም ለጥ ብለው ይታዘዛሉ፤ የሚፈለግባቸውን መስፈርት ሁሉ ለማሟላት በሚገባ ይተጋሉ። የሚፈልጉትን ሲያገኙ ግን ስውር ዓላማቸው እየተገለጠ ይመጣል። ከዚያም ቤተክርስቲያንን ያተረማምሳሉ።

ሰዎች የቤተክርስቲያንን የአገልግሎት መስፈርት አሟሉ ማለት እግዚአብሔር ጠራቸው ማለት አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። የወንጌል አገልግሎት የሚሠራው እግዚአብሔር ራሱ በጠራቸው አገልጋዮች ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በአዝጋሚ ጥሪ ሰዎች በራሳቸው ፈቃደኝነት እግዚአብሔርን በማገልገል ላይ እያሉ በአንድ ወቅት ከእግዚአብሔር ጋር በልዩ ሁኔታ ሊገናኙ ይችላሉ። እግዚአብሔርን ከዚህ በፊት አይተውት በማያውቁት ሁኔታ ያዩታል። እግዚአብሔር በግልጽ እነርሱ ማገልገል የሚገባቸውን አገልግሎት ያሳያቸውና ለዚህ አገልግሎት ስኬታማነት ደግሞ የሚያስፈልጋቸውን ኃይል ያስታጥቃቸዋል።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች አሉ። ሳሙኤል እናቱ በስለት የወለደችው ልጅ ስለሆነ ዕድሜውን ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ወደ እግዚአብሔር ቤት አመጣች (1ሳሙ.1፡24፣28)። ሳሙኤል ከብላቴንነቱ ጀምሮ በጊዜው ካህን በነበረው በዔሊ ፊት ሆኖ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር (2፡11፣18)። ሳሙኤል በእውቀቱና በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ ሄደ። ሳሙኤል ያገለግል የነበረው ምናምቴ ከሆኑ አገልጋዮች ጋር ቢሆንም በእነርሱ አሳብና ድርጊት ሳይበከል እግዚአብሔርን በመፍራትና በመኖር ነበር አገልግሎቱ (2፡26)። ሳሙኤል በእግዚአብሔር ፊት በጽድቅና በቅድስና ይመላለስ እንጂ *"ገና እግዚአብሔርን አላወቀም ነበር። የእግዚአብሔርም ቃል ገና አልተገለጠለትም ነበር"* (1ሳሙ.3፡7)። ይህ የሚያሳየው ሳሙኤል ቀጥተኛ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ከእግዚአብሔር ጋር እንዳልነበረው ነው። ሆኖም ከካህኑ ጋር በመሆን እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ሳይኖራቸው በእግዚአብሔር ቤት ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይኼውም እግዚአብሔርን ማገልገል ደስ ስለሚላቸው ወይም ወላጆቻቸው እግዚአብሔርን

እንዲያገለግሉ ግፊት ስላደረጉባቸው ወይም እግዚአብሔርን በማገልገል አንዳንድ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ወይም በሌሎች ምክንያቶችም ሳይጠሩ እና እግዚአብሔርን በግላቸው ሳያውቁ ሊያገለግሉ ይችላሉ።

ከልጅነቱ ጀምሮ እግዚአብሔርን በዔሊ ሥር ሆኖ እያገለገለ እያለ አንድ ቀን ግን ሳሙኤል እግዚአብሔር ለሰዎች መገለጥ ባቆመበት ዘመን ከእግዚአብሔር ዘንድ ራእይን አየ። እግዚአብሔር በቀጥታ ሳሙኤልን ማናገር ጀመረ። የመጀመሪያው አገልግሎቱ በእግዚአብሔር ቤት በማደጉ ምክንያት የተገኘ ሲሆን አሁን ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጠው መልዕክት ላይ በመመርኮዝ ማገልገል ጀመረ።

ሳሙኤልን ለአገልግሎት ብቁ ያደረገው በነሀኑ በዔሊ ሥር ሆኖ በማደጉና አገልግሎቱን በመለማመዱ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት በቅድስናና በቅንነት መመላለሱ እንዲሁም የእግዚአብሔር ለእርሱ መገለጥ ነበር። ሳሙኤልም በአገልግሎቱና እግዚአብሔርን በማወቅ እያደገ ሄደ። እግዚአብሔር ቃሉን ለሳሙኤል ይገልጥ ነበር። ከእግዚአብሔር የተገለጠለትንም ቃል ስለሚናገር "ከቃሉም አንዳች በምድር ላይ አይወድቅም ነበር።" ከዚህም የተነሳ በእስራኤል የመጀመሪያው ትንቢት ተናጋሪ ባይሆንም የመጀመሪያው ነቢይ ሆነ። በዚህ የነቢይነት ሚናውም የእግዚአብሔርን ቃል ለሕዝቡ ያስተምር ነበ(3:19-21)፣ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት መልካም መሆኑን በሕይወቱ ታማኝነትና ምሳሌነት ያሳይ ነበር (2:35)፣ የእስራኤልን ሕዝብ ለንስሐና ለተሐድሶ ይጠራ ነበር (7:3)፣ በሕዝቡ ላይ ይፈርድ ነበር እንዲሁም በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል የአማላጅነት ሚና ይጫወት ነበር (7:8-9)።

እንግዲህ ያለ እግዚአብሔር ጥሪ በእግዚአብሔር ቤት መወለድና ማደግ እንዲሁም በልጅነት አገልግሎትን መጀመር ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቁ አያደርግም። ሳሙኤል በዔሊ ፊት እንዳደገ ሳለ የሳሙኤል ልጆችም ከአባታቸው አገልግሎትን እያዩ ነበር ያደጉት። ሳሙኤል በሸመገለ ጊዜ እርሱ ወደ አገልግሎት በመጣበት መንገድ ልጆቹን ወደ አገልግሎት አስገባ። ልጆቹን በእስራኤል ላይ እንዲፈርዱ ፈራጆች አድርጎ ሾማቸው። ሆኖም ከእግዚአብሔር ጥሪ ስላልነበራቸው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት አልቻሉም። እግዚአብሔር ማን እንደሆነና አገልግሎቱ በምን መንፈስ መሰጠት እንዳለበት አላወቁም። ከእግዚአብሔር ጋር በግላቸው አልተገናኙም። ስለዚህ ባህርያቸው መልካም አልነበረም (1ሳሙ8:1-3)።

አገልግሎት የሚገኘው በልምምድ ወይም በውርስ ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥሪ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከክርስቲያን ቤተሰብ የተወለዱ ወይም ከልጅነታቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ እያገለገሉ ያደጉ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማገልገል ዝንባሌ ሲኖራቸው የአገልግሎት ጥሪ አላቸው ተብሎም አይጠየቅም። ሰዎች ሁሉ ስለሚያውቁአቸው በተለይ ደግሞ አገልግሎታቸው ፍሬ ካለው እንደ ሌሎቹ ለአገልግሎት ለማስማራት አስቸጋሪ ሂደት አይኖረውም። ልምምድ ወደ አገልግሎት ለመግባት አስፈላጊ ቢሆንም ወሳኝ ግን አይደለም። ወላጆች አገልጋዮች ከሆኑ ድነትን ለልጆቻቸው ማውረስ እንደማይችሉ አገልግሎትንም ለልጆቻቸው ማውረስ አይችሉም። ሆኖም ልጆቻቸው የእግዚአብሔር ሰዎች

እንዲሆኑና እግዚአብሔርን ማገልገል መልካም መሆኑን ማሳየት ይችላሉ።

አገልግሎት እንደ ውርስ ሲወሰድ የእግዚአብሔር ኃይል መሥራት ያቆማል። የታወቁ አገልጋዮች የሆኑ ወላጆች አገልግሎታቸውን ለልጆቻቸው ሲያወርሱ አገልግሎቱ ወላጆቻቸው ያገለግሉ እንደነበር አይሆንም። እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎቱ ካልጠራ በስተቀር የእግዚአብሔር ኃይል አይሠራም። ስለሆነም አገልግሎትን ማውረስ ቢቻልም የእግዚአብሔርን ኃይል ግን ማውረስ አይቻልም።

አዝጋሚ ጥሪን ከድንገተኛ ጥሪ ልዩ የሚያደርገው በአዝጋሚ ጥሪ የሚጠሩ ሰዎች አስቀድሞ ስለእግዚአብሔር ቤት ሥራ እውቀት ያላቸውና አገልግሎትም መስጠታቸው ነው። አስቀድሞ ለሚያገለግሉት አገልግሎት ወይም ለሚያውቁት አገልግሎት ልዩ መረዳትና ኃይል ያገኛሉ። በድንገት የሚጠሩ ሰዎች ግን ስለእግዚአብሔር አገልግሎት ምንም አሳብ ያልነበራቸው ሰዎች ናቸው።

እግዚአብሔር ከሁለቱ በአንዱ መንገድ ሰዎችን ለአገልግሎት ይጠራል። ከሁለቱ በአንዱ መጠራታቸው አንዱ ከሌላው እንዲበልጥ ወይም እንዲያንስ አያደርገውም። በዚህ ሁሉ የሚፈለገው የሰዎቹ መጠራት ነው እንጂ እንዴት እንደተጠሩ አይደለም።

---

## ጥያቄዎች

1. በድንገተኛና በአዝጋሚ ጥሪዎች መካከል ያለው ተመሳሳይነትና ልዩነት ምንድነው?
2. አገልግሎት በልምምድ ወይም በውርስ አይገኝም የተባለው ለምንድነው?
3. አንተ ወደ አገልግሎት የመጣኸው በየትኛው ነው? እንዴት አወቅህ?

# 3

## የእግዚአብሔር ጥሪ እንዴት እንደሚመጣ መገንዘብ

እግዚአብሔር እንዲጠራኝ የት ቦታ? በምን ሰዓት? በምን ሁኔታ? መገኘት አለብኝ ብለው የሚጠይቁ ሰዎች አያሌ ናቸው። በእግዚአብሔር ለመጠራት ትክክለኛው ቦታና ጊዜው ምንድነው? ይህ ጥያቄ ተገቢ ጥያቄ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ቃል አኳያ ምላሽ ሊያገኝ ይገባል።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ እነርሱ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ይመጣል። እግዚአብሔር ለሰዎች የጥሪውን መልዕክት ከመናገሩ በፊት ትኩረታቸውን ወደ ራሱ ይስበዋል። ሰዎቹ ለእግዚአብሔር ትኩረት ሲሰጡ መልዕክቱን ያስተላልፋል። እግዚአብሔር የሰዎችን ትኩረት ለማግኘት የሚጠቀምበት ዘዴዎች የተለያዩ ናቸው።

እግዚአብሔር ሙሴን የጠራው እርሱ በምድረ በዳ በጎችን ሲጠብቅ ነበር። አንድ ጊዜ ሙሴ ሕዝቡ ነጻነት እንዲያገኙ በማሰቡ በራሱ ጊዜ ሕዝቡን ለመርዳት አስቦ ነበር። ሆኖም ሳይሳካለት ቀረና ስደት አመጣበት። በምድረ በዳ ከግብጽ ንጉሥ ተደብቆ የበጎች እረኛ ሆነ። ከዚያም ትዳር መስርቶ ልጆችን ወለደ። ሙሴ አርባ ዓመት የበጎች እረኛ ሲሆን በውስጡ የነበረው አሳብና ራዕይ ምን እንደ ነበር ማወቅ ብዙዎቻችንን ያጓጓናል። ሆኖም ይህን በእርግጥ ለማወቅ ያስቸግራል፤ ምክንያቱም አልተጻፈም። ግን በኀልማሳነቱ በውስጡ የነበረው ራዕይ ጠፍቷል ማለት ያስቸግራል። አሳቡ ቢኖርም ሙሴ ከማሰብ እና ምናልባትም ባለመሳካቱ ከማዘኑ በቀር አንድ ቀን ይህ ራዕይ እውን ይሆናል የሚል እምነት ያለው አይመስልም። የዘወትር ተግባሩ በጎችን መጠበቅ ነበርና።

በሙሴ ቦታ ራሳችንን አስቀምጠን ብንመለከተው ሙሴ በምድረ በዳ ስለነበረው ሕይወት እንዲህ ማለት እንችላለን። ሙሴ እግዚአብሔር ሳይጠራው በራሱ መንገድ የማይገባውን ነገር ስለሠራ ብድራቱን እየተቀበለ እንደሆነ ያስብ ይሆናል። «ሳይጠሩት አቤት ሳይልኩት ወዴት» እንደሚባለው ሙሴ ሳይጠራ አቤት ብሎ እና ሳይላክ ራሱን ልኮ ፍዳውን እያገኘ እንደሆነ ሊያስብ ይችላል። «ወይኔ እንዲህ ባላደርግ ኖሮ ከቤተመንግሥት ወጥቼ በምድረ በዳ የበጎች እረኛ ባልሆንኩ ነበር» በማለት ያስብ ይሆናል። መቼም ሁሌ እንዲህ ባያስብም ሲብሰበት ሆዱ እንዲህ ሳያስብ አይቀርም።

ነገር ግን ባልተጠበቀበት ሥፍራ አንድ ቀን ያልተጠበቀ ነገር ተገለጠ። እግዚአብሔር በምድረ በዳ ውስጥ ተገለጠለት። ሙሴ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማግኘት ንጉሥ ፈርዖን በሚኖርበት በግብጽ ዋና ከተማ ውስጥ ወይም አንድ አገልጋይ እንደተናገረው "እስራኤላውያንን በማስተባበር ወይም ጥሩ የሆኑ ለመሪነት የሚያበቁ ልምምዶች በሚያደርግበት፣ ለመሪነት ለመመረጥ እራሱን ለማስተዋወቅ በሚሯሯጥበት፣ ቅናቱን በተግባር በሚገልጥበትና ሰዎችም ይህ ሰው መሪ

ነው ብለው ሊመሰክሩለት በሚችሉበት ቦታ አልነበረም።"[1] እግዚአብሔር ማንም በማይጠብቅበት ምድረ በዳ በእሳት በሚነድድ ቁጥቋጦ ውስጥ ተገልጦ ሙሴን በስሙ ጠራው (ዘጸ3:3-4)።

እግዚአብሔር ለብዙ ዓመታት ከቤተሰቦቻቸውና ከወገናቸው ተለይተው፣ ሰዎች ሊያስታውሷቸው በማይችሉበት እና በሕይወት ስለመኖራቸው እንኳ በተረሳበት ሁኔታ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ያሉበት ሥፍራ በመገኘት ይጠራቸዋል። የእግዚአብሔር ዓይኖች በምድር ዙሪያ ስለሆኑ ሊያገለግሉት የሚችሉትን ሰዎች ከየትም መጥራት ይችላል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ሥራ ሸክም ያላቸው ሰዎች የቤተክርስቲያን መሪዎች ረስተውናል ብለው ተስፋ መቁረጥ የለባቸውም። እግዚአብሔር ሲጠራ በኃይል ሞልቶ ሰዎች መቋቋም በማይችሉት ጸጋ ይልካል። እግዚአብሔር ሲያስታውስ ሰዎችም ዓይኖቻቸው ተከፍተው <ለካስ እገሌ አለ> ማለት ይጀምራሉ።

እግዚአብሔር ባልተጠበቀ ቦታና በማይታሰብ ሁኔታ ራሱን ለሰዎች ገልጦ ለአገልግሎት ሊጠራቸው ስለሚችል ሰዎች እግዚአብሔርን በሁኔታዎች ውስጥ ለማየት የሚያስተውል ልቦና ያስፈልጋቸዋል። ሙሴ ወደ ሚነድደው ቁጥቋጦ የሄደው ያየው ነገር አዲስና አስገራሚ ስለሆነ ምን እንደሆነ በሚገባ ለማየት ነው እንጂ እግዚአብሔር በዚያ ውስጥ ይናገረኛል ብሎ አልነበረም። ዛሬም እግዚአብሔር በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ በመገለጥ ሰዎችን ይጠራል። አንዳንዱ እግዚአብሔር የሚገለጥበት ሁኔታ የሚያስደስትና የሚያስገርም ሲሆን አንዳንዱ ደግሞ የሚያሳዝንም ሊሆን ይችላል። ሰዎች በሚገጥማቸው አዲስ ልምምድ ውስጥ እግዚአብሔር ምን ይላል? የሚል ጥያቄ ቢጠይቁ የእግዚአብሔርን መልዕክት ያገኛሉ። እግዚአብሔር በሁኔታዎች ውስጥ ሰዎችን ሊጠራ ይችላል ስለተባለም ሁኔታዎችን ሁሉ በመንፈሳዊ እይታ ብቻ መመልከትና ለሁኔታዎች ሁሉ መንፈሳዊ ትርጉም መስጠት ወይም እግዚአብሔርን በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ እንዲናገር መጎትጎት አስፈላጊ አይደለም።

*በቀለ መሐከለኛ የትምህርት ችሎታ ያለው ወጣት ነው:: ትምህርቱን አጥንቶ 12ኛ ክፍል ሲፈተን ኮሌጅ የሚያስገባውን በቂ ውጤት ሳያገኝ ቀረ:: በዚህም በጣም ተናደደና ለጥቂት ወራት ሥራ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ተዘዋወረ:: ነገር ግን ምንም ሥራ ሳያገኝ ወደ ቤተሰቡ ተመለሰ:: ከዚያም የቤተክርስቲያን መሪዎች ለወንጌል አገልጋይነት ራሱን የሚሰጥና ወደ ሥልጠና ሊሄድ የሚችል ወጣት እንደሚፈልጉ ሰማና ወደ እነርሱ ሂዶ «ምናልባት እግዚአብሔር 12ኛ ክፍል እንዳላልፍ ያደረገው ጌታን እንዳገለግል የሆናል» በማለት ነገራቸው:: በቀለም ሆነ መሪዎቹ እርሱ በትምህርት የጠበቀውን ውጤት አለማግኘት ወደ አገልግሎት እንዲገባ እግዚአብሔር ያደረገው መለኮታዊ ምሪት እንደሆነ አድርገው ተቀበሉና በቀለን ለወንጌል አገልጋይነት ሥልጠና ላኩ::*

እግዚአብሔር ሰው ያሰበው ቦታ እንዳይደርስ በማሰናከል ኑሮ ሳይሳካለት ቀርቶ ወደ አገልግሎት እንዲገባ አልፎ አልፎ ቢያደርግም ይህን እንደ መሠረታዊ እውነት መቀበል ትክክል አይደለም:: እግዚአብሔር ሰው

[1] ምስክር ቁ. 30. ገጽ 4

የተመኘውን ነገር ሁሉ ካገኘም በኋላ መጥራት ይችላል። አንድ ሰው «ወይኔ! የምፈልገውን ነገር ሳላገኝ እግዚአብሔር ወደ አገልግሎት በግድ አስገባኝ» ብሎ እንዳይከሰው እግዚአብሔር ሰውየውን ያስጨርሷል።

እንደዚሁም እግዚአብሔር እንደጠራቸው በልባቸው እያወቁ ነገር ግን ከእርሱ በላይ ለአንድ ነገር ቅድሚያ በመስጠት ለጥሪው ፈቃደኛ በማይሆኑበት ወቅት እግዚአበሔር በሕይወታቸው ውስጥ ጣዖት የሆነባቸውን ነገር ያነሳል። በዚህ ጊዜ ሰዎቹ የሚወዱትን ነገር በማጣታቸው ያዝናሉ። እግዚአብሔር ያን ጊዜ መልዕክቱን ሊሰሙ በሚችሉበት ሁኔታ ይነግራቸዋል። በአጠቃላይ እግዚአብሔር በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሊናገር ስለሚችል በማስተዋል መመላለሱ መልካም ነው።

እግዚአብሔር ጌዴዎንን የጠራው እርሱ ተሸሽጎ ስንዴ ይወቃ በነበረበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ጌዴዎን በነበረበት ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር መጥቶ እንደሚጠራው በጭራሽ መገመት የሚችልበት አዕምሮ አልነበረውም። ጌዴዎን የነበረበት ሁኔታ መልካም አልነበረም። የውስጥ ሕይወቱን ስንመለከተው በተስፋ መቁረጥና በመጠራጠር የተሞላ ሰው ነበር። ሆኖም ጌዴዎን እግዚአብሔር በአባቶቹ ዘመን የሠራቸውን ተዓምራት ሰምቶ በልቡ ይዟል። ነገር ግን እውቀት ብቻ ሆነበት። እግዚአብሔር የጥንት እንጂ የዛሬ አምላክ አይደለም የሚያሰኝ ሁኔታ ውስጥ ነበር። እንዲህ እንዲያስብ ያደረገው ነገር ምንድነው? ቢባል እስራኤል በጠላት እየተጠቃ ነው። የእግዚአብሔር ኃይል ተገልጦ ሕዝቡን እንዳያድን ያደረገው የእግዚአብሔር ማርጀት ሳይሆን የሕዝቡ እግዚአብሔር በሚጠብቅበት ሁኔታ አለመገኘት ነበር። ጌዴዎን ግን "እግዚአብሔር ማዳን የሚችል ከሆነ ለምን ዛሬም ሕዝቡን አያድንም?" የሚል ጥያቄ ነበረው። እግዚአብሔር አዕምሮአቸው በጥያቄ የተሞሉትንና ተጠራጣሪዎችን ሰዎች አይጠላቸውም። ይልቅስ ይጠራቸውና ለጥያቄዎቻቸው መልስ በመስጠት በእርሱ እንዲያምኑ ያደርጋቸዋል። የጌዴዎን ጥያቄ "ነጻ የምታወጣው የጥንቷ ብርቱ የእግዚአብሔር ክንድ ወዴት አለች?" የሚል ነበር። ከዚያ አኳያ ሲታይ ጌዴዎን ሕዝቡ ከጠላት ጭቆና ነጻ እንዲወጣ ከፍተኛ ቅንዓት ያለው ሰው እንደነበር መገመት ይቻላል።

ጌዴዎን የነበረበትን ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ሁኔታ ስንመለከት ሕዝቡ እግዚአብሔርን እንዲጠብቅ የሚያደርገው ሁኔታ ውስጥ አልነበረም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕዝብ ማዕከላዊነት በሌለው ሁኔታ በልባቸው በመሰላቸው ነገር የሚመሩበት ወቅት ነበር። የእግዚአብሔርን ነገር ለሰዎች በሚገባ የሚያስተምር አካል አልነበረም። በማህበራዊ ኑሮም ሕዝቡ በችግር ውስጥ ነበር። በጠላት እጅ የወደቁ ስለነበር ነጻነት አልነበራቸውም። ጌዴዎንም ጠላቶቹ አግኝተውት ስንዴውን እንዳይወስዱበት እነርሱ በማይጠብቁበት ቦታ መውቃት ጥሩ መሆኑን በማሰብ በወይን መጥመቂያ ውስጥ ስንዴ ይወቃ ነበር። ጌዴዎንም እንደ ሙሴ ከጠላት ሸሽቶ ባለበት ቦታ ነው እግዚአብሔር የተገናኘው (መሳ6)።

እግዚአብሔር እንደ ጌዴዎን «እግዚአብሔር የጥንት እንጂ የዘመናችን አምላክ አይደለም፣ እርሱ ስለእኛ አይገደውም» የሚሉትንም

ሰዎች ይጠራቸዋል። እግዚአብሔር ጉዳዩ በልባቸው ውስጥ ካለው ቅንነት ጋር ነው። ጌዴዎን ደብቅ ሰው አልነበረም። በአዕምሮው ውስጥ የሚመላለሰውን ጥያቄ እግዚአብሔርን በግልጽ ጠየቀው። እንደ ነገር ለምን ሆነ? ብለው የሚጠይቁ ሰዎች ስለሚጠይቁት ነገር በሚገባ ያስቡበታል። ጥያቄ የሚፈጥር ነገር እያለ በውስጣቸው ጥያቄ የሌላቸው ሰዎች ደግሞ ግድየለሾች ናቸው። እግዚአብሔር የእርሱና የሕዝቡ ጉዳይ የሚከነክናቸውን ሰዎች ይፈልጋል። ለጥያቄዎቻቸው ምላሽ በመስጠት ዓላማውን እንዲፈጽሙ ይልካቸዋል። ስለዚህ «ይህ ሁሉ ሲሆን እግዚአብሔር የት አለ? እግዚአብሔር እንደ ሐዋርያት ዘመን ለምን ተዓምር አይሠራም?» የሚሉ ካሉ እግዚአብሔር እነርሱንም ይጠራቸዋል። ሰዎች ያሉበት ሁኔታ እና በአዕምሮአቸው ያለው ጥያቄ እግዚአብሔር ወደ እነርሱ መጥቶ እንዳይጠራቸው አያግደውም።

እግዚአብሔር ሳሙኤልን የጠራው በቤተመቅደስ ሲያገለግል ውሎ ወደ እንቅልፉ ከሄደ በኋላ ነበር። ሳሙኤል የተወለደው በስለት ስለነበር እናቱ፣ እግዚአብሔርን እንዲያገለግል ለእግዚአብሔር ሰጠችው። በዚህ ሁኔታ ሳሙኤል ያደገው በቤተመቅደስ ከዔሊ ልጆች ጋር ነበር። በቤተመቅደስ ለዔሊ ሲታዘዝ ያደገ ልጅ ነበር። ከሳሙኤል ጋር ያገለግሉ የነበሩ የዔሊ ልጆች እግዚአብሔርን የሚፈሩ አልነበሩም። የድፍረትን ኃጢአት በእግዚአብሔር ቤት ያደርጉ ነበር። በዚህ ሁሉ ሳሙኤል ግን በእኩዮቹ አሳብና ድርጊት አልተወሰደም ነበር። ሳሙኤል «ከእግዚአብሔር ካህን የተወለዱም እንዲህ ካደረጉ እኔ ደግሞ ምንድነኝ?» በማለት የሥጋውን ፍላጎት አልተከተለም። እንግዲህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች የተባሉ ሰዎች ኃጢአት የሚለማመዱበት ጊዜ በመሆኑ እግዚአብሔር ለሕዝቡ መናገር ያቆመበት ዘመን ነበር። ሕዝቡ ራእይ አልነበረውም።

ሳሙኤል በእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ ሁሌ ይተኛ ነበር። አንድ ቀን ግን የተለየ ድምጽ ሰማ። ሳሙኤል እስከዚያ ቀን ድረስ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ አያውቅም ነበር። በድምጽ የራሱን ስም ሲሰማ ወደ ዔሊ ሄዶ ለምን ጠራኸኝ? አለው። ዔሊ እንዳልጠራው ሁለት ጊዜ ከነገረው በኋላ ዔሊ ምናልባት እግዚአብሔር ጠርቶት ይሆናል በማለት ሳሙኤል ማድረግ የሚገባውን መከረው። እግዚአብሔር ሳሙኤልን ለሥራው ለየው (1ሳሙ3)። ሳሙኤል የእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ስለነበረ እግዚአብሔር በቅርብ አገኘው እንል ይሆናል። ነገር ግን ሳሙኤል በአካል በቤተመቅደስ ውስጥ መገኘቱ ሳይሆን በልቡ ለእግዚአብሔር ቅርብ መሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ሰጠው። እንደ ልባቸው የሚመላለሱ ከሳሙኤል ጋር ያገለግሉ የነበሩ ሌሎች ሰዎች አልተጠሩም። እንግዲህ ከልጅነታቸው ጀምረው ራሳቸውን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሰጡ ሰዎችም አንድ ቀን በተለየ ሁኔታ እግዚአብሔር ተገናኝቶአቸው ሊጠራቸው ይችላል ማለት ነው።

እግዚአብሔር ለሳሙኤል የተገለጠው ልምድ ባለውና በዕድሜም በሸመገለው በካህኑ በዔሊ በኩል ሳይሆን ብላቴና ለሆነው ለራሱ ለሳሙኤል ነበር። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ሰዎች በሚጠብቁበት መንገድ አይመጣም። እንደ ሰዎች ሁኔታ ቢሆን እግዚአብሔር በዔሊ በኩል ለሳሙኤል ቢገለጥ ጥሪው ያለምንም ችግር ተቀባይነት ያገኝ ነበር።

እግዚአብሔር ግን ልጅ ለተባለው ራሱን ገልጦ ትልቅ ለተባለው መልዕክት አስተላለፈ። ይህ ከተለመደው ባህላዊ አሠራር ውጭ ስለሆነ ግራ የሚያጋባ ሊመስል ይችላል። ስለዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን በለመዱት ወይም ይገለጣል ብለው በሚያስቡት መንገድ ብቻ ከመጠበቅ እንደ ቃሉ በጽድቅ ሕይወት እየተመላለሱና ለእርሱ የሚመች ሕይወት እየኖሩ እግዚአብሔር ሲናገር መስማት መቻል መልካም ነው።

እግዚአብሔር ኤልሳዕን የጠራው እርሻ በማረስ ላይ እያለ ነበር። ኤልሳዕ ኑሮ የተመቸውና እርሻ በማረስ የሚተዳደር ገበሬ ነበር። ኤልሳዕ አንድ ቀን እግዚአብሔር ይጠራኛል ብሎ ያስብ ነበር ለማለት አይታሰብም። እግዚአብሔር ግን ኤልሳዕን ለአገልግሎት ያጨው እርሱን የቀባው ኤልያስ እንኳ ሳያውቅ ነበር። ከኤልያስ በኋላ ነቢይ የሚሆነውን የጠቆመው ኤልያስ ሳይሆን እግዚአብሔር ራሱ ነበር። ለኤልሳዕ የእግዚአብሔር ጥሪ የመጣለት እርሻ ቦታ በበሬዎቹ እያረሰ ነበር። እግዚአብሔር ገበሬንም በእርሻ ቦታው ድረስ በመሄድ የሚጠራ አምላክ ነው (1ነገ19፡19-21)።

ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ እንድርያስን፣ ያዕቆብና ዮሐንስን የጠራቸው ዓሣ በማጥመድ ላይ እያሉ ነበር። ጌታ እነዚህን ሰዎች ለማግኘት ወደ ባሕር አካባቢ መሄድ ነበረበት። ስለዚህ ወደ ገሊላ ባሕር ሄዶ እዚያ ሲመላለስ አያቸውና ጠራቸው። ለእነርሱ ያቀረበው መልዕክት "በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ" የሚል ነበር። ይህችን መልዕክት ሰምተው አለን የሚሉትን መተዳደሪያቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ተከተሉት (ማቴ4፡19-22)። ዓሣ የማጥመድ ሥራ መተዳደሪያ ቢሆንም እንኳ አስቸጋሪ ሥራ ነው። ይህን ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ደግሞ ያልተማሩ ሰዎች እንደነበሩ ይነገራል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማቴዎስን የጠራው ቀረጥ እየሰበሰበ ባለበት ሁኔታ ነበር። አንድ ቀን ኢየሱስ መንገድ ሲሄድ ማቴዎስ በመቅረጫው ላይ ተቀምጦ አየውና ጠራው። ለማቴዎስ የተሰጠው መልዕክት "ተከተለኝ" የሚል ብቻ ነበር። በዚያን ዘመን ቀረጥ የሚሰበስብ ሰው በሕዝቡ ዘንድ የተጠላና የተናቀ ሰው ነበር። በወቅቱ በነበረው አሳብ ማቴዎስ በጌታ ኢየሱስ ይጠራል ብሎ ማንም ላያስብ ይችላል። ጌታ ኢየሱስ ግን አየና ጠራው (ማቴ9፡9)።

ዛሬም እግዚአብሔር በሥራቸው ምክንያት በኅብረተሰቡ መካከል ተቀባይነት የሌላቸውን ሰዎች ሊጠራ ይችላል። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚመለከተው በሚሠሩት ሥራ ውስጥ ሳይሆን በአምላካዊ መነጽሩ ስለሆነ በሚናቅ ሥራ ምክንያት ሰዎችን አይንቅም። በእኛ ዘመን የማቴዎስ ዓይነት ሥራ (የሂሳብ ሠራተኛነት) የሚያከብር እንጂ የሚያስንቅ ሥራ አለመሆኑ ቢታወቅም በዘመናችንም የሚናቁ የሥራ ዓይነቶች አሉ።

እግዚአብሔር ጳውሎስን የጠራው እርሱ የጌታን ደቀመዛሙርት ለማሳደድ መንገድ ላይ በነበረበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር የተመለከተው የጳውሎስን ተግባር ሳይሆን ያን ለመፈጸም ያሰበበትን የውስጥ ዓላማውን ነበር። ዓላማው ለእግዚአብሔር ከመቅናት የተነሳ ስለሆነ እግዚአብሔር ወዶታል። እግዚአብሔር ጳውሎስ ትክክለኛውን ነገር አውቆ እንዲያገለግለው ጠራው። ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ላይ

የጌታን ደቀመዛሙርት ለማሳደድ ሲሄድ ጌታ ኢየሱስ ለአገልግሎቱ ይጠራኛል ብሎ በፍጹም ሊያስብ አይችልም። ጳውሎስ የነበረበት ሁኔታ የእግዚአብሔርን ጥሪ ወደ እርሱ ከመምጣት አልከለከለውም። ይልቅስ ለጥሪው መምጣት ሁኔታዎችን አመቻቸለት። ጳውሎስ «አንተ ማን ነህ?» ብሎ ሲጠይቀው ጌታ ኢየሱስ "አንተ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ" ብሎ ተናገረው። ከዚህም የተነሳ ጳውሎስ እርሱን እየጠራው ያለው ማን እንደሆነ ማወቅ አላዳገተውም። ወዲያውም "ጌታ ሆይ ምን አደርግ ዘንድ ትወዳለህ?" በማለት ሲመልስለት እንመለከታለን (የሐዋ 9፡1-9)።

እነዚህ ምሳሌዎች እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎቱ በሚጠራበት ጊዜ እነርሱ ወዳሉበት ሥፍራ እንደሚመጣና እንደሚፈልጋቸው ያሳዩናል። ስለዚህ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማግኘት ብለው ወደ ተለየ ቦታ መሄድ ወይም የተለየ ልምምድ ውስጥ መግባት አይጠበቅባቸውም። እግዚአብሔር ሰዎችን የሚፈልግ አምላክ ስለሆነ ሰዎች ያሉበት ሁኔታ ጥሪውን ወደ እነርሱ ከማስተላለፍ አይገታውም። የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማግኘት በአስፈላጊ ጊዜ በአስፈላጊ ቦታ መገኘት አያስፈልግም። እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ሊጠራን ከፈለገ እኛ ያለንበት ቦታ ድረስ ይመጣል። ይህ ሲባል ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያለን መንፈሳዊ ሕይወታችን እንደተጠበቀ ሆኖ ነው።

እንግዲህ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚጠራው እነርሱ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ በመገኘት ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ በመምጣቱ ሰዎች በእርግጥ እግዚአብሔር ወደ እነርሱ መጥቶ እንደጠራቸው ማመን ያቅታቸዋል። ሰዎቹ እግዚአብሔርን የሚጠብቁት ልዩ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ስለሆነ እርሱ በዓይናቸው ፊት ተራ ነው በሚሉት ነገር ውስጥ ሲገለጥ እግዚአብሔር መሆኑን ይጠራጠራሉ።

የአገልግሎት ጥሪ የተለያየ ቢሆንም እግዚአብሔር የሚጠራቸው ሰዎች ግን ምን ዓይነት ናቸው? የእግዚአብሔርን የሙሉጊዜ አገልጋይነት የመምረጫ መስፈርት አሟልተው ሊመረጡ የሚችሉ ሰዎች እነማን ናቸው? እግዚአብሔር ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይነት እነማንን ይጠራል? የሚቀጥለው ምዕራፍ ለእነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።

---

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት የሚጠራው መቼና የት ቦታ ነው?
2. በእግዚአብሔር ለመጠራት ሰዎች በምን ሁኔታ ውስጥ መገኘት ይኖርባቸዋል?
3. እግዚአብሔር አዕምሮአቸው በጥያቄ የተሞላ ሰዎችን የሚጠራው ለምንድነው?
4. እግዚአብሔር አንተን/አንቺን የጠራው በምን ሁኔታ ውስጥ ሳለህ/ሳለሽ ነበር?
5. ዛሬስ እግዚአብሔር በምን ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎችን ይጠራል?

# 4

## ለአገልግሎት ምን ዓይነት ሰው እንደሚጠራ ማወቅ

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር የሚጠራቸው ሰዎች ዓይነትን እንመለከታለን። እግዚአብሔር ወንጌልን ሰምቶ በማመን ድነት እንዲያገኙ በዓለም ውስጥ ያሉትን ሰዎች ሁሉ እንደሚጠራ ተመልክተናል። እግዚአብሔር ወደ ቤቱ ተጠርተው ከመጡ ሰዎች መካከል ማንንም ለሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት መጥራት ይችላል። እግዚአብሔር የተማሩትን፣ ያልተማሩትን፣ ድሆችን፣ ባለጠጎችን፣ ደካሞችን፣ ብርቱዎችን፣ ወጣቶችን፣ ጎልማሶችን እንዲሁም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ይጠራቸዋል።

አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ የሚጠራቸው ሰዎች ደካማ የሆኑትን ነው። እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ሚዛን መሠረት ከምንም የማይቆጠሩ ሰዎችን ይመርጥና በኃይሉ በመሙላት ክብሩን ያሳያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም ሲታይ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ታላላቅ የሆኑ ነገሮችን የሚሠራው በሰው ዘንድ በጣም የማይረቡ የተባሉትን ሰዎችና ነገሮችን በመጠቀም ነው። እግዚአብሔር ለአገልግሎት የሚጠራቸው ሰዎች ደካማ ወይም እውቀትና ችሎታ የሌላቸው እንዲሁም ያልተማሩ ሰዎች ናቸው ብለው ያምናሉ።

እግዚአብሔር ደካሞችን ይጠራል የሚለውን አሳብ በሁለት መልኩ መመልከት ይቻላል። በአንድ በኩል አሳቡ ትክክል ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ደካሞችን በመጠቀም የሚፈልገውን አገልግሎት ማከናወን ይችላል። እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ለመሥራት ሲነሳ የሰዎች ድካምና አለመማር እንቅፋት ሊሆኑበት አይችሉም። እግዚአብሔር ምናምቴ የተባሉትን ሰዎች በኃይልና በችሎታ ሞልቶአቸው ማንም በእውቀቱና በችሎታው ማድረግ የማይችለውን ነገር ማከናወን እንዲችሉ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ በዚህ ጎኑ በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ መታመን ይሆናል። ብዙዎች እንደሚሉት "እግዚአብሔር ያልበቁትን ሰዎች ጠርቶ ብቃት እንዲኖራቸው ያደርጋል።"

በሌላ በኩል ግን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚፈለጉ ሰዎች በዓለም ሚዛን የተጣሉ ሰዎች ናቸው ወደሚል የማጠቃለያ አሳብ ያመጣናል። ይህ አስተሳሰብ የመጣው ደግሞ የእግዚአብሔር አገልግሎት ሰዎች በዓለም ከሚሠሩት ሥራ ያነሰ ቦታ የሚሰጠው ነገር ነው ከሚል አሳብ የመነጨ ይመስላል። በሰዎች ዘንድ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ከእግዚአብሔር አገልግሎት ይልቅ የዓለም ሥራ ነው።

*ተሰማ የሚባል አንድ ወጣት ነበር። ተሰማ ከዩንቨርሲቲ እንደተመረቀ የእግዚአብሔር ጥሪ ስለነበረው ለአገልግሎት ሲወጣ ብዙዎች ተቃውመውታል። እርሱን የሚያውቁ አማኝ ያልሆኑ ሰዎች "ይህ ልጅ አበደ" አሉ። አማኝ ባልሆኑቱ ዘንድ ጥሩ የሆነ የዓለምን ሥራ መፈለግ ትቶ እግዚአብሔርን ለማገልገል መወሰን የእብደት ምልክት እንደሆነ ተቆጠረ። አማኞች ደግሞ "የሚመክረው ጓደኛ የለውም እንዴ?" አሉ። አንዳንዶቹም ቀርበው "የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ከምትሆን*

ጥሩ ሥራ ይዘህ ተከብረህ እግዚአብሔርን በትርፍ ጊዜህ ማገልገል ይቻልሃል" ይሉት ነበር። እነርሱም ቢሆን ጥሩ የአዕምሮ ችሎታ ያለው ሰው የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን የለበትም የሚል አሳብ ያላቸው ይመስላል።

ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔርን ማገልገል የሚመረጠው ሌሎች አማራጭ የሥራ መስኮች ከተዘጉ ብቻ እንደሆነ ተደርጎ እንደ ተወሰደ ነው። ሥራ ቢጠፋ አገልጋይነት አይጠፋም ማለት ነው። እንዲህ ማለት አገልግሎት በዓለም ሥራ ላጡ ሰዎች የተዘጋጀ የመጨረሻ አማራጭ የሥራ ዕድል ነው ማለት ነው። ይህ ከመጽሐፍ ቅዱስ አሳብ ጋር የሚጋጭ አመለካከት ስለሆነ መለወጥ አለበት።

በዚህ ዓለም መሥፈርት ተቀባይነት ያላቸው ሰዎችስ በእግዚአብሔር አይጠሩም? እግዚአብሔር ከፍተኛ ትምህርት የተማሩትን፣ የተለያየ ሙያ ያላቸውን ሰዎች ጠርቶ ለወንጌል አገልግሎት የማያስማራበት ምክንያት ምንድነው? "እግዚአብሔር የደካሞች አምላክ ነው፤ የሚሠራውም በደካሞች ሕይወት ነው" የሚለው አሳብ የተወሰደው በ(1ቆሮ.1፡26-29) ላይ ካለው አሳብ ነው። ይህ ክፍል በቅድሚያ የሚናገረው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ስለመጠራት ሳይሆን ለድነት ስለመጠራት ነው። ያም ቢሆን እግዚአብሔር ወደ መንግሥቱ የሚጠራቸው ሰዎች ሁሉ ደካሞች፣ መደበኛ ትምህርት ያልተማሩ እና በኅብረተሰቡ ዘንድ እንደ ተራ የሚቆጠሩ ሰዎችን ብቻ እንደሆነ አይናገርም።

በቆሮንቶስ ወደ ጌታ የመጡ ሰዎች ብዙዎቹ በዓለም መስፈርት ቦታ የሚሰጣቸው ሰዎች አልነበሩም። ይህ ማለት ግን በእነርሱ (በተጠሩት ምዕመናን) መካከል ጥበበኞች፣ የተማሩ እና በኅብረተሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ስፍራ የሚሰጣቸው ሰዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር መንግሥት ለሁሉም ዓይነት ሰዎች ክፍት ናት። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ ድሃ፣ ያልተማረ፣ በዓለም ተራ የሆነ... እያለ አይደለም። እግዚአብሔር ሁሉንም ዓይነት ሰው ይጠራል፤ ድምጹን ሰምቶ መከተል የፈለገ ደቀመዝሙር ይሆናል። ከእነዚህ ከተጠሩት መካከልም ለአገልግሎት ሲጠራ በራሱ መስፈርት እንጂ በዓለም መስፈርት አይጠራም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራቸውን ሰዎች ስንመለከት በትምህርት፣ በኑሮ ደረጃ፣ በሥራ... በጣም የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። እግዚአብሔር እረኞችን ለመሪነት፣ ገበሬዎችን ለነቢይነት፣ ዓሣ አጥማጆችን ለሐዋርያነት፣ ሐኪሞችን ለወንጌል አገልጋይነት፣ የሃይማኖት ሊቃውንትን ለወንጌል ሚስዮናዊነት ጠርቷል። ስለዚህ እግዚአብሔር ማንንም ጠርቶ ለአገልግሎቱ ያሰማራል። እግዚአብሔር ደካሞችን ብቻ እንደሚወድና ለአገልግሎትም እንደሚጠራ ማሰብ ደካሞች እግዚአብሔር የእኛ ብቻ ነው ብለው ከብርቱዎች ጋር ራሳቸውን ለማነጻጸር የፈጠሩት የሥነ-ልቦና መከላከያ ይመስላል።

የተማሩትም ሰዎች ሆኑ ያልተማሩት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የተጠሩት በጸጋው እንደሆነ ሁሉ ለአገልግሎት የተጠሩትም በእርሱ ምህረት መሆኑን በሚገባ ተረድተው በተጨማሪም በእርሱው

በመታመንና በመደገፍ በተሰጣቸው ስጦታ ሲያገለግሉት እግዚአብሔር ደስ ይሰኛል። እግዚአብሔር መማርን አይጠላም፤ ያለመማርንም አያደግፍም። እግዚአብሔር የእርሱን ፈቃድ ለማድረግ የተነቃቃ መንፈስ ያለውን ሰው ይፈልጋል።

ከዕድሜ አኳያስ እግዚአብሔር እነማንን ይጠራል? እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ያስፈልጉኛል ያላቸውን ሰዎች ያለምንም የዕድሜ ገደብ መጥራት ይችላል። እግዚአብሔር ብላቴናዎችን፣ ጎልማሶችንና አዛውንቶችን ይጠራል። እግዚአብሔር በእያንዳንዱ የዕድሜ ክልል ባሉት ሰዎች መሥራት የሚፈልገው ሥራ አለው። አብዛኛዎቹ ሰዎች ለእግዚአብሔር ለመኖርና የእርሱን ፈቃድ ለማገልገል ራሳቸውን የሚሰጡት በወጣትነትና በጎልማሳነት ዘመናቸው በዓለም የሚወዱትን ነገር እንደ ልባቸው ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ ነው። የጎልማሳነት ጉልበታቸው ካለቀ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ዞር ይላሉ። ለእግዚአብሔር የሕይወታቸውን እላቂ ይሰጣሉ። መቼም እግዚአብሔር ቸር ስለሆነ ራሳቸውን ለእርሱ ሲሰጡ የት ነበራችሁ? በማለት አያገፈትራቸውም።

እግዚአብሔር የእርሱን ሥራ እንዲሠሩ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ይፈልጋል። በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞሉ፣ ጉልበቶቻቸው ገና ሮጠው ያልደከሙ፣ ራእያቸው ገና ትኩስ የሆነ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ይሻል። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥም ሲታይ እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራቸው ሰዎች በዕድሜያቸው ጡረታ የወጡትን ሳይሆን ገና መሥራት የሚችሉትን ሰዎች ነው።

እግዚአብሔር ሙሴን ሲጠራው ሙሴ የሰማንያ ዓመት ሰው ነበር። በአሁኑ ጊዜ እድሜ ሲሰላ ሙሴ ጡረታ የወጣ ሰው ይሆናል። በዚያን ዘመን ግን ሙሴ የተጠራበትን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ሙሉ አቅም ነበረው። ሳሙኤልና ኤርምያስም ሲጠሩ ብላቴናዎች ነበሩ። ይህ ብላቴና የሚለው ቃል በወጣትነት ዕድሜ ክልል ያሉትን ሰዎች ያጠቃልላል። ጢሞቴዎስ ለአገልጋይነት ሲሾም ገና ለጋ ጎልማሳ ምናልባትም በሰላሳዎቹ አጋማሽ ወይም ከዚያ በታች እንደሆነ ይገመታል (1ጢሞ.4:12)።

ከዕድሜ አኳያ መነሳት የሚገባው አንድ ጥያቄ ቢኖር የተጠራው ሰው የተጠራበትን አገልግሎት በሚገባ ማከናወን ይችላል ወይ? የሚል ነው። ተጠሪው የተጠራበትን አገልግሎት በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን በሚያስችለው ዕድሜ ላይ ከሆነ መቀበሉ ችግር ላይኖረው ይችላል። ነገር ግን ከጥሪው በኋላ የተጠራውን ሰው አሰልጥኖ ማስማራትን የሚጠይቅ ከሆነ ቤተክርስቲያን ለብዙ ጊዜ ሊያገለግላት በማይችል ሰው ላይ ያላትን ነገር ማባከን ይገባታልን? የሚለው ጥያቄ ከዕቅድና ከሥነምግባር አኳያ ተገቢውን ምላሽ ሊያገኝ ይገባል።

ከዚሁ ጋር አብሮ የሚነሳው ሌላው ነገር ደግሞ የዕድሜ ተፈላጊነት እንደ አገልግሎት መስኩና እንደ አካባቢው ሁኔታ ይወሰናል። ለአንዳንድ የአገልግሎት መስኮች ለምሳሌ አዳዲስ ቦታዎች በመሄድ ወንጌልን ማሰራጨት ለወጣቶቹ ቀላል ሲሆን የቤተክርስቲያን አስተዳደር ደግሞ ለሽማግሌዎቹ ቢሆን የበለጠ ፍሬያማ መሆን ይቻላል። ስለዚህ እነዚህን ሁኔታዎች ማየት ይጠቅማል። አካባቢን በተመለከተ ደግሞ

በብዙ የሀገራችን ክፍሎች ወጣት የሆኑ ሰዎች እንደ ልጅ ስለሚቆጠሩ መልካም ነገር እንኳ ቢናገራቸውም ተቀባይነታቸው እምብዛም ነው። ስለሆነም ለባህላዊ ነገር ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። ይህ ማለት ግን ባህላዊውን ነገር በመደገፍ ሽበት ያላቸውን እንጂ ወጣቶችን ለአገልግሎት መጥራት የለብንም ማለት ሳይሆን አውዱን በማጥናት በጥበብ መሥራት መልካም እንደሆነ ለማሳየት ነው።

ከጾታ አኳያስ እግዚአብሔር ወንዶችን ወይስ ሴቶችን ለአገልግሎት ይጠራል? በመሠረተ አሳብ ደረጃ እግዚአብሔር ወንዶችንም ሆነ ሴቶችን ለአገልግሎት ይጠራቸዋል። እግዚአብሔር ሲጠራ ጾታን ብቻ እንደመሥፈርት በመውሰድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት አያደርግም። ሁለቱንም የፈጠራቸው እርሱ ስለሆነ እግዚአብሔር ለአንዳቸው አያዳላም። ነገር ግን እግዚአብሔር የወንዶችንና የሴቶችን የተፈጥሮ ጠንካራና ደካማ ጎን ስለሚያውቅ ለአገልግሎት ሲጠራቸው በየትኛው አገልግሎት ቢሰማሩ ስኬታማ አገልግሎት መስጠት እንደሚችሉ ስለሚያውቅ አንዳቸውን ለአንድ ዓይነት ለሌላው ዓይነት ደግሞ ሌሎቹን ሊጠራ ይችላል።

ሴቶች ከወንዶች እኩል በእግዚአብሔር ቤት እንዳያገለግሉ ያደረጋቸው የእግዚአብሔር ሴቶችን ለአገልግሎት አለመጥራት ሳይሆን የባህል ጉዳይ ነው። ኅብረተሰቡ ለሴቶች ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ስለሆነ ሴቶች የእግዚአብሔርን ሥራ በኃላፊነት እንዲሠሩ አገልግሎት ቤተክርስቲያን አትሰጣቸውም። ይህ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ይታያል። በክርስቶስ አካል ውስጥ ወንዶችና ሴቶች እኩል ሚና ካላቸው እግዚአብሔር ለወንዶች መንፈሳዊ ስጦታ ሰጥቶ ለሴቶች የማይሰጥበት ምክንያት አይኖርም። እግዚአብሔር ጠርቶአቸው ለአገልግሎት የሚያስፈልጋቸውንም ጸጋ ሲሰጣቸው ሴቶችን ለአገልግሎት(በተለይም የወንዶች በሚባሉ ሥፍራዎች ለምሳሌ ሽማግሌ፣ መጋቢ፣ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ፣ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን አስተማሪ... አደርጎ መሾም) በቤተክርስቲያን ዘንድ ይፈራል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳልሆነ ይሰበካል። ስለዚህ ሴቶች ዲያቆን፣ ዘማሪ፣ የልጆች የሰንበት ትምህርት አስተማሪ፣ አልፎ አልፎ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት አስተማሪ እና በመሳሰሉት አገልግሎቶች ብቻ እንዲያገለግሉ ይፈቀድላቸዋል።

እግዚአብሔር ስለመንፈስ ቅዱስ መምጣት በብሉይ ኪዳን ሲናገር "መንፈሴን በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፣ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልምን ያልማሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፣ ደግሞም በዚያ ወራት በወንዶችና ሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ" (ኢዩ.2:28-29) ብሏል።... እግዚአብሔር በሰዎች መካከል በጾታ፣ በዕድሜና በማህበራዊ ኑሮ ደረጃ ልዩነት ሳያደርግ የእርሱ የሆኑትን ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ይሞላቸዋል። ይህ መንፈስ ወደ እያንዳንዱ ሰው በሚመጣበት ጊዜ የተለያዩ ሥራዎችን በሕይወታቸው በኩል ይሠራል። የእግዚአብሔር ባሪያ የተባሉና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልተው ተልዕኮውን የሚፈጽሙ ሰዎች ወንዶችም ሴቶችም እንደሆኑ ይናገራል (2:29)። የዚህ ትንቢት ፍጻሜ ሲጀመር

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል የሚወክሉ ነበሩ (ሐዋ.1፡12-17፤ 2፡16-21)።

እግዚአብሔር ለድነት ሲጠራ ሰዎችን ሁሉ ይጠራል። እግዚአብሔር ለድነት ጥሪ ሲያቀርብ በዘር፣ በቋንቋ፣ በጾታ፣ በትምህርት ወይም በኑሮ ደረጃ አድልዎ ሳያደርግ ሁሉንም ሰው ይጋብዛል። ወደ ቤተክርስቲያን ከመጡም በኋላ እግዚአብሔር ለወንድም ሆነ ለሴት ልጆቹ የሚያስፈልጋቸውን ጸጋ በመስጠት በአካሉ ውስጥ በተሰጣቸው ስጦታ እንዲያገለግሉ አድርጓል። በአንድ በኩል እግዚአብሔር ለሴቶችም ቤተክርስቲያንን ያገለግሉ ዘንድ ጸጋን እንደሰጣቸው እየታወቀ በሌላ በኩል ደግሞ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ እንዲሆኑ አይጠራቸውም ብሎ መናገር ከራስ ጋር መጋጨት ነው።

የሴቶችን የሙሉጊዜ የወንጌል አገልጋይነት ጥሪን በተመለከተ ሁለት አሳቦችን መናገር ይቻላል። የመጀመሪያው እግዚአብሔር ወንዶችን እንጂ ሴቶችን ለሙሉጊዜ የወንጌል አገልጋይነት አይጠራም ብሎ ስለሚያስቡ የቤተክርስቲያን መሪዎች ለሴቶች የወንጌል አገልጋይነት ጥሪ ሥፍራ አልሰጡም ማለት ነው። በዚህ አሳብ መሠረት የቤተክርስቲያን መሪዎች የሴቶች ጥሪ የእግዚአብሔር አሳብ አለመሆኑን ተረድተዋል ማለት ነው። ሁለተኛው አሳብ ደግሞ እግዚአብሔር በወንድና በሴት መካከል ልዩነት ሳያደርግ ሁለቱንም ለወንጌል አገልጋይነት ይጠራቸዋል። ነገር ግን የቤተክርስቲያን መሪዎች በወንዶች የበላይነት የሚያምኑ ስለሆኑ ለሴቶች ትኩረት አልሰጡም ማለት ነው። ይህ ደግሞ የቤተክርስቲያን መሪዎች የእግዚአብሔርን አሳብ በትክክል አለመረዳታቸውን ያመለክታል።

እግዚአብሔር በጾታ እኩልነት ቢያምንም ለወንድና ሴት ተመሳሳይ ሚና አልሰጣቸውም። የወንድ ሚና ከሴት ሚና የተለየ ነው። ወንዶችና ሴቶች ተመሳሳይ ስጦታና ሚና አላቸው ማለት ሚዛናዊ አሳብ አይመስልም። እንደዚሁም በወንድ የትምክህተኝነት ስሜት ተነድፎ ሴቶች በእግዚአብሔር ቤት እርሱ በሰጣቸው ስጦታ እንዳያገለግሉ ማገድ ትክክል አይደለም። ቤተክርስቲያን በጾታ ሳይሆን ማን ጥሪ አለው? በማለት የተጠሩ ወንዶችና ሴቶችን ለጌታ ሥራ ማሰማራት ይገባታል።

ቤተክርስቲያን ለማሰማራት በእግዚአብሔር አሳብ መሠረት የአገልጋዮችን ስምሪት ለማድረግ ከባህል ተጽዕኖ መውጣት ይኖርባታል። በአንዳንድ ሁኔታ ቤተክርስቲያን ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ለባህል ትኩረት በመስጠት እንደ እግዚአብሔር አሳብ ለመሥራት ድፍረት ታጣለች።

እንግዲህ እግዚአብሔር ከምዕመኑ መካከል በተለየ ሁኔታ የእርሱን ሥራ እንዲሠሩ የጠራቸውን ሰዎች ወደ አገልግሎት ሲያሰማራቸው ለምን ያህል ጊዜ እንዲያገለግሉት ይፈልጋል? የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ከአገልግሎቱ ጡረታ መውጣት አለበት ወይስ እስከሞት ድረስ ማገልገል ይጠበቅበታል? እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራው አገልጋይ ለወንጌል ሠራተኛነት ለጊዜያዊነት መቀጠር መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን? ለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ስለእነዚህ ጥያቄዎች ምን ይላል? ተከታዩ ምዕራፍ ምላሹን ይዞ ቀርቧል።

## ጥያቄዎች

1. ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር የደካሞች አምላክ እንደሆነ የሚያስቡት ለምንድነው?
2. አንድ ሰው ትምህርት ወይም ሥራ ካልተሳካለት ወይም እድሜ ከተሳካለት በኋላ ወደ ቤተክርስቲያን አገልግሎት ቢመጣ ስለጥሪው ትክክለኛነት ምን ያህል ግምገማ ይደረጋል?
3. ወጣቶችን ወደ አገልግሎት ማስገባት ወይም መከልከል በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ምን አዎንታዊና አሉታዊ ጎን አለው?
4. እግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶችን ለአገልግሎት የሚጠራ ከሆነ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሴት አገልጋዮች ቁጥር ለምን ጥቂት ሆነ?
5. በአገልግሎት ጥሪ ተግባራዊነት ላይ ባህል ያለው ተጽዕኖ ምንድነው?
6. ባልና ሚስት ለአገልግሎት አንድ ላይ ቢወጡ ያለው ጉዳትና ጥቅም ምንድነው?

## እግዚአብሔር ሰዎችን ለምን ያህል ጊዜ እንደሚጠራ ማወቅ

የሙሉጊዜ አገልግሎት ማለት ሌሎች ሥራዎችን በመተው የወንጌልን ሥራ ብቻ መሥራት ነው ወይስ እስከ ሞት ድረስ የተጠሩበትን አገልግሎት ማገልገል ነው? አገልጋይ ሁሉ ለሙሉጊዜ አገልግሎት ከተጠራ በጊዜያዊነት ማገልገል አይገባውም ማለት ነውን? ለሙሉጊዜ አገልግሎት የተጠሩ አገልጋዮችን ጡረታ እንዲወጡ ማድረግ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ ነውን? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

በተለምዶ እግዚአብሔር ሰዎችን ለወንጌል አገልግሎት ሲጠራ ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ይጠራል ብለን እንናገራለን። ይህ አባባል ምን ማለት ነው? ለዚህ ጥያቄ ሁሉን የሚያስማማ መልስ ማግኘት ቢያስቸግርም ግንዛቤ ሊያስጨብጡን የሚችሉ አሳቦችን ማስቀመጥ ይቻላል። አንዳንዶች የሙሉ ጊዜ አገልግሎት የሚባለው "አንድ ሰው ሥራዬ ብሎ የያዘው ሥራን የሚያመለክት ነው" ይላሉ። ሌሎች ደግሞ "ሙሉ ጊዜውን፣ ኃይሉን፣ ጉልበቱንና እውቀቱን የሰጠበት ሥራ ወይም አገልግሎት ነው" ይላሉ። በዚህ መሠረት የሙሉ ጊዜ አገልግሎት የሚባለው አንድ ሰው ዘወትር የሚሠራው ሥራ ነው።

አንድ ሰው መተዳደሪያው ግብርና ከሆነ የሙሉጊዜ አገልጋይ ሊባል ይችላል ማለት ነውን? አሳቡ እንዲህ አይደለም። ሥራው ማንኛውም ዓይነት ሥራ ሳይሆን የወንጌል አገልግሎት መሆን አለበት። አንድ ሰው ሙሉጊዜውን የወንጌል ሥራ የሚሠራ ከሆነ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ነው ማለት ይቻላል። በዚህ አሳብ መሠረት ለመተዳደሪያቸው ሌላ ሥራ እየሠሩ በትርፍ ጊዜያቸው የወንጌልን ሥራ የሚሠሩ የሙሉጊዜ አገልጋዮች አይባሉም።

አንዳንዶች ደግሞ "ሙሉ ጊዜ አገልግሎት የሚባለው አንድ ሰው ከአንድ ሠራተኛ የሚጠበቀውን ሰዓት በወንጌል አገልግሎት ላይ ተሰማርቶ ሲያገለግልና ላገለገለበት ጊዜ ቀለብ ሲሰጠው ነው" ይላሉ። ይህ ማለት መተዳደሪያው የወንጌል አገልግሎት የሆነ ሰው የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ይባላል ማለት ነው። ስለአገልግሎቱ፣ በቤተክርስቲያን የወር ቀለብ የማይሰጠው ሰው የበጎ ፈቃድ አገልጋይ እንጂ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ አይባልም።

ሌሎች ደግሞ "የሙሉጊዜ አገልግሎት አንድ ሰው ዕድሜ ልኩን ለማገልገል የተጠራበት የሥራ መስክ ነው" ይላሉ። አንድ ሰው ይህን አገልግሎት ከጀመረ እስከ ዕድሜው ፍጻሜ ድረስ በዚያ አገልግሎት ውስጥ ጸንቶ መቆም እንደሚጠበቅበትም ይጠቁማል። ስለዚህ በዚህ መልኩ ሲታይ እንደ ሌሎች ሥራዎች አይደለም ማለት ነው። የሕይወት ዘመን ቋሚ ሥራ ነው። አንድ ሰው ሲፈልግ የወንጌል አገልጋይ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ሌላ ሥራ የሚቀይር ከሆነ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ አይባልም ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች ሙሉጊዜ የሚለውን ሙሉ ዕድሜ በሚል አሳብ ተክተውታል።

እንዲሁም አንዳንዶች ደግሞ "የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ማለት ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት ሙሉጊዜውን በመስጠት በአጥቢያ ወይም በአጠቃላይ ቤተክርስቲያን ሥር ሆኖ የሚያገለግል ሰው" እንደሆነ ይናገራሉ። ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ጥሪ ኖሮት በተጠራበት የአገልግሎት መስክ ተሰማርቶ እግዚአብሔር እርሱ እንዲሰራው ያዘዘውን አገልግሎት የሚያገለግል ነው።

የሙሉ ጊዜ አገልግሎት የሚለው አሳብ እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ለምን ያህል ጊዜ ይጠራል? ለሚለው ጥያቄ በቂ ምላሽ የሚሰጥ አይመስለኝም። ምክንያቱም ቃሉ አሻሚ ስለሆነ የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መልክ ይተረጉሙታል። ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ለዚህ በቂ ምላሽ ይሰጥ እንደሆነ አብረን እንመልከት።

በብሉይ ኪዳን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ከተጠሩት ሰዎች መካከል ካህናት ይገኙበታል። ካህናት የሚሆኑ ደግሞ የሌዊ ልጆች ነበሩ። እነዚህ የሌዊ ልጆች በእግዚአብሔር ቤት ከማገልገል ውጭ ሌላ ሥራ አልነበራቸውም። ጥሪያቸው ለሕይወት ዘመን እንዲሁም ከልጅ ወደ ልጅ የሚተላለፍ ሁኔታ ነበረው። ሌዋውያን ለኑሮአቸው የሚሆነውን ነገር የሚያገኙት የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር ጎተራ ከሚያመጣው በኩራት፣ አሥራትና ስጦታ እንደሆነ ተደንግጎላቸዋል። ይህን ቀለባቸውን እያገኙ በቤተመቅደስ ውስጥ ዘወትር እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ማገልገል የዕለት ተግባራቸው እንደነበር እንመለከታለን።

አሮን በክህነት እግዚአብሔርን ያገለገለው እስከሚሞትበት ወቅት ነበር። እርሱ ሊቀካህን ስለነበር ከእርሱ ጋር እግዚአብሔርን የሚያገለግሉ ሌሎች ካህናት ነበሩ። አሮን ዕድሜው እያረጀ ሲመጣ እርሱን የሚተካ ሌላ ካህን ተዘጋጅቶ ነበር። ያውም አልዓዛር የሚባል ልጁ ነበር። አሮን ከመሞቱ በፊት አልዓዛር ሊቀ ካህን ሆኖ ተሾመ። አሮንን ከክህነት አገልግሎቱ የለየው ሞት ነበር (ዘኁ.20:22-28)።

ኤልሳዕም እግዚአብሔርን ያገለገለው እስኪሞት ድረስ ነበር። እግዚአብሔር አሁን አርጅተሃል ብሎ በእርሱ ከመጠቀም አልተቆጠበም። በበሽታ ታሞ አልጋ ላይ ተኝቶ ሲሰቃይ እንኳ እግዚአብሔርን ያገለግል ነበር (2ነገ.13:14፣20)። ከእግዚአብሔር አገልግሎት ጡረታ የሚያስወጣው የዕድሜ እርጅና ሳይሆን የእግዚአብሔር በሰው ሕይወት መሥራት ማቆም ነው። እግዚአብሔር በአገልጋዩ ሕይወት በኩል መሥራቱን እስካላቆመ ድረስ ተፈላጊነቱ አይቀንስም። የጌታ ኃይል ከእርሱ ጋር ከሆነ ደግሞ አዳባባይ መውጣት ባይችል እንኳ ሰዎች አልጋው ላይ እያለ ይፈልጉታል።

እግዚአብሔር ግን ይበቃቸዋል ሲላቸው አገልጋዮች ማቆም አለባቸው። እግዚአብሔር አሮንን ይበቃሃል ሲለው አሮን አገልግሎቱን ወደሚቀጥለው አገልጋይ አስተላለፈ። ዛሬም የእግዚአብሔር አገልጋዮች እንደ አሮን የክህነት ልብሳቸውን አውልቀው ለሚተካቸው አገልጋይ ማልበስ አለባቸው። አገልግሎቱ የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ አይደለም። ይህን አስተውሎ አገልግሎትን ለሚቀጥለው አገልጋይ ማስተላለፍ ትልቅ አስተዋይነትና ክብርን የሚያመጣ ነው። የእግዚአብሔር አገልጋዮች አገልግሎቱ የእግዚአብሔር እንደሆነ በሚገባ ስለሚያውቁት የተሰጣቸውን

የአገልግሎት ድርሻና ኃላፊነት የራሳቸው እንደሆነ አድርገው ሙጭጭ ብለው አይዙም።

በአዲስ ኪዳንም ስንመለከት እግዚአብሔር ሰዎችን የሚጠራው ለዕድሜ ልክ አገልግሎት ነው እንጂ በኮንትራት ወይም በጊዜያዊ ሠራተኛነት አይደለም። አገልጋዮቹ ራሳቸው በዓለም ምኞትና አሳብ ተስበው የተጠሩበትን ተልዕኮ ካልተው በስተቀር እግዚአብሔር "ያብቃችኋል" ብሎ አገልግሎት ያስቆማቸው አገልጋዮች እንደነበሩ በአዲስ ኪዳን አናነብም።

በእግዚአብሔር የተጠሩ አገልጋዮች ዕድሜ ልካቸውን ማገልገል ይችላሉ ስንል ግን ምን ዓይነት አገልግሎት ማገልገል ይችላሉ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። በወጣትነታቸውና በጎልማሳነት ዕድሜያቸው ሲያገለግሉ የነበረውን ዓይነት አገልግሎት ላያገለግሉ ይችላሉ።

እግዚአብሔር ሰዎችን የሚጠራው ለዕድሜ ልክ አገልግሎት እንደሆነ ከተቀበልን ጡረታ መውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለመሆኑ እንዴት ልንመለከተው ይገባናል? እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ከጠራቸው ዕድሜ ልካቸውን ሊጠቀምባቸው ይችላል። አንድ ሰው እግዚአብሔር ከጠራበት አገልግሎት ጡረታ መውጣት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም። ነገር ግን ለተተኪ አገልጋዮች ሥፍራን ከመልቀቅ አኳያ ጡረታ ማውጣት፣ የሚሰፈረውን ቀለብ መቀነስና ለሌሎች እንዲውል ማድረግ ክፉት ላይኖረው ይችላል። የተጠራ አገልጋይ ከተጠራበት አገልግሎት ሳይሆን ከሚሠራበት መሥሪያ ቤት ጡረታ ይወጣል።

በአሁኑ ዘመን በሀገራችን ቤተክርስቲያን አስቸጋሪ እየሆነ የመጣው ነገር ጥሪ ያላቸው የበሰሉ አገልጋዮች በጡረታ ከአገልግሎት መገለላቸው ሳይሆን የአገልግሎት ቦታውን በመያዝ ተተኪ የወንጌል አገልጋዮችን ሳያፈሩ ለዘላለም እንደሚኖሩ አድርገው ማሰባቸው እና ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጡረታ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔር ጠርቶናል ብለው ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት በአገልግሎት ላይ ተሰማርተው እውነተኛ ጥሪ ያላቸውን ወጣቶች እንዳያገለግሉ እንቅፋት የሚሆኑ አገልጋዮች መታየታቸው ነው። በአንዳንድ ቦታዎች ቤተክርስቲያን የጡረተኞች መጠሪያ ጣቢያ ትመስላለች።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ የተጠሩት ሰዎች ሙሉ የሕይወት ዘመናቸውን የወንጌል አገልግሎት እንዲያገለግሉ ይፈልጋል። እግዚአብሔር ሰዎችን ለኮንትራት አይጠራም። ሆኖም ቤተክርስቲያን የእያንዳንዳቸውን ጥሪ እውነተኛነት ለማረጋገጥ ለወንጌል ተጠርተናል የሚሉትን ሰዎች በጊዜያዊነት የወንጌልን ሥራ እንዲሠሩ ማስማራት ትችላለች። ይህም ሰዎቹ በእርግጥ ጥሪ እንዳላቸው ለማረጋገጥና በአገልግሎታቸው ፍሬያማ መሆናቸውን ለማጤን ነው። ጥሪው ሲታወቅ የኮንትራቱን ሁኔታ ወደ ቋሚነት መለወጥ ይገባታል።

ሰዎች በሚያስደንቅ ወይም ተራ በሚባለውም መንገድ በእግዚአብሔር ሲጠሩ በእርግጥ እግዚአብሔር እንደጠራቸው የሚያውቁት በሕይወታቸው ምን ሲከናወን ነው? ሌሎች ሰዎችስ እነዚህ ሰዎች በትክክል በእግዚአብሔር ስለመጠራታቸው እንዴት ሊያውቁ ይችላሉ?

## ጥያቄዎች

1. የሙሉ-ጊዜ አገልግሎት ማለት ምንድነው? የእግዚአብሔር ቃል የሚለውንና ቤተክርስቲያን የምትለውን አነጻጽር።
2. አማኞች ጥሪ አለን ብለው ሲመጡ በኮንትራት በወንጌል ሥራ ላይ ማስማራትና መገምገም ትክክል ነውን? ለምን? ቃሉስ ምን ይላል?
3. የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች እስከ ስንት ዓመታቸው ማገልገል አለባቸው? በጡረታ መውጣት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውን? ጥቅሙንና ጉዳቱ ምንድነው?

# 6

## የአገልግሎት ጥሪ መለያ ምልክቶችን አጥርቶ መለየት

አንዳንድ ሰዎች ስለመንፈሳዊ ሥራዎች ሲሰሙ ወይም መንፈሳዊ ሥራዎችን ሠርተው ደስ ደስ ሲላቸው እግዚአብሔር ለሙሉጊዜ የወንጌል አገልጋይነት የጠራቸው እንደሆነ ያስባሉ። ሌሎች ደግሞ ቃሉን ሲያጠኑ ልዩ መረዳት ሲያገኙ እንዲሁም ሌሎች ደግሞ ሲጸልዩ መልዕክት በማግኘት እግዚአብሔር እንደጠራቸው ይናገራሉ። ለመሆኑ አንድ ሰው ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለሙሉጊዜ አገልጋይነት መጠራቱን እንዴት ሊያውቅ ይችላል? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የአገልግሎት ጥሪ መለያ ምልክቶችን እንመለከታለን።

አንድ ሰው እግዚአብሔር እንደጠራው እንዴት ይታወቃል? የቤተክርስቲያን መሪዎች አንተ ወይም አንቺ ጥሪ አለሽ ብለው አንዱን ለመቀበልና ሌላውን ለመተው የሚጠቀሙበት መሥፈርቶች ምንድናቸው? እነዚህ መሥፈርቶችስ ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው?

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ እግዚአብሔር ለአገልግሎት የጠራቸውን ሰዎች ስንመለከት ማንኛውም የእግዚአብሔር ጥሪ በውስጡ አራት ዋና ዋና ነገሮችን እንደያዘ እንመለከታለን። ይህ ማለት አንድ ሰው ከእግዚአብሔር የሆነ ጥሪ ሲያገኝ እነዚህ አራቱ ነገሮች በሕይወቱ ወይም በሂደቱ ሊታዩ ይገባቸዋል።

### 1. ከእግዚአብሔር ቅድስና ጋር መገናኘት

የእግዚአብሔር ጥሪ ለሰዎች የሚመጣው የእግዚአብሔር ቅድስና ሲገለጥ ነው። እግዚአብሔር የጥሪውን መልዕክት ከማሰማቱ በፊት ራሱ ማን እንደሆነ በትክክል ያስተዋውቃቸዋል። ስለተልዕኮ ከመነጋገር በፊት ማንነቱን መግለጽ ይቀድማል። እግዚአብሔር ሰዎቹ ከዚህ በፊት ተለማምደውት በማያውቁት ሁኔታ የራሱን ቅድስናና ታላቅነት ያሳያቸዋል። እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ማለትም ከኃጢአትና ከክፉ ነገር ፍጹም የተለየ እና በጽድቅ ባህርይ የተሞላ አምላክ መሆኑን ይገልጥላቸዋል።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራቸው አስቀድሞ የራሱን ማንነት የሚገልጥላቸው ተጠሪዎቹ የጠራቸውና ለአገልግሎት የሾማቸው የሚያገለግሉት አምላክ ቅዱስና ታላቅ መሆኑን ዘወትር እንዲያስታውሱት ነው። እግዚአብሔር ማን እንደሆነ ለሰዎች ከማሳየቱ በፊት ሰዎችን አይጠራም፤ ምክንያቱም የጠራቸው ማን እንደሆነ ያላወቁ ሰዎች ከጠሪው ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖራቸውና እርሱ እንደሚፈልገው ሊያገለግሉ እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕዝብ መታነጽ ምክንያት ሊሆኑ አይችሉም። የእግዚአብሔር ራሱን ለሚጠራቸው ሰዎች ማስተዋወቅና

የእነርሱም ደህን መለማመድ ከሌሎች ሰዎች በተለየ ሁኔታ እግዚአብሔርን እንዲያውቁና ለእርሱ እንዲገዙ ያደርጋቸዋል።

እግዚአብሔር ለሙሴ ሲገለጥና ሲያናግረው በመጀመሪያ የተናገረው "*ወደዚህ አትቅረብ፣ አንተ የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ*" (ዘጸ3:5) በማለት ነበር። ሙሴ በዚያ ቦታ ምናልባት ብዙ ጊዜ ሳይመላለስበት አይቀርም። አሁን ያን ቦታ ቅዱስ ያደረገው የቅዱሱ እግዚአብሔር መገኘት ነው። እግዚአብሔር ቅዱስ መሆኑን ለሙሴ በመግለጽ ሰዎች ደህን ቅዱሱን እግዚአብሔር ለመቅረብ ማድረግ የሚገባቸው ነገር እንዳለ አመለከተው። ሙሴ ጫማውን ከእግሩ በማውጣት፣ ለእግዚአብሔር ቅድስና ክብርን ሰጠ። በእግዚአብሔር ፊት በትሕትና ቀረበ። ከዚያም እግዚአብሔር መናገር ሲጀምር ፊቱን እንደሸፈነ ተጠቅሷል (ዘጸ3:6)። ሙሴ እግዚአብሔር በደፋ ሲገለጥለት ያወቀው በቅድስናው ስለሆነ በሕይወት ዘመኑ ቅዱሱን እግዚአብሔርን ሲፈራና ሲያከብረው ኖረ።

ጌዴዎን ተገልጦለት የጠራው እግዚአብሔር ስለመሆኑ ተጠራጥሮ ነበር። እግዚአብሔር ግን በምልክት እርሱ መሆኑን ሲያስረግጥለት "*አቤቱ አምላኬ ሆይ ወዮልኝ የእግዚአብሔርን መልአክ ፊት ለፊት አይቻለሁና*" (መሳ6:22) በማለት ተናገረ። እያናገረው ያለው ማን እንደሆነ በእርግጠኛነት ሲያውቅ ፈራ። ጌዴዎን ደህን እግዚአብሔርን በማየቱ የሚሞት መሰለው። እግዚአብሔር ሲገለጥ ግን ክብሩን ለማሳየት እንጂ ለመግደል እንዳልሆነ በማሳየት ሕይወቱን በሰላም ሞላው። ከዚያም ጌዴዎን እግዚአብሔር የሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም እንደተነሳ እንመለከታለን።

ዛሬም እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራቸው ቅድስናውን ይገልጥላቸዋል። ደህን ያላዩ አገልጋዮች እግዚአብሔርን እንደ ጓደኛቸው ወይም እንደማይናገር አምላክ በመቁጠር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት ይመሰርታሉ። በዚህ ሁኔታ ሲመላለሱ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ይጋጫሉ። ከእግዚአብሔር ጋር መጋጨት ደግሞ የንስሐ ልብ ከሌለ ለመቅሰፍት አሳልፎ ይሰጣል።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ሁከትን የሚፈጥሩ አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ጋር የትውውቅ ጊዜ ያልነበራቸው ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝተው ከተዋወቁ በኋላ በሕይወታቸው መንፈሳዊ ድንዛዜ ያጋጠማቸው፣ የተለያዩ ዓለማዊ ምኞቶች የተጠናወታቸው እና እግዚአብሔርን በታማኝነት ከማገልገል የግል ጥቅምን ወደ ማሳደድ ዘወር ያሉ አገልጋዮች ናቸው። እነዚህ ቃልኪዳናቸውን ያልጠበቁ ወይም በእግዚአብሔር ሳይሆን ያለጥሪያቸው በቤተክርስቲያን መሪዎች ብቻ የተሾሙ አገልጋዮች ናቸው።

እግዚአብሔር ለሚጠራቸው ሰዎች በሚገለጥበት ጊዜ ቅድስናውና ታላቅነቱን ብቻ ሳይሆን ስሙንም ጭምር ይገልጣል። የእግዚአብሔር ስም የማንነቱ መግለጫ ነው። አንዳንድ ጊዜ ከሰዎች ጋር ተገናኝተን ብዙ ጊዜ አሳልፈን ስማቸውን ግን ሳንጠይቅ ወይም እነርሱም ሳይነግሩን ይቀሩና በኋላ ለሌሎች ሰዎች «ከእንዲህ ዓይነት ሰው ተገናኝተን አብረን ነበርን» ስንል «ስሙ ማን ይባላል? ማን ትባላለች?»

ሲሉን «አናውቀውም» ማለት እፍረት ነው። ከሰዎች ጋር ስንተዋወቅ ስማቸውን የማናውቅ ከሆነ ሙሉ መተዋወቅ አይሆንም። ሰዎቹን የምናውቃቸው በምልክት እንጂ በስም ካልሆነ ለሌሎች ለመግለጽ እንዲሁም ሰዎቹን በምንፈልግበት ጊዜ ለመጥራትም አንችልም። ስለዚህ በስም መተዋወቅ መልካም ነው።

እግዚአብሔር ለሙሴ በተገለጠበት ጊዜ ራሱን ሲያስተዋውቀው "እኔ የአባትህ አምላክ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ" (ዘጸ3፡6) በማለት ነበር። ሙሴ ይህ እየናገረው ያለው አምላክ ማን እንደሆነ ማወቅ አላስቸገረውም። ምክንያቱም ከልጅነቱ ጀምሮ ስለአብርሃም፣ ስለይስሐቅና ስለያዕቆብ አምላክ ከእናቱ ተምሯል። እግዚአብሔር ሙሴ ከሚያውቀው ታሪክ በመነሳት ራሱን ስለገለጠለት ሙሴ የሚያናግረው እግዚአብሔር እንግዳ እንዳልሆነ ተረድቷል። ግን ሙሴ የበሰለ ሰው ስለነበር እግዚአብሔር ከታሪክ ጋር አያይዞ ራሱን ቢገልጽለትም የሚጠራበት ስሙ ማን እንደሆነ ጠየቀው። ምክንያቱም ተልዕኮውን ለመፈጸም በሚሄድበት ጊዜ የጠራውን አምላክ በትክክለኛ ስሙ የማያውቅ ከሆነ የእስራኤል ሕዝብ ሊቀበለው እንደማይችል በሚገባ ተረድቷል። እግዚአብሔርም ስሙን ያለና የሚኖር በማለት ነገረው። እግዚአብሔር ለሙሴ የሚጠራበትን ትክክለኛ ስምና በታሪክ ውስጥ የሚታወቅበትን ስሙን በመግለጽ ሙሴን ላከው።

ዛሬም በእግዚአብሔር የሚጠሩ ሰዎች የጠራቸው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በስሙ ሊያውቁት ይገባል። እግዚአብሔር በግላቸው ተገናኝቶ ሲጠራቸው ራሱን ማን ብሎ ነው የገለጠላቸው የሚለውን ለራሳቸውም ማወቅ ለሌሎችም ማስረዳት መቻል ይገባቸዋል። ይህ በእውቀት ደረጃ እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ስለራሱ የተናገራቸውን የማንነቱ መግለጫዎችን መናገር መቻል ሳይሆን በቃሉ የተገለጠላቸው እግዚአብሔር በሕይወታቸው ውስጥ በራሳቸው አውድ በልዩ ሁኔታ ተገልጦ ሲረዳት የተሰጡት ስም ነው። ለእኔ እግዚአብሔር... ወይም የተገለጠልኝ እግዚአብሔር... ብለው መናገር መቻል ነው። እግዚአብሔር በተገለጠላቸው ሁኔታ ግን በቃሉ ውስጥ ከተጠቀሰው ባህርያቱ ጋር በማይጋጭ መልኩ መግለጥ መቻል እግዚአብሔርን በግላቸው ስለመገናኘታቸውና ማንነቱን ስለመረዳታቸው አጥጋቢ ማስረጃ ይሆናል።

## 2. የራስን ማንነት (ደካማ ጎን) ማየት

በእግዚአብሔር የተጠሩ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት ተገናኝተው ጥሪው ሲነገራቸው ስለራሳቸው ሁኔታ ማየት ይጀምራሉ። ከእግዚአብሔር ታላቅነትና ክብር የተነሳ ለጥሪው ብቃት እንደሌላቸው ይሰማቸዋል። ሁሉን ለሚችልና ታላቅ ለሆነው ለእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን እንደማይችሉ በማሰብ ቶሎ እሺ ብለው ጥሪውን ለመቀበል ይቸገራሉ።

ሙሴ እግዚአብሔር ሲጠራውና የጠራበትን ዓላማ ሲነግረው "ወደ ፈርዖን የምሄድ የእስራኤልንም ልጆች ከግብጽ የማወጣ እኔ ማን ነኝ? (ዘጸ3፡11) በማለት መለሰለት። ይህ ሙሴ በእግዚአብሔር ለመላክ ላሰበበት

ዓላማ ፈቃደኛ አለመሆኑን ለመግለጽ ያቀረበው የመጀመሪያው ምክንያት ነበር። \ ሙሴ ወደ ግብጽ ንጉሥ በመሄድ በባርነት ሥር ያሉትን የእስራኤል ሕዝብ ለማውጣት ምንም አቅም እንደሌለው ተገነዘበ። ሙሴ ራሱን ሲያይ ለዚህ ተልዕኮ ብቁ እንዳልሆነ አሰበ።

ሙሴ እንዲህ ማሰቡ ከትሕትና ወይም ከፍርሃት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ሙሴ ከግብጽ ቤተመንግሥት ከወጣ በኋላ በምድያም ምድረ በዳ አርባ ዓመት በጎችን ሲጠብቅ ነበር። በእረኝነት ባሳለፋቸው በእነዚህ ዓመታት ትሕትናን በእርግጥ ተምሯል። ስለዚህ ሙሴ ወደ ግብጽ ለመሄድ እኔ ማን ነኝ? ማለቱ የትሕትና ምልክት ሊሆን ይችላል። የታላቁን የእግዚአብሔርን ተልዕኮ ለመፈጸም መሳሪያ ለመሆን ልመረጥ አይገባኝም ማለቱ ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሙሴ እምቢ ማለቱ ፍርሃቱን መግለጹ ይሆናል። ከዚህ በፊት በውስጡ ከነበረው ቅንዓት የተነሳ የእስራኤልን ልጆች ለማዳን የወሰደው እርምጃ አልተሳካለትም። እርምጃው ለስደት አሳልፎ ሰጠው፣ በምድረ በዳ አንከራተተው። ስለዚህ ሙሴ ዳግመኛ ወደዚያ ሁኔታ ውስጥ ለመግባት አልፈለገም ይሆናል። ሙሴ «ወደ ግብጽ ሂድና የእስራኤልን ልጆች ነጻ አውጣ» የሚለውን መልዕክት ሲሰማ በውስጡ «እንደከዚህ በፊቱ ትሸነፋለህ፣ አይሳካልህም» የሚል ድምጽ ተሰምቶት ይሆናል። ሰዎች በራሳቸው ተደጋጋሚ ሙከራዎችን በማድረግ ማድረግ ያሰቡት ነገር ካልተሳካላቸው በሌላ ጊዜ ቢሞክሩት ሊሳካላቸው የሚችልበት ሁኔታ እንኳ ተመቻችቶላቸው እያለ ያንን ነገር እንደገና ለመሥራት ልባቸው አይነሳሳም። በአዕምሮአቸው ውስጥ «አሁንም አይሳካልህም፣ አትሞክር» የሚል ድምጽ ይደውልባቸዋል። ሰዎቹ ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ስለሚያስቡ ከዚያ ነገር ራሳቸውን ያገላሉ። ተመልሰው ወደዚያ አሳብና ድርጊት መግባት አይፈልጉም። ምናልባት ሙሴም ተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ገብቶ ይሆናል።

ከእነዚህም ተጨማሪ ደግሞ ሙሴ እየሠራ ያለው ሥራ ለመሪነት የሚያበቃው ሥራ እንደሆነ አይታሰብም። ሙሴ ለአርባ ዓመት የበጎች እረኛ ነበር። እረኛ ነጻ አውጭና የሕዝብ መሪ ለመሆን ብቃት አለኝ ብሎ አያስብም። ከዚህም በላይ የበጎች እረኛ መሆን በእስራኤል እንጂ በግብጻውያን ዘንድ የተናቀ ሥራ ነበር። ሙሴ እስራኤላዊ ቢሆንም በፈርዖን ቤተመንግሥት ከነበረው ልምምድ በግ እረኝነት የተናቀ ሥራ እንደሆነ በሚገባ ያውቃል። እግዚአብሔር እርሱ ፈርዖን ቤተመንግሥት እያለ ጠርቶት ቢሆን ኖሮ መሪ መሆን ያምርበት ነበር። አሁን ግን የበጎች እረኛ ስለሆነ ለመሪነት እበቃለሁ የሚል አሳብ ከአዕምሮው የተፋቀ ይመስላል። እዚያ እያለ ያልሆነለት አሁን ከበጎች እረኝነት ቢሄድ እንደሚሳካለት ማሰብ ተሳነው። በሰው አስተሳሰብ የሙሴ አሳብ ድጋፍ ሊኖረው ቢችልም ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ችሎታ አኳያ በቂ ምክንያት አይሆንም። ሙሴ ከበጎች እረኝነት ለመሪነት የተማረው ነገር ቢኖርም ልምምዱን እንደቁም ነገር የቆጠረው አይመስልም።

ሙሴ «እኔ ማን ነኝ?» ማለቱ ምን ማለቱ ነው የሚለው ጥያቄው ተገቢ ነበር። እግዚአብሔርም ጥያቄውን አልተቃወመውም፣ ለጥያቄው

ተገቢውን ምላሽ ሰጠው እንጂ። ይህን የእግዚአብሔር ምላሽ በሚቀጥለው አሳብ ሥር እንመለከታለን።

የእግዚአብሔር ጥሪ ጌዴዎን ለሚባል ሰው ሲመጣ ጥሪውን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበረም። እግዚአብሔር "በዚህ በጉልበትህ ሂድ፣ እስራኤልንም ከምድያም እጅ አድን እነሆ ልኬሃለሁ" (መሳ6:14) ባለው ጊዜ ጌዴዎን ለዚህ ተልዕኮ ብቁ እንዳልሆነ ለመግለጽ ጊዜ አልፈጀበትም። ጌዴዎን ለእግዚአብሔር ጥሪ ብቁ እንዳልሆነ ለማስረዳት ኃይል እንደሌለው፣ በወገኑ ደግሞ ከተናቀ ወይም ከተጠቃ ከሁሉም ታናሽ ከሚባለው ከምናሴ ወገን እና ከአባቱም ቤት የሁሉም ታናሽ እንደሆነ ተናገረ (መሳ6:15)። ጌዴዎን እግዚአብሔር ዓይኑን ወደዚህ በሁሉም አናሳ ወደሆነው ሰው ላይ ይጥላል ብሎ ማሰብ አልቻለም። እንደ እርሱ አሳብ እግዚአብሔር የሰው ዓይን የሚጣልበትን እንጂ እንደ እርሱ ተራ የሆነውን ሰው መምረጥ አይገባውም ነበር።

ኤርምያስም እግዚአብሔር ሲጠራው ብቃት እንደሌለው ተሰምቶት ነበር። ኤርምያስ ብቃት እንደሌለው ለማስረዳትነት ያቀረበው ምክንያት ብላቴና መሆኑን ነበር። ኤርምያስ "ወዮ ጌታ እግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም" (ኤር1:6) በማለት ተናገረ። ኤርምያስ ነቢይ ለመሆን የሚያበቃው ምንም ልምምድ አልነበረውም። ስለዚህ ለነቢይነት እንደማይበቃ አሰበ።

በአብዛኛው ወጣት የሕይወት ልምምድ የለውም። ሰዎች ደግሞ ብቃት አለው ብለው የሚያስቡት የሕይወት ልምምድ ያለውን ሰው ነው። እግዚአብሔር ወጣቶችን ቢጠራም ሽማግሌዎች እንደ ጠቢባን በሚቆጠሩበት ኅብረተሰብ ውስጥ ወጣት አገልጋዮች ተቀባይነት ወይም ተሰሚነት ለማግኘት ይቸገራሉ።

*ተሰማ ለአገልግሎት የተጠራው ገና ወጣት በነበረበት ወቅት ነው። የተማረ ሰው ቢሆንም ዕድሜው ከሚያገለግላቸው ሰዎች ያነሰ ስለሆነ ብዙዎች እርሱን እንደ አገልጋያቸው ለመቀበል ይቸገሩ ነበር። ተሰማም ይህ ስለገባው እነርሱ የሚያከብሩአቸውን ሽማግሌዎች ይዘው እየተዘዋወረ ማገልገል ጀመረ። ኅብረተሰቡ ሽማግሌዎች በተሰማ ጎን በማየታቸው ብቻ የእርሱን አገልግሎት እየተቀበሉ መጡ። ከዚያም ተሰማ መልካም ነገር እንዳለው ገባቸው።* በዚህ ዓይነት ባህል ውስጥ ተቀባይነት የሚያስገኘው ሽበት እንጂ ችሎታ ወይም እውቀት አይደለም። ሰዎቹ ከባህላቸው የተነሳ ወጣት አገልጋዮችን ለመቀበል ቢቸገሩም በጥበብ በመጠቀም እግዚአብሔር ወጣትንም ጠርቶ ሊጠቀምበት እንደሚችል ማሳየት የተሻለ ነው።

እንግዲህ አንዳንድ ጊዜ በዕድሜ ወጣት የሆኑና ልምምድ የሌላቸው ወጣቶች የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣላቸው ራሳቸውንም ከመናቅ አኳያ ብቻም ሳይሆን ኅብረተሰቡ ላይቀበለን ይችላል ከሚል ሁኔታም ወደ አገልግሎት ቶሎ ለመግባት ፈቃደኞች ላይሆኑ ይችላሉ።

አንዳንድ ወጣቶች ግን በተቃራኒው በእግዘአብሔር ተጠርተው ለአገልግሎት ሲወጡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ለብዙ ጊዜ ከቆዩና የልምምድ ባለጠጎች ጋር በጥበብ ተባብረው ከማገልገል ይልቅ እነርሱን ገፋ በማድረግ በራሳቸው አሳብ መሄድ ይፈልጋሉ። ይህ ሲሆን

በሽማግሌዎቹና በወጣት አገልጋዮች መካከል ክፍፍል ይፈጠርና ትግል ይጀመራል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከተገባ ደግሞ የተጠሩበትን የእግዚአብሔር አገልግሎት ትተው የራሳቸው የሆነውን የሥልጣን ትግል ከግብ ለማድረስ ግልጽና ስውር ጥቃት ይካሄዳል። ይህ ለአገልግሎት እንቅፋት ስለሆነ ወጣት አገልጋዮች በተሰጣቸው ሥፍራ በታማኝነት በማገልገል ቀስ ብለው ማደግን ቢማሩ የተሻለ እንደሆነ አስባለሁ።

ከላይ በአንዳንድ ምሳሌዎች እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ ጠራኝ ብለው እልል ያሉ ሰዎች በቃሉ አልተጠቀሱም። የሰዎቹ የመጀመሪያ ምርጫ ወደ አገልግሎት አለመግባት ነው። በዘመናችን ግን ያለው ሁኔታ ተቃራኒ ነው። እግዚአብሔር ጠርቶኛል ብለው ወደ አገልግሎት መግባት የሚፈልጉ ብዙ ሰዎች አሉ። አንዳንዶ እግዚአብሔር ሳይጠራቸውም የራሳቸውን ልቦለድ ታሪክ በመፍጠር እግዚአብሔር እንደጠራቸው በማስመሰል ወደ አገልግሎት ለመሰማራት ይጥራሉ። እነዚህ ሰዎች እንዲህ የሚያደርጉት አገልግሎት የሚለው አሳብ ስላልገባቸው ነው። ለእነርሱ አገልግሎት የምድራዊ በረከት መሰብሰቢያ፣ ዝና የማግኛ፣ የትምህርት ዕድል የማግኛ እና የመሳሰሉት ነገሮች መድረክ ነው። አገልግሎትን የሚፈልጉትን ነገር የማግኛ መሣሪያ እንደሆነ ከተመለከቱት ትኩረታቸው በአገልግሎቱ ላይ ሳይሆን በሚፈልጉት ነገር ላይ ነው። የሚፈልጉትን ነገር እስኪያገኙ ድረስ በአገልግሎት ይቆያሉ። ከዚያ በኋላ ግን የራሳቸውን የተመቻቸ ኑሮ መኖር ይጀምራሉ። የሚያገለግሉት አገልግሎት ባይሳካም ግድ የላቸውም።

### 3. *የእግዚአብሔርን የማበረታቻ ቃል ማግኘት*

እግዚአብሔር የጠራቸው ሰዎች የእርሱን ክብርና የተልዕኮውን ታላቅነት በማየት ለጥሪው ፈቃደኛ ለመሆን ፍርሃታቸውን በሚገልጹበት ጊዜ እግዚአብሔር አይቆጣቸውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰዎቹ በራሳቸው ኃይልና ችሎታ የእርሱን ሥራ መሥራት እንደማይችሉ በሚገባ ያውቃል። እግዚአብሔር ቀስ ብሎ አሳቡን እንዲረዱ ያደርጋቸዋል።

የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው ከእግዚአብሔር በሚሰጥ ኃይልና ችሎታ እንጂ በሰው ነገር አይደለም። እግዚአብሔርም የሚፈልገው ሰዎችን መሣሪያ በማድረግ በእነርሱ ውስጥ ሆኖ በዓለም ያለውን ዓላማውን መፈጸም ነው። ስለዚህ በእርሱ የተጠሩ ሰዎች እምቢ ሲሉ እግዚአብሔር ወዲያውኑ "እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ" የሚል የማበረታቻ ቃል ይሰጣቸዋል። የሰዎቹ ብቃት ማጣት ለእግዚአብሔር ጉዳዩ አይደለም። የእርሱ ከእነርሱ ጋር መሆን ለብቃት ማጣታቸው ተወዳዳሪ የሌለው መልስ መሆኑን ያውቃል። «እኔ አልችልም» ለሚል ሰው የእግዚአብሔር መልስ «እኔ ከአንተ/ከአንቺ ጋር እሆናለሁ» የሚል ነው። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ከሆነ ለሁሉም ጥያቄ መልስ ይሆናል።

እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር በሚሆንበት ጊዜ የላካቸውን ሰዎች ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸዋል፣ ለሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን ይሰጣል፣ ለሥራ በሚያስፈልጋቸው ሁሉ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያቀርብላቸዋል።

የአገልጋዮቹ ድርሻ የእግዚአብሔርን ምሪት ተከትለው እርሱ በሚፈልግበት ቦታ በአስፈላጊው ጊዜ መገኘት ነው። የሥራው ባለቤት እግዚአብሔር ራሱ ነው።

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እሆናለሁ ብሎ ለተናገራቸው አገልጋዮች ሁሉ ከእነርሱ ጋር በመሆን የተጠሩበትን ተልዕኮ ከግብ እንዲያደርሱ አድርጓቸዋል። እግዚአብሔር አላሳፈራቸውም። በዚህ ላይ አንድ ማስተዋል ያለብን አሳብ እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር በሚሆንበት ጊዜ ምንም ተግዳሮትና ፈተና አያጋጥማቸውም ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር እያለ ችግር፣ መከራ፣ ተግዳሮት፣ ፈተና...ያጋጥማል። ተግዳሮቱ በግል ሕይወት፣ በቤተሰብ ወይም በአገልግሎት ላይ ሊመጣ ይችላል። በእግዚአብሔር ተጠርተው ነገር ሁሉ ጨርቅ የሆነላቸው አገልጋዮች የሉም። ሁሉም በተለያዩ ፈተናዎች ውስጥ አልፈዋል።

ሙሴ ተጠርቶ ለእግዚአብሔር ተልዕኮ ከወጣ በኋላ መንገዱ ሁሉ ያለተግዳሮት አልነበረም። ተልዕኮውን ለመፈጸም ሲሰማራ ለመጀመሪያ ጊዜ ተግዳሮት የገጠመው ከግብጽ ንጉሥ ከፈርዖን ነበር። ፈርዖን ራሱን እንደ አምላክ የሚቆጥር ስለነበር በሙሴ በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን መልዕክት ለመቀበል ፈቃደኛ አልሆነም። የፈርዖን የልብ ደንዳናነት ለእግዚአብሔር አሳብ ይገዛል ብሎ ተስፋ የሚጣልበት ባይሆንም ሙሴ ተስፋ ሳይቆርጥ የእግዚአብሔርን መልዕክት ይዞ ፈርዖን ፊት ይቀርብ ነበር። ፈርዖን መልዕክቱን እምቢ በሚልበት ቁጥር ሙሴ ጉዳዩን በራሱ መንገድ ከመፍታት ይልቅ ወደላከው ወደ እግዚአብሔር ይጮኽ ነበር። እግዚአብሔርም ማድረግ የሚገባውን ያሳየው እንደነበር እንመለከታለን። ሙሴ የፈርዖንን ተግዳሮት ያሸነፈው በእግዚአብሔር በመታመንና ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ ሆኖ በመሥራቱ ነበር። እግዚአብሔር ታላቅ ኃይሉን በመግለጥ የሙሴን ተልዕኮ አሳካው። ከሙሴ ጋር እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ ሙሴ እንኳን የእስራኤልን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ማውጣት ቀርቶ በፈርዖን ፊትም መቅረብ ባልቻለም ነበር።

የመጀመሪያው ተግዳሮት ሲያልፍ ደግሞ ሌላ በእግሩ ተተካ። የእስራኤል ሕዝብ ከባርነት ሀገር ወጥተው በጉዞ ላይ እያሉ ፈርዖን አሳቡን ለወጠና አሳዶ ለመመለስ በኋላቸው ተከተላቸው። የእስራኤል ሕዝብ ደግሞ ቀይ ባሕር አጠገብ ደርሰዋል። ሕዝቡ አጣብቂኝ ውስጥ ገባ፤ ከፊቱ ቀይ ባሕር ከኋላው ደግሞ በቁጣ መንፈስ የተሞሉ የፈርዖን ወረኞች ነበሩ። በዚህ ሁኔታ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ከመሆን ሞት የሚመረጥበት ጊዜ ነበር። እስራኤላውያን ሕዝብ ከኋላቸው የመጡባቸውን የግብጽ ሰረገሎች ባዩ ጊዜ እጅግ ፈሩ። ከፍርሃታቸው ብዛት የተነሳ ከግብጽ ባልወጡ ኖሮ እንደሚሻላቸው በመናገር ሙሴን *"በግብጽ መቃብር ስላልነበረ በምድረ በዳ እንሞት ዘንድ አወጣኸንን? ከግብጽ ታወጣን ዘንድ ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው? በምድረ በዳ ከምንሞት ብንገዛላቸው ይሻላል"* በማለት ተናገሩት (ዘጸ 14:11፣12)። ሙሴ ይህን ተግዳሮት ለማለፍ እንደ ዋነኛ አማራጭ የወሰደው ነገር ቢኖር በእግዚአብሔር መታመንና ወደ እርሱ መጮኽን ነበር። እግዚአብሔር

የሙሴን ጩኸት ሰምቶ በነገሩ ጣልቃ ገባ። እግዚአብሔር ባሕሩን(የተፈጥሮ ተግዳሮትን) ለሁለት ከፈለውና ሕዝቡን አሻገረ፤ እንዲሁም የሚያስፈሩትን የፈርዖን ሰረገሎችን ደግሞ በባሕሩ ውስጥ አስገባቸውና ገደላቸው።

ሙሴ ይህን ተግዳሮት ሲያልፍ ሌሎች ተግዳሮቶች ተራ በተራ ተፈራረቁበት። ከእነዚህም አንዱ የውኃ እጦት ነበር። የጉዞው መስመር ምድረ በዳ ውስጥ ስለነበር ውኃ ማግኘት አስቸጋሪ ነበር። የእስራኤልም ሕዝብ በሙሴ ላይ እንዲያጉረመርም ያደረገው አንዱ የውኃ እጦት ነበር። እንደለመደው ለገጠመው ተግዳሮት ወደ እግዚአብሔር በመጮኽ ሙሴ የመጣበትን ተግዳሮት አሸነፈ። ምግብ ማጣትም በተመሳሳይ ሁኔታ እልባት አግኝቷል።

ሙሴ ከጠላቶችም ተግዳሮት መጥቶበት ነበር። የእስራኤል ሕዝብ በምድረ በዳ ሲጓዝ አማሌቃውያን ተዋጉት። ሕዝቡ ከባርነት ገና የተላቀቀ እንጂ ጦርነትን የተለማመደ ሕዝብ አልነበረም። ሙሴ ይህን የተገዳደረውን ጠላት ማሸነፍ የሚቻለው በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ እንደሆነ በመረዳት፥ የእግዚአብሔርን በትር ይዞ ወደ እግዚአብሔር ያነሳ ነበር። በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ሌሎች የተመረጡ ጎልማሶች ጠላትን ይዋጉ ነበር። በእግዚአብሔር በመታመን ጠላትን ተዋግተው አሸነፉ። ሙሴ ከጸሎትም በተጨማሪ ሰዎች ማድረግ የሚገባቸውን ነገር እንዲያደርጉ ኃላፊነት ሰጥቶአቸው ነበር። የድሉ ምስጢር በእግዚአብሔር መታመንና መጸለይ ቢሆንም በሜዳው ላይ ትግሉን የሚያደርጉ ሰዎች መኖር ነበረባቸው (ዘጸ17፡8-16)።

በሙሴ ላይ ተግዳሮት ከውጭ ብቻ ሳይሆን ከቤተሰቡም መጥቶበት ነበር። አንድ ጊዜ ሙሴ ጥቁር ሴት በማግባቱ፥ ወንድሙ አሮንና እህቱ፥ ማርያም በሙሴ ላይ ተነሱ። መቼም ሙሴ ጎልማሳ በመሆኑ ለራሱ የሚበጀውን ነገር መወሰንና ማድረግ ቢችልም እንደ ወንድምና እህት ምክር ወይም አሳብ መስጠት ክፉት አልነበረውም። ሆኖም አሮንና ማርያም ይህን ምክንያት በማድረግ የሙሴን ሥልጣን ሲጋፉ ይታያሉ። እግዚአብሔር ለጉዳዩ የሰጠውን ምላሽ ስንመለከተው ከአሳባቸው በስተጀርባ የተሰወረ ዓላማ መኖሩን እንረዳለን። በዚህ ጊዜ የሙሴ መሪነት ከቤተሰቡም ጥያቄ እንዳመጣበት እንመለከታለን። ይህ ሲሆን ሙሴ ስለራሱ ሳይናገር እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ የተነሳበትን ተግዳሮት አስወገደው። ሙሴ በሥልጣኑ ላይ የተነሱትን ሰዎች ለመበቀል የራሱን መንገድ አልተጠቀመም፤ ይልቅስ በማርያም ላይ በደረሰባት ፍርድ በማዘን እግዚአብሔር እንዲፈውሳት ለመነ (ዘኁ12)። እግዚአብሔር ለጠራው አገልጋይ ጠበቃ ነው።

ሙሴን ከቤተሰብ ውጭም በሦስት ሰዎች በቆሬ፣ ዳታንና አቤሮን ከሚመራው ከእስራኤል ሕዝብ በተመረጡ ዝና ካላቸው አለቆችም ሌላ ተግዳሮት ገጥሞት ነበር። እነዚህ ሰዎች በቀጥታ ሙሴ በእግዚአብሔር የተጠራ መሪ እንዳልሆነ አድርገው በመቃወም ተነሡበት። ለዚህ ተቃውሞ ሙሴ የሰጠው ምላሽ እግዚአብሔር እርሱ የመረጠውን መሪ ለሕዝቡ ያሳውቃል የሚል ነበር። ሙሴ በዚህ ጊዜ ምንም ስሜት አልነበረበትም ማለት አይቻልም። በሆነ ነገር ተቆጥቷል፣ ልቡም

አዝናል። ሆኖም እግዚአብሔር በተቃዋሚዎቹ ላይ በፈረደበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ምሕረትን በመለመን ይጸልይ ነበር። እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ የምሕረት ልቡ ሰፊ ነው። የእግዚአብሔር ፍርድ ተገልጦ ተቃዋሚዎቹን ከሚያጠፋ ሰዎቹ ወደ እግዚአብሔር ቢመለሱ ይወዳል (ዘኁ16)።

ሙሴ በአገልግሎት ዘመኑ የገጠሙትን ብዙ ተግዳሮቶችን በእግዚአብሔር በመታመን አልፎ ነበር። ሆኖም አንድ ማለፍ ያልቻለው ተግዳሮት ቢኖር ከራሱ የመጣበትን ተግዳሮት ነው። ሙሴ ባሳለፈው የአገልግሎት ዘመኑ የተዳከመ፣ የሕዝቡን ሮሮ መስማት የሰለቸው፣ ትዕግስቱ የተሟጠጠበት... ይመስላል። ከዚህም የተነሳ ይሆናል ሙሴ እግዚአብሔር ያላዘዘውን ነገር ያደረገው። እግዚአብሔር ድንጋዩን እንዲናገረው ሲያዘው ሙሴ ግን በቁጣ መንፈስ ድንጋዩን መታ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ተቆጣው (ዘኁ2012፣13)። ሙሴ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብዙ መስዋዕትነት የከፈለና እንደ እግዚአብሔር መልዕክተኛ ትልቅ ሥራ የሠራ አገልጋይ ቢሆንም ከራሱ የመጣበትን ተግዳሮት ማሸነፍ ባለመቻሉ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሳይገባ ቀረ። ይህ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ቀንደኛ ጠላት ከራሳቸው የሚመጣባቸው አሳብና ምኞት እንደሆነ ያመለክታል።

### *በአገልግሎት ተግዳሮት ለምን ይገጥማል?*

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር እያለ ለምን ፈተና ወይም ተግዳሮት ያጋጥማል? ብለን እንጠይቃለን። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለሆነ እንቅፋትን ሁሉ ከፊታችን አስወግዶ የእርሱን ሥራ ያለምንም እንቅፋት መሥራት እንድንችል ሁኔታዎች ለምን አያመቻችም እንላለን። እግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር እያለ በአገልግሎታቸው ተግዳሮት የሚመጣበት ምክንያቶች የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ። ለግንዛቤ ያህል ግን የሚከተሉት አሳቦች ይጠቀሳሉ።

የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በክፉ በተያዘ ዓለም ውስጥ ስለሆነ ዘወትር ትግል አለበት። የዚህ ዓለም ገዥ የሆነው ሰይጣን የእግዚአብሔር ሥራ በተሳካ ሁኔታ ተሠርቶ ሰዎች ከጨለማ ግዛት ወጥተው ወደ ብርሃን እንዳይመጡ በተቻለው ኃይል የእግዚአብሔርን ሥራ ለማደናቀፍ እንቅፋቶችን ይፈጥራል። ክፉው የአገልጋዮችን ጤንነት ሊያውክ፣ ከቤተሰቦቻቸውና ከሚያገለግሉአቸው ሰዎች ጭቅጭቅ እንዲሁም ከማያምኑ ሰዎች ስደትን ሊያስነሳባቸው ይችላል።

ሁለተኛው ተግዳሮት ሲገጥመን ምን ያህል ጸንተን እንደምንቆምና በእርሱ እንደምንደገፍ ለማወቅ እግዚአብሔር በአገልግሎታችን ላይ ተግዳሮት እንዲመጣ ሊፈቅድ ይችላል። ይህ ሲሆን እግዚአብሔር ለጊዜው ዝም ሊለንና ለካስ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የለም ብለን ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ሊቆይ ይችላል።

ሦስተኛው እግዚአብሔር ከአገልጋዮች ችሎታና አቅም በላይ የሆኑ ተግዳሮቶች እንዲመጡ በማድረግ ታላቅነቱን ይገልጻል። ይህ

መንገድ እግዚአብሔር በተከታታይ አገልጋዮቹ በእርሱ በመታመን እንዲያገለግሉት የሚያደርግበት መንገድ ነው። ከአገልጋዮች ችሎታ በላይ የሆነ ነገር ሲመጣ "እግዚአብሔር ሆይ ና!" ማለት ይጀምራሉ። ይህ ደግሞ ዘወትር በእግዚአብሔር ችሎታ እንዲደገፉ ስለሚያደርጋቸው ከእግዚአብሔር ጋር ሆነው በአገልግሎት እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል።

እንግዲህ እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ሲጠራቸው ተግዳሮት እንደማይገጥማቸው ተስፋ አልሰጣቸውም። ሰዎችን ለአገልግሎት ሲጠራቸው እግዚአብሔር የሚላቸው አንድ ነገር በተላኩበት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆን ነው። የተጠሩ ሰዎች ሁኔታዎችን አይተው እኔ አልችልም ሲሉ እግዚአብሔር እኔ ከአንተ ጋር ነኝ በማለት ምላሽ ይሰጣቸዋል። ይህ በብሉይ ኪዳን ለተጠሩ አገልጋዮችም ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮችም የተነገረ ቃል ነው። ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርትን ወደ ዓለም ሲልክ "እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" (ማቴ28:20) አላቸው።

የእግዚአብሔር ከአገልጋዮቹ ጋር መሆን ለእነርሱ ትልቅ ዋስትና ነው። ጌታ ኢየሱስ በዓለም መከራና ችግር እንዳለ ተናግሯል (ዮሐ.16:33)። ሆኖም ሞትን ድል አድርጎ የተነሳ ጌታ ስለሆነ አገልጋዮቹ በእርሱ ምሪት በሚሄዱባቸው በማናቸውም ቦታና ሁኔታ ከእነርሱ ጋር ሆኖ ድልን እንደሚሰጣቸው ተስፋ ገብቶላቸዋል። አገልጋዮች ለጌታ ሥራ በሚሄዱበት ሥፍራ ሁሉ ብቻቸውን አይደሉም፤ ጌታ ራሱ ከእነርሱ ጋር አለ። የታላቁ ተልዕኮ አዝማች ዘወትር ከዘማቾቹ ጋር ነው። የእግዚአብሔር ከአገልጋዩቹ ጋር መሆን "ለጥሪው የጥንካሬ ምንጭ፣ ለሥራው የስኬት መሠረት" ነው። አገልጋዮች ለተጠሩበት ዓላማ ልቦቻቸው እንዲጨክኑ የሚያደርገውና በዚህ ክፉ ዓለም ውስጥ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሥራ ሲሠሩ ስኬትን የሚሰጣቸው የእግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር መሆን ነው። ሌሎች ነገሮች ለአገልግሎት መሳካት አስተዋጽኦ ቢኖራቸውም የስኬቱ መሠረት የእግዚአብሔር መገኘት ነው።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከአገልጋዮቹ ጋር በመሆን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ይረዳቸዋል(ዮሐ14:16)። ይህ በውስጣቸው የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ለአገልጋዮች ምሪትና ኃይልን ይሰጣቸዋል።

አገልጋዮች በተሰማሩበት መስክ ሁሉ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነው ማለት ግን አገልጋዮች ስለራሳቸውና ስለአገልግሎታቸው እቅዱት መመላለስና ማገልገል እንዳለባቸው ጥንቃቄ ማድረግ አይኖርባቸውም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን ወደ አገልግሎት ሲልካቸው "እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ" (ማቴ10:16) በማለት አስጠንቅቋቸው ነበር። የእግዚአብሔር አገልጋዮች የእርሱን ፈቃድ ለማድረግ ስለሚኖሩ በዚህ ዓለም ካለው ክፋት ከፍተኛ ተግዳሮት ይገጥማቸዋል። እንደ በጎች ራሳቸውን ለመከላከል የማይችሉ ናቸው። ይህንንም ስለሚያውቁ ዘወትር የላካቸው ጌታ ከእነርሱ ጋር በመሆን ከተኩላዎች እንዲጠብቃቸው በእርሱ ላይ መደገፍ ይኖርባቸዋል። የእግዚአብሔር መለኮታዊ ከለላ ያስፈልጋቸዋል። ይህ አሳብ ሐዋርያው

ጳውሎስ ለሮሜ ክርስቲያኖች *ልበን ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ* (ሮሜ16:19) ከሚለው አሳብ ጋር ተዛምዶ ይኖረዋል።

በአገልግሎት ላይ ችግር የሚፈጠረው አገልጋዮች እግዚአብሔርን ወደኋላ ትተው ራሳቸው የሥራው ባለቤት መሆን ሲጀምሩ ነው። ብዙ ጊዜ የሚታየው ሰዎች በእግዚአብሔር ተጠርተው በቤቱ ማገልገል ሲጀምሩ ለእግዚአብሔር ያላቸው መታዘዝና ትሕትናቸው ያስደስታል። ብቃታቸው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ስለሚያምኑም አገልግሎታቸው መልካምና ስኬታማ ይሆናል። ነገር ግን ለጥቂት ጊዜ በአገልግሎት ሲቆዩና አገልግሎታቸው መስመር እየያዘ ሲሄድ እግዚአብሔርን ከጫወታው ሜዳ ውጭ በማድረግ ራሳቸው ኮከብ ተጫዋች መሆን ይጀምራሉ። ይህ ሲሆን በፊት እየቀናላቸው የሄደው አገልግሎት መልኩን እየለወጠ ይሄዳል።

በእግዚአብሔር ተጠርተው አገልግሎቱን በመጀመር አገልግሎቱ እየተሳካላቸው ሲሄድ አገልጋዮቹ የእግዚአብሔርን አጀንዳ ወደኋላ በመተው የራሳቸውን አጀንዳ ማስተናገድ ይጀምራሉ። በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ ሲወቅሳቸው ካልተመለሱ እግዚአብሔር ከእነርሱ ይለያል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ከእነርሱ እንደተለየ ሳያውቁ ሌላ ጊዜ ደግሞ እግዚአብሔር አብሮአቸው እንደሌለ እያወቁ አገልግሎቱን በሥጋቸው አሳብ ማገልገል ይቀጥላሉ። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ የራሳቸውን አሳብ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደሆነ በማስመሰል ያቀርባሉ። ከእነርሱ ጋር የሚያገለግሉ ሌሎች እግዚአብሔር አብሮአቸው የሚሠራ አገልጋዮች የእነርሱን አሳብ ሲቃወሙ በሥጋዊ መንገድ ማሸነፍ ይፈልጋሉ። በመንፈስ ከመሄድ በሥጋ መንገድ መሄድ ይቀላቸዋል። የበፊቱ ጸጋቸው ከእነርሱ የተለየ ስለሆነ እንዳለ ለማስመሰል የሚያገለግሉአቸውን ሰዎች ያታልላሉ። ቀስ በቀስ እውነቱ እስኪገለጥ ድረስ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያተረማምሳሉ።

### *4. ለአገልግሎት አቅጣጫ ወይም ምሪት ማግኘት*

እግዚአብሔር ሰዎችን በዓላማ ይጠራቸዋል። እያንዳንዱን የተጠራውን ሰው በልዩ ሁኔታ ጠርቶ ለልዩ አገልግሎት ያሰማራዋል። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ እነዚያ የተጠሩ ሰዎች ምን እንደሚያገለግሉ፣ የት እንደሚያገለግሉ እንዲሁም እነማንን እንደሚያገልግሉ ያስታውቃቸዋል። እግዚአብሔር የዓላማ አምላክ ስለሆነ ሰዎችን እንዲሁ አይጠራቸውም።

ስለዚህ አንድ አገልጋይ እግዚአብሔር ጠርቶኛል በሚልበት ጊዜ ምን ለማገልገል፣ የት ለማገልገል እና እነማንን ለማገልገል እንደተጠራ ማወቅና ሌሎች ለሚጠይቁትም ማስረዳት መቻል አለበት። በጥሪ ውስጥ የሚሰራው የአገልግሎቱ ዓይነት፣ አገልግሎቱ ለእነማንና የት እንደሚሰጥ መግለጽ አለበት። እነዚህ ነገሮች በጥሪው ውስጥ ከተካተቱ የተጠሩት ሰዎች ያለምንም ችግር በተጠሩበት አገልግሎት ላይ መሰማራት ይችላሉ። እግዚአብሔር ሰዎችን በዓላማ ስለሚጠራ ግልጽ ያልሆነ ወይም ትክክለኛ

አቅጣጫ የሌለው ጥሪ አይሰጣቸውም። ስለዚህ እግዚአብሔር ጠርቶናል ብለው ግን ምን፣ እነማን እና የት እንደሚያገለግሉ በእርግጥ የማያውቁ ሰዎች ጥሪያቸው ከእግዚአብሔር ስለመሆኑ ያጠራጥራል። ጥሪ እንዳላቸው የሚናገሩ ከሆኑ እግዚአብሔር ለምን ዓይነት አገልግሎት እንደጠራቸው ለይተው ማወቅ ይኖርባቸዋል።

በሕይወት ዘመኑ ምን እንደሚሠራ የማያውቅ አገልጋይ የሚገባውን ፍሬ ሊያፈራ እንደማይችል እግዚአብሔር ያውቃል። ስለዚህ ግልጽ የሆነ የአገልግሎት ዓይነት ሳይሰጠው አይልከውም። የሚያገለግለውን አገልግሎት በግልጽ የማያውቅ አገልጋይ በቤተክርስቲያን ያገኘውን ወይም ሥራ የተባለውን ሥራ ይሠራል። በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉንም ነገር የሚሠራ አገልጋይ በመጨረሻ ላይ አንዳችም ነገር ሳይሠራ ይቀራል። ስለዚህ ለእግዚአብሔር ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠት የሥራን ዓይነት ማወቅ አስፈላጊ ነው። ሰው አንድ መሥሪያ ቤት ሲቀጠር የመሥሪያ ቤቱን ሥራዎች ሁሉ አይሠራም። ሲቀጠርም የተወሰነ ሥራ እንዲሠራ ስለሆነ የተሰጠውን ተግባር በሚገባ እንዲያከናውን ይጠበቅበታል። አገልጋይ የሆኑም ሰዎች ሁሉንም ዓይነት አገልግሎት እንዲያገለግሉ ሁሉም ዓይነት ጸጋ አልተሰጣቸውም። ስለዚህ የተሰጣቸው ምን እንደሆነ ከጠራቸው እግዚአብሔር መጠየቅና ማወቅ ይገባቸዋል።

የአገልግሎት ዓይነትን በግልጽ አለማወቅ ለማደናገርና ለማጭበርበር ያመቻል። ምክንያቱም አገልጋዩ በአገልጋይነት ስም ብቻ ይኖራል። የሚሠራው ሥራ በግልጽ ስለማይታወቅ ምን ያህል ፍሬ እያፈራ ነው? ተብሎ አይገመገምም። ስለዚህ ከግምገማ ነጻ ለመሆን ጥሩ መንገድ ያለምንም የአገልግሎት ጥሪ እንዲሁ በአገልጋይ ወይም የወንጌል ሠራተኛነት ስም መሠማራት ነው። "አገልግሎትህ ምንድነው?" ሲባል "አገልጋይ ነኝ" ይላል እንጂ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ ወይም አስተማሪ ወይም ሌሎችን በማለት በእርግጠኛነት መናገር አይችልም። መጋቢ ወይም አስተማሪ ካለ በተሰጠው የአገልግሎት መስክ ምን ያህል እያገለገለ እንዳለ ይታወቃል። አለበዚያ ይህንንም ያንንም ሆኖ መኖር ይቻላል።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ሲጠራ ግልጽ አቅጣጫ እንደሚሰጣቸው የሚያሳዩ ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰው እናገኛለን።

እግዚአብሔር ሙሴን ሲጠራው ወደ ግብጽ በመሄድ በባርነት ሥር ያሉትን የእስራኤል ሕዝብ ከባርነት ነጻ እንዲያወጣ ነበር። ስለዚህ ሙሴ ሲጠራ ምን መሥራት፣ ወዴት መሄድ እና እነማንን ማገልገል እንዳለበት በእርግጥ ያውቅ ነበር (ዘጸ.3 ና 4)።

እግዚአብሔር ኤልሳዕን ሲጠራው ሁለት ነገሮችን እንዲያከናውን ነበር የጠራው። የኤልሳዕ ተልዕኮ የሶርያን ንጉሥ አዛሄልንና የእስራኤል ንጉሥ ኢዩን በማገዝ የእግዚአብሔር ጠላቶችን እንዲደመስስ እና ለእግዚአብሔር ለታመኑ ቅሬታዎች የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ነበር (1ነገ19:16-18)።

እግዚአብሔር ኤርምያስን ሲጠራው ለአሕዛብ ነቢይ አድርጎ ነበር። እግዚአብሔር ሲጠራው "ወደምልክህም ሁሉ ትሄዳለህ" (ኤር1:7) ብሎ ተናገረው።

እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ጠርቶ "*ወደ ዐመጹ ወደ ዐመፀኞች ሰዎች ወደ እስራኤል ልጆች*" ላከው (ሕዝ2:3)።

በአዲስ ኪዳንም ጳውሎስን እንደምሳሌ መውሰድ እንችላለን። እግዚአብሔር ጳውሎስን ሲጠራ የእርሱን ወንጌል ይዞ ወደ አሕዛብ፣ ነገሥታትና ወደ እስራኤል ልጆች እንዲሄድ ነበር (የሐዋ9:15)። ስለዚህ ጳውሎስ ወንጌልን መስበክ አገልግሎቱ እንደሆነ ቢረዳም በቅድሚያ የተጠራው ለአሕዛብ ወንጌልን ለመስበክ ነበር። ራሱንም ሲጠራ የአሕዛብ አስተማሪ ብሎ ነበር (1ጢሞ2:7)። ስለዚህ አንድ ሰው ጥሪው ከእግዚአብሔር መሆኑ ከሚታወቅበት ምልክቶች አንዱ ግልጽ የሆነ አቅጣጫ መቀበሉ ነው።

በአሁኑ ዘመን ያለን አገልጋዮች በአብዛኛው እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት ጠርቶናል ብለን በየአደባባዩ እናወራለን። ነገር ግን ጠጋ ብለው ሰዎች ቢጠይቁን አንዳንዶቻችን ስለተጠራንበት አገልግሎትና ሥፍራው ግልጽ የሆነ የሚታየን አቅጣጫ የለም። ብዙዎች ጥሪያቸው ወደ ከተማ ወይም ወደ ውጭ አገር እንደሆነ ይናገራሉ እንጂ ውኃና መብራት ወደሌለበት ቦታ እንደሆነ የሚናገሩ አገልጋዮች እምብዛም አያጋጥሙም። እግዚአብሔር ለከተማ ወይም ለውጭ አገር ሰዎችን አይጠራም ማለት ሳይሆን ሁልጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ ያደርጋል ማለት እንዲሁም የማያሻማ ትክክለኛ ጥሪና በረከት ያለበት ጥሪ እንዲህ ዓይነቱ ነው ብሎ መናገር ድፍረት ካልሆነ በቀር ትክክለኛ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ የለውም።

*አበበ ጌታ ኢየሱስን የተቀበለው ገና ወጣት ሆኖ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማር ነበር። ጌታን ከተቀበለ በኋላ ተከታታይ ትምህርት መማር ጀመረ። ይህን ትምህርት ሲማር አስተማሪው ሲያስተምር በልቡ ውስጥ "አንተም አንድ ቀን እንደዚህ አስተማሪ ቆመህ ቃሌን ታስተምራለህ" የሚል አሳብ ይመላለስ ነበር። አበበ በጌታ ገና ልጅ ስለሆነ ይህ አሳብ ምን እንደሆነ አላስተዋለም። ሆኖም ይህ አንድ ቀን ብቻ ሳይሆን በተከታታይ በልቡ የሚመላለስ አሳብ ነበር። ዩንቨርስቲ ገብቶ በትምህርት ላይ እያለም መጽሐፍ ቅዱሱን ሲያነብ እና መንፈሳዊ ጉባኤዎችን ሲካፈል ይህ ቃል ሳይቋረጥ ወደ ልቡ ይፈሳል። ከዚያም ስለዚህ ቃል መጸለይ ጀመረ። እግዚአብሔርም ለወንጌል አገልግሎት እንዲለይ እንደሚፈልገው ገለጸለት።*

*አበበ አሳቡን ቢቀበልም ግን በቅርብ ጊዜ ቢሆን ፈቃደኛ እንደማይሆን በማሰብ ጸሎቱን ቀጠለ። በዚህ ጊዜ የት ማገልገል እንዳለበት በልቡ ስለአንድ ቦታ ሸክም እየተሰማው መጣ። ትምህርቱን ከጨረሰ በኋላ በውስጡ የሞላውን ጥሪ ለቤተክርስቲያን መሪዎች ተናገረ። መሪዎቹ ከጠየቁት ጥያቄዎች አንዱ የት ማገልገል ትፈልጋለህ? የሚል ነበር። አበበ ያለምንም ችግር በውስጡ የተቀመጠውን ሥፍራ ተናገረ። መሪዎቹ ያልጠበቁት ምላሽ ነበር። ምክንያቱም የተማረ ሰው የሚፈልገው መሐል ሀገርን እንጂ ንጹሕ ውኃና መብራት የሌለበት ቦታ*

*እንዳልሆነ ስለሚታሰብ ነው። መሪዎቹ አሳቡን ከተቀበሉ በኋላ አጭር የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና ወስዶ ከመሐል አገር በጣም ሩቅ ወደሆነ ሥፍራ ሄደ።*

እዚህ ላይ ግን አንድ ልብ ልንል የሚገባን አሳብ አለ። ከተማ ውስጥ የሚኖር ሰው ሆኖ እግዚአብሔር ለገጠር አገልግሎት ጠርቶኛል የሚል ሁሉ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ጥሪ አለው በማለት መደምደም እንደማይቻል ሊታወቅ ይገባል። ለኑሮ አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተሟልቶላቸው ነገር ግን ሰላምና ደስታ ካላገኙ በአገልግሎት አማካኝተው ከደበራቸው ኑሮ ለመውጣት የሚታገሉ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። የተማሩ ሰዎች ወይም በጥሩ ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ ያሉ ሰዎች እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት ጠርቶናል ሲሉ ጥሪያቸው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ይመስለናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ልባቸውን ባያሸንፍ ኖሮ ይህን የመሰለ ነገራቸውን ትተው ለወንጌል አገልግሎት አይወጡም ወይም ለመውጣት አያስቡም እንላለን። ከዚህም አስተሳሰብ የተነሳ አንዳንዴ ጥሪያቸውን ያለምንም ሚዛን እንቀበላለን። ይህ ስህተት ነው። በዚህ ምሳሌ ለመናገር የተፈለገው አሳብ አንድ ሰው ሲጠራ የት እንደሚሄድ ማወቅ አለበት የሚል ነው።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ ወደ አንድ ቦታ እንዲሄዱ ሲልካቸው አንዳንድ ጊዜ ቤተክርስቲያን ፈቃደኛ ላትሆን ትችላለች። በዚህ ጊዜ አገልጋዩ ከእግዚአብሔርና ከቤተክርስቲያን የትኛውን እንደሚታዘዝ ግራ ይገባል።

ይህም ብቻ ሳይሆን አንድ ሰው በጥሪው አንድ ቦታ እያገለገለ እና አገልግሎቱም እየተሳካለት እያለ ቤተክርስቲያን ወደ ሌላ ቦታ ሂድ ብትለው አገልጋዩ መሄድ አለበት ወይስ የለበትም? የሚሉ ጥያቄዎችም አነጋጋሪ ናቸው።

*ወርቅነህ እግዚአብሔር ጠራኝ ወዳለው ቦታ ሄዶ እንዲያገለግል ከቤተክርስቲያን ተፈቅዶለት አንድ ትንሽ ከተማ ውስጥ ማገልገል ጀመረ። የአካባቢው ምዕመናን እግዚአብሔር መልካም አገልጋይ እንደላከላቸው በማየት እግዚአብሔርን በማመስገን ተቀበሉት። አገልግሎቱ በአብዛኛው አገልጋዮችን በማፍራት ላይ ትኩረት ያደረገ ነበር። ቀስ በቀስ አገልግሎቱ እየተወደደና እያደገ መጣ። ቤተክርስቲያናት አገልጋዮች ተገቢውን ትምህርት በማግኘት አገልግሎታቸው ፍሬያማ እንዲሆን በመደረጉ ጌታን አመሰገኑ። ወርቅነህ በዚያ አካባቢ ለሁለት ዓመት እንዳገለገለ የቤተእምነቱ ዋና መሥሪያ ቤት እርሱ ወደሌላ ቦታ እንዲሄድ ጥያቄ አቀረበለት።*

*ወርቅነህን ያነጋገረው የቤተክርስቲያን መሪ "አንተን ወደ ከተማ መሳብ እንፈልጋለንና ምን ታስባለህ? እግዚአብሔርስ ምን ተናገረህ?" አለው። ወርቅነሀ በዚህ ጉዳይ ከእግዚአብሔር ምንም ምሪት እንዳላገኘ ገለጸላቸው። ግን ቤተክርስቲያን ያለችውን ሁሉ እንደሚያደርግ በመጠቆም አሳቡን ጨረሰ። የቤተክርስቲያን መሪው ግን "ቤተክርስቲያን ሰው ናት፤ ዛሬ የወሰነችውን ነገር ነገ ልታፈርስ ትችላለች። ስለዚህ ከእግዚአብሔር ካልሰማህ የቤተክርስቲያንን አሳብ መከተል ትክክል አይደለም" አለው። ይህ አባባል ለወርቅነህ እጅግ አስቸጋሪ መልስ ነበር።*

በእርግጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ያለእግዚአብሔር ምሪት ውሳኔዎችን የሚወስኑ ከሆኑ ውሳኔዎቹ የሰዎች ስለሆኑ ሰዎቹ ዛሬ የወሰኑትን ነገ ሊሽሩት ይችላሉ። ወርቅነህም የሰውን ውሳኔ ከተከተለ የእግዚአብሔርን አሳብ ሳይፈጽም ይቀራል።

በሌላ በኩል ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ያስቀመጠው እግዚአብሔር ስለሆነ ምንም ቢሆን ለእነርሱ መታዘዝ አለበት የሚል አሳብ መከተል ይቻላል። ወርቅነህ ያሰበው ምናልባት ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪ ውሳኔዎች እንዴት እንደሚወሰኑ ስለሚያውቁ ስለወርቅነህ የተወሰነው ውሳኔ የሰው ውሳኔ እንደሆነ ተናግሮ ይሆናል። ይህ ካልሆነ ደግሞ አባባሉ ወርቅነህ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውሳኔ ምን ያህል እንደሚታዘዝ የልቡን ለማወቅ የቀረበ መስቀለኛ አሳብ ይመስላል። ምንም ቢሆን ወርቅነህ ግልጽ የሆነ የእግዚአብሔር ምሪት ካላገኘ በስተቀር ለቤተ ክርስቲያን መታዘዝ ለክፉ አሳልፎ እንደማይሰጥ ያምን ስለነበር ቤተ ክርስቲያንን ታዞ ማገልገልና ፍሬ ማፍራት የጀመረበትን ሥፍራ ለቆ ወደ ከተማ ሄደ። አንተ ወርቅነህን ብትሆን ምን ዓይነት ውሳኔ ትወስን ነበር?

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ለሰዎች ተገልጦ ለአገልግሎት ሲጠራቸው ሰዎች የራሳቸውንና አካባቢያዊ ሁኔታዎቻቸውን በመመልከት ይህ ሊሆን አይችልም በማለት በእርግጥ ጥሪው ከእግዚአብሔር መሆኑን ይጠራጠራሉ። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ጌዴዎን ነው። እግዚአብሔር ሲያናግረው "በአንተ ፊት ሞገስ ካገኘሁ የምትናገረኝም አንተ እንደሆንህ ምልክት አሳየኝ" (መሳ6:17) በማለት ጠየቀው። ጌዴዎን ለምን እግዚአብሔርን በመጠራጠር ምልክት ጠየቀው? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። የራስን ደካማ ጎን ብቻ አጉልቶ በማየቱ ጌዴዎን ስለራሱ ያለው አለመካከት የእግዚአብሔርን ጥሪ እንዳይቀበል እንቅፋት ሆኖበታል። ወገኑ የተጠቃ በአባቱ ቤት ደግሞ የሁሉ ታናሽ ስለነበር እግዚአብሔር ይህን ሁሉ እያወቀ የጠራው ስለመሆኑ እርግጠኛ መሆን ነበረበት። ጌዴዎን እርግጠኛ ለመሆን ምልክት ሲጠይቅ እግዚአብሔር አልተቆጣውም ነበር። ነገር ግን ጌዴዎን የጠየቀውን ምልክት አሳየው። ከዚያም ጌዴዎን እርሱን የጠራው በእርግጥ እግዚአብሔር መሆኑን አወቀ።

ዛሬም እግዚአብሔር ሲጠራቸው ሰዎች የጠራቸው በእርግጥ እግዚአብሔር መሆኑን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ማስረጃ እንዲሰጣቸው መጠየቁ መልካም ነው። እግዚአብሔር ከጠራ ለሚጠራቸው ሰዎች በትክክል እንደጠራቸው ያረጋግጥላቸዋል። በእግዚአብሔር ለመጠራታቸው እርግጠኛ ሳይሆኑ ለአገልግሎት መውጣት ብድራት የሌለው ዋጋ ያስከፍላል። ሁለት ጊዜ ለመኖር ዕድል በማይኖረን አንዲት ሕይወት እግዚአብሔር እኛን ባለፈለገበት ሁኔታ ውስጥ ራሳችንን አስገብተን ብንጨርሳት መጨረሻው ፍሬ የሌለው ጸጸት ብቻ ይሆናል። ስለዚህ በትዕግስት ጥሪን አረጋግጦ መውጣት አማራጭ የለውም። እግዚአብሔር ከጠራን ደግሞ ጥሪውን ያረጋግጥልናል። የእኛ ድርሻ እርሱ እስኪያረጋግጥ መታገስ ነው። ከዚያም ጌታ ለእያንዳንዳችን ሊገባን በሚችል መንገድ ያረጋግጥልናል። በእግዚአብሔር ተጠርተን ስለመላካችን

ከእርሱ ዘንድ የማረጋገጫ ደብዳቤ ከሌለን የክርስቶስ አካል እኛን ተቀብላ ለማስተናገድ ግዳጅ የለባትም። ስለዚህ ደብዳቤው እስኪሰጠን በጸሎት እየተዘጋጀን እንጠብቅ።

*በእግዚአብሔር እንደተጠሩ ለሌሎች ማካፈል*

ሰዎች የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣላቸው ከእግዚአብሔር ጋር በዚህ ሁኔታ መገናኘትን ከዚህ በፊት ተለማምደው ስለማያውቁ ግራ ይገባቸዋል። ስለዚህ በዚህ አዲስ ልምምድ ውስጥ ሲገቡ የሚረዷቸው ሌሎች ሰዎች ያስፈልጓቸዋል። እነዚህ ሰዎች መልካምና የበሰለ መንፈሳዊ ልምምድ ያላቸው፣ ስለመንፈሳዊ ሕይወታቸው የተመሰከረላቸውና በቤተክርስቲያን የታወቁ ሰዎች ሊሆኑ ይገባቸዋል።

ሙሴ በእግዚአብሔር ፊት ሲቀርብ እርሱ ማድረግ የሚገባውን ነገሮች ያስረዳው እግዚአብሔር ራሱ ነበር። እግዚአብሔር ጫማውን ከእግሩ እንዲያወልቅ ነገረው። ሳሙኤልን ስንመለከት ደግሞ የእግዚአብሔርን ድምጽ ሰምቶ ስለማያውቅ
ዔሊ የጠራው መስሎት ወደ ዔሊ እንደተመላለሰ እናያለን። ሳሙኤል በእግዚአብሔር ቤት ቢያገለግልም እስከዚህ ቀን ድረስ እግዚአብሔርን በዚህ ልዩ በሆነ ሁኔታ ተገናኝቶ አያውቅም። ካህኑ ዔሊ በመጀመሪያ ግራ ቢገባውም በመጨረሻ እግዚአብሔር እንደጠራው አስተዋለና ሳሙኤልን *"ሂደህ ተኛ ቢጠራህም አቤቱ ባሪያህ ይሰማልና ተናገር በለው"* (1ሳሙ3:10) በማለት መከረው። ከዚያም ሳሙኤል ከእግዚአብሔር ጋር ተገቢውን ግንኙነት ማድረግ ቻለ። ለሐዋርያው ጳውሎስም ጥሪ ሲመጣለት አዲሱን ልምምድ በማስረዳት ፊር ያስያዘው ሐናንያ የተባለ ሰው ነበር (የሐዋ9:17)።

ሰዎች በአንድ ልዩ ሁኔታ ወይም ከተለማመዱት ልምምድ ለየት ባለ መልኩ የእግዚአብሔር መልዕክት ሲመጣላቸውና በተለይም ለአገልግሎት እንደጠራቸው ካስተዋሉ በኋላ ከመውጣታቸው በፊት የበሰሉ መንፈሳዊ ሰዎችን ማማከር እጅግ ይጠቅማል። እነዚህ የበሰሉ ሰዎች ተጠራን የሚሉት ሰዎች በተለማመዱት አዲስ ልምምድ ውስጥ የእግዚአብሔር መልዕክት በእርግጥ ምን እንደሆነ እንዲመረምሩ ያግዙአቸዋል፤ ከእነርሱም ጋር በመጸለይ የእግዚአብሔር አሳብና ፈቃዱ በግልጽ እንዲታወቅ ይደግፉአቸዋል። አንዳንድ ጊዜ እነዚህ የበሰሉ ሰዎች የሚባሉቱ በልባችን ውስጥ የሞላውን አሳብ ሊያጨልሙ ይችላሉ። ይህም የእኛ መረዳት ትክክል ሳይሆን ቀርቶ እግዚአብሔር ሳይጣራን እንደጠራን በስህተት በማሰባችን ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በራሳቸው ሚዛን ብቻ የእኛን ልምምድ በመመዘን በራሳቸው እይታ ብቻ በማየት የእግዚአብሔር ጥሪ ኖሮን እንደሌለን ሊቆጥሩ ይችላሉ።

አዲስ ለተጠሩ ሰዎች ትልቁ ተግዳሮት እግዚአብሔር እንደጠራቸው በእርግጠኛነት ማወቅ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር በግላቸው ተገናኝቶ ከጠራቸው በኋላ እግዚአብሔር እንደጠራቸውና ጥሪያቸው ትክክለኛ ጥሪ እንደሆነ ለሌሎች በተለይም ለቤተክርስቲያን መሪዎች መናገርና ማሳመኑ ላይ ነው። መሪዎቹ እግዚአብሔር ለአንተ ከተናገረ

ለእኛም ይንገረን ይላሉ። በእርግጥ እግዚአብሔር አገልጋዮችን ከጠራ በኋላ እርሱ እንደጠራቸው ለሚያሰማሩ ክፍሎች መናገር ይችላል። እነዚያ መሪዎች የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ ለማወቅ ክፍት ልቦናና ትጋት ካላቸው እግዚአብሔር ላስቀመጣቸው መሪዎች ማድረግ የሚገባቸውን ነገር የማይናገር አምላክ አይደለም። ችግሩ እነዚያ መሪዎች በእግዚአብሔር ያልተሾሙና የእግዚአብሔርን አሳብ ለማወቅ ልብ ከሌላቸው ነው። ይህ ትልቅ ተግዳሮት ነው።

እግዚአብሔር ከተገለጠለት በኋላ ሙሴ ለእግዚአብሔር ጥሪ እምቢ ለማለት ካቀረባቸው ምክንያቶች አንዱ ይህ ነበር። *"እነሆ አያምኑኝም ቃሌንም አይሰሙም እግዚአብሔር ከቶ አልተገለጠልህም ይሉኛል"* (ዘጸ4:1) በማለት ተሟገተ። ሙሴ የተሰጠውን ተልዕኮ ላለመቀበል እንደምክንያት ቢያቀርብም አሳቡ በእርግጥ ሊገጥም የሚችል ጉዳይ ነው። ሕዝቡን ነጻ ለማውጣት ከመነሳቱ በፊት ሕዝቡ እግዚአብሔር ጠርቶ የላከልን አገልጋያችን ነው ብሎ መቀበል ነበረበት። እግዚአብሔርም የሙሴ ጥያቄና ፍርሃት ትክክል እንደሆነ ስላወቀ ሙሴ ከእግዚአብሔር ስለመላኩ የሚያሳይ ምልክት ሰጠው። ይህ ምልክት በእግዚአብሔር ኃይል ተዓምር የማድረግ ሥልጣን ነበር።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ መሪ እንደላከላቸው አልተናገረም። ነገር ግን ለሙሴ አፍ እንደሚሆንለት ለተናገረው ለአሮን ተገለጠና ወደ ምድረ በዳ ሄዶ ከሙሴ ጋር እንዲገናኝ አዘዘው። ይህ ለሙሴ አንድ ጥሩ መንገድ ነው። ሙሴና አሮን ከተለያዩ አርባ ዓመታት አስቆጥረዋል። በምድረ በዳ ለሙሴ የተገለጠው እግዚአብሔር በጊዜው በግብጽ ምድር ለነበረው ለአሮን ተገልጦ ለሙሴ ተልዕኮ መሳካት ሁኔታዎችን ማመቻቸቱ፡ እግዚአብሔር የበላይ መሪ መሆኑን ከማሳየቱም በላይ ለሙሴም መላክ ተጨባጭ ማረጋገጫ ነው። ሙሴ አሮንን ከጎኑ ካደረገ በኋላ የሚቀጥለው እርምጃ ለእስራኤል ሕዝብ ሽማግሌዎች ስለጥሪውና ተልዕኮው ማስረዳት ነበር።

በዚህ ጊዜ ስለሙሴ ጥሪና ተልዕኮ የተናገረው አፍ እንዲሆንለት በእግዚአብሔር የተመረጠው ወንድሙ አሮን ነበር። ከዚያም እግዚአብሔር ምልክት አድርጎ የሰጠውን ተአምራት በሕዝቡ ፊት አደረገ። ሕዝቡም ቃሉን ከሰሙና ተአምራቱን ካዩ በኋላ ሙሴ በእርግጥ በእግዚአብሔር ተጠርቶ ሕዝቡን ከባርነት ሥር ለማውጣት እንደተላከ አመኑ። እግዚአብሔርም ስላሰባቸውና ነጻ አውጪ ስለላከላቸው አመሰገኑ (ዘጸ4:27-31)።

ዳዊት ለመሪነት ሲቀባ "በወንድሞቹ መካከል" ነበር። ጥሪው የመጣው ምስክሮች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ ነበር። ዳዊት ለመሪነት በነቢዩ ሳሙኤል ሲቀባ በጊዜውና በቦታው የነበሩት ምስክሮች በቂ ነበሩ። ዳዊትን በሳውል አጠገብ ያየ ሰው ከንጉሡ አገልጋዮች እንደ አንዱ ይቆጥረው ይሆናል። ነገር ግን ዳዊት ንጉሥ ለመሆን ተራውን የሚጠብቅ የተቀባ ሰው ነበር (1ሳሙ.16:13)።

ሐዋርያው ጳውሎስም በዚህ ዓይነት ልምምድ ውስጥ አልፏል። ጌታ ኢየሱስ ከጳውሎስ ጋር መገናኘቱን ሐናንያ ለሚባል ደቀመዝሙር ነገረው። ሐናንያ ጳውሎስን ለመቀበል የተዘጋጀ ልብ ባይኖረውም ጌታ

ጳውሎስን እንደለወጠውና ማድረግ የሚገባውን ነገር የሚነግረውን ሰው እየጠበቀ እንደሆነ ሲያስረዳው ወደ ጳውሎስ ሄደ። ጳውሎስንና ሐናንያን ያገናኘው ጌታ ኢየሱስ ነበር (የሐዋ.9፡10-19)። እግዚአብሔር አንድን ሰው ሲጠራ ስለመጠራቱ ለሌሎች ሰዎች ያሳውቃል። እግዚአብሔር ራሱ የጠራውን ሰው ለሌሎች ያስተዋውቃል። በዚህ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ስለአንድ ሰው መጠራት የሰሙ ሰዎች አሳቡ ቶሎ ሲገባቸው ከእግዚአብሔር በቀጥታ መልዕክቱን ያልሰሙ ሰዎች ይህን ሰው መቀበል ይከብዳቸዋል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር አንድን ሰው መጥራቱን የሚናገረው በቤተክርስቲያን ውስጥ ለታወቀ ሰው ላይሆን ይችላል። ይህ ደግሞ በራሱ ሌላ ችግር ነው። በዚህ የሽግግር ወቅት የተጠሩትን ሰዎች መርዳት የሚችሉ ሰዎችን ለማሳደግና ለመርዳት ዝንባሌ ያላቸው ምዕመናን ናቸው። ለጳውሎስ በርናባስ ከፍተኛ እገዛ አደረገለት። ለነባር አገልጋዮች እርሱን ለማስተዋወቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ምናልባት በርናባስን ባያገኝ ኖሮ ጳውሎስ በጣም ይቸገር ነበር ማለት ይቻላል።

በቤተክርስቲያን አካባቢ ከሚደረገው ሁኔታ ሲታይ ተጠራን ብለው የሚናገሩ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ጉድ ጉድ የሚሉና መልካም ሕይወት እንዳላቸው የተመሰከረላቸው ሰዎች ከሆኑ ጥሪያቸውን መቀበል አስቸጋሪ ሲሆን አይታይም። ነገር ግን እግዚአብሔር ጠራን የሚሉ ሰዎች ልታይ ልታይ ባዮች ካልሆኑ እና ጠንካራ ወይም ኃይለኛ ስብዕና ያላቸው ሰዎች ማለትም ለተረዱት እውነት የሚቆሙ ዓይነት ሰዎች ከሆኑ የቤተክርስቲያን መሪዎች ጥሪያቸውን ለመቀበል ይቸገራሉ። "እስቲ እግዚአብሔር እንደተናገረህ ለእኛም ይናገረን" እያሉ ሳይቀበሉት ዓመታት ያስቆጥራሉ። እንዲህ ዓይነት ሰዎች ተስፋ ቆርጠው ይተዋሉ ወይም ደግሞ ቤተክርስቲያናቸውን ትተው ወደሌላ ይሄዳሉ። አንዳንዶች ደግሞ ዐመጽም ያስነሳሉ።

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ ነገር ሁሉ ግልጽ ሆኖ እንደሚታይ መገመት አስቸጋሪ ይሆናል። አንድ ሰው እግዚአብሔር ሲጠራው የጥሪውን ዓይነት ማወቅ አለበት ሲባል በተለይ በመጀመሪያ ጊዜ የጥሪው ዓይነት ኩልል ብሎ ይታያል ማለት አይደለም። በዚህ ጊዜ ተጠርተናል የሚሉ ሰዎች እግዚአብሔር በከፈተላቸው መስክ ላይ ሆነው እግዚአብሔር የሰጣቸውን የአገልግሎት ጸጋ መፈተሽ ይችላሉ። እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጸጋ እየፈተሹ የበለጠ ፍሬ የሚያፈሩበትን አገልግሎት ለይተው ማወቅ አጭር ወይም ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል። አንዳንድ ቤተክርስቲያናት የአገልግሎት ዓይነት በልምምድ ሳይፈተሽ በመጀመሪያ ጥሪ ብቻ አይታወቅም የሚለውን ከመጠን በላይ በማጥበቅ ጥሪ አለን የሚሉትን ሰዎች ሁሉ በአንድ ቋት ውስጥ እንዲያልፉ ያደርጋሉ። እያንዳንዱ የአገልግሎት ዓይነቶች መለያ እርምጃዎች ውስጥ ሳያልፉ እግዚአብሔር ለጠራቸው ዓላማ መሰማራት አይችሉም።

እንግዲህ አንድ ሰው ለአገልግሎት በእግዚአብሔር ስለመጠራቱ ጥሩ የመለያ ምልክት የሚሆኑ የሰውየው ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቶ የእግዚአብሔርን ባህርያትና እርሱን በመፍራት ማክበር፣ በራስ ችሎታ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለመቆም ብቃት እንደሌለው መገንዘብ፣

የእግዚአብሔርን አብሮ መገኘት የተስፋ ቃል ወይም ማረጋገጫ ማግኘት እና ስለተጠራበት አገልግሎት ግልጽ ራእይ መቀበል ናቸው።

አንድ ሰው የአገልግሎት ጥሪው በእርግጥ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ከተረዳ ምን ያህል ጊዜ ቆይቶ ለአገልግሎት መሰማራት አለበት? በጥሪና በስምሪት መካከል ምን ያህል ጊዜ መቆየት ይቻላል? ከጥሪ በኋላ ለአገልግሎት ጊዜ ወስዶ መዘጋጀት አስፈላጊ ነውን? ዝግጅት ካስፈለገ ምን መምሰል አለበት? አንድ ሰው ዕድሜ ልኩን ለማገልገል ለተጠራበት አገልግሎት ምን ያህል መዘጋጀት አለበት? የሚሉ ጥያቄዎች ደግሞ በሚቀጥለው ምዕራፍ መልስ ያገኛሉ።

---

## ጥያቄዎች

1. የእግዚአብሔር ጥሪ ትክክለኛነት የሚታወቀው እንዴት ነው? አንድ ሰው ጥሪው በእርግጥ ከእግዚአብሔር ስለመሆኑ ምን ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉት?

2. አንድ ሰው እግዚአብሔር የሰጠውን የአገልግሎት ሸክምና የራሱን ስሜት እንዴት መለየት ይችላል?

3. አንድ ሰው በእግዚአብሔር መጠራቱን ቢያውቅና ቤተክርስቲያን ግን በአገልግሎት ለማሰማራት ፈቃደኛ ባትሆን ያ ሰው ምን ማድረግ አለበት ብለህ ታስባለህ? ለምን?

4. ዛሬ ቤተክርስቲያን የምትጠቀምባቸው የአገልግሎት ጥሪ ማረጋገጫ መንገዶች ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ናቸው? ምንስ መደረግ አለበት ትላለህ?

5. የአንተ የአገልግሎት ጥሪ ከእግዚአብሔር ስለመሆኑ ምን ተጨባጭ ማስረጃዎች አሉህ?

# ለአገልግሎት መዘጋጀት

ማንኛውም አዲስ ሥራ ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊ ዝግጅት ሊደረግ እንደሚገባ የታወቀ ጉዳይ ነው። በቂና አስፈላጊ ዝግጅት ሳይደረግ የሚጀመር ሥራ ስኬታማነቱ ያጠራጥራል። እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የተጠሩ ሰዎች ለአገልግሎት ከመሠማራታቸው በፊት ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ ወዲያውኑ በአገልግሎት ላይ ማሰማራት እየቻለ ግን ጊዜ ወስደው ስለሚያገለግሉት አገልግሎት ምንነትና እንዴት ማገልገል እንደሚገባቸው እንዲያስቡና እንዲያሰላስሉ ይፈልጋል። ዝግጅቱ ራስን ለአገልግሎቱ ማሰናዳትና አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ለማሟላት ይረዳል።

እግዚአብሔር ሰዎችን ይጠራና ለተጠሩበት አገልግሎት ብቃት እንዲያገኙ ያዘጋጃቸዋል። እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው የሚያዘጋጅበት መንገድ የተለያየ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ታሪካቸው የተዘገበውን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ስንመለከት እግዚአብሔር ወደ አገልግሎት ከጠራቸው በኋላ በተለያየ መልክ ሲያዘጋጃቸው እንደነበር እንረዳለን። ለአገልግሎት መዘጋጀት የሚለው አሳብ በሁለት መልክ ሊታይ ይችላል።

የመጀመሪያው እግዚአብሔር ሰዎችን ይፋዊ በሆነ መንገድ ሳይጠራቸው ግን ወደፊት ሊጠራቸው ላሰበው አገልግሎት እነርሱ ሳያውቁ እነርሱን የሚቀርጽበት ዝግጅት ነው። ይህ ዝግጅት ግልጽ የሆነ የእግዚአብሔር ጥሪ ሳይመጣ የሚደረግ ነው። በዚህ ዓይነት ዝግጅት ወይም ሥልጠና ውስጥ ያለፉ የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ። ከእነርሱም አንዱ ሙሴ ነው። ሙሴ በልጅነቱ የእግዚአብሔርን ቃል ከእናቱ ሲማር ለንጉሥ ቤተሰብ የሚሰጠውን የግብጽ ትምህርት ደግሞ ከግብጻውያን ተምሮ ነበር (ሐዋ.7:22)። ሙሴ ዕብራዊ እንደሆነ ስለተረዳ ከቤተመንግሥት ኑሮ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር እነርሱ በነበሩበት ሁኔታ ለመኖር ልቡን እንደቆረጠ የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክርለታል። የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ *"ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፉን እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ"* (ዕብ.11:24-25) በማለት ይናገራል።

ሙሴ ይህን እርምጃ ሲወስድ ገና አፍላ ጎልማሳ ነበር። ይህን የእምነት እርምጃ ሲወስድ ደግሞ እምነቱን በተግባር ማሳየት ጀመረ። በተሰማው በራስ የመተማመን ስሜቱ ተነድቶ በባርነት ሥር ያሉትን ወገኖቹን ነጻ ለማውጣት ሙከራ አደረገ። መቼም በለጋ ጎልማሳነት ወቅት ሰዎች ሁሉን ነገር እንደሚችሉ አድርገው ያስባሉ። ሙሴም ይህ ዓይነቱ ፈተና ሳይደርስበት አልቀረም። ሙሴ እስራኤልን ከግብጽ ባርነት ነጻ ለማውጣት ትክክለኛ ሰው ነበር። ተልዕኮውም ትክክለኛ ነበር። ሆኖም ተልዕኮውን ለመፈጸም ሙሴ የወሰደው እርምጃ ትክክል አልነበረም።

ይህም ብቻ ሳይሆን ተልዕኮው የሚፈጸምበት ጊዜ ገና አልደረሰም። ሙሴ እግዚአብሔር አድርግ ሳይለው አደረገ። ተልዕኮውን ለመጀመር ገና አርባ ዓመት ይቀረው ነበር። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጊዜ አርባ ዓመት ቀደም ብሎ እርምጃ ወሰደ። ሙሴ ይህን እርምጃ የወሰደው በሕዝቡ በእስራኤል ላይ ይደረግ የነበረው ግፍ ስላሳሰበው ነው። በዚህ ድርጊቱም "ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉትም" (ሐዋ.7:25)።

ሙሴ ያለእግዚአብሔር ጊዜ የእስራኤል ነጻ አውጪ ለመሆን ሲነሳ ሕዝቡ "በእኛ ላይ አንተን ማን አለቃ ወይስ ዳኛ አደረገህ?" (ዘጸ2:14) በማለት ተቃወሙት። ስለዚህ እርምጃው ተቀባይነትን ወይም የዓላማ መሳካትን ሳይሆን ስደትን አመጣበትና ወደ ምድረ በዳ ወሰደው። ይህ ደግሞ እግዚአብሔር ሙሴን ለተልዕኮው የሚያዘጋጅበት ትምህርት ቤት ሆነ።

የሙሴን የዝግጅት ጊዜ በስፋት ለማየት ከመሄድ ቀደም ብሎ ግን ሰዎች ያለእግዚአብሔር ጊዜ ለአገልግሎት እንዲወጡ ሊያደርጉአቸው የሚችሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ መመልከቱ መልካም ይሆናል።

1. **የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ቅንዓታቸው ከፍተኛ በመሆኑ።** እግዚአብሔርን ከመውደዳቸው የተነሳ ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ ያስቡና ይህንንም ለማድረግ የተሻለ መንገድ ነው ብለው የሚያስቡት ለእግዚአብሔር ሥራ ሙሉጊዜያቸውን መስጠት ነው። እነርሱ እያሉ የወንጌልን ሥራ በብቃት የሚሠራ ሰው አለመኖሩ ያሳስባቸውና ራሳቸውን ለአገልግሎቱ ይለያሉ። እንግዲህ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ከመቅናት የተነሳ በበጎ ሕሊና የሚደረግ መስጠት ቢሆንም እግዚአብሔር ውጣ ሳይል መውጣት መልካም አይደለም። ለእግዚአብሔር አገልግሎት መቅናት በራሱ ለአገልግሎት ብቁ አያደርግም። የእግዚአብሔር ጥሪ መኖር አለበት።

2. **ስለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት ሲያስቡ ወይም አንዳንድ አገልግሎቶችን ሲያገለግሉ የሚሰማቸው ጥሩ ጥሩ ስሜቶችን ዘወትር ለመለማመድ።** አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ለምሳሌ ወንጌል ሲሰብኩ ወይም ሲያስተምሩ ወይም ሲያማክሩ ጥሩ ስሜት ከተሰማቸው እግዚአብሔር ለዚህ አገልግሎት እንደሚፈልጋቸው ያስባሉ። ከዚያም በላይ እነዚህ መልካም ስሜቶች ስለራሳቸው ጥሩ አመለካከት እንዲኖራቸው ያደርጉአቸዋል። ስለዚህ እነዚህን ጥሩ ስሜቶች ሁሌ ለመለማመድና ስለራሳቸውም ጥሩ ምስል ለማግኘት ለአገልግሎት ይወጣሉ።

3. **ትኩስ የወጣትነት ዕድሜ ተጽዕኖ።** ወጣቶች ወደፊት ምን እንደሚሆኑ አያውቁም። በዚህ ዕድሜያቸው መንፈሳዊን ነገር የሚወዱና በቤተክርስቲያንም የሚያገለግሉ ከሆኑ ሌሎች ሥራዎችን ሳይፈልጉ ለእግዚአብሔር መኖርና እርሱን ማገልገል አለብኝ የሚል ውሳኔ ይወስናሉ። ለእግዚአብሔር በወጣትነት ጊዜዬ አንድ ነገር ማድረግ አለብኝ

ይላሉ። እግዚአብሔርን ለማስደሰት ይፈልጋሉ። ከዚህም በተጨማሪ ከለመዱትና ዋስትና አለው ብለው ካሰቡት አገልግሎት ውጭ መጥተው ሌሎች ሥራዎችን ሙከራ ለማድረግ ይፈራሉ። ውሳኔያቸው ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝተው ስለተጠሩ ሳይሆን ከማንነት ትርጉም ማግኛ ጋር የተያያዘ ነው። ከጥቂት የአገልግሎት ዘመን በኋላ ያሰቡት ነገር ካልተሳካላቸው ግራ የተጋባ ሕይወት ይኖራሉ። ከሁለቱም (በእግዚአብሔር የተጠራ መልካም አገልጋይ ወይም በዓለም የራሱን ሥራ እየሠራ እግዚአብሔርን የሚያገለግል ሰው) ሳይሆኑ እንደቀሩ ይሰማቸዋል።

4. **አንድ ጊዜ ወደ አዕምሮአቸው የመጣውን አሳብ አቆይተው ከማሰላሰል ይልቅ ቶሎ ውሳኔ ለመወሰን የሚቻኮል ስብዕና መኖር።** አንዳንድ ሰዎች ወደ አዕምሮአቸው ለመጣው ነገር ቶሎ ውሳኔ መስጠት ይፈልጋሉ። ይህንንም የሚያደርጉት በውሳኔያቸው ምክንያት የሚመጣውን ጊዜያዊ ደስታ ለማግኘት ነው። ለዘላቂ ደስታ ብለው ለጊዜው ብቻ የሆነውን ደስታቸውን ማስተላለፍ አይችሉም። ባህርያቸው እንደልጆች ነው። የተሰማቸውን ነገር ወዲያውኑ ለማድረግ ያስባሉ። እንዲህ ዓይነት ባህርይ ያላቸው ሰዎች አንድ ሰው ስለአገልግሎት መልካምነትና የሚያስገኘውን መልካም ብድራት ሲያስተምር ልባቸው ከተነካ ወዲያውኑ ለአገልግሎት ለመውጣት ይወስናሉ።

5. **የሁኔታዎች ግፊት፡** አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ለአገልግሎት የሚወጡት በውስጣቸው የእግዚአብሔር ጥሪ ተሰምቶአቸው ሳይሆን ለእግዚአብሔር መልካም አመለካከት እያላቸው በተጨማሪም አንዳንድ ሁኔታዎች ግፊት ሲያደርጉባቸው ነው። ለምሳሌ የኮሌጅ ትምህርት እየተከታተሉ እያሉ ትምህርቱ ሳይሳካላቸው ይቀራል። በዚህ ጊዜ ምናልባት እግዚአብሔር ይህ እንዲሆን ያደረገው እኔን ለአገልግሎት ስለፈለገኝ ነው ብለው ይተረጉሙታል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሌሎች ሰዎች እንዲህ ዓይነት ትርጉም ይሰጡአቸዋል። በዚህ ሁኔታ ተገፍተው በፊት ለመሥራት ቅድሚያ ያልሰጡትን አገልግሎት ለመሥራት ራሳቸውን ይሰጣሉ። እግዚአብሔር በሁኔታዎች በኩል መናገር ቢችልም ለሁኔታዎች ሁሉ መንፈሳዊ የሆነ ትርጉም መስጠት አደገኛነት አለው።

6. **መንፈሳዊ ብስለት ማጣት።** አንዳንድ ሰዎች ገና ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ሲያምኑ ለአገልግሎት ልውጣ ይላሉ። ይህን የሚያደርጉት በጌታ ያገኙት አዲስ የሕይወት ልምምድ በጣም ስላስደሰታቸው ለዚህ ምላሽ ይሆን ዘንድ እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሳቸውን ለመስጠት ብለው ነው።

7. **የከፋ ተጽዕኖ።** ሰይጣን እግዚአብሔር ሰዎች ለአገልግሎት እንዲወጡ ከሚፈልግበት ጊዜ ቀደም ብለው እንዲወጡ ተጽዕኖ በማድረግ አገልግሎታቸውን ለማበላሸት ይጥራል።

ሙሴ ምድረ በዳ በትምህርት ላይ የቆየው ለአርባ ዓመት ነው። መቼም የአርባ ዓመት ትምህርት ምን ዓይነት ዲግሪ እንደሚያስገኝ አይታወቅም። በዚህ ዓለም የሚሰጡ ዲግሪዎች ይህን ያህል ዓመት አይፈጁም። ሙሴ ዲግሪ ባያገኝም ለአገልግሎቱ የሚጠቅመውን ብዙ መልካም ነገሮች እንደተማረ መገመት ይቻላል። የትምህርት ወይም የዝግጅት ዋና ተልዕኮ የሚማረውን ሰው በባህርይ በመለወጥ ለሚፈለግበት ዓላማ ማሰለፍ ነው። ከዚህ አኳያ እግዚአብሔር ሙሴን በምድረ በዳ ቀርጾ ለእስራኤል ሕዝብ መሪነት አዘጋጅቶታል። ሙሴ ለእግዚአብሔር ጊዜ ወደ ወገኖቹ ሲመጣ ሕዝቡ አስቀድሞ ያልፈለጉትን ሰው እንደገና ሲቀበሉት እንመለከታለን (ሐዋ.7:35)። ሰዎች አገልጋዮችን የሚቀበሉት እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ጠርቶአቸውና አሰልጥኖአቸው ሲልካቸው ነው።

እግዚአብሔር ለአገልግሎት ከመጥራቱ በፊት ያዘጋጀው ሌላው ሰው ደግሞ ዳዊት ነው። እግዚአብሔር ዳዊትን የጠራው ከእረኝነት ተግባር ላይ ነበር። እግዚአብሔር ዳዊት እረኛ በነበረበት ጊዜ ያለማመደው ነገር ነበር። ዳዊት እረኝነት የዕለት ተግባሩ ስለሆነ ያከናወነው ነበር እንጂ በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያስተምረኝ ነገር አለ ወይም እግዚአብሔር ለወደፊት አገልግሎቴ እያዘጋጀኝ ነው ብሎ አልነበረም። በዚህ የእረኝነት ወቅት ዳዊት የተማረው አንዱ ዋነኛ ነገር በእግዚአብሔር ላይ መደገፍን ነው። ዳዊት የሚጠብቀውን መንጋ ከአውሬ ለመታደግ ከአውሬ ጋር ይታገል ነበር። በዚህ ትግል ውስጥ ውጊያን ከመማሩም በላይ እግዚአብሔር ከክፉ አውሬዎች እንዴት እንደጠበቀውም ያስተውል ነበር።

ዳዊት ለሚጠብቀው መንጋ ብሎ ራስን መስጠትንም ተምሯል። በእጁ አደራ የተሰጡትን የአባቱን በጎች ደህንነት መጠበቅ ኃላፊነቱ ነበር። ይህንንም ኃላፊነት ለመወጣት ከጠላት ጋር ፊልሚያ ያደርግ ነበር። ከጎልያድ ጋር ሲጋጠምም ያደረገው ይህንኑን ነበር። የእግዚአብሔርን ሕዝብ ያስፈራራውን ጠላት ለመታገል ራሱን ሰጠ። ለመንጋው ደህንነት ራሱን የሚሰጥ ሰው ሆኖ ወጣ (1ሳሙ.17:34-37)።

ሁለተኛው ዝግጅት ደግሞ ሰዎቹ በግልጽ በእግዚአብሔር ከተጠሩ በኋላ የሚሰጣቸው ዝግጅት ነው። ይህን የተጠሩ ሰዎች እያወቁ ይሳተፉበታል። ከጥሪ በኋላ የሚደረገው ይፋዊ ዝግጅት በሚከተሉት ሁኔታዎች ይከናወናል።

የመጀመሪያው ልምድ ባላቸው የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሥር ሆኖ በቃልና በተግባር መማር ነው። ኤልሳዕ እግዚአብሔር ከጠራው በኋላ ወዲያውኑ በአገልግሎት ላይ አልተሰማራም። ለነቢይነት ቢጠራም ነቢይ ከመሆኑ በፊት የኤልያስ አገልጋይ ሆነ። በኤልያስ እግር ሥር ሆኖ አገልግሎትን መለማመድ ነበረበት።

ዳዊትም በእግዚአብሔር ከተጠራ በኋላ የዝግጅት ጊዜ ውስጥ አልፏል ነበር። ዳዊት በአንድ ጊዜ ንጉሥ አልሆነም። ደረጃ በደረጃ እየተራመደ ወደተጠራበት ዋና ተልዕኮ የመጣው ከብዙ ውጣ ውረዶች በኋላ ነው። አንዱ የዳዊት የዝግጅት ጊዜ በሳውል ሥር ሆኖ ማገልገል ነበር። ይህ ለዳዊት እጅግ ፈታኝ ሥልጠና ወቅት ነበር።

ሁለተኛው መንገድ የእግዚአብሔርን ቃል መማር ነው። ለአገልግሎት ከመውጣት በፊት የእግዚአብሔርን ቃል መማር መሠረታዊ ነገር ነው። ቃሉ የአገልግሎት መሠረትና መሣሪያ ነው። ቃሉን በሚገባ የማያውቅ አገልጋይ ምን እንደሚያገለግልና ምን መመገብ እንዳለበት አያውቅም። ስለዚህ የቃሉ እውቀትና ኑሮ አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ሲጠራቸው ከመላኩ በፊት ቃሉን በሚገባ እንዲማሩት ያናገራቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን ወደ ዐመጸኛ የእስራኤል ልጆች ሲልከው አስቀድሞ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲመገብ አዞት ነበር። እግዚአብሔር *"የሰው ልጅ ሆይ የገኘኸውን ብላ፣ ይህን መጽሐፍ ብላ፣ ሂደህም ለእስራኤል ቤት ተናገር አለኝ። አፌንም ከፈትሁ መጽሐፉንም አጎረሰኝ"* (ሕዝ.3:1-2)። መጽሐፉን ለቅምሻ ብቻ መማር ሳይሆን *"የሰው ልጅ ሆይ አፍህ ይብላ፣ በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ"* (ሕዝ.3:3) በማለት ሲያዘው እንመለከታለን። ከዚያም ሕዝቅኤል በላ በአፉም እንደ ማር ጣፈጠ። አንድ አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች መናገር የሚችለው ራሱ ቀጭ ብሎ ቃሉን ከበላ ብቻ ነው። እግዚአብሔር አገልጋዩ ለሌሎች ሄዶው ቃሉን እንዲናገር የሚያዘው መጀመሪያ ከእግሩ ሥር ቁጭ ብሎ ከተማረ በኋላ ነው። ቃሉን መብላት ቃሉን ከመናገር ይቀድማል።

የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ ለአገልግሎት ከመሰማራት በፊት ብቻ እንደሆነ ማሰብ ስህተት ነው። ለዝግጅት መማር ጠቃሚ ቢሆንም ቃሉን መመገብ ግን የዕለት ተግባር እንዲሆን በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ታዝናል። እግዚአብሔር ጀማሪ አገልጋይ የነበረውን ኢያሱን *"የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፣ ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው የዚያን ጊዜም መንገድህ ይቀናልሃል ይከናወንልሃልም"* (ኢያ.1:8) ብሎ አዘዘው። ስለዚህ አገልጋይ ለዝግጅት ብቻ ሳይሆን ሁሌ ቃሉን መማርና በቃሉ መኖር ይጠበቅበታል።

በአሁኑ ጊዜ ከእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ የተቀበሉ ሰዎች ለአገልግሎት ከሚዘጋጁባቸው መንገዶች አንዱ የእግዚአብሔርን ቃል መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው በመማር ነው። በሀገራችን እምብዛም የተለመደ ባይሆንም ሰዎች እግዚአብሔርን በሙሉ ጊዜ አገልጋይነት ለማገልገል ጥሪ እንዳላቸው ሲሰማቸው በቅድሚያ የሚወስዱት እርምጃ መንፈሳዊ ኮሌጅ ገብተው የሥነመለኮት ትምህርት መማር ነው። ይህ ትምህርት ቤት ሰዎቹ ስለጥሪያቸው ትክክለኛነት የሚያረጋግጡበት ቦታ ከመሆኑም ባሻገር ስጦታቸውን ለመለየት የሚሞክሩበትና ለአገልግሎት የሚታጠቁበት ሥፍራ ነው።

አንድ ሰው ከእግዚአብሔር የአገልግሎት ጥሪ ከተቀበለ በኋላ የሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ገብቶ መማር ያስፈልገዋልን? አገልግሎት ያለሥነመለኮት ትምህርት ስኬታማ ሊሆን አይችልምን? የአገልግሎት ስኬታማነት በትምህርት ችሎታ ይለካልን? አንድ ሰው ሥነመለኮት ትምህርት ቤት ገብቶ የሚሰጠውን ትምህርት በአጥጋቢ ሁኔታ መጨረስ ካልቻለ በአገልግሎቱ ጥሩ አገልጋይ መሆን አይችልም?

ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርትን ከጠራቸው በኋላ ለሦስት ዓመት ተከትል አስተማራቸው። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔር ያልተማሩ ሰዎችን መርጦ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይቀባቸውና ይጠቀምባቸዋል ብለው ያስባሉ። ለዚህም ማስረጃ ይሆናቸው ዘንድ የሚጠቅሱት የጌታን ደቀመዛሙርት ነው። በእርግጥ የጌታ ደቀመዛሙርት በዘመናቸው ሁኔታ ሲታዩ ብዙዎቹ የተማሩ ሰዎች አልነበሩም። ጌታም ሲመርጣቸው የትምህርታቸውን ነገር እንደ መሥፈርት አልቆጠረውም። ለመማራቸውንም እንደ መሥፈርት አልተጠቀመበትም። ያልተማሩ ሰዎች ቢጠሩም ወደ አገልግሎት ከመሠማራታቸው በፊት ግን የሦስት ዓመት ተከትል ትምህርት ተምረዋል። የሚገርመው ደቀመዛሙርትን ያስተማረው መምህር በዚህ ዓለም ላይ ተወዳዳሪ የሌለው "ፕሮፌሰር" ጌታ ኢየሱስ ነበር።

ሰዎች በተራ መምህራን እንኳ ተምረው ምን ያህል ለውጥ እንደሚያመጡ እናውቃለን። በጌታ ኢየሱስ ለሦስት ዓመት ተከትል ተምረው ደግሞ ምን ያህል የተለወጡ ሰዎች እንደሆኑ ማሰብ አያዳግትም። ደቀመዛሙርት የተማሩት ዘወትር ከእርሱ ጋር በመሆን ነበር። በእነዚያ ዓመታት ከእርሱ አልተለዩም ነበር። የተማሩትም እርሱ በቃል የሚያስተምራቸውን ብቻ ሳይሆን ከሕይወቱ ምሳሌነትም ጭምር ነበር። ስለዚህ ደቀመዛሙርት ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት የሥነመለኮት ትምህርት ተምረው ነበር።

በዝግጅት ውስጥ የሙከራ ጊዜ ይሰጣል። በተለይ በመደበኛ ሁኔታ የሚሰጠው ዝግጅት ወደማለቂያው አካባቢ ሲደርስ የመስክ የተግበር ፍተሻ ይደረጋል። በሀገራችን በአብዛኛው ለመስክ ሙከራ የሚወጡ መምህራን ለመሆን የሚሰለጥኑ እጩ መምህራን ናቸው። እነዚህ እጩ መምህራን ሥልጠናቸውን ወደ መጨረሱ አካባቢ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች ይመደቡና ለተወሰኑ ወራት ያስተምራሉ። በቃል የተማሩት ነገር ከሕይወታቸው ጋር ተዋህዶ ምን ያህሉን በተግባር ማሳየት እንደሚችሉ የሚገመገሙበት ጊዜ ነው። በዚህ ሙከራ ላይ ሰልጣኞቹ ማስተማር ማለት ምን እንደሆነ በተግባር ከማየታቸውም በላይ መምህር ለመሆን ምን ያህል ብቃት እንዳገኙ በተግባር ይፈተሻል። ከሙከራው በኋላ አሠልጣኙ የእጩ መምህራኑን ጠንካራና ደካማ ጎኖች ያሳያቸዋል። ይህ ደግሞ ደካማ ጎናቸውን ወደፊት በማሻሻል ጥሩ መምህራን እንዲሆኑ ያደፋፍራቸዋል።

ጌታ ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱ የተማሩትን ነገር በሙተግበር እንዲያሳዩት ትምህርቱ ከማለቁ በፊት ለመስክ አገልግሎት ልኮአቸው ነበር። ደቀመዛሙርቱ ሥልጠናቸውን ሊጨርሱ አካባቢ ጌታ ደቀመዛሙርቱን ተልዕኮ ሰጥቶአቸው ላካቸው (ሉቃ.10:1-20)። ተልዕኮአቸው ድውዮችን መፈወስና የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እነርሱ እንደቀረበች መናገር ነበር። ዓላማውም የእግዚአብሔር መንግሥት በክርስቶስ በኩል ለሰዎች እንደቀረበች በማሳየት ንስሐ እንዲገቡ ለማስተማር ነው። ይህ የጌታ ኢየሱስ ትልቁ መልዕክት ነበር። ደቀመዛሙርትም እንዲያደርሱት የተላኩት ይህንኑን መልዕክት ነው።

ለተልዕኮ የወጡ ደቀመዛሙርት ወደ ጌታ ሲመለሱ በደስታ ነበር። ደስ እያላቸው ተመለሱ። ይህም ብቻ ሳይሆን ሪፖርትም አድርገዋል። ካቀረቡት የመስክ አገልግሎት ሪፖርት አንዱ "ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል" የሚል ነበር።

ጌታ ኢየሱስ ሪፖርታቸውን ከሰማ በኋላ ለደቀመዛሙርቱ፥ የደስታቸው ምንጭ በሰይጣንና በእርሱ ሥር በሚሰሩት መናፍስት ላይ የበላይነት ማግኘት መሆን እንደሌለበት አሳያቸው። ሰይጣን ከጌታ የተነሳ በእግዚአብሔር ሰዎች እግር ሥር ወድቋል። ጌታ አሸንፎታል። ስለዚህ የተሸነፈን ኃይል ከሰዎች በማስወጣት መፎከርና ደስ መሰኘት ዋና ነገር አይደለም። አንዳንድ አገልጋዮች በጌታ ኢየሱስ ስም አጋንንት ሲያስወጡ እጅግ ደስ ይላቸዋል። እንደ ትልቅ ገድልም ያወራሉ። ይህ ግን ዋና ነገር እንዳልሆነ ጌታ ከመስክ አገልግሎት ለተመለሱት ደቀመዛሙርት ገለጾላቸዋል። እንደ ጌታ ትምህርት አገልጋዮች ደስ ሊሰኙበት የሚገባው ነገር በአገልግሎታቸው መሳካት ሳይሆን እግዚአብሔር ጠርቶአቸው የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች እንዲሆኑና የዘላለም መታሰቢያ እንዲኖራቸው በማድረጉ መሆን አለበት። ትኩረቱ፥ በአገልግሎት ላይ ሳይሆን በድነት ላይ መሆን እንዳለበት ያሳስባል። በእግዚአብሔር ተጠርቶ የዘላለም ሕይወት ማግኘት በእግዚአብሔር ስም ማንኛውንም የክፋት ኃይላትን ከማንበርከክ ይልቃል።

በእግዚአብሔር ስም ተዓምር መስራት የአገልጋዮች የደስታ ምንጭ መሆን የለበትም። ምክንያቱም በጌታ አምነው ድነት ያላገኙ ሰዎችም ተዓምር ሊሰሩ ይችላሉ። በቤተክርስቲያን በጌታ ስም የሚያገለግሉና ራሳቸውን እንደ ክርስቶስ አገልጋዮች የሚቆጥሩ ብዙዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነርሱ ራሳቸውን እንደ ጌታ አገልጋዮች ቢቆጥሩም እግዚአብሔር ግን በእርግጥ አያውቃቸውም (ማቴ.7:22)። ይህ የሚያሳየው በአንዳንድ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ብቅ ብቅ ማለት አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን የጠበቀ ግንኙነት ሊያመለክት አለመቻሉን ነው። ስለዚህ በአገልጋይ ሕይወት ቅድሚያ ሊያገኝ የሚገባው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው መንፈሳዊ ግንኙነት ነው። የዚህ ግንኙነት መልካም መሆን የደስታው ምንጭ ሊሆን ይገባል። የአገልግሎት ስኬት ደስታ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚመጣ ነው።

በመደበኛ የሥነመለኮት ትምህርት መመረቅ ብቻ ለአገልግሎት ብቃት ማግኘትን አያመለክትም። ከትምህርት በኋላ ወንጌል የሚሰራበት ኃይል ያስፈልጋል። ደቀመዛሙርት የተመደበላቸውን የሥነመለኮት ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ምናልባት በመጨረሻው አራት ጊዜ የምረቃ ሥነሥርዓት ተደርጎላቸው ይሆናል። ሆኖም ቢመረቁም ወደ አገልግሎት ከመሰማራታቸው በፊት አንድ እጅግ በጣም የሚያስፈልጋቸው ነገር ነበር። ይኼውም የመንፈስ ቅዱስን ኃይል መቀበል ነው (ሉቃ24:49፤ የሐዋ1:8)። መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች አዲስ ነገርን ያስተምራል። እንደዚሁም ሰዎች የተማሩትን ነገር በአስፈላጊው ሥፍራና ሁኔታ በማስታወስ የእግዚአብሔርን አሳብ እንዲያገለግሉ ያደርጋል። ከትንሣኤ በኋላ ደቀመዛሙርት የተማሩትን ነገር እንዲያስታውሱና አሳቡንም በግልጽ ያለምንም ፍርሃት እንዲናገሩ ረድቷቸዋል (የሐዋ.2)።

ያለመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ አገልግሎት መግባት ያለጦር መሣሪያ ትጥቅ ጦር ሜዳ እንደ መሄድ ያህል ነው። በእግዚአብሔር የተጠሩ አገልጋዮች ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞሉ ሰዎች ነበሩ። ለምሳሌ ያህል ጌዴዎን (መሳ.6:34)፣ ሳምሶን (መሳ.13:25፤14:6፣19)፣ ሳኦል (1ሳሙ.10:9-10)፣ ዳዊት (1ሳሙ.16:13)፣ ኤልሳዕ (1ነገ.2:9-15)፣ ጌታ ኢየሱስ (ሉቃ.4:14) እና ሌሎችም ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የተሞሉ ነበሩ። ስለዚህ እያንዳንዱ የአገልግሎት ጥሪ የተቀበለ አገልጋይ በእግዚአብሔር መንፈስ በኃይል እስኪሞላ ድረስ እግዚአብሔርን መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ይህ መጠበቅ ደግሞ እንደ ደቀመዛሙርት የእግዚአብሔርን ፊት እየፈለጉ መሆን አለበት። ሐዋርያትና ሌሎችም መንፈስ ቅዱስ በኃይል እስኪወርድባቸው ድረስ አብረው በጸሎት ይተጉ ነበር።

እንግዲህ ከአገልግሎት በፊት ሥልጠና መውሰድ አስፈላጊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሆኖ እያለ አንዳንድ ጥሪ አለን የሚሉ ሰዎች ሥልጠና እንዲያገኙ በተለይም ሥነመለኮት እንዲማሩ ሲጠየቁ ፈቃደኛ አይሆኑም። እነዚህ ሰዎች ወደ ሥነመለኮት ትምህርት ቤት ላለመግባት የሚያቀርቡአቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ከእነዚህም ለምሳሌ ያህል "ትምህርት ጸጋን ይገድላል/ያስጥላል" "ትምህርት ያስታብያል" እና "የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በትምህርት ቤት አይገኝም" የሚሉ ይገኙበታል። መቼም ሁሉም ዓይነት ምግብ ለሰውነት ተመሳሳይ ጥቅም እንደማይሰጥ ሁሉ ሁሉም የሥነመለኮት ትምህርት ሰዎችን እኩል ለአገልግሎት አያዘጋጅም። ይህም የሚወሰነው በትምህርቱ ይዘትና አሰጣጥ ይሆናል። የሚሰጡ ትምህርቶች የአገልጋዮችን ሁለንተናዊ ሕይወት የሚገነቡና ለአገልግሎት የሚያዘጋጁ ካልሆኑ እንዲሁም አሰጣጡ የአገልጋዮችን አውድ ያገናዘበ ካልሆነ ፍሬያማ ላይሆን ይችላል። በዚህ ሁኔታ አንዳንዶች ከመጽሐፍ ቅድስ ትምህርት ቤት የወጡ አገልጋዮችን ሲያዩ አንዳንዶች የተሻሉ ሆነው ሌሎች ደግሞ ቀድሞ የነበራቸውንም መልካም ነገር ጥለው ሊወጡ ይችላሉ።

አንድ ማስተዋል ያለብን ነገር ግን አገልጋዮች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተምረው ሲወጡ ረጋ ማለት ይታይባቸዋል። ሲያገለግሉ ሕዝቡን በስሜት ከማናወጥ ይልቅ ጠለቅ ያለ የእግዚአብሔርን ቃል በእርጋታ ያስተምራሉ። የስሜት ስክነት መንፈሳዊ ድርቀትን አያመለክትም፣ ይልቅስ የብስለት መለኪያ ይሆናል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብቶ መማርን የሚቃወሙ ሌሎች ሰዎች ደግሞ ራሳቸውን ለመከላከል የሚያቀርቡት ምክንያት ይመስላል። ራሳቸው ትምህርት ቤት ገብተው መማር ስለማይችሉ ትምህርቱ ፍሬ እንደሌለው በማውራት ያጣጥሉታል። አሳቡ "እኔ መማር ስለማልችል ጥሩ አይደለም" እንደማለት ነው። ይህ ደግሞ እውነት አለመሆኑን እናውቃለን።

**ሦስተኛው ካለፈው የሕይወት ልምምድና ትምህርት መልካም ነገርን መቅሰም ነው። ይህ አንድ ሰው ካሳለፈው ሕይወት ለአገልግሎቱ የሚጠቅመውን መልካም ነገር ለመማር የሚያስላስልበት ወቅት ነው።**

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ዓይነት ዝግጅት ውስጥ አልፏል። ጳውሎስ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጥሪ ከተቀበለ በኋላ ወደ አረብ ሀገር በመሄድ ለተወሰነ ጊዜ ብቻውን ቆየ (ገላ.1:17)። በዚህ የቆይታ ጊዜ ውስጥ በፊት የተማራቸውን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን በአዲስ ሁኔታ ማሰላሰል ጀመረ። እርሱ የሚያውቃቸው ቅዱሳት መጽሐፍት ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወትና ሞት የሚናገሩትን ነገሮች ከአዲሱ መገለጥ ጋር በማነጻጸር ለመረዳት ያሰላስልና ያብሰለስል ነበር። ከዚያም በወንጌል የተገለጠውን የእግዚአብሔር ጸጋ በመሞላት ወጣ። በዚህ ቆይታው ጳውሎስ ለወደፊት አገልግሎቱ፣ በሚገባ ተዘጋጀ።

እንግዲህ አንድ ሰው ዕድሜውን ሁሉ ለማገልገል ለተጠራበት አገልግሎት በቂ የዝግጅት ጊዜ ሊኖረው ይገባል። ዝግጅት መደበኛ ወይም መደበኛ ባልሆነ ሁኔታ ሊደረግ ይችላል። ተፈላጊነቱ፣ ለአገልግሎት የሚያበቃ ዝግጅት ማድረግ ላይ ነው። ሥልጠና የጨረሰ ወታደር ወደ ጦር ሜዳ እንደሚሄድ ዝግጅቱን ያጠናቀቀ አገልጋይም ወደ አገልግሎት መስክ ይሰማራል። በዚህ አዲስ መስክ አገልጋይ እንዴት ማገልገል እንዳለበት በሚቀጥሉት ተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ እንመለከታለን።

---

## ጥያቄዎች

1. ለአገልግሎት ከመውጣት በፊት የዝግጅት ወቅት ለምን ያስፈልጋል?
2. ሰዎች ለምን ያህል ጊዜ መዘጋጀት አለባቸው? በዚያ ዝግጅት ጊዜስ ምን ይሠራሉ?
3. ለአገልግሎት ለመዘጋጀት የሥነመለኮት ትምህርት ቤት መግባት የግድ ያስፈልጋልን? ይህ በአገልግሎት ላይ ያለውን አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ግለጽ።
4. ለአገልግሎት ከመውጣትህ በፊት እንዴት ተዘጋጀህ? ገና ለአገልግሎት ካልወጣህስ እንዴት እየተዘጋጀህ ነው?

## 8
## ለአገልግሎት መሾም

ወደ ሙሉጊዜ አገልግሎት የሚመጡ አገልጋዮች አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት መሾም ይገባቸዋል? ሹመትስ ለአገልግሎት አስፈላጊ ነውን?

ሹመት የሚለው አሳብ በቤተክርስቲያን ውስጥ ጥቅም ላይ የዋለው አንድን በእግዚአብሔር የተጠራን ሰው እግዚአብሔር ለጠራበት አገልግሎት መመደብን ለማመልከት ነው። በዚህ መልኩ ሹመት የተጠራን ሰው በተጠራበት ሥፍራ የመመደብና ዕውቅና የመስጠት ሥርዓት ነው። ሹመት ሲከናወን ሥርዓት ሊኖር ወይም ላይኖር ይችላል።

የሹመት ሥርዓት መፈጸም በራሱ የሚያመጣው መለኮታዊ ኃይል ወይም ባርኮት የለውም። እጅ ጭኖ መሾም በቤተክርስቲያን አንድ ሰው እግዚአብሔር ለአንድ የአገልግሎት መስክ ቀብቶ እንደሾመው ለማመልከት የሚደረግ ሥርዓት ነው። ቤተክርስቲያን አገልጋይን ስትሾም "እግዚአብሔር ለዚህ ወይም ለዚያ አገልግሎት እንደጠራህ እናውቃለን፤ በአገልግሎትህም ከአንተ ጋር እንቆማለን" ማለትዋ ነው። ስለዚህ ሹመት ሁለት ነገሮችን ያመለክታል። የመጀመሪያው እግዚአብሔር አንድን አገልጋይ ለአገልግሎት መጥራቱና ለአገልግሎት መሾሙን ነው። ይህ የተጠራው አገልጋይ በግል ሕይወቱ የሚያውቀው ጉዳይ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ቤተክርስቲያን እግዚአብሔር አገልጋዩን እንደጠራው በመረዳት ከፈቃዱ ጋር መስማማትዋን የምትገልጽበት መንገድ ነው።

በብሉይ ኪዳን በእስራኤል ሕዝብ ታሪክ ካህናት፣ ነቢያት እና ነገሥታት ይሾሙ እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመለከታለን።

ሹመት በአብዛኛው እጅ በመጫን ከመጸለይ ጋር የተያያዘ ክንውን ነው። በአዲስ ኪዳን እጅ መጫን በተለያዩ ሁኔታዎች ተገልጿል። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ነገሮች መጥቀስ ይቻላል።

**የመጀመሪያው ከፈውስ ስጦታ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ነው።** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በበሽተኞች ላይ እጁን በመጫን ሲፈውሳቸው ነበር (ማቴ.9፡18፤ ማር.6፡5)። ሐዋርያትም እንዲሁ ያደርጉ ነበር (ሐዋ.28፡8)።

**ሁለተኛው ሌላውን ሰው ለመባረክ ነው።** ጌታ ኢየሱስ ወደ እርሱ የመጡትን ልጆች እጁን በመጫን ባረካቸው። ልጆችን ወደ ጌታ ያመጡ ሰዎችም ልጆቹን ወደእርሱ ያመጡት እጁን ጭኖባቸው እንዲባርካቸው ነበር። ጌታም እንዲሁ አደረገ። ይህ በዚያን ዘመን እጅ ጭኖ መባረክ የተለመደ ነገር መሆኑን ያመለክታል (ማቴ.19፡13-15)።

**ሦስተኛው ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት ነው።** በጌታ ያመኑ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ እንዲሞሉ አገልጋዮች እጃቸውን ጭነው ለምዕመናን ይጸልያሉ (ሐዋ.8፡17-19፤ 19፡6)።

**አራተኛው ለተለየ ሥራ ሰዎችን ለመለየት ነው።** ይህ ከሹመት ጋር የተያያዘ እጅ መጫን ነው። ሰዎችን እጅ በመጫን ለአገልግሎት መለየት የተጀመረው ጌታ ኢየሱስ ካረገና ቤተክርስቲያን ከተመሰረተች በኋላ ነው። ይህን ሥርዓት የጀመሩት ሐዋርያት ነበሩ። ጌታ ኢየሱስ

ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን በተለይም አስራ ሁለቱን የጠራቸውና የላካቸው ያለምንም እጅ የመጫን ሥርዓት ነበር። ጌታ ኢየሱስ የእጅ መጫን ወይም የሹመት ሥነሥርዓት ባይፈጽምም በሥልጣኑ ሐዋርያትን ለመረጣቸው ተልዕኮ ልኮአቸዋል።

*እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀመዛሙርት አድርጓቸው* (ማቴ.28:19).

ሐዋርያት ግን ይፋዊ የሆነ የሹመት ሥነሥርዓት በማድረግ የመጀመሪያዎቹን ዲያቆናት ሾሙ።

*ይህም ቃል ሕዝቡን ሁሉ ደስ አሰኛቸው...መረጡ። በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፣ ከጸለዩም በኋላ እጃቸውን ጫኑባቸው*(ሐዋ.6:5-6)።

ሐዋርያት እነዚህን ሰባት ሰዎች እጅ በመጫን ሲሾሙአቸው ሰዎቹ በእግዚአብሔር ፊት መልካም የሆነ ሕይወት እንደነበራቸው ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለቤተክርስቲያን ማሳወቃቸው እና እግዚአብሔር ለጠራቸው አገልግሎት መለየታቸው እንዲሁም እነርሱም የእግዚአብሔርን ጥሪ በመታዘዝ የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመቀበል ፈቃደኞች መሆናቸውን የሚያመለክት ክስተት ነው።

በአንጾኪያ ቤተክርስቲያን የነበሩ አገልጋዮች በርናባስንና ሳውልን እግዚአብሔር ለጠራቸው አገልግሎት ከመላካቸው በፊት *"ከጦሙና ከጸለዩም እጃቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው"* (የሐዋ.13:3) ይላል-የእግዚአብሔር ቃል።

አምስተኛው በቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች በተጠሩ አገልጋዮች ላይ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች እንዲመጡ ለማነሳሳት ነው።

*በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል* (1ጢሞ4:14)።

- እጅ መጫን ወይም ሹመት በራሱ ተዓምራዊ የሆነ ኃይል የለውም።
- እጅ የሚጭነው ወይም የሚሾም አገልጋይ በራሱ የሚያመጣው ተዓምር የለውም።
- በሹመት ወይም እጅ በመጫን ጊዜ መልካም ነገር ቢከሰት የተከሰተው በጸሎት አማካኝነት ከእግዚአብሔር ነው። ሰዎች በእጅ መጫን ቢፈወሱ ወይም በመንፈስ ቅዱስ ቢሞሉ ይህን ያደረገው እጅ የጫነው አገልጋይ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለሆነ ለእርሱ የሚገባውን ክብር መስጠት ይገባል።

የሹመት ሥነሥርዓት በሚፈጸምበት ጊዜ በተደጋጋሚ የሚደረጉ ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች ከሹመት ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው። እነርሱም ጸሎት፣ ጾምና የሚሾሙትን ሰዎች ለጌታ አደራ አሳልፎ መስጠት ናቸው (ሐዋ.14:23)።

የሹመት ሥርዓት ሲደረግ ማን ማድረግ አለበት? የሚለው እንደ ቤተእምነቱ ወግና ደንብ የተለያየ ቢሆንም የእግዚአብሔርን ቃል ስንመለከት የሚከተሉት ሰዎች ሌሎችን ይሾማሉ።

- ነባር አገልጋዮች አዳዲሶችን ይሾማሉ። ለምሳሌ ሙሴ ኢያሱን
- ነቢያት ነገሥታትን ለምሳሌ ሳሙኤል ሳውልን፣ ዳዊትን
- ሐዋርያት ሽማግሌዎችን
- ሽማግሌዎች ጢሞቴዎስን(አገልጋይን)

ስለዚህ አንድን አገልጋይ እግዚአብሔር ለጠራበት አገልግሎት የሚሾመው ከአገልጋዩ በላይ ሥልጣን ያለው የቤተክርስቲያን አገልጋይ ቢሆን መልካም ነው። ሰባቱ ዲያቆናት በሐዋርያት ተሾሙ (የሐዋ.6:5-6)፣ በርናባስና ሳውል የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችን ሾሙ (የሐዋ.14:23)። በሿሚና በተሿሚው መካከል ግንኙነት አለ (1ጢሞ5:22)።

ሹመት የተሰጠው አገልግሎት የዕድሜ ልክ መሆኑንም ያመለክታል። ዩተሾመ አገልጋይ ከተሾመበት አገልግሎት ላይ የሚነሳው በስህተት ትምህርት ውስጥ ገብቶ ሲገኝ፣ ግልጽ የሆነ ኃጢአት ሲፈጽም እና በራሱ ፈቃድ አገልግሎቱን ሲያቋርጥ ነው። የተሾመ አገልጋይ በኃጢአት ምክንያት ከአገልግሎት ታግዶ ወደ አገልግሎት እንዲመለስ ሲደረግ እንደገና የሹመት ሥርዓት አይደረግለትም።

አንዳንድ ቤተክርስቲያናት የተሾመ አገልጋይ ከሌላ ቤተእምነት ወደእነርሱ ሲመጣ እንደ አገልጋይ ሳይሆን እንደ አባል ብቻ ይቀበሉና የእነርሱን መስፈርት ሲያሟላ ብቻ እንደገና ይሾሙታል። ሌሎች ደግሞ የተሾመውን አገልጋይ እንዳለ ይቀበላሉ።

የሹመት ሥነሥርዓት ለአገልጋዮች ቢደረግ መልካም ነው። ከሚሰጣቸው ጥቅሞች ጥቂቶቹ፡-

- ቤተክርስቲያን አገልጋዩ በተጠራበት አገልግሎት ስጦታ እንዳለው ስለተቀበለች አገልጋዩ የበለጠ እንዲያገለግል የተከፈተ በር ያገኛል። ለአገልግሎት ስጦታው እውቅና ተሰጠው ማለት ነው።
- ምዕመናን ወይም እርሱ የሚያገለግላቸው ሰዎች አገልግሎቱን ይቀበላሉ። ከዚህም የተነሳ በተሰጠው ስጦታ ለማገልገል "ሥልጣን" ያገኛል። ምዕመናንም አገልጋዩን እንደ እግዚአብሔር ባሪያ የሚገባውን አክብሮት ይሰጡታል፣ ይታዘዙታል። ለአገልግሎቱም ስኬታማነት ከእነርሱ የሚጠበቅባቸውን ድርሻ ያከናውናሉ።
- አገልጋዩ ከፍተኛ ኃላፊነት እንደተሰጠው ስለሚረዳ ኃላፊነቱን በሚገባ ለመወጣት እግዚአብሔር በሰጠው ስጦታ በትጋት እንዲያገለግል ያግዘዋል። የተሰጠው ሹመት የስም ብቻ ሳይሆን በአገልግሎቱ ፍሬ ይበልጥ እንዲገለጥ የሚገባውን ነገር እንዲያደርግ ብርታት ይሰጠዋል።
- አገልጋዩ ሹመቱን ሲቀበል ተጠያቂነቱ ለማን እንደሆነ በግልጽ እንዲያውቅ ይረደዋል። አገልግሎት የሚከናወነው በሌሎች የእግዚአብሔር ሰዎች ሥልጣን ሥር መሆን እንደሆነ በሕዝብ ፊት የሚያስተጋባበት ሥርዓት ነው።

በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ መታወቅ ያለበት የሹመት ሥርዓት መደረግና አለመደረግ ሳይሆን ለሹመት የሚያበቃ የአገልግሎት ስጦታና የአገልጋዩ መሰጠት መኖሩ ነው። ስጦታው ካለ አገልጋዩ አገልግሎቱን ማከናወን ይችላል። የሹመት ሥርዓት ለሙሉ ጊዜ አገልጋዮች መደረጉ መልካም ቢሆንም ለአገልግሎት ስኬት እንደ ወሳኝ ነገር አይቆጠርም።

የአንድ አገልጋይ የአገልግሎት ስኬት የሚለካው በመሾሙ ወይም ባለመሾሙ ሳይሆን በሚኖረው የአገልግሎት ሕይወትና በሚሰጠው የአገልግሎት ፍሬ ነው። የአገልጋይ ሕይወትና አገልግሎት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያሳዩ አያሌ ምሳሌዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነዚህን ምሳሌዎችና ያላቸውን ምልከታ በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን።

---

## ጥያቄዎች

1. ሹመት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለመሆኑ ምን ማስረጃዎች አሉ?
2. የሹመት ጥቅምና ጉዳቱ ምንድነው?
3. የሚሾሙ አገልጋዮች እነማን ናቸው? የማይሾሙስ? ለምን?
4. አንተ/አንቺ ስለሹመት ምን አመለካከት አለህ/አለሽ? ለምን?

## 9
## የአገልግሎት ስጦታን መለየት

አንድ ሰው እግዚአብሔር ለአገልግሎት እንደጠራው እርግጠኛ በመሆን የዝግጅት ጊዜውን አጠናቅቆ ወደ አገልግሎት ቢሰማራም የአገልግሎት ስጦታውን ማወቅ ግን በቀላሉ የሚከናወን ጉዳይ አይደለም። የአገልግሎት ስጦታን የሚለየው በሂደት ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች ስለሚኖሩ አንዳንዴ ተስፋ መቁረጥ ያጋጥማል።

አንድ ሰው ለአገልግሎት ከተጠራ በኋላ መስጠት የሚገባውን አገልግሎት ከስጦታው አኳያ ለመለየት የሚረዱ አንዳንድ ነጥቦች አሉ። እነዚህ ነጥቦች አሳቦች እንጂ ሕጎች አይደሉም። ለአንዳንዶች በጥሩ ሁኔታ ሲረዱ ለሌሎች ደግሞ በተመሳሳይ መልኩ ላይረዱ ይችላሉ። ሆኖም በአግባቡ ለተጠቀመበት ሰው ጥቅማቸው የላቀ ነው።

### 1. የአገልግሎት ስጦታዎችን በዝርዝር ማወቅ

አንድ አገልጋይ የአገልግሎት ስጦታው ምን እንደሆነ ለማወቅ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጠቀሱትን የአገልግሎት ስጦታዎችን በሚገባ ማወቅ ይኖርበታል። ከዚያ ከተጠቀሱት ውስጥ የእርሱ የትኛው እንደሆነ መለየት ይችላል። የአገልግሎት ስጦታዎች ምን እንደሆኑ የማያውቅ አገልጋይ ስጦታውን እንዲህ ወይም እንዲያ ነው ብሎ ለመናገር አይችልም።

አንድ አገልጋይ ከአንድ በላይ ስጦታዎች ሊኖሩት ይችላል። ለምሳሌ አንድ አገልጋይ የማስተማር፣ የመምራት እና የማማከር ስጦታ ሊኖረው ይችላል። ብዙውን ጊዜ አንዱ ስጦታ ከሌሎች ይልቅ ተገልጦ ስለሚወጣ ሌሎች ስጦታዎች ተደብቀው የመቅረታቸው ዕድል ከፍተኛ ነው።

አንድ ዓይነት ስጦታ በተለያዩ አገልጋዮች ውስጥ በተለያዩ የአገልግሎት መስኮች ይገለጣል። ለምሳሌ ሁለት አገልጋዮች የማስተማር ስጦታ ቢኖራቸው የአንዱ ልጆችን በማስተማር ሲገለጥ የሌላው ደግሞ ጎልማሶችን በማስተማር ይገለጣል። ይህ የአገልግሎት ስጦታን መለየት ብቻ በቂ እንዳልሆነና ስጦታው በከፍተኛ ደረጃ የሚጠቀምበትን የአገልግሎት መስክ ማወቅም አስፈላጊ መሆኑን ያሳየናል።

### 2. በተለያዩ አገልግሎቶች ተሳትፎ መፈተሽ

ለአገልግሎት የተጠራ ሰው የአገልግሎት ስጦታ ምን እንደሆነ ቢያውቅም በቤተክርስቲያን በተከፈተለት የአገልግሎት መስክ ሁሉ ገብቶ ለማገልገል ፈቃደኛ መሆን አለበት። በተከፈተለት የአገልግሎት መስኮች ሲያገለግል መንፈስ ቅዱስ ቀስ በቀስ የእርሱን ስጦታ እየገለጠለት ይመጣል።

የአገልግሎት ስጦታን ለመለየት ዓይነተኛ መንገድ ዝም ብሎ መጸለይ ሳይሆን እየጸለዩ የተገኘውን ማገልገል ነው። ስጦታ እየጠራ

የሚመጣው በአገልግሎት ላይ ነው። ከተለመደው የአገልግሎት ዓይነት ወጣ ብሎ ያልለመዱትንም መሞከር ያልተገለጠው የአገልግሎት ስጦታ ገሃድ እንዲወጣ ይረዳል። እዚህ ላይ ግን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ የአገልግሎት ስጦታዎችን ለምሳሌ መስበክ፣ ማስተማር፣ መምራት፣ ማማከር እና የመሳሰሉትን መለማመድ ይቻላል። አንዳንዶቹን ግን እንደዚያ መለማመድ እንደሚቻል መናገር አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው የእምነት ስጦታ እንዳለው ለመፈተሽ አባይ ወንዝ ውስጥ ገብቶ በእግሩ በደረቅ መሬት ላይ ለመሻገር አይሞክርም። የትንቢት ስጦታ እንዳለው ለማወቅ ትንቢት መናገር አይጀምርም። ስለዚህ መለማመድ የሚቻለው ለልምምድ የሚመቹትን ብቻ ነው።

### 3. የራስን ዝንባሌ ማጤን

በአብዛኛው ዝንባሌ ያለበት አካባቢ የአገልግሎት ስጦታው መኖሩን ያመለክታል። እግዚአብሔር አገልጋዩ በአንድ የአገልግሎት ስጦታ ላይ እንዲያዘነብል በማድረግ ያ ስጦታ እንዳለው ያሳየዋል። ስጦታ ከመገለጡ በፊት በዚያ መስክ ዝንባሌ ይታያል።

ዝንባሌ አንድ የአገልግሎት ስጦታ ለመኖሩ ዋስትና አይሆንም። እኔ የሙዚቃ መሣሪያ ለመጫወት ያለኝ ፍላጎት በጣም ከፍተኛ ነበር። ከዚህም የተነሳ ለመነሻ ያህል በጣም ቆንጆ ክራር አስራሁና መለማመድ ጀመርኩ። ከአንድ ዓመት ልምምድ በኋላ የክሮቹን ድምጾች ለመለየት እንኳ አልቻልኩም። ያኔ ትምህርት ቤት ስለነበርኩ እኔ ዘንድ የሚመጡ አንዳንድ ጓደኞቼ ጥቂት በመለማመድ ብቻ የፈለጉትን መዝሙር በክራር መዘመር ቻሉ። ሙከራዬን ለአንድ ዓመት ሳላቋርጥ ካደረኩ በኋላ ምንም ፍሬ ሳጣበት አቆምኩኝ። የሙዚቃ መሣሪያ ለመጫወት ፍላጎት ቢኖረኝም ስጦታው ግን ስለሌለኝ ለምን ጊዜዬን በዚህ ላይ አጠፋለሁ ወደሚል መደምደሚያ ላይ ደረስኩ። ስለዚህ ፍላጎት ሁልጊዜ የስጦታውን መኖር ላያመለክት ይችላል። ሆኖም ዝንባሌው ካለ መሞከርና ማየት ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም።

### 4. ስጦታን ማነሳሳት

ስጦታ በጭላንጭሉ ከታወቀ በኋላ ለማሳደግ እንቅስቃሴ መደረግ አለበት። ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስን *"ብትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል"* (1ጢሞ.4:14) በማለት ይመክረዋል። የጸጋ ስጦታ ቸል ከተባለ ይጠፋል ወይም ገሃድ ሳይወጣ ይቀራል። ስለዚህ የጸጋ ስጦታ እንዲገለጥ ከተፈለገ ማነሳሳት አስፈላጊ ነው። ይህን በተመለከተ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ "በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታነሣሣ አሳስብሃለሁ" (2ጢሞ.1:6) በማለት ያደፋፍረዋል። የጸጋ ስጦታ መኖሩ ብቻ በቂ አይደለም። መኖሩ እንዲታወቅና በሥራ ላይ እንዲውል መጠቀም መጀመር አስፈላጊ ነው። ዝም ብሎ ያለሥራ የተቀመጠ የአካል ብልት እንደሚበላሽ ሁሉ ያልተነሳሳ የአገልግሎት ስጦታም ይጠፋል ወይም

ተቀብሮ ይቀራል። እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ ባለማንሳሳት ማጥፋት ወይም መቅበር በእርሱ ፊት ያስጠይቃል። እግዚአብሔር ከሰጠ መጠቀም የተቀባዩ ፈንታ ነው።

አገልጋይ እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ ማንሳሳት ሲጀምር የአገልግሎት ስኬቱ፣ እየጨመረ ይሄዳል። ማንሳሳት የሚለው አሳብ በአንድ በኩል የጸጋ ስጦታ (ዓይነቱ፣ ምን እንደሆነ ባይታወቅም) መኖሩን ሲያመለክት በሌላ በኩል ደግሞ ስጦታው ራሱን ገልጦ እንዲወጣ በአገልግሎት ላይ መፈተሽ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። አገልጋይ በውስጡ በተሰማው ስጦታ ማገልገል ሲጀምር ሌሎች ብዙ ስጦታዎች እንዳሉትም እየተረዳ ይሄዳል። ስለዚህ በውስጡ እንዳሉት የሚያስባቸውን ስጦታዎች ማንሳሳትና ለማሳደግ እርምጃ መውሰድ የአገልጋይ ድርሻ ነው። እግዚአብሔር ስጦታን እንደ ዘር ይሰጣል። እግዚአብሔር የሰጠውን የስጦታ ዘርን ማሳደግ ግን የአገልጋይ ድርሻ ነው።

## 5. የደስታ መንፈስ

አንድ አገልጋይ እግዚአብሔር የሰጠውን ስጦታ ሲያገኝ በሕይወቱ፣ የእግዚአብሔር ሰላምና ደስታ ይሰማዋል። በዚያ በተሰጠው ስጦታ ሲያገለግል ይደሰታል እንጂ እንደ ግዳጅ ሥራውን ለመሥራት ያህል ብቻ አይሠራም። ስጦታውን የለየ አገልጋይ ሲያገለግል በሕይወቱ፣ ውስጥ ቅር የሚለው ስሜት አይኖርም። ከዚህ ተቃራኒ የሆነ ስሜት ከተሰማው ስጦታውና አገልግሎቱ፣ አለመጣጣማቸውን ያመለክታል። በአገልግሎቱ፣ ቅር የሚለው ነገር ካለ እርሱን ትቶ ሌላ ዓይነት አገልግሎት ማገልገል መልካም ይሆናል።

*ገና መሉጊዜዬን ሰጥቼ ማገልግል ስጀምር በአንድ የቤተክርስቲያናችን ክልል ጽ/ቤት ውስጥ የቢሮ ሥራዎችን እየሰሠራሁ እንዳስተባብር ተመደብኩ። በተቻለኝ መጠን የቢሮ ሥራዎቼን እሠራ ነበር። ከዚያም በተጨማሪ ወደ ተለያዩ አጥቢያዎች እየሄድኩ አገልጋዮችን አስተምር ነበር። እቢሮ ውስጥ ተቀምጬ የቢሮ ሥራዎችን (ለምሳሌ ደብዳቤ መጻፍ፣ ፋይሎችን ማዘጋጀት፣ አጀንዳ ማዘጋጀት፣ ቃለጉባኤዎችን ማስተካከል.....) ስሠራ በውስጤ መሥራት የማይገባኝን ሥራ እየሠራሁ እንደሆነ ይሰማኝ ነበር። እንዲህ ዓይነት ቢሰማኝም አደራ የተሰጠኝን ሥራ ግን በትጋት እሠራ ነበር። በውስጤ የደስታ ስሜት ያልተሰማኝ ሥራው ስላልተሳካልኝ ሳይሆን በውስጤ እግዚአብሔር ያስቀመጠው ሸክም ሌላ የአገልግሎት መስክ በመሆኑ እንደሆነ እረዳለሁ። በአንጻሩ ደግሞ አገልጋዮችን ሳስተምር በውስጤ የሚሰማኝ የደስታና የሰላም መንፈስ ነበር። ከአገልግሎቴ በኋላ በጣም ደስ ይለኛል። የአገልግሎት እርካታም ነበረኝ።*

## 6. የስጦታውን ስኬት መገምገም

አገልጋይ የአገልግሎት ስጦታው ምን እንደሆነ ለመለየት በሚያደርገው እርምጃዎች ሁሉ እያገለገለ ባለበት የአገልግሎት መስክ ምን ያህል ስኬታማ እንደሆነ ራሱን መገምገም አለበት።

## 7. የቤተክርስቲያን ምስክርነት

አገልጋይ በተመደበበት የአገልግሎት መስክ ሲያገለግል በውስጡ የሚሰማው ስሜት ግላዊ ስለሆነ አንዳንድ ጊዜ ብቻውን የስጦታውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አይችልም። ከግል የስሜት ማረጋገጫ በተጨማሪ የሌሎች ሰዎች ወይም የቤተክርስቲያን ምስክርነት አስፈላጊ ነው። ምዕመናን አገልጋይ በሚያገለግልበት መስክ ስጦታ እንዳለው እና እንደሌለው ያወቁታል። ስለዚህ የቤተክርስቲያን ምስክርነት በአዎንታዊ እንዲሁም በአሉታዊ ጎኑም አስፈላጊ ነው።

አንድ ጊዜ ከብዙ አጥቢያ ቤተክርስቲያናት ለመጡ ምዕመናን መንፈሳዊ ጉባኤ ላይ እንድሰብክ ተጋበዝኩኝ። ለመስበክ ፈቃደኛ ሆኜ እግዚአብሔር በረዳኝ መጠን ተዘጋጅቼበት ሄድኩኝና ለ45 ደቂቃ ያህል "ሰበኩ"። በዚያ ጉባኤ ውስጥ የሚቀርበኝ አንድ አገልጋይ የሆነ ጓደኛዬ ነበር። ከ"ስብከቱ" በኋላ ወደ እኔ መጣና "እነዚህ ሰዎች ዛሬ ሰባኪ ባለማግኘታቸው በጣም አዝናለሁ። አንተም ብትሆን አውርተህ ነው ከመድረክ የወረድከው" አለኝ። እርሱ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ሰዎች በሌላ ጊዜ የስብከት ስጦታ እንደሌለኝ ይናገራሉ። ይህን ደግሞ ውስጤም ይመሰክርልኛል። ልሰብክ ስል አስተምራለሁ። ስለዚህ አገልጋይ የራሱን የአገልግሎት ስጦታ ለመለየት የቤተክርስቲያንን ምስክርነት መስማት ይኖርበታል። ምዕመናን ይህን ወይም ያን ዓይነት ስጦታ አለህ ወይም የለህም ብለው ሲናገሩ ማዳመጥ እጅግ አስፈላጊ ነው።

የአገልግሎት ስጦታን መለየት ቀላል ሳይሆን በረጅም ጊዜ ውስጥ የግል ውስጣዊ መንፈስና ስሜት መፈተሽ፣ የአገልግሎት ስኬትን መገምገም እና ሌሎች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉና የአገልግሎት ልምድ ያላቸውን እንዲሁም መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን የለዩ ሰዎችን ምክር ማግኘት ይጠይቃል።

---

### ጥያቄዎች

1. የአገልግሎት ስጦታ መለያ መንገዶች ምንድናቸው?
2. የአገልግሎት ስጦታህ ምንድነው? እንዴት አወቅህ?
3. ሰው የአገልግሎት ስጦታውን ሳያውቅ እንዲሁ በተመደበበት መስክ ቢያገለግል ምን ችግር አለው?
4. አንዳንድ አገልጋዮች በሰዎች ዘንድ በጣም የሚፈለግ ስጦታ የሚመኙት ለምንድነው?
5. አንተ/አንቺ የምትፈልገው/ጊው ስጦታ ምንድነው? ለምን?

## የአገልጋይን ሕይወትና አገልግሎት ምሳሌዎችን በማወቅ መከተል

ይህ ምዕራፍ አገልጋዮች ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ምን መምሰል እንዳለበት የሚያስረዳ ክፍል ነው። እግዚአብሔር አገልጋዮቹ የተጠሩበትን አገልግሎት ሲያገለግሉ እንዴት መኖር እንዳለባቸው በቃሉ ውስጥ ገልጿል።

አገልጋዮች ምን መምሰል እንዳለባቸው የሚያመለክቱ የተለያዩ ምሳሌዎች ወይም ተምሳሌት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነዚህ ተምሳሌት ስለአገልጋይ ሕይወትና አገልግሎት ምሳሌያዊ በሆነ መንገድ ይናገራሉ። በዚህ ክፍል የእነዚህ ተምሳሌት ትርጉምና ስለአገልጋይ ሕይወትና አገልግሎት ምን እንደሚናገሩ እንመለከታለን።

### የክርስቶስ ሎሌዎች (1ቆሮ.4:1)።

ሎሌ ማለት ምን ማለት ነው? ሎሌ የሚለው አሳብ የመጣው በጥንት በግሪካውያን ዘንድ ከበላይ የሚሰጠውን ማንኛውንም ዓይነት ሥራ የሚሠራ በዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ የሚገኝ ሰው ነው። በዚህ አሳብ ላይ መሠረት አገልጋዮች እንደ ሎሌዎች ከእግዚአብሔር የሚሰጣቸውን ማንኛውንም ተልዕኮ ለመፈጸም ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች መሆን አለባቸው። ይህ ራስን መስጠትና ሙሉ መታዘዝ ደግሞ የሚመጣው ከትሕትና ሕይወት ነው። የክርስትና እምነት የትሕትና እምነት ነው። ምክንያቱም የእምነቱ መሠረትና ጀማሪ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ትሑት ስለነበረና ትሕትናውንም በተግባር ያሳየ በመሆኑ ነው (ማቴ.11:29)።

እንግዲህ ሎሌነት ከትሕትና አኳያ ሌሎችን ማገልገል እንጂ በሌሎች መገልገል አይደለም። ጌታ ኢየሱስም ሌሎችን በትሕትና ማገልገል ተቀዳሚ ተግባሩ እንደሆነ ተናግሯል። የክርስቶስ ልብ በትሕትና የተሞላ ነው። ከቃል ትምህርትም አልፎ የሎሌነት አገልግሎቱን የደቀመዛሙርቱን እግር በማጠብ በተግባር ገልጿል (ዮሐ.13:3-10)። እግዚአብሔር ዓላማውን የሚያከናውነው በትሕትና ሌሎችን ለማገልገል ራሳቸውን በሰጡ አገልጋዮች ሕይወት ውስጥ ነው። የትሕትና አለመኖር የአገልግሎት እንቅፋት ነው። ሕይወታቸው በትሕትና ያልተሞላ አገልጋዮች በሕይወታቸውም ሆነ በአገልግሎታቸው አያድጉም። ምክንያቱም ከሌሎች ለመማር ፈቃደኞች አይደሉም። አንዳንድ ጊዜ በአገልግሎት ዘመናቸው፣ ስለክርስቶስ መከራ በመቀበላቸው እንዲሁም ለወንጌል ብለው የነበራቸውን ዕድል ሳይጠቀሙበት እንደቀሩ እየተረኩ እግዚአብሔር ሊያስተምራቸው በሚፈልግበት መስመር መማር አይፈልጉም።

አገልጋዮች ከሌሎች ምዕመናን በተለየ ሁኔታ ትሕትና መልበስ ይገባቸዋል። መንፈሳዊ አገልግሎት ያለትሕትና አይታሰብም። ትሑቱን ጌታ የሚያገለግል አገልጋይ ትሑት መሆን ይጠበቅበታል። ጥሪውና

ተልዕኮ ራሱ በትሕትና ዝቅ ብሎ ሌሎችን ማገልገል ነው። ስለዚህ የትሕትና ባህርይ የክርስቶስ አገልጋዮች መለያ ምልክት ነው።

አገልጋዮች የማን ሎሌዎች ናቸው? ሲባል ደግሞ ቃሉ የክርስቶስ ሎሌዎች ብሎ ይመልስልናል። አገልጋዮች ሁልጊዜ እሺ የሚሉት ለክርስቶስ ነው። ለክርስቶስ እሺ የሚል ሕይወት ከሌላቸው በምንም የእርሱ አገልጋዮች ሊሆኑ አይችሉም። ለክርስቶስ እሺ ማለት ለቤተክርስቲያን መሪዎች መታዘዝን ቢያጠቃልልም ለቤተክርስቲያን መሪዎች መታዘዝ ሁልጊዜ ለክርስቶስ እንደ መታዘዝ አይቆጠርም። ስለዚህ እነዚህ የክርስቶስ ሎሎች በክርስቶስ ወኪል ባለሥልጣናት ሲታዘዙ ትዕዛዙ የዋናው ጌታ መሆኑን በእርግጥ ማወቅ አለባቸው። ካልሆነ የክርስቶስ ሎሌዎች ከመሆን የጥቂት ቤተክርስቲያን መሪዎች ሎሎች መሆንን ያስከትላል።

ሎሌዎች ከባሪያዎች የተለዩ ናቸው። ባሪዎች የራሳቸው የሆነ መብት የላቸውም። ሎሌዎች ግን የራሳቸው የሆነ መብት አላቸው። የክርስቶስ ሎሌዎች ጌታን ሲያገለግሉ እርሱ መብታቸውን ያከብራል። ግን አንዳንድ ጊዜ የእርሱ ወኪል ባለሥልጣናት የክርስቶስ ሎሌዎችን እንደ ባሪያዎች ለመግዛት ያስባሉ። ይህ ሲሆን የክርስቶስ ሎሎች ለመብታቸው ክብር መከራከር ይገባቸዋልን? የክርስቶስ ሎሌዎች ለራሳቸው ጠበቃ ባይቆሙም ግፍ ሲደረግባቸው አይተው ዝም ማለት ጽድቅ የለውም። በእነርሱ ላይ የሚደረግ በደል ካለ በደሉን በእርግጥ መናገርና እንዲት ሊወገድ እንደሚገባ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት የመፍትሔ አቅጣጫን ማሳየት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን እንደ ሠራተኛ ማህበር ለአገልጋዮች መብት መታገል ከሎሌነት ወደ ተቀጣሪ ሠራተኛነት ዝቅ ያደርጋል። ስለዚህ የመብት መደፈርን መናገር ሳይሆን ትክክል ያልሆነው አላፊ በመሄድ የሚያስገምት እርምጃ መውሰድ ነው።

የክርስቶስ ሎሌነት የሚያሳየው አገልጋዮች በቅድሚያ ተጠያቂነታቸው ለጠራቸው ለታላቁ ጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ነው። በእርሱ ፊት በንጹሕ ሕሊና መመላለስ ይገባቸዋል። የጌታ ሎሌዎች ሌሎች ሰዎች በማያውቁት ነገር እንኳ እግዚአብሔር ዘወትር እንደሚያያቸው በማሰብ በሰዎች ፊት ብቻ ሳይሆን በጌታ ፊት ያለሕሊና ፍርድ መኖር ይጠበቅባቸዋል። ሰዎች ሲያዩአቸው እንደ ክርስቶስ ሎሌዎች የማያስቡአቸው ቢሆንም ሕሊናቸው በጌታ ፊት ንጹሕ ከሆነ ጌታ አንድ ቀን እውነትን ወደ ብርሃን ስለሚያወጣ የተሳሳተ የእርምት እርምጃ ከመውሰድ መቆጠብ ይገባቸዋል። ይህ ማለት ግን አገልጋዮች ከሰዎች የሚሰጣቸውን አስተያየትና ወቀሳ መስማት የለባቸውም ማለት አይደለም። አገልጋዮች ፍጹማን ስላይደሉ ሊሳሳቱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ የሚያገለግሉአቸው ምዕመናን የአገልጋዮችን ስህተት አውጥተው ሲናገሩ አገልጋዮች ልብ ብለው ማዳመጥ ይገባቸዋል። እንዲህ ያለው አስተያየት አገልግሎታቸውን የበለጠ ፍሬያማ ያደርጋል። የአገልጋዮች ተጠሪነት በመጀመሪያ ለጌታ ከዚያም ለቤተክርስቲያን ነው።

የክርስቶስ ሎሌዎች ለአገልግሎታቸው የሚበቃቸውን ነገር የሚቀበሉት ከላካቸው ከጌታ ነው። በራሳቸው አገልግሎቱን ለማከናወን ምንም ብቃትና መንፈሳዊ ግብአት የላቸውም። ለአገልግሎታቸው መሳካት

አስፈላጊ የሆኑ ጸጋዎች የተሰጡት ከእግዚአብሔር ዘንድ ስለሆነ ያልተቀበሉት በራሳቸው ያገኙት ወይም በእነርሱ ኃይልና ችሎታ የሆነ ነገር ስለሌለ በራሳቸው አይመኩም። የሚመካው በራሱ ብቁ የሆነ ከሌላው ያልተቀበለው ነው (1ቆሮ4:7)።

ልጅ ሳለሁ ሲደረግ የማስታውሰው አንድ ነገር አለ:: አንዳንድ የሠፈር ልጆች ከጓደኞቻቸው ልብስ ወይም ጫማ ይዋሱና ይኩሩበታል። የራሳቸው እንደሆነ ሲሸልሉበት ስናያቸው *horiin ergisaa bule fokkisaa* እንል ነበር። አሳቡ ከሌላ ሰው የተቀበሉትን ነገር እንደግል በመቁጠር በእርሱ መኩራት ሲያድር ያዋርዳል ማለት ነው። በአማርኛም *የሰው ወርቅ አያደምቅ ወይም የተውሶ ይሄዳል ተመልሶ* ይባላል። የክርስቶስ ሎሌዎች ወደ አገልግሎት ከጠራቸው ጌታ የተሰጣቸውን ስጦታ እንደራሳቸው አድርገው መጠቀምና ለራስ ክብር ማዋል ያዋርዳል። ሰጪው የሰጠውን ነገር ሲወስድ ባዶ እጃቸውን ይቀራሉ። የክርስቶስ ሎሌዎች ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን ስጦታ የራሳቸው እንደሆነ ማሰብ ሲጀምሩ ከሎሌነት ተግባራቸው ይሻራሉ። እውነተኛ የክርስቶስ ሎሌዎች የሚያደርጉትን ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ጸጋ እንደሚያደርጉ ይረዳሉ። ለሰጪው የሚገባውን ክብር ይሰጣሉ፤ የእርሱን ክብር ለራሳቸው ለመውሰድ አይሹም።

የክርስቶስ ሎሌዎች አንድ ቀን በክርስቶስ ፊት ቀርበው ስላከናወኑት አገልግሎት መልስ ይሰጣሉ። ስለዚህ ዘወትር በእርሱ ፊት በመልካም ሁኔታ መመላለስ አስፈላጊ ነው። ሰዎች የማያዩትን የአገልጋዮችን ሕይወት (ተግባርና ዓላማ) እግዚአብሔር ያያል። በአሁኑ ዘመን በአገልግሎት ላይ እያሉ በተለያዩ ስውር ኃጢአት የሚወድቁ አገልጋዮች አሉ። የአንዳንዶችን ማንም ሰው አያውቅም። አንዳንድ ጊዜ በስውር የፈጸሙት ኃጢአት የሚገለጠው በኤድስ ተይዘው ሊሞቱ ሲሉ ለቤተክርስቲያን መሪዎች ሲናዘዙ ነው። ለሰዎችም ሳይገለጡ የሚቀሩ ኃጢአቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ከሰዎች መሸፈን ቢቻልም ከእግዚአብሔር መሰወር ስለማይቻል አገልጋዮች እንደ ክርስቶስ ሎሌዎች በቅድስናና በንጹሕ ሕሊና በእርሱና በሰዎች ፊት መመላለስ አለባቸው። ካልሆነ ክፉ ቀን ይጠብቃቸዋል።

## የእግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች (1ቆሮ.4:1)

አገልጋዮች እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የገለጠውን ተደብቆ የነበረውን የድነት ምሥጢር የሚመግቡ መጋቢዎች ናቸው። ይህን ምሥጢር መመገብ አደራ ተሰጥቶአቸዋል። የመመገቡን ተግባር ደግሞ የሚወጡት የተገለጠውን የእግዚአብሔር ቃል በማስተማር ነው። እንደ ባለአደራ አገልጋዮች በመጀመሪያ ለተሰጣቸው ምሥጢር (ለእግዚአብሔር ቃል) ታማኞች መሆን ይገባቸዋል። የባለአደራነት ዋነኛ መለኪያው ለተቀበሉት አደራ ታማኝ መሆን ነው። ይህ ታማኝነት የእግዚአብሔርን ቃል የበላይነት መጠበቅ፣ ቃሉን ሳይጨምሩበትና ሳይቀንሱበት ማስተማርን ያጠቃልላል።

ሌላው ደግሞ በብቃት የመመገቡን አገልግሎት ማከናወን መቻል ነው። አገልጋዮች ታማኝነት ብቻ ሳይሆን የተሰጣቸውን ቃል ለሌሎች ሰዎች ለማስተማር ብቃት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። ታማኝነት ብቻ መልካም መጋቢ አያሰኝም። ለቃሉ ታማኝ በመሆን ቃሉን ዕለት ዕለት በማጥናትና በመመርመር ራስን መግቦ ለሌሎችም ጠቃሚ የሆነ ትምህርት መስጠት ያስፈልጋል። አገልጋዮች ቃሉን አይፈጥሩም። ምክንያቱም ቃሉ ተሰጥቶአቸዋል። የተሰጣቸውን ቃል ግን ለምዕመናቻቸው እንደሚስማማ አድርገው በማዘጋጀት ጥሩ መንፈሳዊ ምግብ ይመግባሉ። የተገልጋዮቹን ሁኔታና ፍላጎት በማወቅ አስፈላጊውን መንፈሳዊ ምግብ የሚያዘጋጁ ከሆኑ በምዕመናን ይወደዳሉ። አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸው ታማኝነት ሲቀንስ ቃሉን ለማጥናትና ለማስተማር ያላቸው ፍላጎት ይቀንሳል። ቃሉን በጥልቀት ለማወቅና ለማስተማር የልብ መነሳሳትን የሚሰጠው አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ቃል ያላቸው አክብሮትና ፍርሃት ነው።

አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ያላቸው ፍላጎት ሲቀንስና ቃሉን ከማስተማር ሽሽት ሲጀምሩ ለእግዚአብሔር ቃል የበላይነት ያላቸው አመለካከት መበላሸቱን መገመት ይቻላል። ይህ ዓይነት ሁኔታ ሲታይባቸው እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ከማጥናት ሌሎች በሰው ለተፈጠሩ ፍልስፍናዎች ትኩረት ይሰጣሉ፤ ይህንንም ወደ ቤተክርስቲያን በማምጣት ያስተምራሉ። የሰዎችን አሳብ በእግዚአብሔር ቃል ከመተቸት ይልቅ በሰዎች አሳብ የእግዚአብሔርን ቃል መተቸት ይጀምራሉ። ይህ ለተሰጣቸው ባለአደራነት ታማኝ አለመሆን ነው።

## የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ (1ቆሮ.4:13)

ከቤት ውስጥ ወጥቶ ቆሻሻ መጣያ ቦታ የሚጣለውን ጥራጊ እና ዕቃ ሲታጠብ የሚደፋውን እጣቢ ሁላችንም እናውቃለን። ጳውሎስ አገልጋይ በዚህ ሁኔታ እንደሚታይ ስለራሱና ከእርሱ ጋር ስለሚያገለግሉት ሰዎች ይናገራል። አገልጋይ መባል በዚህ ዓለም እጅግ በጣም የተናቀ የሥራ መስክ መምረጥ ማለት ነው።

የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን በዚህ ዓለም ሥፍራ የሚያሰጥ ሥራ አይደለም። በኅብረተሰባችን ዘንድ መንፈሳዊ አገልግሎት ክብር የለውም። ከሰማያዊ አገልግሎት ይልቅ ምድራዊ የሆነ ሥራ ዋጋ ይሰጠዋል። የወንጌል አገልጋይ መሆን የሚያሳፍራቸው ሰዎች ሞልተዋል። አገልጋይ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱን የጌታ ባሪያ ብሎ ይጠራል። በፊታዳ ራሱን ለጌታ የሰጠ አገልጋይ መሆኑን ይናገራል (ሮሜ1:1)። ጳውሎስ መንፈሳዊነት ሞኝነት በሚመስላቸው በአሕዛብ መካከል እንኳ በወንጌል እንደማያፍር ይናገራል። በዘመናችን የወንጌል አገልጋይነት ሥራ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት የሚያስገኝ አይደለም። በአንዳንድ አካባቢ የወንጌል አገልጋይ ነኝ ከማለት የአንድ ድርጅት የጥበቃ ሠራተኛ ነኝ ማለት ክብር ያሰጣል።

*አንድ ጊዜ አንድ የወንጌል አገልጋይ የቤተዘመድ ስብሰባ ላይ ተጋብዘው በተገኙ ሰዎች መካከል ነበር። ከጥቂቶች በስተቀር ጌታን*

*ያላመኑ ነበሩ። በግብግቡ ላይ የትውውቅ ጊዜ ነበር። የአገልጋዩ ተራ ሲደርስ ስለሥራው "እኔ በአንድ መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ውስጥ ሠራተኛ ነኝ" በማለት ተናገረ። ከዚያም የእርሱን ሥራ የሚያውቁ አማኞች "ለምን የወንጌል አገልጋይ ነኝ አላልክም ነበር?" ብለው ሲጠይቁት "ሰዎች ምን ይሉኛል? ብዬ ነው" በማለት መለሰላቸው።*

ይህ አገልጋይ ራሱን እንደ ወንጌል አገልጋይ ያልተቀበለ ሰው ነው። አስቀድሞም ወደዚህ አገልግሎት የገባው እግዚአብሔር ጠርቶት ሳይሆን ለሥራ ፍለጋ ነበር። በእግዚአብሔር የተጠራና የተሰማራ አገልጋይ በሌሎች ሰዎች ፊት እንደ ጉድፍ እንደሚቆጠር ቢያውቅም አገልግሎቱን ግን አይደብቅም። አገልጋይ እግዚአብሔር ባሰማራው አገልግሎት ሊያፍር አይገባውም።

የወንጌል አገልጋይነትን ሥራ ያስናቀው ምንድነው? የወንጌል አገልጋይነት በዓለም ሌሎች የሥራ ዕድሎች ሁሉ ካልተሳኩ የሚመረጥ የመጨረሻ የሥራ መስክ ተደርጎ ስለሚቆጠር ነው። ወደዚህ የአገልግሎት መስክ የሚገቡ በዓለም ተወዳድረው የወደቁ ወይም ያልተሳካላቸው ወይም ከሥራ ተባርረው ቦታ ያላገኙ ወይም ጡረታ የወጡ ሰዎች እንደሆኑ ይታሰባል። እንዲህ በሚያስብ ኅብረተሰብ ውስጥ የወንጌል አገልጋይ ነኝ ማለት ራስን ለውርደት አሳልፎ መስጠት ይመስላል። አንዳንድ ጊዜ ሌሎች የሚሉንን ነገሮች ቆም ብለን መመዘን መልካም ይሆናል። ምናልባት እንደምንባለው ሆነን ተገኝተን እንዳንሆን!

ጳውሎስ በወንጌል እንዳያፍር ያደረጉት ምክንያቶች ነበሩ። አንደኛው ወንጌል ኃይል ስለሆነ (ሮሜ 1፡16) እና *ያመነውን* ስለሚያውቅ ነበር (2ጢሞ1፡12)። ጳውሎስ ይህን የተናገረው እስር ቤት ሆኖ ነበር። እስር ቤት የገባበትም ምክንያት መጥፎ ነገር ወይም ወንጀል ሰርቶ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ጥሪ በመታዘዝ የእርሱ አገልጋይ በመሆኑ ነበር። ጳውሎስ በወንጌል ምክንያት በመታሰሩ አላፈረም። ምክንያቱም ዓለም እንደማይጠቅም ወንጀለኛ እስር ቤት ውስጥ ብትጥለውም ለጌታው በመታዘዙ እንደታሰረ ያውቅ ስለነበር አላፈረም።

**የክርስቶስ በጎ ወታደር** (2ጢሞ2፡3-4)።

ስለውትድርና ብዙ እውቀት የለኝም። ሆኖም በ1983 ዓ.ም የደርግ መንግሥት የዩንቨርሲቲ ተማሪዎችን ወደ ውትድርና ማሰልጠኛ ማዕከል ሲከት እኔም አንዱ ነበርኩ። የውትድርና ሥልጠና ምን እና እንዴት ከባድ እንደሆነ ያወቅሁት እዚያ ነው። የጦር ሜዳ ሁኔታ ምን እንደሆነ በማንበብ እንጂ በተግባር አላውቀውም።

ሐዋርያው ጳውሎስ የአገልጋዮች ሕይወትና አገልግሎት ከወታደር ሕይወትና ግዳጅ ጋር እንደሚመሳሰል ይናገራል። ጢሞቴዎስን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር እንዲሆን ይመክረዋል። የአገልጋዮችና የወታደር ሕይወትና አገልግሎት የሚመሳሰለው በአራት ዋና ዋና ነጥቦች ነው።

*ሀ* ወታደር ለተሰለፈበት ዓላማ መከራን ይቀበላል። የውትድርና ሕይወት በመከራ የተሞላ ሕይወት ነው። ከመጀመሪያ ከሥልጠናው

ጀምሮ አስቸጋሪና አድካሚ እርምጃዎች አለበት። ይህን መከራ የሚቀበለው ዓላማ ስላለው ነው። ወታደርን መከራ አይበግረውም። አገልጋዮች የክርስቶስ በጎ ወታደሮች ናቸው። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን የሚጋብዘው ከእርሱ ጋር መከራ እንዲቀበል ነው። መቀበል ብቻ ሳይሆን መከራ በመቀበል እንዲጸና ነው። ለክርስቶስና ለወንጌል አገልግሎት ራሳቸውን የሰጡ አገልጋዮች በመከራ ውስጥ እንዲጸኑ ጥሪ ተደርጎላቸዋል። በማንኛውም አስቸጋሪና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ የተጠሩበትን አደራ ለመወጣት ፈቃደኞች መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ለ. ወታደር አዛዡን ለማስደሰት የተዘጋጀ ነው። ወታደር የራሱን ደስታ ሳይሆን እርሱ በሚያደርገው በማንኛውም ግዳጁ አዛዡን ለማስደስት ይጥራል። እንደዚሁም አገልጋዮች እግዚአብሔርን ማስደስት የመጀመሪያ ዓላማቸው ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚፈልጉ አገልጋዮች ከራሳቸው ይልቅ የእርሱን ፈቃድ ለማገልገል ራሳቸውን የሰጡ ናቸው። ለራሳቸው ደስታ ብለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ አይጥሱም።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ማንን ማስደሰት እንዳለባቸው ዘወትር ይፈተናሉ። ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ለማስተማር፣ የሚያደርጉትን ሁሉ ለማጽደቅ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ለማክበር እና ሰዎችን የማያስከፋ ትምህርት ለመስበክና ለማስተማር ይፈተናሉ። ለዚህ ዓይነት ፈተና ራሳቸውን ከሰጡ ኃጢአትን ለመቃወም ያላቸው አቅም ይዳከማል። ሆኖም ሰዎችን ስለማይቃወሙ የምዕመናቻቸውን ቁጥር ሊጨምር፣ ምስጋናና ሙገሳ ሊያገኙ እንዲሁም የገንዘብ ስጦታ ሊያገኙ ይችላሉ። ሆኖም ግን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን ትክክለኛ ገጽታ ይበላሻል፣ በአማኞችና ባላመኑ ሰዎች መካከል ልዩነት ይጠፋል፣ ቤተክርስቲያን በዓለማዊነት ትሞላለች።

አገልጋዮች የወንጌል እውነተኛ አገልጋዮች ለመሆን ከፈለጉ የወንጌልን እውነት በማመቻመች ሰዎችን ማስደሰት የለባቸውም። አገልጋዮች ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን ለማስደሰት የቆረጡ ሊሆኑ ይገባል። ምንም ቢሆን አገልጋዮች ከሰዎች ይልቅ እግዚአብሔርን በማስደሰት መኖር አለባቸው (ገላ.2፡10፤ 1ተሰ.2፡4-6)።

ሐ. ወታደር ለአዛዡ በሙሉ ልቡ መታዘዝ አለበት። ወታደር ለበላይ አለቃው በሁኔታዎች ላይ ባልተወሰነ ሁኔታ መታዘዝ ይኖርበታል። የወታደር ድርሻ መታዘዝ እንጂ የታዘዘበትን ምክንያት ማወቅ አይደለም።

መ. ወታደር ከውትድርና ሥራ ውጭ በሆነ በሌሎች ሥራዎች ውስጥ ራሱን አያስገባም። የወታደርና ወታደር ያልሆነ ሰው ሥራና የሕይወት ዘይቤ የተለያየ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል፤ ወሰኑንም በመጠበቅ ይኖራል። እንዲሁም አገልጋዮች ከተጠሩበት አገልግሎት ውጭ በሌላ ዓ ለማዊ ሥራ ውስጥ ራሳቸውን አስገብተው አገልግሎታቸውን አይረሱም። አገልግሎታቸውን በሚያስረሳቸውና በሚያስጥላቸው ነገሮች ውስጥ አይጠላለፉም።

## **ለጨዋታ የሚታገል ሰው** (2ጢሞ.4:5)

በጨዋታ የሚታገሉ ሰዎች ለምሳሌ ሯጮች እንደሚገባ አድርገው ባይታገሉ የድል ባለቤት መሆን አይችሉም። እነዚህ ሰዎች በዐቢይነት ሁለት ነገሮችን ያደርጋሉ። የመጀመሪያው ለድል ለመብቃት አስፈላጊ የሆነ ዝግጅት ያደርጋሉ። በአንድ ቀን ድንገት የጨዋታ ሜዳ ውስጥ በመገኘት ብቻ ባለድል መሆን በአጋጣሚ ካልሆነ በስተቀር አይቻልም። ሕይወታቸው በዲሲፕሊን የተሞላ ነው፤ የሚመገቡት ምግብ የተመረጠ ነው፤ የሰውነታቸውን አቅም ወይም ጤንነት ከሚጎዳ ከማንኛውም ነገር ይቆጠባሉ፤ እናም ዘወትር ይለማመዳሉ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ በቂ ዝግጅት ማድረግ ብቻ ሳይሆን የውድድር ሜዳ ውስጥ ከገቡ በኋላ የጨዋታውን ደንብና ሥርዓት መጠበቅ አለባቸው። ማንም በጨዋታ ውስጥ የሚሳተፍ ሰው የጨዋታውን ደንብ ካልጠበቀ ጥሩ ውጤት ቢያስመዘግብም ውጤቱ አይቆጠርለትም።

በተመሳሳይ ሁኔታ የአገልጋዮችም ሕይወት በዲሲፕሊን የተሞላ መሆን ይኖርበታል። አገልጋዮች ራሳቸውንና ሌሎችን ሊጎዱ ከሚችሉ ከማናቸውም መጥፎ ልምዶች መጠበቅ ይገባቸዋል። የጸሎት ሕይወታቸውና የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናታቸው የዘወትር የሕይወታቸው ተግባሮች ሊሆኑ ይገባል።

እግዚአብሔርንም ሲያገለግሉ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት ማገልገል ይጠበቅባቸዋል። የአገልግሎታቸው ይዘትና መለኪያው ቃሉ ስለሆነ ሕይወታቸውና አገልግሎታቸው ቃሉን ያማከለ ሊሆን ይገባል። እንግዲህ ቃሉን ባማከለ ሁኔታ የቤተክርስቲያንን ወግና ሥርዓትን በማገናዘብ ማገልገል አስፈላጊ ነው። እንዲህ የማይሆን ከሆነ አገልጋዮች "ማኖ" ይነካሉ፤ ይህ ደግሞ አገልግሎትን ያደናቅፋል።

**ገበሬ** (2ጢሞ.2:6)።

ገበሬ መሆን ትጋትን ይጠይቃል። የግብርና ሥራ ከባድ ከመሆኑ የተነሳ ብዙ ያደክማል። አባቴ ገበሬ ስለሆነ ገበሬ መሆን ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል አይቻለሁ። አንዳንድ ጊዜ በጣም ደክሞት ይመጣና እራት እስኪዘጋጅ ድረስ አልጋ ላይ ጋደም እንዳለ በዚያው እንቅልፍ ይወስደዋል። አንዴ ከተኛ ደግሞ ድካሙን ሳይወጣ አትቀስቅሱት ይባልና እግሩንም ሳይታጠብ እራቱንም በጊዜ ሳይበላ በዚያው ያድራል። በተጨማሪም ገበሬ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይል በብርድና በዝናም ውስጥ ይሰራል።

ከዚህም በላይ አንድ ገበሬ የድካሙን ዋጋ የሚያገኘው ቶሎ አይደለም። ስለዚህ ገበሬ የደከመበትን ሥራ ፍሬ ለማግኘት መታገስ ይጠበቅበታል። ዛሬ ተዘርቶ ዛሬ አይታጨድም እንደሚባለው ዘር ከተዘራበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚታጨድበት ጊዜ ድረስ ረጅም ጊዜ ይወስዳል። ያለትዕግስት ጥሩ ገበሬ መሆን አይቻልም።

ገበሬ ፍሬውን ለመጠበቅ ብቻ ሳይሆን ያልተጠበቀ ፍሬ ቢገጥም(ማለትም የሚጠበቀውን ያህል ውጤት ሳይገኝ ቢቀሬ እንኳ) መታገስ ይገባዋል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ በአገልግሎቱ ይሆናሉ ብሎ

ያላሰባቸው ነገሮች ይመጡበትና ተስፋ ያስቆርጡታል፤ ያስቆጡታል፤ እንዲሁም ያሳዝኑታል። በዚህ ሁሉ አገልጋይ ትዕግስት ከሌለው ማለፍ አይችልም። አገልጋይ ትዕግስት በማጣት በገባበት ሁኔታ ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ምላሽ ከሰጠ አገልግሎቱ ይበላሽበታል። አገልጋይ ባልጠበቀው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሲገባ ስሜቱን በመግዛት ማለፍ ካልቻለና እንደ አገልጋይ የሚጠበቅበትን አዎንታዊ ምላሽ ሳይሰጥ ከቀረ ተመልካቾች ይህ ሰው ለአገልጋይነት የሚያበቃው ትዕግስት የለውም ማለት ይጀምራሉ።

ገበሬ ሌላም ባህርይ አለው። ገበሬ ባለተስፋ ነው። ገበሬ የሚኖረውና የሚሠራው በተስፋ ነው። "እነሆ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል" (ያዕ.5:7) የሚለው አሳብ የገበሬ ሕይወት በተስፋ በመጠበቅ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ያመለክታል። ገበሬ እግዚአብሔር በየጊዜው ዝናብ እንደሚሰጥ ተስፋ በማድረግ የማሳ ዝግጅት ያደርጋል። ዝናብ ከመጣ በኋላም ዘሩን በተስፋ ይዘራል። የተዘራውም ብዙ ፍሬ እንደሚያፈራ ተስፋ ያደርጋል። እንዲሁ አገልጋይም እግዚአብሔርን ተስፋ በማድረግ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል። የአገልግሎት ፍሬን የሚሰጥ እግዚአብሔር ስለሆነ በእርሱ ላይ በመታመንና እርሱን ተስፋ በማድረግ እንደ አገልጋይ ከእርሱ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት መወጣት ይኖርበታል።

### የማያሳፍር ሠራተኛ (2ጢሞ.2:15)

አንድ ሰው በሚሠራው ሥራ ፍሬያማ ሆኖ ካልተገኘ እርሱም ሆነ አሠሪው ያፍርበታል። አሠሪው የእኔ ሠራተኛ ነው ብሎ ለመናገር ያፍርበታል። ሠራተኛው ግን ታታሪና ፍሬ ያለው ከሆነ አሠሪው ይኮራበታል።

አገልጋይም እንደ ወንጌል ሠራተኛ በአገልግሎቱ የማያሳፍር ሠራተኛ ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል። ይህን ለመሆን ደግሞ እውነት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ በመግለጥ ለሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ አለበት። የማያሳፍር የወንጌል ሠራተኛ የእግዚአብሔርን መልዕክት ግልጽ በሆነ መንገድ ለሰሚዎች የማስተላለፍ ብቃት አለው።

አንድ የወንጌል ሠራተኛ የማያሳፍር አገልጋይ መሆኑን የሚረዳው በግምገማ ዕለት ነው። ለወንጌል አገልግሎት ያሰማራው እግዚአብሔር አገልግሎቱን ሲገመግም አገልግሎቱ ሊያሳፍረው ወይም ሊያከብረው ይችላል። ስለዚህ ከመጨረሻው ደረጃ ሳይደርስ አገልጋይ አገልግሎቱ እግዚአብሔር የሚከብርበት፣ ምዕመናን የሚባረኩበት፣ ቤተክርስቲያን የምታድግበትና የእግዚአብሔርን ቃል ያማከለ መሆኑን መገምገም ይኖርበታል። በዚህም ራሱን እየፈተሸ ስህተቱን እያረመ የበለጠ ፍሬያማ አገልግሎት መስጠት ይችላል።

የወንጌል አገልጋይ የማያሳፍር ሠራተኛ ለመሆን መትጋት አለበት። ያለትጋት ስኬታማነት አይገኝም። አገልጋይ መትጋት ያለበት ብዙ መስኮች ቢኖሩም ዋነኛው እግዚአብሔር በሰጠው የአገልግሎት

ስጦታ መሰረት መሥራቱ ላይ ነው። የእግዚአብሔር ቃል "እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን፤ ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን እንናገር፣ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፣ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፣ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፣ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፣ የሚገዛም በትጋት ይግዛ" (ሮሜ.12:6-8) በማለት አገልጋይ በተሰጠው የአገልግሎት ጸጋ በትጋት መሥራት እንዳለበት ያሳስባል።

እኔ ባደኩበት አካባቢ ስለትጋት አንድ የሚነገረ አባባል አለ። ይኼውም "የማይረባ ሰው ዓላማዩ ብሎ ለቀረጠበት ነገር ብርቱ ነው" የሚል ነው። ምንም አይጠቅምም የተባለ ሰው እንኳን ለአንድ ነገር ልቡ ከቆረጠና ዓላማዬ ብሎ ከተነሳ ያለመበት ግብ ድረስ ይደርሳል የሚል መልዕክት አለው። የስጦታ ልዩነት ቢኖርም ብዙ የስኬት ልዩነትን የሚያመጣው የትጋት መለያየት ነው። እግዚአብሔር ስጦታ ሰጥቶ ካሰማራን በኋላ በትጋት ባለማገልገላችን የእግዚአብሔር ስም መሰደቢያ እንዳንሆን መጠንቀቅ ተገቢ ነው። አገልጋይ ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስቲያን የማያሳፍር የወንጌል ሠራተኛ መሆን ይጠበቅበታል። እግዚአብሔር ስጦታውን ከሰጠ እንዲሁም ቤተክርስቲያን የአገልግሎት ሁኔታን ካመቻቸች የአገልጋዩ ድርሻ በትጋት በስጦታው ማገልገል ነው።

## የክርስቶስ መዓዛ (2ቆሮ.2:15)

የጌታ አገልጋይ መዓዛ ያለው ሽታ የሚኖረው ከራሱ ማንነት የተነሳ ሳይሆን ክርስቶስ መልካም መዓዛ እንዲኖረው ስላደረገው ነው። አገልጋይ ከራሱ የሆነ መልካም መዓዛ የለውም። አገልጋይ እውነተኛ የሆነውን ንጹህ ወንጌል በሰዎች ልብ ውስጥ በሚዘራበት ጊዜ የወንጌል እውነት የሰዎችን ልብ ለውጦ ሕይወታቸው መልካም መዓዛ እንዲኖረው የማድረግ ኃይል አለው። አገልጋይ የክርስቶስን መልካም መዓዛ የሚሸተው ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን "ተረቶች" በመተረክ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበለውን ትክክለኛ የወንጌል ቃል ማስተማር ነው።

ወንጌልን የሚሰሙ ሰዎች እውነተኛውን ቃል ለመቀበልና በእርሱ ለመኖር ፈቃደኞች ባይሆኑም የአገልጋይ መዓዛ በእግዚአብሔር ፊት አይለወጥም። የእውነተኛው ወንጌል ቃል አስተማሪዎች በእነዚህ ሰዎች ፊት የሞት ሽታ ይሸታሉ። ምክንያቱም መልካም መዓዛ ሊያመጣ የሚችለውን እውነተኛውን ቃል ተቀብለው የሕይወት ሽታ እንዲኖራቸው አልፈቀዱምና ነው። የተሰበከላቸው መልካም ቃል ፍርድ ይሆንባቸዋል።

የሰዎች አቀባበል አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ቢሆንም የአገልጋይ ትልቁ ድርሻ ንጹሑን ወንጌል ማስተማር እንጂ ሰዎች ለትምህርቱ የሚሰጡትን አሉታዊ ምላሽ በማሰብ እነርሱ መስማት የሚፈልጉትን "ወንጌል" ማስተማር አለመሆኑ ሊታወቅ ይገባል። በአገልጋይ በኩል የሚተላለፈው መልካም መዓዛ የሚያመጣው የእውነት ቃል በሰዎች አለመታዘዝ ሽታው አይለወጥም፤ ነገር ግን ለታዘዙት የሕይወት ሽታ ሲሆንላቸው፣ ላልታዘዙት ደግሞ የሞት ሽታ ይሆንባቸዋል።

ለእግዚአብሔር መልክም መዓዛ ያለው ለዓለም መጥፎ ሽታ ይመስላል። እንግዲህ አገልጋይ የክርስቶስ መዓዛ የሚኖረው እውነተኛውን ወንጌል በማስተማር የሰዎች ሕይወት በቃሉ ኃይል ሲለወጥ ነው።

## መዝገብ የያዘ የሸክላ ዕቃ (2ቆሮ.4:7)

መዝገብ የተባለው እጅግ ውድ የሆነ ዕቃ ነው። በአብዛኛው ውድ የሆኑ ዕቃዎች የሚቀመጡበት ከእነርሱ እጅግ በጣም አነስተኛ ዋጋ ባላቸው ዕቃዎች ውስጥ ነው። ለምሳሌ. ወርቅ ውድ ዕቃ ነው ግን የሚቀመጠው ከወርቅ አነስተኛ ዋጋ ባለው ሳጥን ውስጥ ነው። በጥንት ዘመን ውድ ዕቃዎች የሚቀመጡት ከሸክላ በተሠሩ ዕቃዎች ውስጥ ነበር። የሸክላ ዕቃ ከውጭ ሲታይ በውስጡ የተቀመጠው ወድ ዕቃ እንዳለ አይታወቅም።

የእግዚአብሔር አገልጋይ ውድ የሆነው የእግዚአብሔር መልዕክት የሚተላለፍበት "የሸክላ ዕቃ" ነው። የአገልጋይ ውጫዊው ማንነት ለምሳሌ የሰውነት ቁመና፣ ትምህርት ወዘተ የእግዚአብሔር ክብር በሕይወቱ እንዳይገለጥ እንቅፋት አይሆንበትም። እግዚአብሔር ሰዎች እንደ ሸክላ ዕቃ ዋጋ የለውም ወይም ዋጋው ጥቂት ነው ብለው በሚያስቡት ሰው ተጠቅሞ እጅግ ታላቅ ነገር ማድረግ ይችላል። ስለዚህ አንድ አገልጋይ በሰዎች ዘንድ የሚታይ ውጫዊ ማስታወቂያ ስለሌለው ብቻ እግዚአብሔር እንደማይጠቀምበት ታስቦ ሊናቅ አይገባውም። እግዚአብሔር በሰዎች ለመጠቀም ውጫዊ ነገሮችን እንደ መሥፈርት አይጠቀምም።

የእግዚአብሔር ታላቅነት በአገልጋይ ድካም ይገለጣል። የሸክላ ዕቃ ውድ ዕቃዎችን ለመያዝ የቻለው በራሱ ጥንካሬ እንዳልሆነ ሁሉ አገልጋይም የእግዚአብሔር ታላቅ ኃይል መገለጫ የሆነው በራሱ ሳይሆን በእግዚአብሔር ምሕረት ነው። የሸክላ ዕቃ በቀላሉ ሊሰበር ይችላል። የአገልጋይ የሕይወት ዋስትና በጠራውና ባሰማራው በእግዚአብሔር እጅ ነው። በዚህ ዓለም ባለው የሕይወት ውጣ ውረዶች አገልጋይ በውስጡ የተቀመጠውን ውድ የሆነውን የእግዚአብሔር ክብር እንዳይጥል የሚጠብቀው እግዚአብሔር ራሱ ነው። በአገልግሎት መጽናት የሚመጣው ከእግዚአብሔር የማበርታት ጸጋው ነው። ስለዚህ አገልጋይ ለሕይወቱም ሆነ ለአገልግሎቱ ቀጣይነትና ስኬት በእግዚአብሔር ላይ መደገፍ አማራጭ የሌለው የሕይወቱ ተቀዳሚ ተግባር መሆን ይኖርበታል።

## የክርስቶስ መልዕክተኛ (2ቆሮ.5:20)

መልዕክተኛ የሚለው አሳብ እንደ አምባሳደር ወደ አንድ ቦታ ተልኮ የላኪውን ጉዳይ የመሥራትን ወይም የማስፈጸምን ተግባር ያመለክታል። ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ተልዕኮ ፈጽሞ በመስቀል ላይ በመሞት ለሰው ልጆች የድነት መንገድ ከከፈተ በኋላ ወደ ሰማይ ዐርጓል። አሁን በአካል በዚህ ምድር ላይ የለም። ዛሬ የእርሱ

መልዕክተኞች በዋነኛነት የእርሱ አገልጋዮች ናቸው። አገልጋይ በዚህ ዓ ለም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በመወከል በሕይወትና በቃሉ ክርስቶስን በማሳየት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር እርቅ መጥራት ይጠበቅበታል። የማስታረቅ አገልግሎት አገልጋይ እንደ አምሳደር ለመፈጸም የተላከበት ተቀዳሚ ተልዕኮው ነው። ይህ አገልግሎት ቀላል አይደለም። ከመናገርም አልፎ አዎንታዊ ተጽዕኖ በማድረግ ሰዎችን ወደ እርቅ ማምጣትን ይጠይቃል።

አገልጋይ የክርስቶስ አምባሳደር ስለሆነ ከሚጠበቅበት ደረጃ በታች መኖር አይገባውም። አገልጋይ የወከለውን መንግሥት እንደሚገባ የማያሳይ ከሆነ ከሥልጣኑ ይሻራል። የአምባሳደርነትን ደረጃና ክብር ጠብቆ መኖር አለበት። አለበለዚያ የመንግሥቱን ስም ስለሚያጠፋ ከሥራው ይባረራል። በተመሳሳይ መልኩ የጌታ አገልጋይ ክርስቶስን በማያስከብር ሁኔታ ውስጥ ተገኝቶ ሰዎች እርሱን አይተው እግዚአብሔርን እንዳይሰድቡ ሕይወቱና አካሄዱ ጥንቃቄ በማድረግ እንደ ቃሉ መሆን ይገባዋል።

## የእግዚአብሔር የሥራ ባልደረባ (2ቆሮ.6:1)

የእግዚአብሔር አገልጋይ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የሚሠራ የሥራ ባልደረባ ነው። ይህ ከእግዚአብሔር ጋር ለመሥራት ዕድል ማግኘት መልካም ዕድል ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር አብሮት ሲሠራ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን ኃይል ይሰጠዋል። ማንኛውም ችግር ቢመጣ ለማማከር ከተፈለገ እርሱ ከአገልጋዩ ጋር አለ። በተፈለገበት ጊዜ የሚገኝ የሥራ ባልደረባ ነው።

በሌላ መልኩ ደግሞ የእግዚአብሔር የሥራ ባልደረባ የሆነ አገልጋይ ከሌሎች የእግዚአብሔር የሥራ ባልደረባ ከሆኑ አገልጋዮች ጋር አብሮ የመሥራት ልብ ሊኖረው ይገባዋል። ሁሉም አገልጋዮች የእግዚአብሔር የሥራ ባልደረቦች ናቸው። ስለዚህ በመካከላቸው መስማማትና ተቻችለው የማገልገል ግዴታ አለባቸው።

እግዚአብሔር ትጉ ሠራተኛ ስለሆነ የእርሱ የሥራ ባልደረቦችም ትጉዎች መሆን ይጠበቅባቸዋል።

## የተመረጠ ዕቃ (ሐዋ.9:15)

የተመረጠ ዕቃ የሚለው ሐረግ የእግዚአብሔር አገልጋይ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መሣሪያ መሆኑን እንጂ ሰብዓዊ መብት የሌለው ግዑዝ መሆኑን አያመለክትም። አገልጋይ እግዚአብሔር በዚህ ዓ ለም ለመሥራት ያሰበውን ሥራ በእርሱ ውስጥ ሆኖ እንዲሠራ የተመረጠ ዕቃ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር የተመረጠ ዕቃ ነበር። የእግዚአብሔርን ሥራ በተለየ ሁኔታ ለመሥራት በእግዚአብሔር የተለየ ሰው ነው። እግዚአብሔር በእርሱ በኩል አሕዛብንና የእስራኤል ሕዝቦችን በወንጌል ለመድረስ የመረጠው ዕቃ ነበር። ጳውሎስ ለዚህ ለተመረጠበት ተልዕኮ ትጉ እንደነበር ከጻፋቸው መልዕክቶቹ ውስጥ እንመለከታለን።

ለእግዚአብሔር የተመረጠ ዕቃ መሆን መልካም ቢሆንም መከራ ያለው መስክ ነው። ለእግዚአብሔር ሥራ መመረጥ በወንጌል አገልግሎት ምክንያት የሚመጣበትን ማንኛውንም መከራ መቀበልንም ያጠቃልላል። የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን የወንጌል በረከት ተካፋይ እንደሚያደርግ ሁሉ የክርስቶስ መከራ ተቋዳሽም ያደርጋል።

ለእግዚአብሔር የተመረጠ ዕቃ መሆን የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ ለማድረግ መለየት ነው። የተመረጠ ዕቃ የመራጩን ፈቃድ ይፈጽማል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከመረጠው እግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። በሕዝቦች ዘንድ የእግዚአብሔርን ስም ለመሸከም መመረጥ ትልቅ ኃላፊነት ነው። አገልጋይ በእግዚአብሔር "ከተመረጠ ትውልድ" (1ጴጥ.2:9) መካከል የተመረጠ ዕቃ ነው። ይህም ከምዕመናን ይልቅ ለአገልጋይ የተሰጠው ኃላፊነት ከባድ መሆኑን ያሳያል።

እንግዲህ ከላይ የተጠቀሱት ጥቂት ምሳሌዎች አገልጋይ ለእግዚአብሔር የተሰጠ ሰው፣ የእግዚአብሔር ባለአደራ፣ በሰዎች ዘንድ የተናቀ የሚባለውን ሥራ የሚሠራ፣ ላሰማራው አካል የሚያሳፍር ሠራተኛ፣ በራሱ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ጸጋ ላይ የሚደገፍ በእግዚአብሔር የተመረጠ ዕቃ፣ በየትም ቦታ ክርስቶስን የሚሸት መሆኑን ሲያመለክት አገልግሎት ደግሞ ትጋትን፣ ቅራጥነትንና ዲሲፕሊንን የሚጠይቅ ሥራ መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ አገልጋዮች ከእነዚህ ምሳሌዎች አኳያ ራሳቸውን መፈተሽ አለባቸው።

---

## ጥያቄዎች

1. የክርስቶስ ሎሌ መለያ ምልክቶች ምንድናቸው?
2. የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን እንዴትና ለምን በዓለም የሚናቅ ሥራ ሆነ? አንተስ የእግዚአብሔር አገልጋይ በመሆንህ በውስጥህ ምን ይሰማሃል? የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆንህን ያልወደድክበት ወቅት ነበር?
3. ለአገልግሎትህ በሚገባ መትጋትህን የሚያሳዩ ነጥቦች ምንድናቸው?
4. ሕይወትህ የክርስቶስ መልዕክተኛ መሆንህን ምን ያህል ለሰዎች ይመሰክራል?

# በአገልግሎት ቅድሚያ ለምን እንደሚሰጥ ማወቅና ማድረግ

የአገልጋይ ሕይወት የሚለው አሳብ እንደ አገልጋይ እንደ አማኝ፣ እንደ ባለትዳርና ወላጅ እንዲሁም እንደ ቤተክርስቲያን አገልጋይ /ሠራተኛ እንዴት መኖር አለበት? የሚለውን ጥያቄ የሚመልስ ነው። የአገልጋይ ሁለንተናዊ ሕይወት ምን ይመስላል? በሀገራችን ሁኔታ አገልጋይ ሕይወቱን እንዴት እየኖረ ይገኛል? ይህ የኑሮ ዘይቤ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ላይ የሚያስከተለው አዎንታዊና አሉታዊ ተጽዕኖ ምንድነው? አገልጋይ ስኬታማ የወንጌል አገልጋይ ለመሆን ለምን ዓይነት ነገሮች ቅድሚያ መስጠት አለበት? በዚህ ክፍል እነዚህንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንመልሳለን።

## አገልጋይ እንደ አማኝ

እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ አስቀድሞ የሚጠራው ለድነት እንደሆነ የታወቀ ነው። ለአገልግሎት መጠራት ከድነት በኋላ የሚመጣ ነው። የአገልግሎት መሠረቱ ከእግዚአብሔር ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ መታረቅ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ራሱን እንደ አገልጋይ ከማየቱ በፊት ራሱን እንደ አማኝ ማየት አለበት። አንድ አገልጋይ አማኝ መሆኑ ቀረ ማለት ከአገልጋይነቱ ተሻረ ማለት ነው። አንድ ሰው አገልጋይ የሚባለው አማኝ በመሆን እስከኖረበት ጊዜ ነው።

አገልጋይ አማኝ መሆኑን ሲዘነጋ መንፈሳዊ ሕይወቱ እየከሰመ ይሄዳል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነቱ ይላላል። ይህ ደግሞ የሕይወት ባዶነትና ትርጉም ማጣትን ያስከትላል። ከዚያም አገልግሎቱ ይደርቅበታል። በፊት የነበረው ደስታና እርካታ ይጠፋበታል። ይህን የውስጥ ባዶነቱንና በአገልግሎት እርካታ ማጣቱን በመገንዘብ ራሱን ማስተካከል የማይፈለግ ከሆነ አገልገሎቱ አሰልቺ ሥራ ይሆንበታል:: ከዚያም በውስጡ የተፈጠረውን አለመረጋጋት ላለማሳወቅ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሁከት እንዲፈጠር ያደርጋል:: በቤተክርስቲያን ውስጥ ችግር የሚፈጥሩ አገልጋዮች ትክክለኛ አማኝ መሆን የተሳናቸው ሰዎች ናቸው:: ስለዚህ አገልጋይ የግል ሕይወቱም ተበላሽቶበት ቤተክርስቲያንንም ከማነጽ ይልቅ ማፍረስ እንዳይጀምር ዘወትር ትክክለኛ አማኝ ሆኖ መኖር አለበት፣ ምን ጊዜም አማኝ መሆኑን መርሳት የለበትም።

አገልጋይ እንደ አማኝ መሆንና ማድረግ የሚገባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ከእነዚህም ጥቂቶች ለግንዛቤ እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል።

### እግዚአብሔርን ማወቅ

አገልጋይ እንደ አማኝ እግዚአብሔርን በግሉ ያወቀ ሰው መሆን አለበት። እግዚአብሔርን ማወቅ በአንድ ጊዜ የሚያልቅ ትምህርት

ባይሆንም የሚያመልከውና የሚያገለግለው እግዚአብሔር ማን እንደሆነ በሚገባ ሊያውቀው ይገባል። እግዚአብሔርን በግሉ የሚያውቅ ከሆነ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ በእምነቱ መቆም ይችላል። ሌሎች የተከተሉት ሰዎች እንኳ እግዚአብሔርን ትተው ወደ ሌላ አምልኮ ዘወር ቢሉ እርሱ ግን ጌታ ማን እንደሆነ ስለሚያውቅ በእምነቱ ይጸናል (ዮሐ.6፡66-68)።

አማኝ እግዚአብሔርን ማወቅ የሚችለው በማረፍ ነው። እግዚአብሔር *"ዕረፉ! እኔም አምላክ እንደሆንሁ እወቁ"* (መዝ.46፡10) በማለት ይናገራል። እግዚአብሔርን በትክክለኛ ማንነቱ ማወቅ የሚቻለው ቆም ብሎ ስለእርሱ በማሰላሰል ነው።

*መጸለይ*

አማኝ ያለጸሎት መኖር አይችልም። ጸሎት አማኝ ከእግዚአብሔር ጋር መንፈሳዊ ተራክቦ የሚያደርግበት ዓይነተኛ መንገድ ነው። የአማኝ ሕይወት ከጸሎት ከተለየ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነቱ ይቋረጣል። አማኝ ዘወትር ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ጸሎት ማድረግ ይገባዋል። የእግዚአብሔር ቃል ምዕመናንን ሳያቋርጠ እንዲጸልዩ ይመክራል:: ጌታ ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱ ሳይታክቱ ዘወትር መጸለይ እንዳለባቸው የሚያሳስብ አንድ ምሳሌ ነግሮአቸው ነበር (ሉቃ.18፡1-8):: ጳውሎስም ምዕመናን በእግዚአብሔር ፊት ዘወትር በጸሎት መቅረብ እንዳለባቸው «ሳታቋርጡ ጸልዩ» (1ተሰ.5፡17) በማለት አሳስቦአቸዋል:: የምዕመናን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

አገልጋይ እንደ አማኝ በጸሎት የሚተጋ መሆን አለበት። ያለጸሎት ጥሩ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር አይቻልም። ያለ መልካም መንፈሳዊ ሕይወት ደግሞ የእግዚአብሔርን የልቡን አሳብ ማገልገል አይታሰብም። በአሁኑ ወቅት አገልጋዮች እንደሚገባ እንዳይጸልዩ ያደረጋቸው የአገልግሎት መብዛት ነው:: በእርግጥ የአገልጋዮች እጥረት ባለበት ሁኔታ የአገልግሎት ጫና እንደሚበዛ የታወቀ ነው:: ሆኖም ለጸሎት ትኩረት መስጠት ለሕይወትና ለአገልግሎት ስኬት ቁልፍ ነው:: አገልጋይ ጸሎት ለሕይወቱና ለአገልግሎቱ አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት መማር ይችላል። ጌታ ምንም አገልግሎት ቢበዛበት እና እርሱን በጣም የሚፈልጉት ሰዎች ቢኖሩም ለጸሎት ትኩረት ወይም ቅድሚያ ይሰጥ ነበር (ማር.1፡32-35፣ 6፡46፣ ሉቃ.5፡15-16፣ 6፡12)።

አገልጋይ ራሱን ካስለመደ አገልግሎቱን በማይነካ ሁኔታም መጸለይ ይችላል:: አንድ አገልጋይ ማለዳ በመነሳት በእግዚአብሔር ፊት ቢቀርብ ለቀን አገልግሎቱ የሚበቃውን ኃይል ከጌታ ዘንድ ተቀብሎ ይወጣል:: ይህን ለማድረግ ማለዳ ለመነሳትና ለመጸለይ ራስን ማስለጠን ያስፈልጋል:: አገልጋይ የማለዳውን ጸሎት ከቤተሰቡም ጋር መጸለይ ይችላል:: የጸሎት ጊዜው የግድ ረጅም መሆን አያስፈልገውም:: ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት የሚያገኘው ወይም ኃይል የሚኖረው ለረጅም ጊዜ ስለጸለይን ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ባለን እምነታችን ልክ ነው:: ይህ ማለት ግን ለጥቂት ደቂቃ መጸለይ ብቻ ይበቃል ማለት ሳይሆን ትኩረት መደረግ ያለበት በልምምዱ ላይ እንጂ በጸሎት በምናሳልፈው ጊዜ ላይ መሆን

የለበትም ማለት ነው:: ሁኔታዎች ሲመቹ ለረጅም ጊዜ መጸለይ ካልሆነ ደግሞ ቢያንስ ለዚህ ደቂቃ ያህል ማለዳ ማለዳ በእግዚአብሔር ፊት መቆየት አለብን የሚል ደንብ ቢኖረን መልካም ነው::

አገልጋይ ማለዳ ብቻ ሳይሆን ማታም መጸለይ ይኖርበታል:: አገልግሎቱን ጨርሶ ማታ ወደ ቤቱ ሲገባ ከቤተሰቡ ጋር መጸለይና ቃልን መካፈል እጅግ አስፈላጊ ነው:: ቀን ሌሎችን ሰዎች ሲያገለግል ይውላል፣ ማታ ደግሞ ቤተሰቡን ያገለግላል:: ይህን የቤተሰብ አምልኮ ልንለው እንችላለን:: የቤተሰብ አምልኮ ለጥሩ ቤተሰብ ግንባታና ለአገልግሎት ስኬት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ነገር ግን አገልጋይ ማለዳና ማታ ብቻ መጸለይ አለበት ማለት አይደለም:: ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች ለአንድ አገልጋይና ለቤተሰቡ እንደ ደንብ ሆነው ሁሌ የሚያደርጋቸው ቢሆኑ መልካም መሆኑን ለማሳየት እንጂ አገልጋይ ለሰዓታት ወይም ለቀናት በእግዚአብሔር ፊት ሆኖ መጸለይ ይችላል:: አልፎ አልፎ የሚደረጉ ድርጊቶችን እንደ ሕይወት ዘይቤ መውሰድ አስቸጋሪ ይሆናል::

ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር እንደሆነ ስለሚታመን ሰዎች በጸሎት ላይ ያለን ሰው አይረብሹም:: ሰው ሲፈልገውም «ጸሎት ላይ ነው» ይባላል:: በሀገራችን ሰዎች በሕይወታቸው ከሌሎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የተወሰነ ወሰን ባይኖራቸውም በጸሎት ግን ወሰናቸውን ይጠብቃሉ:: ከዚህም የተነሳ አንድ ሰው እየጸለየ እያለ ከጸሎት ላይ ማቋረጥ የተለመደ አይደለም:: ስለዚህ ጸሎት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው መንፈሳዊ ተግባር እንደሆነ ይታመናል:: ይህ አስተሳሰብ መልካም ነው:: አንድ ሰው እየጸለየ ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ስለሆነ ማንም ሰው ጣልቃ ገብቶ መረበሽ የለበትም:: ስለዚህ አገልጋይም ሲጸልይ ምዕመናን "እንተን ለአገልግሎት እንፈልግሃለን" በማለት እንዳይጸልይ እንቅፋት ሊሆኑበት አይገባቸውም::

አገልጋይ የጸሎት ጊዜ ሳይኖረው ዘወትር ከምዕመን ጋር መገናኘቱ በራሱ ሙሉ አገልግሎት አይደለም:: የአገልጋይ ከምዕመኑ ጋር መሆን ፍሬያማ የሚሆነው አገልጋይ በእግዚአብሔር ፊት ቆይቶ ከእነርሱ ጋር ሲገናኝ ነው:: ጸጋ ያለው አገልግሎት የሚመጣው ከጌታ ጋር ቆይታ ካደረጉ በኋላ ነው:: ይህ ማለት ግን አገልጋይ ከምዕመናን ጋር ከመገናኘት ይልቅ ዝም ብሎ መጸለይ አለበት ማለት አይደለም:: ለሁሉም ነገር የተመደበ ጊዜ ሊኖር ይገባል:: ስለዚህ ምዕመናን የአገልጋዮችን የጸሎት ጊዜ ሊያከብሩና ወሰኑን ሊጠብቁ ይገባቸዋል:: የአገልጋይ መጸለይ ጥቅሙ ለአገልጋዩ ብቻ ሳይሆን ለሚያገለግላቸውም ምዕመናን ጭምር ስለሆነ በሁሉም ዘንድ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል::

### *የእግዚአብሔርን ቃል መመገብ*

አንድ ሰው በዚህ ዓለም ለመኖር ለሥጋው የሚያስፈልገውን ምግብ ማግኘት የግድ ነው:: እንደዚሁም ሁሉ ለመንፈሳዊ ሕይወትም መንፈሳዊ ምግብ መመገብ አስፈላጊ ነው:: ይህም መንፈሳዊ ምግብ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: አማኝ የእግዚአብሔርን ቃል ዕለት ዕለት መመገብ ይኖርበታል:: አንድ አማኝ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ማደግ የሚችለው ተመጣጣኝ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ ማለትም የእግዚአብሔርን ቃል

ሲመገብ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ዘወትር የሚያጠና አማኝ ቃሉ በአዕምሮው ውስጥ በሙላት ይኖራል በዚህም "የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ" (ቆላ.3፡16) የሚለውን ትዕዛዝ በተግባር ይተረጉማል። የእግዚአብሔር ቃል በአማኝ ሕይወት ውስጥ በሙላት ሲኖር አማኙ በሕይወቱ የሚመጣበትን ማንኛውንም ፈተና ለመቋቋም ኃይል ያገኛል፤ ድል የነሳ የክርስትን ሕይወት መኖር ይችላል።

አገልጋይ ልክ እንደ አንድ ምዕመን ቃሉን መመገብ አለበት። አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ለመመገብ ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያጠና ከሆነ መስመሩን ስቷል። አገልጋይ ሌሎችን ምን ላስተምር ብሎ ከማሰቡ በፊት እግዚአብሔር ለሕይወቴ ምን ይለኛል? በማለት ቃሉን ለራሱ ሕይወት ማጥናት አለበት። የአገልጋዩ ሕይወት ከተገነባ በኋላ ለሌሎች የሚሆነውን መልዕክት ከእግዚአብሔር ያገኛል። የእግዚአብሔርን ቃል ለግል መመገብ የሚለው አሳብ ቃሉን ለሌሎች ከማስተማሩ በፊት አገልጋይ ከቃሉ አኳያ የራሱን ሕይወት መመልከትና መመዘን እንዳለበት ያመለክታል። ቃሉ አስቀድሞ በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ ሥራ ሠርቶ ካለፈ ሰሚዎች ይባረኩበታል። አገልጋዩ ከቃሉ አኳያ የት እንዳለ በማሳየት እርምጃውን እንዲከተሉ አቅጣጫ ያሳያቸዋል።

ስለዚህ አገልጋይ ለሌሎች ምግብ የሚያዘጋጅ ብቻ ሳይሆን ለግሉም ምግቡን አዘጋጅቶ የሚባላ ሰው መሆን ይገባዋል። መልካምን ምግብ አዘጋጅቶ በልቶ ያላጣጣመ ሰው እንዴት መልካም ነው ብሎ ለሌሎች መስጠት ይችላል? ስፖንጅ በውስጡ ውኃን የሚያስተላልፈው ለራሱ የሚበቃውን ያህል ውኃ ከመጠጠ በኋላ ነው። አገልጋይም በሕይወቱ ሞልቶ ከተረፈው ቃል ለሌሎች ማስተላለፍ ይጠበቅበታል። ይህ አገልጋይ በእግዚአብሔር ቃል የተሞላ እና ቃሉን አስቀድሞ በሕይወቱ በተግባር ላይ ያዋለ መሆን እንዳለበት ያመለክታል።

ይህ ማለት ግን አገልጋይ በሕይወቱ ያልደረሰበትን ነገር ማስተማር የለበትም ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። አገልጋይ በሕይወቱ መሆንና ማድረግ የሚገባውን ግን ያልደረሰበትን መልካም አሳብ በማስተማር ሰሚዎች ወደዚህ መልካም ዕድገት እንዲመጡ ሊጋብዛቸው ይችላል። እርሱና ምዕመናኑ በዚያ ትምህርት አኳያ አብረው ወደፊት ይራመዳሉ። አንዳንድ ከአገልግሎት ሥነምግባር የጎደለ ሕይወት የሚኖሩ አገልጋዮች ያልሆኑትን ወይም ያልደረሱበትን ነገር እንደሆኑትና እንደደረሱበት አድርገው ይናገራሉ። እንዲህ ዓይነት ድርጊት ግብዝነት ስለሆነ ውሎ አድሮ እየተገለጠ ይመጣል:: አገልጋይ አሁን እዚህ ነን፤ ግን ከዚህ ሁኔታ ወጥተን እግዚአብሔር ወደሚፈልገው ደረጃ እልፍ ማለት አለብን በማለት ማስተማር ይችላል። ራሱም ሆነ የሚያገለግላቸው ምዕመናን ወዳልደረሱበት ሙላት እንዲደርሱ ቃሉን ያማከለ ትምህርትና ልምምድ ማስተማር ኃላፊነቱም ነው::

*በመንፈስ ቅዱስ መሞላት*

የክርስትና ሕይወት ሰው በራሱ ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል የሚኖረው ሕይወት ነው። አማኝ ጌታ ኢየሱስን ሲቀበል

የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ይሆናል። ይህ ማለት ግን መሙላቱ እያስፈልግም ማለት አይደለም። በሀገራችን በተከሰተው የዝናብ እጥረት ሳቢያ የግድቦች የውኃ መጠን በመቀነሱ የኤሌክትሪክ ፍጆታ በፈረቃ መሆኑ ለሁሉም ግልጽ ነው። ይህ ማለት ውኃ ጠፋ ማለት ሳይሆን ያለው ውኃ ለሥራው ከሚፈለገው መጠን በታች መሆኑን ያሳያል። በተመሳሳይ መልክ አማኝ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ መሆኑ ብቻ በቂ አይደለም። መንፈስ በሕይወቱ በሙላት በመኖር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወትና አገልግሎት እንዲኖር ሊያደርገው ይገባል።

የመንፈስ በሕይወቱ ውስጥ መኖር ብቻ ሳይሆን በሙላት መገኘት አስፈላጊ ስለሆነ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ይኖርበታል። ይህ ሲሆን አሸናፊ የሆነ ሕይወት ይኖራል። መንፈስ ቅዱስ በሙላት በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሲኖር የሚያደርጋቸው ተግባሮች ብዙ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ ምዕመናንን ያበረታታል፣ ይመራል፣ ያስተምራል፣ ኃጢአት ሲሠሩ በመውቀስ ወደ እግዚአብሔር አሳብ ይመልሳቸዋል፣ እንደ እግዚአብሔር ቃል ለመኖርና እግዚአብሔርን እንደ ፈቃዱ ለማገልገል የሚበቃቸውን ኃይል ይሰጣቸዋል። ምዕመናን እግዚአብሔር በሕይወታቸው ስለሠራው መልካም ነገር ላላመኑ ሰዎች መመስከር የሚችሉት መንፈስ ቅዱስ ሲሞሉ ነው። ጌታ ይህን ወደ አባቱ ከማረጉ በፊት "ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ....ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" (ሐዋ 1:8) በማለት ለደቀመዛሙርቱ ነገራቸው። የጌታ ምስክሮች ከመሆን በፊት ከጌታ ጋር በሚገባ መተዋወቅና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሞላት የግድ ነው። በመንፈስ ቅዱስ ያልተሞላ አማኝ ለጌታ ምስክር መሆን አይችልም። የምስክርነት ብቃትን የሚሰጠው በአማኝ ሕይወት ውስጥ ሞልቶ የሚሠራው መንፈስ ነው።

*ጌታቸው ጌታ ኢየሱስን ያመነው በስደቱ ወቅት ነበር። በዚያን ጊዜ ከጥቂት የትምህርት ቤት ወገኖች ጋር በመሆን አብሮአቸው ይጸልይ ነበር። እነዚያ ወንድሞችና እህቶች በጌታ የቆዩና በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ነበሩ። ለጸሎት ሲሰበሰቡ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ። ደስ እያላቸው እየዘለሉ ይጸልያሉ። አንዳንድ ጊዜ ጎረቤት እስኪሰማቸው ድረስ ይጮሁ ነበር። ጌታቸው የሚያደርጉት ነገር እንግዳ ስለሆነበት የኅብረቱ መሪ የነበረውን ወንድም ይጠይቃል። ያ ወንድም ስለመንፈስ ቅዱስና ስለሙላቱ ለጌታቸው አስረዳው። ጌታቸውም ልቡን ቢያዘጋጅና እግዚአብሔርን ቢጠይቀው እንደሚሞላው ነገረው።*

*ከዚያም ጌታቸው ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት መጸለይ ጀመረ። እግዚአብሔር እንዲሞላው ለብዙ ወራት ከጸለየ በኋላ ምንም ምላሽ አላገኘም። ከዚያም ወንድሞች እንዲጸልዩለት ጠየቃቸው። እነርሱም ጸለዩለት። ግን አልተሞላም። ይህን በተከታታይ ለስድስት ወራት አደረገ። በዚህ ወቅት ጌታቸው አንድ ነገር ማሰብ ጀመረ። "እኔ መንፈስ ቅዱስ ተሞልቼ እንደነዚህ ወገኖች በልሳን መናገር ካልቻልኩ ይህ እምነት ሐሰተኛ እምነት ነው። ከተሞላሁ ግን ይህ እምነት ትክክለኛ ስለሆነ በሕይወቴ ዘመን እከተለዋለሁ" በማለት ወሰነ። ምናልባት ሰው የውኃ*

ጥምቀት ሳይወስድ በመንፈስ ቅዱስ ላይሞላ ይችላል ብሎ ስላሰበ ጸሎቱን አላቋረጠም።

አንድ ቀን ከገጠር ትምህርቱን ወደሚማርበት ከተማ ለምዝገባ መጣና አንድ ጌታን የማያውቅ ቤተሰብ ቤት ውስጥ በእንግድነት አደረ። ሰዎቹ ጌታን የማያውቁ ስለሆነ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት አካባቢ ተነስቶ መጸለይ ጀመረ። ድንገት ሳያስብ ከዚህ በፊት ተናግሮ በማያወቅ አዲስ ቋንቋ መናገር ጀመረ። ሕይወቱ በታላቅ ደስታ ተሞላ። ዝለል! ዝለል! የሚያሰኘው ትልቅ ሐሴት በውስጡ ሞላው። ከዚያም ድምጹን ሳያሰማ እስከንጋት ድረስ ጸለየ። ጌታቸው በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት እውነት እንደሆነ ተረዳ። እስከዛሬም በጌታ ቤት አለ። ከዚያም በላይ እግዚአብሔርን በሙሉ ጊዜው እያገለገለ ይገኛል። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት በሕይወቱ ትልቅ መንፈሳዊ ልምምድ እንደሆነና ለሕይወቱም ሆነ ለአገልግሎቱ መሰረት እንደሆነ ያምናል።

አንድ አማኝ መንፈስ ቅዱስ መሞላቱ በምን ይታወቃል? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ታሪክ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ማስረጃ ሆኖ የቀረበው በልሳን መናገር ነው። በአዲስ ልሳን መናገር መጀመር የመንፈስ ቅዱስ ሙላት አንዱ መታወቂያ መንገድ ነው። ሌሎችም አስፈላጊ ማወቂያ ምልክቶች አሉ። ለምሳሌ ያህል

- እግዚአብሔርን በሙሉ ልብ ማመስገን (ሐዋ 2:4፣47፤ 10:46፤ 1ቆሮ.14:2)። መንፈስ ቅዱስ የተሞላ አማኝ በሆነለትና እና ባልሆነለት ነገር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ከማጉረምረም ይልቅ እግዚአብሔር በሕይወቱ ያደረገውን ጥቂቱን ነገር በመቁጠር ጌታን ያመሰግናል። ከችግር ነጻ እንደሆነ ያውቻል ማለት ሳይሆን የሕይወትን መልካም ገጽታ ለማየት የተከፈተ ልቡና ይኖረዋል። በምስጋና ውስጥ ድል እንደሚገኝ ያምናል። ስለዚህ ጌታን ያመሰግናል። የምስጋና ርዕስ አያልቅበትም።
- ኃጢአትን የሚጸየፍ ሕይወት መኖርና እግዚአብሔር ኃጢአተኝነትን እንደሚጠላ በማወቅ የጽድቅ ሕይወት ለመኖር መመኘትና ራስን ከዓለም እርኩሰት ማራቅ። መንፈስ ቅዱስ ዓለምን ስለኃጢአት ይወቅሳል። በመንፈስ የተሞላ ሰውም ስለኃጢአት ማንም ሳይነግረው ይረዳል (ዮሐ.16:8)።
- እግዚአብሔርን የሚያስከብር መልካም ሕይወት ይኖራል። የሕይወቱ ዓላማ ጌታ ኢየሱስን ለማክበር ነው። የራሱን ክብር አይፈልግም (ዮሐ.16:13-14፤ ሐዋ.4:33)።
- በሕይወቱ የተለያዩ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች ይገለጣሉ። ቤተክርስቲያንን የሚያንጹ ስጦታዎችን ያገኛል፤ በእነዚያም ስጦታዎች የክርስቶስን አካል ይገነባል (1ቆሮ 12:4-10)።
- ከሌሎች በስመ ክርስቲያን ከሚመላለሱ ሰዎች ይልቅ የበለጠ የጸሎት ሕይወት ይኖረዋል። ጸሎትን የሚናፍቅ ሕይወት አለው። ጸሎት አይሰለቸውም። ግን ሥራ ትቶ እቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ሁሌ ይጸልያል ማለት ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርን ሁሌ ይናፍቃል፣ ያደርግማል ለማለት ነው (ሐዋ.3:1)።

- ለእግዚአብሔር ቃል የጠለቀ ፍቅር አለው። ከዚህም የተነሳ ቃሉን ለመረዳት ጊዜ ሰጥቶ ያጠናል (ዮሐ.16:13፤ ሐዋ.2:42)።
- እግዚአብሔርን እንደ አፍቃሪ አባት ማየት ይጀምራል (ገላ.4:6)። በጌታ የዳነ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነም መንፈሱ በውስጡ ይመሰክርለታል (ሮሜ.8:15)።

በተለይ አገልጋይ ሆኖ የእግዚአብሔርን ሥራ በዚህ ክፉት በሞላበት ዓለም ውስጥ መሥራት ያለእግዚአብሔር መንፈስ ሙላት እጅግ አዳጋች ነው። ለዚህም ነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት፣ ወደ ዓለም ከመሄዳቸው በፊት በመንፈስ ቅዱስ መሞላት እንደሚያስፈልጋቸው የነገራቸው (ሉቃ24:49)።

መንፈስ ቅዱስ በኃይል በእነርሱ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልና ድፍረት በማግኘት የእግዚአብሔርን መልዕክት ለሕዝብ አስተላለፉ። በዚህም መልዕክት የብዙዎች ልብ ተነክቶ በጌታ አመኑ፣ ወደ ቤተክርስቲያንም ተጨመሩ (ሐዋ. ምዕ. 2)። የሚገርመው ሙላቱ በአንድ ጊዜ ያበቃ አልነበረም። እነዚሁ ሰዎችና ሌሎችም በሌላ ጊዜም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል። በአንድ ጊዜ መንፈሳዊ ልምምድና የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ብቻ ዕድሜ ልክ ማገልገል አይቻልም። አገልጋይ የመንፈስ ቅዱስ ሙላትን በአስፈላጊው ወቅት ማግኘት አለበት።

ሐዋርያት(በሐዋ.2) ላይ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው የእግዚአብሔርን ሥራ በሚገባ መሥራት ቻሉ። ከዚያም ስደት፣ እየበረታባቸው መጣ። ብዙ መሰናክሎች ከፊታቸው ተደቀኑ። በወቅት፣ የነበሩ ያሃይማኖት መሪዎች ሐዋርያት ወንጌልን እንዳይሰብኩ ከለከሉአቸው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ በውስጣቸው የሞላው መንፈስ የቀነሰ ይመስላል። ይህን ስለተረዱ በአንድ ልብ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። *"...አሁንም ጌታ ሆይ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፣ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፣ ባሪያዎችህም በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው"* (ሐዋ.4:29-30) በማለት ከጸለዩ በኋላ ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፣ የእግዚአብሔርንም ቃል በፍጹም ግልጥነት መናገር ቻሉ። ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወት ሲደክም እና አገልግሎት ሲሰለች እንዲሁም የተለያዩ መሰናክሎች ሲበዙ እግዚአብሔር በመንፈሱ እንዲሞላን መጸለይ ይገባናል። የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ከችግሩ በላይ ያስኬደናል።

*የመንፈስ ፍሬ ማፍራት*

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መልካምና አስፈላጊ ነገር ቢሆንም የመንፈስ ፍሬ ተከትሎ የማይመጣ ከሆነ ሙሉ ያልሆነ ሕይወታችን ሙሉ አይሆንም። አንድ ሰው አማኝ መሆኑ የሚታወቀው በልሳን በመናገሩ ሳይሆን በሕይወቱ የመንፈስ ፍሬ በመታየቱ ነው። በልሳን መናገርንስ ክፉም ሊሰጥ ይችላል። የመንፈስ ፍሬ ግን የማይከረጅ የክርስቲያን መታወቂያ ነው።

የመንፈስ ፍሬ የሚባሉት መንፈስ ቅዱስ በአማኝ ሕይወት ውስጥ በሙላት በመኖሩ የሚታዩ የሕይወት ባህርያት ናቸው። እነዚህም (በገላ.5:22-23) ላይ ተጠቅሰዋል። "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው።" እነዚህ የመንፈስ ፍሬ ተብለው የተጠቀሱት ባህርያት አንድ ምዕመን ከሌሎች ሰዎች ጋር በመስማማት ይኖር ዘንድ ሊኖረው የሚገባውን አመለካከትና ተግባሮችን የሚያሳዩ ናቸው።

እንግዲህ አገልጋይ እንደ አንድ ምዕመን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በተከታታይ የማይለማመዳቸው ከሆነ ለአገልግሎት ሲወጣ የነበረው የውስጥ ኃይሉ ተማጦ ያልቃል፣ መንፈሳዊ ቅንዓቱ ይለዝባል፣ በሕይወቱ ባዶነት ይሰፍናል፣ የተለያዩ ፈተናዎችን መቋቋም ያቅተዋል፣ ከዚያም በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይገባል። ይህ እንዳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጸሎትና ቃሉን በማጥናት መትጋት እንደዚሁም ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ ላይ በመደገፍ መኖር ይገባዋል።

ስለዚህ አገልጋይ ከማንኛውም አገልግሎት ይልቅ ለራሱ መንፈሳዊ ሕይወት ትኩረትና ቅድሚያ መስጠት ይጠበቅበታል። አማኝ እነዚህን ነገሮች የሚያደርጋው ለሌሎች ብሎ ሳይሆን ለግል ሕይወቱ በማሰብ እንደሆነ ሁሉ አገልጋይም አስቀድሞ የሚያደርጋቸው ነገሮች ለግል ሕይወቱ ጥቅም እንደሆኑ መገንዘብ ይኖርበታል። አገልግሎት ሙያ ሳይሆን ሕይወት ስለሆነ አስቀድሞ አገልጋዩን ሠርቶ ለሌሎች ሊተላለፍ ይገባል። የአገልግሎት የኃይል ምንጩ አገልጋይ እንደ አማኝ የሚኖረው መንፈሳዊ ሕይወት ነው። የአገልጋይ መንፈሳዊ ሕይወት ጠንካራ ሲሆን አገልግሎቱ ፍሬያማ ይሆናል።

## አገልጋይ እንደ ባለትዳር/ወላጅ/

ከላይ እንደተጠቀሰው አንድ አገልጋይ ከአገልግሎት በፊት ለግል መንፈሳዊ ሕይወቱ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ እንዳለበት አይተናል። ወደ ቤተሰብ ጉዳይ ስንመጣ ደግሞ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ለቤተሰብ ነው ወይስ ለአገልግሎት? የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ከሆነ የቤተሰብ ሕይወት ከአገልግሎት በፊት መምጣት አለበት።

አገልጋይ ከአገልግሎት በፊት ቤተሰቡን ማስቀደም አስፈላጊ መሆኑን ቢያውቅም ይህን ሲያደርግ አለመታየቱ ራሱንና ቤተሰቡን እንዲሁም አገልግሎቱን ለአደጋ በማጋለጥ ላይ ይገኛል። አገልጋይ እንደ ባለትዳርና ወላጅ ለቤተሰቡ ሊሰጥ የሚገባውን ትኩረት የማያደርገው ለምንድነው? ለዚህ ጥያቄ የተለያዩ መልሶች ሊሰጡ ቢችሉም ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. *እግዚአብሔርን ማገልገል ለቤተሰብ ትኩረት ከመስጠት እንደሚበልጥ ማሰብ፡-* አንዳንድ አገልጋዮች እግዚአብሔርን እንዳገለገሉ የሚያስቡት ከቤተሰባቸው ውጭ ሲያገለግሉ ነው። ለዚህ ዓይነቱ አስተሳሰብ መሠረት የሆነውን አንድ ሰው ቤተሰቡን ካልተወ በስተቀር እግዚአብሔርን መከተል አይችልም የሚለውን ቃል በተሳሳተ መንገድ መተርጎም ነው። ጌታ ኢየሱስ እርሱን መከተል የሚሹ ሰዎች ሁሉ ከማንም በላይ እርሱን መውደድ እንዳለባቸው ሲያስተምር የተናገራቸውን

አሳቦች ከአውዱ ውጭ የሆነ ትርጉም በመስጠት በአገልግሎት ስም ቤተሰቦቻቸውን የሚሠዉ አገልጋዮች አሉ። ጌታ ኢየሱስ «ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን፣ ሚስቱንም፣ ልጆቹንም፣ ወንዶሞቹንም፣ እኅቶቹንም፣ የራሱንም ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ሳይጠላ ደቀመዝሙሬ ሊሆን አይችልም» (ሉቃ.14:26) ማለቱ አገልጋይ ቤተሰቡን በመጥላት ለአገልግሎት እንዲወጣ የሚጋብዝ ጥሪ አይደለም። ታዲያ እንዲህ ካልሆነ ጌታ ስለምን ለማስተማር ነው ይህን ቃል የተናገረው? .......

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን አገልግሎት የሚጀምረው ከቤተሰብ ነው። ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ብቁ ሊሆን የሚችለው ቤተሰቡን እንደሚገባ የሚያገለግልና የሚመራ ሰው ነው። ለኤጲስ ቆጶስነት ከተጠቀሱት መስፈርቶች አንዱ "ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር" (1ጢሞ3:7) መሆን እንደሆነ ይናገርና "ሰው የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን እንዴት ይጠብቃል?" በማለት የአገልግሎት ብቃት መፈተኛ ቦታ ቤተሰብ መሆኑን ያስረዳል።

2. *በአገልግሎት ምክንያት ከቤተሰብ ችግር መሸሽ፦* አገልጋይ ቤተሰቡ ውስጥ(በተለይም ከትዳር ጓደኛው ጋር) ስምምነት ከሌለው ችግሩን ላለመጋፈጥ የሚሸሽበት አንዱ መንገድ በአገልግሎት ስም ከቤት ውጭ ብዙውን ጊዜ ማሳለፍ ነው።

*ታመነ አገልግሎት ከጀመረ ሁለት አስርት ዓመታት አስቆጥሯል። ከሚስቱ ሁለት ልጆችን ወልዷል። ሚስቱ በአንድ መሥሪያ ቤት ውስጥ ተቀጥራ ጥሩ ደመወዝ ታገኛለች። ታመነና ሚስቱ ብዙ ጊዜ ስምምነት የላቸውም። ነገር ግን በመካከላቸው ያለውን ችግር የሚያውቁ በጣም የሚቀርቡአቸው ጓደኞቻቸው ብቻ ናቸው። ሁለቱ ችግሮቻቸውን መናገር አይፈልጉም። ከዚህ ችግራቸው ለመሸሽ ታመነ ሁሌጊዜ ለመስክ አገልግሎት ይወጣል። ብዙውን ጊዜ ከክልል ወደ ክልል እየተዘዋወረ ያገለግላል። አንድ ሳምንት አንድ ቦታ ከሄደ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሌላ ክልል ይሄዳል። እቤት የሚያድረው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ሲመጣ ብቻ ነው። ልጆቹ የአባታቸውን ፍቅር አያውቁም፣ የምታሳድጋቸው እናታቸው ናት። ታመነ አገልግሎትን ስለወደደ ሳይሆን አገልግሎትን ከትዳር ችግር የማምለጫ መንገድ ስላደረገው ከቦታ ቦታ ያለማቋረጥ ይዞራል።*

እንደ ታመነ ዓይነት ሰው በቤተክርስቲያን ሥር ሆኖ የሚያገለግል ከሆነ ቤተክርስቲያን ስለቤተሰቡ ሁኔታ ልትጠይቀው ይገባታል። በራሱ ፈቃደኝነት ችግሩን ለመፍታት እርምጃ መውሰድ ባይፈልግም ቤተክርስቲያን ቤተሰብ እየፈረሰ አገልግሎቱን መቀበል የለባትም። አገልጋዩ የሚያስተምረው ትምህርት አስቀድሞ በቤተሰብ ሕይወቱ ውስጥ በተግባር ሊተረጎም ይገባል።

ከቤተክርስቲያን ውጭ በተለያዩ ሚኒስትሪዎች የሚያገለግሉ አገልጋዮችም ቢሆን አገልግሎታቸውን የሚቀበሉ ወገኖች የአገልጋዮቹን የቤተሰብ ሁኔታ መጠየቅ ይገባቸዋል። በማንኛውም ደረጃና ሁኔታ እግዚአብሔርን አገለግላለሁ የሚል አገልጋይ ስለቤተሰቡ ሲጠየቅ እውነተኛና ግልጽ የሆነ ምላሽ ሊሰጥ ይገባዋል። አንድ አገልጋይ «እኔ ቤተሰቤን ለእግዚአብሔር ሰውቻለሁ» «እግዚአብሔር ለቤተሰቤ እንደሚያስብላቸው

አምናለሁ» «የእኔ ቤተሰብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው» ማለት ከጀመረ ስለቤተሰብ ባለው አመለካከት ወይም በቤተሰቡ ውስጥ ችግር መኖሩን ያመለክታል። ከቤተሰቡ ጋር ያለውን ችግር መንፈሳዊ ልብስ እያለበሰው ለማለፍ መሞከር ለጊዜው ለሚያዩት ከማታለል ያለፈ ፍሬ ስለማይኖረው የራስን ስህተት ተቀብሎ ለተገቢው ነገር ቅድሚያ መስጠት ያዋጣል። በቤተሰብ ሕይወት ግንባታ ያልተሳካለት አገልጋይ ቤተክርስቲያንን ለማነጽ ብቃት አይኖረውም።

3. *ከቤተሰብ ኃላፊነት መሸሽ፡* የቤተሰብ ኃላፊ ሆኖ ለቤተሰብ የሚያስፈልገውን ሁሉ ማድረግ በራሱ ትልቅ አገልግሎት ሆኖ ሳለ አንዳንድ አገልጋዮች ልጆችን ማሳደግና መንከባከብን ለሚስቶቻቸው በመተው በአገልግሎት ስም ከቦታ ቦታ ይዞራሉ። የቤተሰብን ኃላፊነት ከባድ ነው። ባሎች በአገልግሎት ስም ሲዞሩ የቤተሰብ ኃላፊነት የምትሸከመው ሚስት ናት።

አገልጋይ እንደባለትዳር /ወላጅ/ የቤተሰቡን ቁሳዊ፣ ማህበራዊ፣ መንፈሳዊና ሌሎችም አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሊያሟላ ይገባዋል። አገልጋይ የሚያገኘው ቀለብ የቤተሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት እንዳለበት ቢታመንበትም የብዙ አገልጋዮች ቤተሰብ የሚበሉት፣ የሚለብሱት ነገር አጥተው መቸገራቸው "አገልጋይ ከመሆንስ ለማኝ መሆን ይሻላል" ያሰኛል።

አገልጋይ ቀለቡን በተመለከተ ለቤተሰቡ የማይበቃ ከሆነ ለቤተክርስቲያን መሪዎች መናገር አለበት። ቀለቡን የማሻሻል ሥራ ግን እርሱ ማድረግ የማይችለው ነገር ነው። ሆኖም ከመናገር መቆጠብ የለበትም። ቤተሰቡ እየተራበና እየታረዘ እያየ በይሉኝታ ተይዞ ዝም ማለት አይገባውም። ይህ መንፈሳዊነት አይደለም።

አገልጋይ ተጠርቶ በሚሠማራበት ጊዜ ስለቀለቡ ከቤተክርስቲያን ጋር መነጋገር አለበት። ከቤተክርስቲያን እንደሚሰጠው ተስፋ የተገባለት ቀለብ ለቤተሰቡ እንደሚበቃው ከትዳር ጓደኛው ጋር መወያየት ይኖርበታል። በቤተሰቡ ላይ በራሱ ብቻ መፍረድ አይገባውም። አገልጋይ ስንት ይከፈለኛል? ብሎ መጠየቅ ያልተለመደ ነገር ቢሆንም በኋላ ከማጉረምረም አስቀድሞ መጠየቅ የተሻለ ነው። በአንዳንድ ቦታዎች ስለሚሰጠው ቀለብ የሚጠይቅ አገልጋይ ለቀለብ ብቻ ብሎ እንደሚያገለግል ተደርጎ እንደሚቆጠር የታወቀ ነው። ሆኖም «ስንት ይከፈለኛል?» ብሎ መጠየቅ ግልጽነት እንጂ ስግብግብነት አይደለም። ይህ ቀለብ የማይበቃው ከሆነ በዚህ ቀለብስ ቤተሰቤን ማስተዳደር አልችልም ብሎ በሚበቃው ቀለብ ለአገልግሎት ሊያሰማሩ የሚችሉትን ቤተክርስቲያኖች መፈለግ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ ደግሞ ለራእዩ ብሎ ከቤተሰቡ ጋር በመስማማት በመጠነኛ ቀለብ ወይም ያለምንም ክፊያ ሌላ የገንዘብ ማግኛ መንገድ ፈልጎ ማገልገል ይችላል።

ቤተክርስቲያን ለአንድ አገልጋይ የሚበቃውን ቀለብ መስጠት የማትችል ከሆነች አገልጋዩ ቤተሰቡን በረሃብ አለንጋ ማስገረፍ የለበትም። አገልጋዩ ከቤተሰቡ እና ከቤተክርስቲያን ጋር በመነጋገር ከሚከተሉት አንዱን ማድረግ ይችላል።

- በትርፍ ጊዜው ሌላ ሥራ በመሥራት ቤተሰቡን የሚደግፍበት ገንዘብ ማግኘት
- የትዳር ጓደኛው ለቤተሰብ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት የምትችልበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- በሌላ ቤተክርስቲያን በትርፍ ጊዜው ወይም ግማሽ ጊዜ በማገልገል ቀለብ ከሁለት ቤተክርስቲያናት እንዲከፈለው ማድረግ እና ሌሎች የተለያዩ መንገዶችን መጠቀም ይችላል::

አገልጋይ ለቤተሰቡ በተለይም ለትዳር ጓደኛው ተገቢውን ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ትዳራቸው ሊጎዳ ይችላል:: መልካም ጋብቻን መመሥረት በቂ ጊዜ መስጠትን ይጠይቃል። አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው በቂ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ እንዴት ፍቅር ያለበት የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል? ግንኙነት በተዓምር የሚፈጠር ሳይሆን ጥረትን የሚጠይቅ ነው። አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው በቂ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ግንኙነታቸው ዕለት ተዕለት እየላላ ይሄዳል። አፍሴላዊ ፍች ባያደርጉም ሁለቱ ተለያይተው ይኖራሉ። አገልጋዩ አምሽቶ ወደ ቤት ይገባል። ሚስት ሥራ ካላት ጧት አገልጋዩ ከእንቅልፉ ከመነሳቱ በፊት ወደሥራ ትሄዳለች። ሁለቱም ለምሳ ወደቤት አይገቡም። በዚህ ሁኔታ መቼ የጋራ ጊዜ ይኖራቸዋል? አንዳንዴ ደግሞ ለአገልግሎት እሩቅ ሥፍራ ይሄድና ሰነባብቶ ይመለሳል። የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ ስለአገልግሎት ብትጠየቅ ምን ትናገር ይሆን!

የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ በአገልግሎት ምክንያት ትኩረት እንዲነፈጋት ባትፈልግም እግዚአብሔርን ከመፍራት የተነሳ አገልጋዩን "እባክህን ለእኔም ጊዜ ስጠኝ" ማለትን ትፈራለች። ከዚህም የተነሳ በአምልኮ ቦታ፣ በማህበራዊ ክንውኖች (ለቅሶ፣ ግብዣ...) የአገልጋይ ሚስት ብቻዋን ትታያለች። ሌሎች ባለትዳሮች ጥንድ ሆነው ሲሄዱ እርሷ ለብቻዋ ወይም ከሌሎች ጋር ተዳብላ ትሄዳለች። ባል እያላት ያለባል ሆነች።

ይህን ሁኔታ የተመለከቱ ያላገቡ ሴቶች አገልጋይ ለማግባት ሲጠየቃቸው "ብቻዬን ልቀመጥ ነው እንዴ!" "ያለጊዜ ባልቴት መሆን አልሻም"ይላሉ። ይህ አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው ትኩረት እንደማይሰጥ የታወቀ መሆኑን ያመለክታል። እውነትም የአገልጋይ ሚስት የባልዋን ፍቅር ሳትቀምስ ብቻዋን ልጆቿን የምታሳድግ የልጆች እናት ናት።

ከላይ ለተጠቀሱት ነባራዊ ችግሮች መፍትሔ ሊመጣ የሚችለው አገልጋይ ቤተሰብ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ሲያውቅና ለተግባራዊነቱም እርምጃ ሲወስድ ነው:: እንደ መንፈሳዊ መሪ ይህ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ አማኝ የሚያስፈልገው ነገር መሆኑን ማስተማር ይጠበቅበታል:: ከዚያም የራሱን ቤተሰብ በሚገባ በመንከባከብ የሚያገለግላቸው አማኞች የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉት ማድረግ አለበት::

አገልጋይ የቤተሰቡንም የስሜት ዋስትና ማሟላት ይጠበቅበታል። የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ በአገልግሎት ዙሪያ የተሰማትን ስሜት የመናገር ወይም የመግለጽ ነጻነት ሊሰጣት ይገባል። ባልዋ አገልጋይ ስለሆነ ዘወትር እንደ አገልጋይ ሚስት ደስ ደስ የምትሰኝ ሴት እንድትሆን

የሚጠበቅ ከሆነ አንድ ቀን የታመቀ ስሜትዋ ሲፈነዳ ወደ መጥፎ ባህርያት ሊመራት ይችላል።

አገልጋይ የትዳር ጓደኛው ስለአገልግሎቱም ሆነ ስለቤተክርስቲያን ያላትን አሳብና ስሜት መግለጽ እንድትችል መፍቀድ እንጂ ማፈን አይገባውም። ሚስቱም ስትገልጽለት ትኩረት ሰጥቶ ሊያዳምጣትና ተገቢውን ምላሽ መስጠት ይጠበቅበታል። "የአገልጋይ ሚስት እንዲህ ወይም እንዲያ መናገር ወይም መሆን የለባትም" ማለት ችግርን ከመፍታት ይልቅ ሌላ ችግር ይጨምራል።

በመንፈሳዊ ነገር የአገልጋይ ቤተሰብ ጌታን ትቶ ወደ ኋላ ይመለሳሉ ባይባልም በጌታ ያላቸው ደስታና መንፈሳዊ መነቃቃት ወይም ቅንዓት ሊዳከም ወይም ሊጠፋ ይችላል። አገልጋይ ለሌሎች ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት እንክብካቤ የሚያደርገውን ያህል ለቤተሰቡ አያደርግም። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ አገልግሎትን እንደ ሥራ ይቆጥረውና መንፈሳዊ ተግባሮችን ለምሳሌ ጸሎት፣ ቃል ማካፈል፣ አምልኮ መምራት፣ መዘመር... ሲያከናውን ውሎ ወደ ቤት ሲመጣ ሲሠራ ከነበረው ሥራ ማረፍ ይፈልጋል። ውጭ ሲያደርጋቸው የዋላቸውን ነገሮች እንደገና ቤቱ ማድረግ ይሰለቸዋል። ከዚህም የተነሳ የቤተሰቡን መንፈሳዊ ሕይወት ቸል ይላል።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያካፍለው ሲጋጩ ብቻ ይሆናል። ባልና ሚስት መልካም ግንኙነት ከሌላቸው፣ የትዳር ጓደኛው ሌሎች የሚያውቁትን ደካማ ጎኑን ስለምታውቅ እርሱ የእግዚአብሔርን ቃል ለእርሷ ሲያስተምራት ለመቀበል ፈቃደኛ አትሆንም። ከዚህም የተነሳ አገልጋይ ለቤተሰቡ ማስተማርን ይተዋል። አንድ ጊዜ አንድ አገልጋይ ቤተሰቦቹን በተለይ የትዳር ጓደኛችውን የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር አስፈላጊ መሆኑን ከተማረ በኋላ "ባለቤቴ የጌታን ቃል ሳስተምራት ሆን ብዬ የእርስዋን ደካማ ጎን ወይም ችግር አንስቼ የምነግራት እየመሰላት እኔን መስማት አትፈልግም" በማለት ተናገረ። ባልና ሚስት አብሮ ስለሚኖሩ አንዱ የሌላውን ደካማ ጎንና ችግር እንደሚያውቅ የታወቀ ነው። አገልጋይ ቃል ሲያካፍል ሆን ብሎ የሚስቱን ደካማ ጎን የሚጠቅስ ከሆነ መልካም አቀራረብ አይደለም። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል መከታ በማድረግ ሌላውን መውቀስ ወይም መኮነን ነው። አገልጋይ ለትዳር ጓደኛው እንዲሁም ለቤተሰቡ ቃል ማካፈል ያለበት በቤት ውስጥ ሰላም ሲኖር መሆን አለበት። እንዲህ ከሆነ ሰዎች ቃሉን ከምንም ነገር ጋር ሳያያይዙ በሙሉ ልባቸው መስማትና መቀበል ይችላሉ።

አገልጋይ ከትዳር ጓደኛው ጋር መልካም ግንኙነት ከሌለውና አብረው የእግዚአብሔርን ቃል የማይመገቡ ከሆነ በአገልግሎቱ ስኬታማ አይሆንም። ምክንያቱም አገልጋዩ ዘወትር የሕሊና ወቀሳ ይሰማዋል። በራሱ ቤተሰብ ከሚስቱ ጋር የማይኖረውን ቃል ለሌሎች እንደሚሰብክ ሕሊናው ይወቅሰዋል። እንደዚሁም የበታችነት ስሜት ይሰማዋል። አገልግሎቱ በቤቱ ውስጥ ተቀባይነት እንደሌለው ከሚስቱ ምላሽ አግኝቷል። ከቤተሰብ የጀመረው መናቅ ደግሞ በሌሎችም ሊገጥመው እንደሚችል በማሰብ ተስፋ ይቆርጣል፤ አገልግሎቱም ፍሬ እንደሌለው

አድርጎ እንዲያስብ ያደርገዋል። በመጨረሻም ብቸኝነት ይሰማዋል። በአገልግሎቱ ከእርሱ ጎን በመቆም "አይዞህ በርታ" የሚለው ሰው ያለው አይመስለውም። ምክንያቱም የእርሱ የቅርብ ወዳጅም ከእርሱ ጋር በመሆን አገልግሎቱን እንደማትደግፍ አገልግሎቱን በቤት ውስጥ ባለመቀበል ገልጻለታለች።

ያአገልግሎት ትኩረት የምትፈልገው ሚስት ብቻ ሳትሆን ልጆችም ጭምር ናቸው። አንዳንድ ልጆች ወላጆቻቸው እቤት እንዲሆኑ አይፈልጉም። ወላጆቻቸውን ስለማይወዱአቸው "ምንነው አንድ ቀን እንኳ ከቤት ቢወጡልን" ይላሉ። የብዙ አገልጋዮች ልጆች ደግሞ "መቼ ይሆን አባታችን ጊዜ ኖሮት ከእኛ ጋር የሚጫወተው" እያሉ ያለቅሳሉ። ልጆች ወላጆቻቸውን ሲፈልጉ የወላጆች አለመገኘት ልጆችን ክፉኛ ይጎዳቸዋል። የአገልጋይ ልጆች በአብዛኛው ለእናታቸው የተተዉ ናቸው። ከአባታቸው ጋር የሚገናኙት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ነው። እናታቸው የውጭ ሥራ የምትሠራ ከሆነች ደግሞ የልጆቹ ዕድል ፈንታ በቤት ሠራተኛ እጅ ማደግ ነው።

አገልጋይ ልጆቹ ራሳቸው የቤተክርስቲያን አካል በመሆናቸው እንደ ልጆቹ ብቻም ሳይሆን እንደ ማንኛውም የቤተክርስቲያን አባል አገልግሎት ስለሚያስፈልጋቸው ጊዜ በመመደብ ተገቢውን እንክብካቤ ሊሰጣቸው ይገባል። እንዲህ ካልሆነ ልጆቹ ከአባታቸው አገልግሎት የማያገኙት እነርሱ ከሌሎች ሰዎች ይልቅ ያነሱ በመሆናቸው ይመስላቸዋል።

አንዳንድ የአገልጋይ ልጆች አገልጋይ መሆን መልካም እንዳልሆነ ያስባሉ። እንዲህ እንዲያስቡ ያደረጋቸውም ዋና ምክንያት አገልግሎት አባታቸውን ከእነርሱ በመለየቱ ነው። በተለይ አገልጋዩ ከቤት እሩቅ ወደሆነ ቦታ እየሄደ የሚያገለግልና ለረጅም ጊዜ ከቤተሰብ ተለይቶ የሚቆይ ከሆነ ልጆች አገልግሎት መልካም ነው ብለው ማሰብ አይችሉም። ልጆች «ዛሬ አባባ ለምን ቆየ?» ብለው እናታቸውን ሲጠይቁ እናት «እርሱ እኮ ለአገልግሎት ክፍለ ሀገር ሄዷል» የምትላቸው ከሆነ አገልግሎት አባታቸውን ከእነርሱ እንደለየው ይቆጥራሉ። ስለዚህ አገልጋይ አገልግሎት የሚጀምረው ከቤተሰብ መሆኑን በማወቅ ለቤተሰቡ ትኩረት ሊያደርግ ይገባል።

አገልጋይ ብቻም ሳይሆን ቤተክርስቲያንም አገልጋይ ለቤተሰቡ ትኩረት እንዲሰጥ የአገልግሎት ፕሮግራሞቹን በማመቻቸትና ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን እንክብካቤ መስጠቱን በመከታተል ልትረዳው ትችላለች። ከዚህም በላይ ባልና ሚስትን አንድ ላይ ለአገልግሎት መጥራትም አማራጭ መፍትሔ ሊሆን ይችላል። በአንዳንድ ቤተእምነት ባልና ሚስት አንድ ላይ እንዲያገለግሉ አይፈቀደም። በአገለግሎት እንዲደጋገፉ፣ አብረው መውጣትና መግባት እንዲችሉ አንዱ ሌላውን መጠራጠር እንዳይችል ባል.ና ሚስት ጥንድ ሆነው ማገልገል መቻላቸው መልካም ሆኖ እያለ ይህ አለመፈቀዱ በጣም ያሳዝናል።

ቤተክርስቲያንም አገልጋይ ቤቱን እያፈረሰ የሌላው ቤት እንዲገነባ ከማድረግ ልትቆጠብ ይገባታል። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለች ከጊዜ በኋላ የአገልጋይ ቤተሰብ መንፈሳዊ ሕይወት ሲበላሽ ምሳሌነቱ ክፉኛ

ቤተክርስቲያንን እንደሚጎዳ እንዲሁም ባላመኑት ዘንድ መልካም እንዳልሆነ ማወቅ ይኖርባታል።

## አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ

ቤተክርስቲያን አገልጋይን እግዚአብሔር ጠርቶ ቀብቶ እንዳስነሳው ታምናለች። አገልጋይም በሙሉ ጊዜው በሙሉ ልቡ የወንጌልን ሥራ እንዲሠራ ይጠበቅበታል። የአገልጋይ ትልቁ ሥራ ሁሉንም መንፈሳዊ አገልግሎት ራሱ መሥራት ሳይሆን ምዕመናን እግዚአብሔር በሰጣቸው ልዩ ልዩ ጸጋ ማገልገል እንዲችሉ ማስተባበርና ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ ለሥራ ከፍተኛ የልብ መነሳሳት ያለው ሰው ሊሆን ይገባል። የልብ መነሳሳቱም መምጣት ያለበት እግዚአብሔር በውስጡ ካስቀመጠው የአገልግሎት ሸክም ነው። አገልጋይ የሚያገለግለው ጌታ ለዚያ ሥራ ስለጠራው ነው። የአገልጋይ የልቡ አሳብ በውጫዊ ቀስቃሽ ነገሮች ለምሳሌ በጥሩ ደመወዝ፣ ዝና ወዘተ ነገሮች ብቻ የሚቀሰቀስ መሆን የለበትም። እንዲህ ከሆነማ ለደመወዝ ከሚሠሩት ሰዎች በምን ይለያል! አገልጋይ የአገልግሎት መነሳሳት የሚያገኘው ውጫዊ ነገሮች ሲመቻቹለት ከሆነ ውስጣዊ የልብ መነሳሳቱ እየሞተበት ይሄዳል። ከዚያም የጥሪ ነገር ወደኋላ ይባልና የራሱንና የሌሎች ሰዎችን አሳብ ማገልገል ይጀምራል። አንድ አገልጋይ እግዚአብሔርን ለማገልገል የውስጥ የልብ መነሳሳት የሚኖረው እግዚአብሔር የአገልግሎት ሸክም በውስጡ ሲያስቀምጥ ነው። ውጫዊ ማበረታቻ በልብ ውስጥ የአገልግሎት ሸክም እንዲወለድ የማድረግ ኃይል የለውም። ነገር ግን በአግባቡ ከሆነ በውስጥ ያለውን የአገልግሎት ሸክም እንደሚገባ ለማውጣት ይረዳል።

አገልጋይ ለሥራ የልብ መነሳሳት ያለው ብቻም ሳይሆን የሥራ ዲሲፕሊንን የሚያከብር እንዲሆን ይጠበቅበታል። ከእነዚህም አንዱ የሥራ ሰዓትን ማክበር ነው።ብዙ አገልጋዮች አንድ ሠራተኛ መሥራት ከሚገባው ሰዓት በላይ ሠርተው የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንደማይከፈላቸው የታወቀ ነው። እነዚህ አገልጋዮች አገልግሎት በሰዓት የተገደበ እንደሆነ አያስቡም። አገልግሎት ካለ ማገልገል ተግባራቸው ነው። ከዚህም የተነሳ በጣም ይዝላሉ። አንዳንዶች ደግሞ አንድ ሠራተኛ መሥራት የሚገባውንም ሰዓት አይሠሩም። በጉብኝት አገልግሎት ስም ከቢሮ ወጥተው ከሆነ ከአንዱ ቤት ወደ ሌላኛው ቤት ሲዞሩ ይውላሉ። የሚፈልጉትን ሰው ባያገኙም ካገኙት ሰው ጋር የመጣላቸውን ነገር አውርተው ይመለሳሉ። እቢሮ ውስጥ ከዋሉ ደግሞ ከአንዱ ቢሮ ወደ ሌላኛው ቢሮ እየሄዱ ያወራሉ፣ የሚሠሩትን ሰዎች ሥራ ያስፈታሉ። እንዲህም ሆኖ በወሩ መጨረሻ እንደሠሩ ሠራተኞች ላልሠሩበት ሰዓት ደመወዝ ይቀበላሉ። ይህ ዓይነት ዲስፕሊን የሌለው ሥራ በአገልጋይ ዘንድ እንዳለ መወራት የለበትም።

የጌታ ባሪያ ለአገልግሎቱ ትጉና እግዚአብሔር በከፈተለት የአገልግሎት በር በተሰጠው ጊዜ በተሰጠው መክሊት ይነግዳል። ሰዎችንም ከጨለማው ሥር ለማውጣት ዘወትር ይተጋል። አገልጋይ የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ ጌታ ኢየሱስ «ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል ማንም ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ትመጣለች» (ዮሐ.9:4) ብሎ የተናገረውን ቢያስብ መልካም ነው።

አገልጋይ እንደ አንድ የቤተክርስቲያን ሠራተኛ ዝርዝር የሥራ ድርሻ ያለው ሰው መሆን አለበት:: የሥራ መዘርዝር የሌለው አገልጋይ የሚሠራውን ሥራ አያውቅም:: አገልግሎት የሚመስለውን ሁሉንም ዓይነት ሥራዎችን ይሠራል:: አንድ ቀን ግን ምን እንደተሠራ እርሱም ሆነ ሌሎች ሲገመግሙት ምንም ነገር እንዳልተሠራ ይታያል:: እንግዲህ ተገቢውን ሥራ ለመሥራት የሥራ መዘርዝር እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው:: በሥራ መዘርዝር አስፈላጊነት ላይ ቢታመንም ግን ይህን ለአገልጋይ የሚያዘጋጀው ክፍል ማን ነው? ለአገልጋይ የሥራ መዘርዝር የሚያዘጋጀው አገልጋይ ራሱ ወይም የሚያስተዳደርው ክፍል ሊሆን ይችላል:: አገልጋይ እግዚአብሔር በውስጡ ካስቀመጠው ሸክም አንጻር መሥራት የሚፈልጋቸውን ሥራዎች ዝርዝር ለቤተክርስቲያን መሪዎች ያቀርባል:: ከዚያም መሪዎቹ ተወያይተውበት ከተቀበሉ አገልጋዩ በዚያ መሠረት ማገልገል ይችላል:: ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ መሪዎች ለአገልጋዩ የሥራ መዘርዝር ያወጡለትና ይሰጡታል:: አገልጋዩ አንብቦ ከተረዳ በኋላ ስምምነቱን ካሳየ ያ የሥራ መዘርዝሩ ይሆናል ማለት ነው:: በሁለቱም መንገዶች አገልጋዩና የሚያሰማራው ክፍል በሥራ መዘርዝሩ ላይ የጋራ መግባባት ሊኖራቸው ይገባል::

አገልጋይ ከቤተክርስቲያን የሚሰጠውን የሥራ ኃላፊነት ትቶ በግሉ የሚያስበውን ነገር ማድረግ አይችልም:: ምክንያቱም በዚያች ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግል «የቀጠሩት» መሪዎቹ ናቸው:: ስለዚህ የራሱን ትቶ የእነርሱን መቀበል አለበት:: ነገር ግን እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠውን ራእይ ቀስ በቀስ በሚያገለግለው አገልግሎት በመሪዎችና በምዕመናን እይታ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ እግዚአብሔር ወደሚመራው አቅጣጫ ሊወስዳቸው ይችላል:: ይህን ለማድረግ ግን በትሕትና ማገልገል መጀመር ወሳኝ ነው:: የቤተክርስቲያን መሪዎች የአገልጋይን አሳብ የሚቀበሉት አገልጋዩ የእነርሱን አሳብ እያስተናገደ ግን እግዚአብሔር የሰጠውን ራእይ ቀስ በቀስ በፍቅር ማሳየት ከቻለ ነው:: ራእይ የሚሰጠው በአንድ ሰው በኩል ቢሆንም ተግባራዊ የሚሆነው ግን ብዙሃኑ ሲቀበሉት ስለሆነ አብዮት ከማካሄድ በትሕትና መንገድ መሄድ የጌታ ፈቃድ ነው::

አገልጋይ እንደ እግዚአብሔር ሰውና አገልጋይ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተግባብቶ መሥራት የሚችል ሰው መሆን አለበት:: በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች ሁሉ ለአንዱ ጌታ ክብር የሚሠሩ ናቸው:: ስለዚህ አንዱ ከሌላው ጋር በመስማማት ማገልገል ይጠበቅባቸዋል::

አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ የአገልግሎት ስኬቱን የሚገመግም ሰው ሊሆን ይገባዋል:: በአብዛኛው አገልጋይ ጌታን በሚያገለግልበት ጊዜ የዕድሜ ልክ አገልግሎት እንደ ጀመረ ያስባል:: ስለዚህ በተለመደው መንገድ ከማገልገል ውጭ ቆም ብሎ አገልግሎትን መገምገም የተለመደ አይደለም:: ከዚህም የተነሳ አንዳንድ አገልጋዮች አያገለገሉ ግን ሳያውቁ ከአገልግሎት መስክ ይወጣሉ:: እነርሱ ሳያውቁት የሚያገለግሉበት ሁኔታ ከአገልግሎት ሜዳ ውጭ ያስወጣቸዋል:: አገልግሎታቸው ምን ያህል ፍሬ እንዳለው፣ ምዕመኑ ስለአገልግሎታቸው ምን እንደሚል፣ የምዕመኑን መንፈሳዊ ፍላጎት እያረኩ ስለመሆናቸው ምንም አሳብ የላቸውም:: እነርሱ ለምዕመኑ ያስፈልጋል ብለው ያሰቡትን መልካም በሚመስላቸው መልክ ይሰጣሉ:: መልዕክታቸውና አቀራረባቸው ላሉበት አውድ ተስማሚ መሆኑን አይመለከቱም:: አገልግሎታቸውን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ስለማይገመግሙ የአገልግሎታቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ለይተው

አያውቁም። ይህን ቢያደርጉ ኖሮ ደካማ ጎናቸውን በማወቅ ዕለት ዕለት ራሳቸውንና አገልግሎታቸውን ማሻሻል ይችሉ ነበር።

ተጠርቶ በሚያገለግልበት መስክ አገልግሎቱን በየጊዜው መገምገም የአንድ አገልጋይ የሕይወት ደንብ ሊሆን ይገባል። አንዳንዶች ግምገማ ሥጋዊ እንደሆነ ቢያስቡም አገልግሎትን መገምገም መንፈሳዊ ስለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ይደግፈናል። እግዚአብሔር ራሱ ፍጥረትን ከፈጠረ በኋላ በተከታታይ ግምገማ በማድረግ አስተያየት ሲሰጥ እንደነበር ከቃሉ እናነባለን (ዘፍ.1:4፣31፣ 6:5-8)። ስለአገልግሎቱ ግምገማ የማያደርግ አገልጋይ የሚያደርገውን የማያውቅ፣ አቅጣጫ የጠፋበት፣ መቼ ከአገልግሎቱ እንደሚሰናበት ማወቅ የማይፈልግ፣ ጌታን እንዴት ደስ ማሰኘት እንዳለበት በትጋት የማይፈልግ ሰው ነው። ይህ ደግሞ ከአንድ አገልጋይ የሚጠበቅ ባሕርይ አይደለም። ስለዚህ አገልጋይ በግሉ አገልግሎቱ ምን እንደሚመስል መገምገምና ራሱን ማሻሻል አለበት።

እንግዲህ አገልጋይ እንደ ምዕመን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለተሰጠው ለድነቱ/ለመንፈሳዊ ሕይወቱ/ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትና ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረው ይገባል። ድነትን መጠበቅ ከአገልግሎት እንደሚበልጥ በተግባር የሚያሳይ አማኝ መሆን ይኖርበታል። ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሰዎችን የሚያስገባው አገልግሎታቸው ሳይሆን ድነታቸውን መጠበቅና መንከባከብ መቻላቸው ነው። አገልጋይ እንደ ትዳር ጓደኛና ወላጅም ለቤተሰቡ ሕይወትና ኑሮ የሚጠነቀቅ ሊሆን ይገባዋል። ለቤተክርስቲያን አገልጋይነት ብቁ ለመሆን ለራሱ ቤተሰብ ሁለንተናዊ እንክብካቤ ማድረጉ ለአገልግሎቱ ስኬት ቁልፉ ነው። እንዲህ ሲሆን የቤተሰቡም ሕይወት በመልካም ምሳሌነቱ ስለወንጌልና ስለክርስቲያናዊ ኑሮ ምስክር ይሆናል። ከዚህም በላይ ቤተሰብ ለአገልጋዩ አገልግሎት ድጋፍ ሰጪ አካል ይሆናል። በመጨረሻም አገልጋይ እንደ ቤተክርስቲያን ሠራተኛ የልብ መነሳሳት ያለው፣ የሥራ ዲሲፕሊንን የሚያከብር፣ ከሌሎች አገልጋዮችና የቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር በመግባባትና በፍቅር አብሮ የሚሠራ እንዲሁም በተሰጠው የሥራ ድርሻ የአገልግሎት ስኬቱን የሚገመግምና ከዛሬ ነገ ራሱን የሚያሻሽል መሆን ይጠበቅበታል።

---

## ጥያቄዎች

1. እንደ አንድ አማኝ አለኝ የምትለው የሕይወት ልምምድና ጥራት ምንድነው?
2. አገልጋይ እንዴት አገልግሎቱንና የቤተሰብ ሕይወቱን በሚዛናዊ ሁኔታ መያዝ ይችላል?
3. አንድ አገልጋይ ቤተሰቡ እንዲያገለግል ፈቃደኛ ካልሆነ ምን ማድረግ ይኖርበታል ትላለህ? ለምን?
4. አንድ አገልጋይ ማገልገል ያለበትን ሰዓት እንደ ሌሎች ሥራዎች መወሰን ይቻላል? ለምን?
5. አገልጋይ የሚችለውን ሁሉ ጥረት አድርጎ ስኬት ባያገኝ ምን ማድረግ ይጠበቅበታል? ጥረ ካለ ስኬት የግድ መኖር አለበትን? አሳብህን የሚደግፍ ምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አለህ?

12

## የአገልጋይ መልካም ባህርያትን መኖር

ለአንድ አገልጋይ መልካም ባህርይ ኖሮት መልካም የጌታ አገልጋይ መሆን እጅግ ከባድ መሆኑ የታወቀ ነው። መልካም የተባሉትን ባህርያት ማግኘት የአገልጋዩና የእግዚአብሔር ድርሻ ነው። አገልጋይ እግዚአብሔር ከእርሱ የሚጠብቀው መልካም ባህርይ እንዲኖረው አስፈላጊ የሆነውን ጸጋ ይሰጣል። ሆኖም አገልጋዩ ጸጋውን ተቀብሎ እንደሚገባ ሊኖርበትና ራሱንም በጸጋው ሊያሳድግ ይገባዋል። አገልጋይ እግዚአብሔርን ሲያገለግል ሊኖሩት የሚገባው መልካም ባህርያት አሉ። አገልጋይ የላከውን እግዚአብሔርን ባህርይ መልበስ ይጠበቅበታል። አገልጋይ በአገልግሎቱ፡ ፍሬያማ እንዲሆን መልካም ባህርያት ወሳኝ ናቸው። እነዚህም ምን እንደሆኑ እንደሚከተለው እንመለከታለን።

1 **እግዚአብሔርን መምሰል** (1ጢሞ.4:7)

እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ምን ማለት ነው? እግዚአብሔርን መምሰል ማለት በመልክ የእርሱን "ቅርጽ" መያዝ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። እግዚአብሔርን መምሰል ማለት ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መስጠት፣ ከፍቅር የተነሳ እርሱን በመፍራት ማክበር ነው። እግዚአብሔርን መምሰል እርሱን ከልብ በማክበር የተነሳ እርሱን ደስ የሚያሰኝ መልካምና በቅድስና የተሞላ ሕይወት መኖር ነው። እግዚአብሔርን የሚመስል ሰው እርሱን ይወዳል፣ ያከብራል እንዲሁም ይፈራል። በሌላ አነገገር እግዚአብሔርን የማይዳፈረው ግን የሚገባውን አምላካዊ ክብር የሚሰጥ ሰው ነው።

እግዚአብሔርን መምሰል የውስጥ የልብ ምላሽ ብቻ ሳይሆን በአኗኗር ዘይቤም የሚገለጽ ነው። እግዚአብሔርን እየመሰለ የሚኖር ሰው በአኗኗር ዘይቤው እግዚአብሔርን ማዕከላዊ ያደረገ ሕይወት ይኖራል። እግዚአብሔርን በልቡ በማንገስ በአሳብና በተግባር የእርሱን ባህርይ ይገልጻል።

እግዚአብሔርን መምሰል ቁጭ ብሎ ስለመልካም መንፈሳዊ ሕይወት በማሰብ የሚመጣ ክስተት ሳይሆን ራስን ማስለመድን ይጠይቃል። ይህ ልምምድ ደግሞ ከሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴ ጋር ይመሳሰላል። በተለያዩ ዘመናት ብዙ ሰዎች የአካል እንቅስቃሴዎች በተከታታይነት ማድረግ ለአካል ጤንነት አስፈላጊ መሆኑን ይናገራሉ። ሐኪሞችም የአካል እንቅስቃሴ ማድረግ ለጤንነት ጥሩ እንደሆነ ከመግለጽም ባሻገር እንደ "መድኃኒትም" ያዛሉ። ከዚህም የተነሳ ብዙ ሰዎች ማለዳ ማለዳ ወይም ምሽት አካባቢ የአካል እንቅስቃሴ ሲያደርጉ ይታያሉ። ይህ በአካባቢያችንም እየተለመደ መጥቷል።

በተመሳሳይ መልኩ አገልጋይ ለጤናማ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እግዚአብሔርን ለመምሰል ራሱን ማስለመድ ይገባዋል። እግዚአብሔርን መምሰል ራስን በሥርዓት መምራትን ይጠይቃል። እርሱን መምሰል መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ ይከናወናል።

እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚረዱ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎች ምንድናቸው? ሐዋርያው ጳውሎስ ዝርዝራቸውን አልተናገረም። ሆኖም ሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዲቀርቡ ሊያደርጋቸው የሚችሉ መልካምና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆኑ ልምምዶች ለምሳሌ ቃሉን ዘወትር ማጥናት፣ በተከታታይነት መጸምና መጸለይ፣ ከእግዚአብሔር ሰዎች ጋር መልካም ኅብረት ማድረግ፣ እግዚአብሔርን ማምለክ እና የመሳሰሉት ተግባሮች ይጠቀሳሉ።

በአሉታዊ ጎኑ ደግሞ እግዚአብሔርን ለመምሰል ከማይረዱ ከንቱ አሳቦችና ልምምዶች መራቅ የግድ ነው። "ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶችን ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ" (1ጢሞ.4:7)። አገልጋይ እግዚአብሔርን በመምሰል ለመኖር ከእውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረን ማንኛውንም ትምህርት ማስተናገድ የለበትም። ለጆሮ የሚጥም ወይም ሰዎች በተለምዶ እውነት እንደሆነ የሚተርኩት ፈጠራ ወደ እግዚአብሔር አሳብ አያስጠጋም። ስለዚህ አገልጋይ ከእነዚህ ፈጠራ አሳቦች መራቅ አለበት። በሰዎች ግምት መልካም እንደሆኑና ኑሮን የሚያቃኑ የሚመስሉ አሳቦች ጌታን እየመሰሉ እርሱን ከማገልገል ጋር ሲነጻጸሩ ዘላቂ ውጤት የላቸውም።

እግዚአብሔርን ለመምሰል መትጋትና እርሱን መምሰል ጥቅም አለው። የአካል እንቅስቃሴ ዘወትር ማድረግ ለአካል ጤንነት ጠቃሚ ነው። ከዚህም ሲያልፍ ጥሩ ስፖርተኛ በመሆን ውድድር አሸንፎ ታዋቂ መሆን ወይም ገንዘብ ማግኘትን ያመጣል። እግዚአብሔርን ለመምሰል መትጋት ደግሞ እጥፍ ጥቅም አለው። ጥቅሙ በዚህ ዓለምና በሚመጣው ዓለም የሚታይ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ "ለነገር ሁሉ ይጠቅማል" በማለት ይናገራል። ይህ ምን ማለት ነው? ለምሳሌ መጸለይ ወይም የእግዚአብሔርን ቃል በተከታታይ ማጥናት እንዴት ለነገር ሁሉ ሊጠቅም ይችላል?

*ታሪኩ ተማሪ በነበረበት ጊዜ ችሎታ ቢኖረውም በሥርዓት ትምህርቱን አያጠናም ነበር። ሲያጠናም አሳቡ ሳይገባው እንዲሁ መሸምደድን እንጂ የአሳቡን ብልት እየወጣ መገምገምና ማሰላሰል አያውቅም ነበር። ጌታን ከተቀበለ እና መጸለይ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ከጀመረ በኋላ ግን የሚማረውን ትምህርት በሚገባ ማሰላሰልና አሳቦችን ብልት ብልታቸውን እየወጣ መመርመር ጀመረ። መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ "ዓሣን መብላት በብልሃት" እንደሚባል ስለሆነ አዕምሮው መጽሐፍ ቅዱስን አንብቦ ለመረዳት በሚጠቀመው ዘዴ ትምህርቱን ማጥናት ሲጀምር ከዚያ በፊት ተረድቶ የማያውቀውን እውነት መገንዘብ ጀመረ። ታሪኩ ጌታን ከተቀበለ በኋላ የበለጠ ጎበዝ ተማሪ መሆን ቻለ። ለታሪኩ ጌታን ለማወቅ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናቱ ለትምህርቱም አስተዋጽኦ አድርጎለታል።*

እግዚአብሔርን ለመምሰል ራስን ማስለመድ ለሁለንተናዊ ሕይወት ይጠቅማል። አገልጋዮች እግዚአብሔርን ለመምሰል የሚያደርጉት መንፈሳዊ ተግባሮች ለሥጋዊ እንዲሁም ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይጠቅማቸዋል። መንፈሳዊ ሕይወታቸው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ

በሚመራበት ጊዜ ኑሮአቸውም እንደ እግዚአብሔር አሳብ ይሆንላቸዋል። ይህ ሲሆን ደግሞ በመብዛትም ሆና በመትደል ውስጥ ለእግዚአብሔር የሚመች ሰላም ያለው ሕይወት ይኖራሉ። ይህም ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን መስሎ መኖር ለሚመጣው ዓለምም ትርፍ አለው።

2. **ምሳሌ መሆን** (1ጢሞ 4:12)

አገልጋዮች መሆን ከሚገባቸው ዋነኛ ነገር አንዱ ለሚያገለግሏቸው ሰዎች ምሳሌ መሆን ነው። ምሳሌ መሆን ማለት ሌሎች ሰዎች አይተው መከተል የሚገባቸው ዓይነት ሞዴል መሆን ነው። አገልጋዮች ለተከታዮቻቸው ምሳሌ የሚሆኑት በተለያየ የሕይወት መስክ ነው። ለምሳሌ ያህል በፍቅር፣ በታማኝነት፣ በንጽሕና እግዚአብሔርን በመምሰልና በመጸናት ምሳሌ መሆን ይገባቸዋል።

አገልጋይ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሰዎች የሚያሳይ ሞዴል ሊሆን ይገባል። የእግዚአብሔር ፍቅር ምን እንደሚመስል ሰዎች ስለእግዚአብሔር ባህርይ ከሚያስተምረው ሰው ሕይወት ውስጥ ማየት ይፈልጋሉ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የገለጠው ፍቅር ሰዎች ገና ኃጢአተኞች ሳሉ የወደደ (ሮሜ5:8)፣ በምንም ቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ (ዮሐ3:16) እና ለሰዎች መልካም እንዲሆን እስከሞት ድረስ መስዋዕትነት የከፈለ (ዮሐ.15:13) ፍቅር ነው።

ሰዎች አገልጋይ ለሰዎች ያለውን ፍቅር በማየት "ለካስ እግዚአብሔር ሰዎችን እንዲህ ይወዳል" ማለት የሚያስችል ሰው እንዲሆን ይጠበቅበታል። ሰዎችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚቀበለውን የእግዚአብሔርን ፍቅር የማሳያው መንገድ የአገልጋይ ሕይወት ነው። አገልጋይ ይህን ፍቅር የሚያሳየው ሰዎች ምንም ዓይነት ክፉ ነገር ሲናገሩት ወይም ሲያደርጉበት እንዲሁም መሆን የሚገባቸውን ሆነው ሳይገኙ ሲያይ በራሱም ሆነ በሌሎች ላይ መልካም ሳያደርጉ ሲመለከት ዘወትር እነርሱን ከመጥፎ ባህርያቸው ለመመለስ የሚተጋና በክፉ ፋንታ ክፉን የማይመልስ ሰው በመሆን ነው።

አገልጋይ የሚያገለግላቸው ሰዎች በእርሱ ላይ ክፉ ሲያስቡና ሲያደርጉበት አይቶ ያለምንም የፊት መጨማደድ እነርሱን ማገልገል ከቻለ ፍቅሩ አምላካዊ ፍቅር (አጋፔ) መሆኑን በተግባር ያሳያል። ይህ አገልጋይ ፍቅር ምን ማለት እንደሆነ በተግባር ለእነርሱ በማሳየቱ የሚያገለግላቸው ሰዎች እንዴት እርስ በርሳቸውና ከሌሎች ሰዎች ጋር በፍቅር መኖር እንዳለባቸው ያስተምራቸዋል።

ሰዎች አገልጋይ እንደሚወዳቸው ሲረዱ የእርሱን መሪነትና ትምህርት ለመቀበል ያላቸው ፍላጎት ይጨምራል። አንድ ጌታን ለብዙ ዓመታት ያገለገለ አገልጋይ እኔ ገና ለወንጌል አገልግሎት ራሴን ስሰጥ "ሰዎችን ውደዳቸው፣ እነርሱም ይወዱሃል። ከተወደድክ ደግሞ አገልግሎትህን ይቀበላሉ። ነገር ግን ፍቅርን መጠበቅ ትተህ ከልባቸው እንዳያወጡህ ተጠንቀቅ" ብሎ መከረኝ። የዚህ አገልጋይ ምክር በጣም መሠረታዊ ነው። አገልጋይ ሰዎችን ከወደደና ተገልጋዮችም ተገቢውን ምላሽ ከሰጡት አገልግሎቱ የተቃና ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ ግን

አገልጋዮች በፍቅር ይጀምሩና በጥል ይጨርሳሉ። አገልጋይ እንደ መጀመሪያው ተገልጋዮችን መውደዱን ያቆምና ምዕመኑን ለራሱ ዓላማ ማስፈጸሚያ ለመጠቀም መጠምዘዝ ይጀምራል። ይህን ጊዜ ምዕመናን አገልጋዮን ከልባቸው ውስጥ ያወጡታል። ከዚህ በኋላ ወደልባቸው ተመልሶ ለመግባት በሩ ይዘጋል። ይህ እንዳይሆን አገልጋይ ሁሉጊዜ የሚያገለግላቸውን ሰዎች መወድድ ይገባዋል። ፍቅሩም ከእውነተኛ ልብ የመነጨ እንጂ የሽንገላ መሆን የለበትም። እንዲህ ከሆነ የአገልጋዩ የፍቅር ሕይወት የጌታን ፍቅር ለሰዎች ያሳያል።

በፍቅር ምሳሌ መሆን ማለት ምዕመናን ሲሳሳቱ እውነትን አለመናገር ወይም አለመገሰጽ ማለት አይደለም። የእግዚአብሔር ፍቅር በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተና ኃጢአተኞችን የሚወድ ቢሆንም ከኃጢአት ጋር የሚተባበር አይደለም። አገልጋይ ለሚያገለግላቸው ሰዎች ያለው ፍቅር ኃጢአትን አይሸፍንም። ነገር ግን ኃጢአተኞች ንስሐ ገብተው ራሳቸውን እንዲያስተካክሉ ይጋብዛቸዋል።

አገልጋይ በታማኝነትም ምሳሌ ሊሆን ይገባዋል። አገልጋይ ለተናገራቸው ቃሎች ታማኝ መሆን አለበት። ለሰዎች የተናገረውን ቃል ያለበቂ ምክንያት ማጠፍ የለበትም። "አደርጋለሁ" ካለ ማድረግ አለበት። ቀጠሮን በሚገባ ማክበር ይጠበቅበታል። ይህ ቀላል ነገር ቢመስልም በተከታታይነት ቃሉን የሚያከብር ከሆነ ሰዎች ለሚናገራቸው ነገሮች ሥፍራ ይሰጣሉ፤ ያምኑታልም።

አገልጋይ በአደባባይ ለሚናገራቸው ቃሎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባዋል። በመድረክ ላይ ትኩረት የሚያደርግ ሰው የለም በማለት የማይገባውን መናገር መልካም አይደለም። እንዲሁም ታማኝነቱን ፈተና ውስጥ የሚያስገባ ንግግር ከመናገር መቆጠብ አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ ሰዎች የአገልጋይን ታማኝነት የሚፈትኑት ጉልህ በሆኑ ነገሮች ሳይሆን በጣም ጥንቃቅን ሆነው ትኩረት በማይሰጥባቸው ነገሮች ነው።

አገልጋይ ለእግዚአብሔርም ታማኝ መሆን አለበት። ለእግዚአብሔር ምንም ዓይነት ዋጋ የሚያስከፍለው ነገር ቢመጣ የማይታጠፍ ታማኝነት ያለው ሰው መሆን አለበት። ሁኔታዎች መልካም ሲሆን ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ቀላል ነው። ነገር ግን ሁኔታዎች አልመች ሲሉ፣ ኑሮ ሳይሳካ ሲቀር፣ መሠረታዊ ፍላጎት ለማሟላት ምንም ነገር ሳይኖርም ታማኝ መሆን የእውነተኛ ታማኝነት መገለጫ ነው።

አገልጋይ ለቤተክርስቲያን ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል። አገልጋይ በጥሪው መሠረት ላሰማራችው ቤተክርስቲያን ታማኝ መሆኑ አስፈላጊ ነው። ቤተክርስቲያን የእኔ አገልጋይ ነው ብላ ያሰማራችው አገልጋይ ቤተክርስቲያንን በሚጎዳ በማንኛውም ተግባር ላይ ተሰማርቶ መገኘት የለበትም። አገልጋይ በቤተክርስቲያን መሠረተ እምነትና ደንብ መሠረት ለማገልገል ቃል እንደገባ ሁሉ በማንኛውም ሁኔታ ቃልኪዳኑን ማክበር ይኖርበታል። እንዲህ አለማድረግ በእግዚአብሔርና በሰዎች ፊት የገባውን ቃልኪዳን ማፍረስ ስለሆነ ታማኝነትን ማጉደል ነው። አገልጋይ በተጠራበት ቤተክርስቲያን ማገልገል የማይፈልግ ከሆነ ከቤተክርስቲያኒቱ መሪዎች ጋር በመነጋገር አገልግሎቱን አስረክቦ

ወደሚፈልግበት ሥፍራ መሄድ ይችላል። ውሳኔው የግሉ ሲሆን ታማኝነት በማጉደል ግን አይከሰስም።

አገልጋይ ምሳሌ በመሆን ሲኖር ለራሱና ለተከታዮቹ መልካም ውጤት አለው። አገልጋይ በምሳሌነቱ የራሱን ትክክለኛ ማንነት በግልጽ ማሳየት ይችላል። በዚህ ጊዜ ምዕመናን እግዚአብሔር መልካም አገልጋይ እንደሰጣቸው ይረዳሉ፤ እርሱን በመመልከትም እግዚአብሔርን ወደ መምሰል ያድጋሉ።

ምሳሌ መሆን በቤተክርስቲያን አገልጋዮች ተቀባይነት ሲያገኙ ወይም ሁኔታዎች ሁሉ በተመቻቹበት ወቅት ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮችን የሚቃወሙ ወገኖች ይኖራሉ። እነዚህ ሰዎች የአገልጋዮችን አገልግሎት ከመደገፍ ይልቅ መሰናክል ይሆናሉ። በዚህ ሁሉ ውስጥ የእግዚአብሔር ሰው በመሆን ምሳሌነትን ማሳየት እጅግ አስፈላጊ ነው።

*ገሠሠ ለአገልግሎት ሲወጣ የሃያ ሦስት ዓመት ሊጋ ጎልማሳ ነበር። እርሱ ለማገልገል በተመደበበት አካባቢ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ደግሞ ዕድሜያቸው ከሰላሳ አምስት ዓመት በላይ ከመሆናቸውም በላይ በአገልግሎት ውስጥ ለብዙ ዓመታት የቆዩ ነበሩ። ገሠሠ ከእነርሱ ይልቅ መደበኛ ትምህርት የተማረ በመሆኑ አገልግሎቱ መስመር የያዘ ነበር። የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተምር በሚገባ ተዘጋጅቶበት ፈር ባለው ሁኔታ ያስተምራል። ከዚህም የተነሳ ምዕመናን እየወደዱት መጡ። የቤተክርስቲያን መሪዎችም መደበኛ ትምህርት የተማረና ጌታ የሚጠቀምበት አገልጋይ ስለሆነ የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን እንዲያስተባብር ኃላፊነት ሰጡት። በዚህ ጊዜ ከእርሱ በፊት የነበሩ አገልጋዮች ቀኑበት። የገሠሠን ስም ለማጥፋት መልካም ያልሆኑ ነገሮችን ያስወሩበት ጀመር። ለዋናው የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢም የገሠሠ ሕይወትና አገልግሎት መልካም እንዳልሆነ ሪፖርት አደረጉ። መጋቢው ሁኔታውን ሲከታተል የተወራው ነገር ትክክል አለመሆኑ ተገንዝቦ ዝም አለ። ከጥቂት ወራት በኋላ ገሠሠም የተወራበትን ነገር ሰማ። በጊዜው በነበረው የማስተባበር ሥልጣን ተጠቅሞ ያስወራበትን አገልጋይ መጉዳት ቢችልም ይህ መንገድ ጥሩ አለመሆኑን በመገንዘብ በፊት ያሳየው ከነበረው ፍቅር የበለጠ ፍቅር ማሳየት ጀመረ። በዚህም የአገልጋዩ ልብ ተነካ፣ ስላደረገውም ነገር ይቅርታ ጠየቀ። ገሠሠ አሁን በአካባቢው ምዕመናንና አገልጋዮች ዘንድ የተወደደ አገልጋይ ነው።*

የመምራት ሥልጣን የተሰጣቸው አገልጋዮች ከሚያገለግሏቸው ምዕመን ወይም ከሚመሯቸው አገልጋዮች መካከል የሚቀናቀናቸው ሰው ሲያገኙ በሁለት መንገድ ሁኔታውን ማስተናገድ ይችላሉ። የመጀመሪያው ባላቸው ሥልጣን ተጠቅመው ተቀናቃኙን ማንበርከክ ነው። በዚህ መንገድ ሰዎቹን ማሸነፍ የሚቻለው ለጊዜው ከመሆኑም በላይ የእግዚአብሔር አሳብ ያለበት መንገድ አይደለም። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ መልካም ምሳሌነትን እያሳዩ ማለትም የክርስቶስን ፍቅር እያሳዩ በመልካም ተግባር ማሸነፍ ነው። በዚህ መንገድ ሰዎቹን በዘላቂነት ማሸነፍ ይችላሉ። ይህ የእግዚአብሔር አሳብ ነው።

3. **ከተለያዩ ሰዎች ጋር መልካም ግንኙነት መኖር** (1ጢሞ 5፡1-2፤ 2ጢሞ.2፡22)

በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ። በዕድሜያቸው ያረጁ ወንዶችና ሴቶች፣ ጎልማሶች፣ ወጣቶች፣ ልጆች፣ እንዲሁም ከኑሮ ደረጃ ደግሞ ሐብታሞችና ድሆች፣ ከትምህርት አኳያ ደግሞ መደበኛ ትምህርት ያላቸውና የሌላቸው፣ ከአገልግሎት አኳያ ደግሞ በአገልግሎት ውስጥ የሚሳተፉና የማይሳተፉ ለምሳሌ ሽማግሌዎች እና ተራው ምዕመናን እንዲሁም በተለያዩ መስፈርቶች የተለያዩ ዓይነት ሰዎችን ማግኘት ይቻላል። አገልጋዮች ከእነዚህ የተለያዩ ሰዎች ጋር ጤናማ የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል።

በሀገራችን ባህል ሽበት ክብር አለው። የእግዚአብሔር ቃልም ሽበት ክብር እንደሆነ ይናገራል (ምሳ.16፡31፤20፡29)። ስለዚህ በዕድሜ ያረጁ አባቶችና እናቶች ክብር ሊያገኙ ይገባቸዋል። ምክንያቱም ረጅም ዕድሜን የሚሰጠው እግዚአብሔር በመሆኑ ነው። ስለሆነም አገልጋዮች በዕድሜ ትላልቅ የሆኑ ሰዎችን እንደ አባትና እንደ እናት ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

አገልጋዮች ወጣት ከሆኑ ሰዎች ጋር ደግሞ ንጽሕና ያለው ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። ብዙ ጊዜ የቅድስና ጉድለት የሚመጣው አገልጋዮች ወጣት ከሆኑ ሰዎች ጋር በሚኖራቸው ቅድስና የሌለበት ግንኙነት ነው። ስለዚህ አገልጋዮች ወጣቶችን እንደ ወንድሞችና እህቶች በመቁጠር ተገቢና ወሰኑን የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ አለባቸው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸውም ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ማድረግም ይገባቸዋል። በተለያዩ ምክንያቶች የኑሮ ወይም የተለያየ ችግሮች ያለባቸው ምዕመናን መረሳት የለባቸውም። አገልጋዮች ቤተሰባዊ ትስስር እንዲኖር በማድረግ ምዕመናን እርስ በርሳቸው እንዲረዳዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እና በዚህ ሁኔታ ለመርዳት ከአቅም በላይ የሆኑባቸውን ሰዎች ደግሞ ቤተክርስቲያን እንድትረዳቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ሐብታም የሆኑትን ሰዎች ደግሞ ከሌሎች ይልቅ ሥፍራ መስጠትና የተለየ ክብር መስጠት አይገባም። ባለጠግነት መልካም ነው፤ ሆኖም ባለጠጎች ከእግዚአብሔር ይልቅ በሀብታቸው እንዳይታመኑ ማስተማር አስፈላጊ ነው። አገልጋዮች ሀብታሞች ካላቸው ሀብት ለሌሎች እንዲሁም ለቤተክርስቲያን መስጠትን እንዲለማመዱ መምከር አለባቸው (1ጢሞ.6፡17-19)። አገልጋዮች የባለጠጎችን ሀብት ለራሳቸው ለማግኘት ብለው ከእነርሱ ጋር ጽድቅ የሌለበት ግንኙነት ማድረግ ከቶ አይገባቸውም። በዚህ ዘመን ብዙ አገልጋዮች ሀብት ያላቸውን አማኝ ነጋዴዎችን በተለይ ብዙ ትምህርት የሌላቸውን እንደሚሹ ይስተዋላል። ይህም በእግዚአብሔር ስም እየሄዱ ለራሳቸው ምጽዋት ለመሰብሰብ ነው። አገልጋዮች ራሳቸውን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማስገባታቸው አገልግሎታቸውንና ራሳቸውን ማዋረዳቸው እንደሆነ መገመት አያዳግትም።

አገልጋዮች በቤተክርስቲያን ከሚያገለግሉ ሌሎች አገልጋዮች እና የቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር ተገቢ የሆነ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባቸዋል። አገልጋዮችን እንደ አብረው ሠራተኞች(የሥራ ባልደረባ) ማየትና የእነርሱንም ጸጋና አገልግሎት መባረክ እንዲሁም መደገፍ አስፈላጊ ነው። ሌሎች አገልጋዮችን "ለምን ከእኔ ተሻሉ?" በሚል ዕመንፈስ የእነርሱን ማንነት መንካት፣ አገልግሎታቸውን መተቸትና ማንቋሸሽ የራስን ትክክለኛ ማንነት (የእግዚአብሔር አገልጋዮች አለመሆናቸውን) ለሰዎች ማጋለጥ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። አገልጋዮች ስለሌሎች አገልጋዮች መጥፎነት ሲያወሩ ራሳቸው መጥፎዎች እንደሆኑ መስበካቸው እንደሆነ ሊያስተውሉ ይገባቸዋል። እነርሱም ስለሌሎች በሚናገሩት ነገር ይመዘናሉ። ስለዚህ አገልጋዮች እርስ በርስ መደጋገፍ እንጂ እርስ በርስ መነቃቀፍና ለሹመት ትግል ማድረግ አይጠበቅባቸውም።

በአንዳንድ ቤተክርስቲያናት አንድ ላይ የሚያገለግሉ አገልጋዮች እርስ በርሳቸው አብረው መጸለይና መደጋገፍ ቀርቶ ሰላምታም ሰው ሲኖር ብቻ የሚጠያየቁ አሉ። የቤተክርስቲያን ምዕመናን እንኳ ሰምተው ለማስታረቅ ሲሞክሩ ለመታረቅ እምቢ ብለው ግን በዚያው ቤተክርስቲያን የሚያገለግሉ አገልጋዮች መኖራቸው ያሳዝናል። ለእነዚህ አገልጋዮች የአገልግሎት ምንነት ቀርቶ የክርስትና እምነት ትርጉምም የገባቸው አይመስለኝም። ሌላው ቀርቶ "የምናገለግላቸው ሰዎች ምን ይሉናል?" በማለት እንኳ በመካከላቸው ያለውን ችግር መፍታት ነበረባቸው። አገልጋዮች እርስ በርሳቸው መልካም ግንኙነት ሳይኖራቸው እግዚአብሔር በዚያ ስፍራ መልካም ሥራውን እንደልቡ ያደርጋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል። የእግዚአብሔር ኃይል በሙላት እንዲሠራ መስማማትና አብሮ የእርሱን ፊት መፈለግ አስፈላጊ ነው። አገልጋዮች እርስ በርሳቸው በመልካም ግንኙነት በመኖር ለሚያገለግሉት ምዕመናን ተስማምተው መኖርን በምሳሌነት ማስተማር ይጠበቅባቸዋል።

በተለይ በአሁኑ ወቅት በአገልጋዮች መካከል የግንኙነት ችግር እየፈጠረ ያለው ነገር መጋቢ ሆኖ ለመሾም ሁሉም እሽቅድምድም ማድረጉ ነው። አገልጋዮችን በተጠሩበት የአገልግሎት መስክ ከማሰማራትና ሁሉም የአገልግሎት ስጦታዎች እኩል እንደሆኑ ከማሰብ ይልቅ የቤተክርስቲያን የመጋቢነት አገልግሎትን እንደ ትልቅ የአገልግሎት ደረጃ መመልከት የችግሩ መንስኤ ነው። በእንድ በኩል ቤተክርስቲያን አገልጋዮችን መጋቢ የምታደርገው አገልግሎቱን በማየት ለመልካም አገልግሎቱ እውቅና ለመስጠት ወይም እንደ ደረጃ ዕድገት ስለሆነ ሁሉም ይህችን ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ይህም ቢሆን እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ቦታ ሆኖ በታማኝነት እግዚአብሔርን በማገልገል የአገልግሎት የደረጃ ዕድገት ላገኙትም አገልጋዮች እግዚአብሔርን ማመስገን እጅግ የከበረ ነገር ነው።

ከቤተክርስቲያናቸው ውጭም ቢሆን አገልጋዮች በንጹህ ልብ እግዚአብሔርን ከሚያመልኩና በጽድቅ ከሚኖሩ አገልጋዮችና ምዕመናን ጋር ፍቅርና ሰላም ያለበትን ጤናማ ግንኙነት ማድረግ ይችላሉ። ከማንኛውም ቤተእምነት ቢሆኑ ጌታን በሕይወታቸው ከሚከተሉ

እውነተኛ የክርስቶስ ተከታዮች ጋር መልካም ግንኙነት ማድረግ ይቻላል። ይህ አሳብ እንዲህ ዓይነት ሕይወት ከሌላቸው ሰዎች ጋር ደግሞ የጠበቀ ግንኙነት ማድረግ እንደሚገባቸው አይገፋፋም።

አንዳንድ አገልጋዮች ራሳቸውን ከሰው በላይ ልዩ እንደሆኑ ስለሚቆጥሩ ምዕመናን ወደ እነርሱ ቀርበው በየጊዜው የሚያጋጥማቸውን ችግሮች ማወያየት አይችሉም። ምዕመናኑ ወደ እነርሱ መቅረብ አይፈልጉም፣ አገልጋዮቹም እንዲህ ያሉትን ምዕመናን አይቀርቡም። የምዕመንን ችግር አውቀው በሚገባ ለማገልገል አገልጋዮች ራሳቸውን ከሚያገለግሉአቸው ምዕመናን ጋር ማመሳሰል ይኖርባቸዋል። ምዕመናን "የእኛ ሰው ነው" ወይም "እኛን ይመስላል" ማለት አለባቸው። እንዲህ ከሆነ ከምዕመናን ጋር መልካም ግንኙነት ኖሮአቸው በተገቢው መንገድ ማገልገል ይችላሉ።

4. **ለራስ ጤንነት መጠንቀቅ** (1ጢሞ.5:23)

ሰውነታችን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ስለሆነ አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ተገቢ ነው። ሰውነታችን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው (1ቆሮ.6:19)። ስለሆነም ሰውነትን ከሚጎዳ ከማንኛውም መጥፎ ባህርይ መጠበቅ ይገባል። ይህ ሰውነትን ሊጎዳ ከሚችል ነገር ለምሳሌ ከክፉ አሳብና ምኞት እንዲሁም ድርጊት መራቅን ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ ከአጉል ልማድ ውጭም በሽታ ሲይዝ አስፈላጊውን የሕክምና እንክብካቤ ማግኘትን ያመለክታል። አገልጋዮች ሰውነታቸው ሲታመም እግዚአብሔርን እንደሚገባ ማገልገል ይሳናቸዋል። ስለዚህ ተመጣጣኝ ምግብ በመመገብ እንዲሁም መድኃኒት በመውሰድ ራሳቸውን ከበሽታ መከላከል አለባቸው።

5. **ከገንዘብ ፍቅር መሸሽ** (1ጢሞ.6:11)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ ገንዘብ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ እንደ አምላክ ተቆጥሮ ከእግዚአብሔር ጋር እንደሚፎካከር ጠቅሷል (ማቴ.6:24)። ክርስቲያን ወይም አማኝ መሆን የገንዘብ ማግኛ መንገድ አይደለም። እግዚአብሔርን መምሰል ገንዘብ የማትረፊያ መስመር አይደለም። ሰዎች አማኝ ወይም አገልጋይ የሚሆኑት በዚያ ምክንያት ገንዘብ ለማግኘት ከሆነ የልብ መሻታቸው ከትክክለኛ የእግዚአብሔር አሳብ ለይቶአቸዋል። የእነርሱ እምነትም ሆነ አገልግሎት ከንቱና ስህተት ነው። አገልግሎትን ወይም እምነታቸውን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ሀብት ማካማቸት እንደሆነና እግዚአብሔርን መከተል ወይም ማገልገል ሀብታም ያደርጋል ማለት የጌታ ኢየሱስ እውነተኛ ወንጌል አይደለም። አማኞች (ምናልባትም ጥቂት አገልጋዮች) ሀብታም ሊሆኑ ይችላሉ። ነገር ግን የእነርሱ ሀብታም መሆን የእነርሱን የጽድቅ ሕይወት ወይም የአገልግሎት ታላቅነት አያመለክትም።

አገልጋዮች እግዚአብሔር በሰጣቸው ጥቂት ነገር ደስ እያላቸው ከገንዘብ ስግብግብነት ራሳቸውን መጠበቅ ይገባቸዋል። ለአገልጋዮች

ገንዘብ አስፈላጊ እንደሆነ የታወቀ ነው። እግዚአብሔር አስፈላጊ ሲሆን እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን እየለመኑ ባላቸው ነገር እግዚአብሔርን እየመሰገኑ መኖርን መለማመድ ትልቅ ጸጋ ነው። የአገልጋዮች ልብ በገንዘብ ፍቅር ከተነደፈ ትኩረታቸው ከአገልግሎት ይልቅ ገንዘብን በማሳደድ ላይ ይሆናል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች ሳያውቁ በገንዘብ ፍቅር ይነደፋሉ። አንዳንድ አገልጋዮች ሁልጊዜ እየተጋበዙ በተለያዩ ቦታዎች ያገለግላሉ። ይህንንም የሚያደርጉት በአገልግሎቱ የሚያገኙትን የትራንስፖርት ወይም የአገልግሎት ስጦታ ለመሰብሰብ ነው። በዚያ በሚያገኙት ነገር የቤታቸውን አንዳንድ ቀዳዳዎች ለመሸፈን ያስባሉ። ከጊዜ በኋላ አገልግሎቱ ይረሳና ገንዘቡ ስፍራውን ይይዛል። ከዚያም ደሃ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ሀብት አላቸው ወደሚባሉ ቤተክርስቲያናት ሄደው ማገልገልን ይመርጣሉ። ይህን አሳብ ያነሳነው ከአገልግሎት በኋላ ለትራንስፖርት ተብሎ የሚሰጠውን ገንዘብ መቀበልም ሆነ አለመቀበል ትክክል መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመናገር ሳይሆን ከገንዘብ ጋር የተያያዘውን የአንዳንድ አገልጋዮችን አገልጋዮችን የልብ ሁኔታ በማሳየት እያንዳንዳችን ከገንዘብ ፍቅር እንድንጠነቀቅ ለማስገንዘብ ነው።

*ጥላሁን ለአገልግሎት ወደተለያዩ ቦታዎች ሄዶ ሲያገለግል የትራንስፖርት ገንዘብ ተብሎ ሲሰጠው የቤተክርስቲያን መባ ውስጥ ጨምሩልኝ ይላል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በተለይ አገልግሎቱ ከቤቱ እሩቅ ቦታ ከሆነ ይወስዳል፣ ቅርብ ቦታም ሆኖ የሚወስድበት ሁኔታ አለ። አንዳንድ ጊዜ ዛሬስ ስንት ብር ይሰጡኝ ይሆን? የሚል አሳብ በውስጡ ሲሰማው የትራንስፖርቱን ገንዘብ አይቀበልም። ልቡ ግን ስለገንዘብ የማያስብ ከሆነ ይቀበላል።* በዚህ ሁኔታ አገልጋዮች ልባቸውን ስለሚያውቁ አሳባቸውን መፈተሽና ተገቢ የሆነውን ነገር ማድረግ ይችላሉ።

ገንዘብ በራሱ መልካም ወይም ክፉ አይደለም። ክፉ የሚያደርገው አገልጋይ ለገንዘብ ያለው አመለካከትና አያያዝ ነው። ገንዘብ ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል። ወንጌልን ያለገንዘብ ማገልገል አይቻልም። ለጌታ ኢየሱስም አገልግሎት የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉ ወገኖች ነበሩ (ሉቃ8:3)።

ነገር ግን ገንዘብ ቅድሚያ ከተሰጠውና ፍቅሩ ካየለ ክፉ ይሆናል። የገንዘብ ፍቅር የማይጠገብ ረሃብና የማይረካ ጥም ነው። አንድ ሰው በገንዘብ ፍቅር ከተያዘ ብዙ ገንዘብ ቢያከማችም "በቃኝ" የሚልበት ደረጃ ላይ አይደርስም። የገንዘብ ፍቅር ጨዋማ ውኃ እንደመጠጣት እንደሆነ ይነገራል። ጨዋማ ውኃ በምንም መልኩ የጠጪውን ጥም ሊያረካ አይችልም። እንዲ መጠጣት ከጀመረ አሁንም አሁንም እንዲጠጣ ይገፋፋዋል። ምክንያቱም ጥሙን ማርካት አይችልም። ይህ ሰው መርካት የሚችለው ጨው የሌለበትን ውኃ ከጠጣ ብቻ ነው። ስለዚህ የገንዘብ ፍቅር እርካታ የለውም።

6. **ከክፉ ምኞት መሸሽ** (2ጢሞ.2:21)

እግዚአብሔር ያልነጹትን ሰዎች ማንጻት ቢችልም ለአገልግሎቱ የሚጠቀምባቸው አገልጋዮች ግን ከክፉ ምኞት የራቁ እንዲሆኑ

ይፈልጋል። ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብቁ የሚሆኑ ሰዎች ራሳቸውን በቅድስና የሚጠብቁ ናቸው። በተለይ ወጣት የሆኑ አገልጋዮች ወጣትን ከሚፈታተኑ ክፉ የወጣትነት ምኞቶች መሸሽ ይጠበቅባቸዋል። የወጣትነት ጊዜ ክፉ ምኞቶች ብዙ ቢሆኑም ጥቂቶቹ የወሲብ ምኞት፣ ያለመታዘዝ መንፈስ፣ በራስ የስኬት ምኞት መጋለብ፣ ከሌሎች ሰዎች ጋር ተባብሮ ለመሥራት ፈቃደኛ አለመሆን እና የመሳሰሉት ናቸው። አገልጋይ ከእነዚህና እነዚህን ከሚመስሉ ነገሮች መሸሽ አለበት። መሸሽ የሚለው አሳብ ከኋላ ለመጉዳት ከሚያሳድድ ነገር ለማምለጥ ወደፊት መሮጥ ማለት ነው። ለመጉዳት ለሚያሳድድ ነገር ጀርባን መስጠት ነው።

እንግዲህ ሰዎች አካልን ሊጎዳ ከሚችል ጠላት ለማምለጥ እንደሚሮጡ ሁሉ እንዲሁ አገልጋይም ነፍስንና መንፈስን ከሚጎዳ ከማንኛውም ጎጂ ነገር መሸሽ አለበት። ኃጢአትን ለማሸነፍ ዓይነተኛው መንገድ መሸሽ ነው። ከኃጢአት ጋር በመደራደር ማሸነፍ አይቻልም። አገልጋይ እንደ ዮሴፍ ጀርባውን ለኃጢአት በመስጠት መሸሽ ይገባዋል። የእግዚአብሔር ቃል አገልጋዮች (ምዕመናንም ጭምር) ከዝሙት (1ቆሮ.6:18)፣ ከጣዖት አምልኮ (1ቆሮ.10:14) እና ከገንዘብ ፍቅር (1ጢሞ.6:11) እንዲሸሹ ያስጠነቅቃል።

አገልጋይ ከላይ ከተጠቀሱ ነገሮች በሚሸሽበት ጊዜ ከአንድ ጎጂ ነገር ወደሚጠቅም ነገር ይሮጣል። ከአንዱ ለማምለጥ ሌላውን ደግሞ ለመያዝ ነው- ሩጫው። አገልጋይ ሊከተላቸው የሚገባው መልካም ነገሮች ደግሞ አሉ። መከተል የመሸሽ ተቃራኒ ነው። መሸሽ ላለመያዝ ሲሆን መከተል ደግሞ ለመጨበጥ ነው። ስለዚህ አገልጋይ ከኃጢአት በመሸሽ የጽድቅን ሕይወት ለመያዝ ዕለት ዕለት ወደፊት ይሮጣል። ለእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት የተዋጣለት አገልጋይ መልካም ያልሆነውን ነገር በመተው የእግዚአብሔርን አሳብ ለማወቅና ለማድረግ ወደፊት የሚገሰግስ ነው። አሮጌውን ነገር ጥሎ በክርስቶስ ያለውን አዲስና የተቀደሰ አሳብ ለመያዝ መዘርጋት ለአገልግሎት ወሳኝ ነው። በአንዳንድ ሁኔታ ውስጥ ሲታይ በዘመናችን አንዳንድ አገልጋዮች መሸሽ ወደሚገባቸው ነገር ይሮጣሉ፤ የተጠሩበትን ዓላማ ሊያደናቅፍ ለሚችል ነገር ራሳቸውን እየሰጡ ይገኛሉ።

7. **በተረዳበትና በተማረበት ጸንቶ መኖር** (2ጢሞ.3:14)

አገልጋይ ወደ አገልግሎት ከመምጣቱ በፊትና በኋላ ከታመኑ የእምነት አባቶች የተማረውን ትክክለኛ የእምነት ትምህርት በጽናት መያዝና በዚያም ትምህርት መኖር አለበት። አገልጋይ ከእግዚአብሔር ቃልና ከቤተክርስቲያን አባቶች የተረዳውን መልካሙን ትምህርት እንዲሁም በሕይወታቸው ያየውን መልካም ምሳሌነት መከተል አለበት። አገልጋይ በዘመናዊነት መንፈስ ተሞልቶ በፊት የተማረውን እውነት መጣል የለበትም። እውነትና መልካም ሕይወት ሁልጊዜ አይለወጡም።

አገልጋይ እውነት ከሚመስል ግን ሐሰት ከሆነ ትምህርት በመራቅ ከታመኑ ምንጮች ያገኘውን እውነት አጥብቆ በመያዝ ከኖረበት የተጠራበትን ተልዕኮ ከግብ ማድረስ ይችላል። በአሁኑ ጊዜ አንድ

አገልጋይ በመንፈሳዊ አመለካከቱ ዘመናዊውን የማይቀበል ከሆነ እንደ ኃላ ቀር ይቆጠራል። በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን የሚተላለፈውን መንፈሳዊ ትምህርትና ልምምድ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነውን ነገር እንዲቀበል ግፊቱ ኃይለኛ ነው። የመንፈሳዊ ዕውቀትና ልምምድ ማደግ መልካም ነው። ግን አዲሱ ትምህርትና ልምምድ ቀድሞ የተማርነውንና የተረዳነውን እውነት የሚያፈርስ ከሆነ ልናስተናግደው አይገባንም። ዘመናዊ የሆኑትን መንፈሳዊ ትምህርቶችንና ልምምዶችን እየተከተልን ምዕመኖቻችን እንዲያውቁና እንዲጠነቀቁ ማስተማርም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ እውነትን ለሰዎች በማስተማር እውነት ያልሆነውን ነገር እንዲያውቁ ማድረግ ነው። ምክንያቱም ሰዎችን አርነት የሚያወጣው እውነትን መረዳት ነው እንጂ ስህተት የሆነውን ነገር ማወቅ አይደለም (ዮሐ.8፡32)።

### 8. **በጊዜውም አለጊዜውም ጸንቶ ማገልገል** (2ጢሞ.4፡2፣5)

በጥሪ ለወንጌል አገልግሎት መውጣት መስዋዕትነት ያስከፍላል። አገልጋይ ሁኔታዎች ምቹ ቢሆኑም ባይሆኑም አገልግሎቱን መቀጠል ይጠበቅበታል። ሁኔታዎች በተመቻቹበት ጊዜ (ለምሳሌ ከውስጥና ከውጭ ፈተናና ስደት በሌለበት ጊዜ) አገልጋይ በተገኘው መልካም አጋጣሚ በመዘናጋት አገልግሎቱን ችላ ማለት እንደሌለበት የእግዚአብሔር ቃል ያሳስባል። ምቹ ጊዜ ለወንጌል አገልግሎት ጥሩ እንደሆነ ሁሉ እንቅፋትም ሊሆን ይችላል። አገልጋይ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ትኩረቱ ከወንጌል አገልግሎት የዓለምና የግል ሥጋዊ ነገሮችን ወደ ማሳደድ በመመለስ ለወንጌል አገልግሎት የነበረው ቅንዓት ሊቀንስ ይችላል።

አለጊዜውም የሚለው አሳብ ደግሞ ሁኔታዎች ለወንጌል አገልግሎት የማይመቹበት የመከራና የስደት ጊዜ ነው። በዚህ ሁኔታ የወንጌል አገልጋይ መሆን ዋጋ ያስከፍላል። አገልጋይ በሕይወቱ በመውረድ ማገልገል የግድ ይሆንበታል። አንዳንድ አገልጋዮች ስደት ሲመጣ አገልግሎታቸውን ትተው እንደምዕመን ብቻ ለመኖር ይወስናሉ፣ አንዳንዶች ደግሞ ስደቱን በመፍራት ጌታን ትተው ወደ ዓለም ይገባሉ። መከራና ስደት ሲመጣ አንድ ቀን የሚያልፍና መልካም ዘመን እንደሚመጣ አይታሰባቸውም። በስደትና በመከራ ውስጥ ሆኖ "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው፤ በዚህ አስቸጋሪ ወቅት የሚያሳልፈኝን ጸጋ ይሰጠኛል፤ ብሞትም ብኖርም ለጌታ ነው" ብሎ መወሰን እና ማመን ቀላል አይደለም። ጥቂቶች ግን እንዲህ ዓይነት ቆራጥ ውሳኔ በማድረግ በማይመች ሁኔታ ውስጥ ሆነው ጌታን ያገለግላሉ። እውነትም የጌታን ሥራ ለመሥራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ራሳቸውን ለሰጡ አገልጋዮች ጸጋው ይበዛላቸዋል።

መከራና ስደት አንዳንድ አገልጋዮችን ከአገልግሎት ቢመልሳቸውም አንዳንዶችን ግን የበለጠ በማጥራት በአገልግሎት እንዲጸኑ አድርጓቸዋል። ከመከራና ስደት ይልቅ አገልጋዮችን ለዘብተኛ የሚያደርጋቸው ምቾት ነው። አንዳንድ የዘመኑ አገልጋዮች ልባቸው የተሰለበ ወታደሮች ናቸው። በመድረክ ላይ ከመሬሙኝ ያለፈ ለወንጌል መስዋዕትነት ለመክፈል

ፈቃደኞች አይደሉም። ምቹ ጊዜ ሲመጣ የአገልጋዮች አጀንዳ ከወንጌል ወደ ድርጅታዊ፣የቡድን ወይም ግላዊ አጀንዳዎች ይለወጣል። አገልጋዮች እንዴት ወንጌል ይስፋፋል? ምዕመናን እንዴት የተሻለ መንፈሳዊ አገልግሎት ያገኛሉ? የሚሉትን ነገሮች ተወት በማድረግ እንዴት ትምህርት ቤት ገብቼ ራሴን ላሻሽል? እንዴት ባደርግ የደመወዝ ጭማሪ ማግኘት እችላለሁ? የቤተክርስቲያን መሪ እንዴት ልሁን? የሚሉ አጀንዳዎች ትኩረት እያገኙ ይመጣሉ። እነዚህ አጀንዳዎች በራሳቸው ክፉዎች ባይሆኑም የወንጌልን አጀንዳ ወደኋላ የሚያስቀሩ ከሆኑ ግን ወንጌልን ለማራመድ መሣሪያዎች ከመሆን ይልቅ ወንጌል እንዳይስፋፋ እንቅፋት ይሆናሉ።

ስለዚህ አገልጋይ ምንጊዜም(ማለትም ሁኔታዎች ሲመቹም ሆነ ሳይመቹ) ትኩረቱ በተጠራበት የወንጌል አገልግሎት ላይ መሆን ይኖርበታል። እንዲህም ሆኖ አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ በሚያገለግልበት ወቅት የተለያዩ ተግዳሮቶች ያጋጥሙታል። እነዚህ ተግዳሮቶችና መንስኤዎቻቸው ምን እንደሆኑ፣ እንዴትስ ማሸነፍ እንደሚቻል ማወቁ ጠቃሚ ነው።

እንግዲህ ለአገልግሎት ስኬት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ለአገልጋዩ የሚሰጠው የእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ሳይሆን አገልጋዩ ያለው ባህርያትና የሕይወት ዘይቤውም ጭምር ነው። አገልጋይ የሚኖረው የሕይወት ዘይቤ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተ ከሆነና በኑሮውም ሆነ ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት «ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር ምን ይላል?» በሚል መርሕ አሳብ ከሆነ ራሱን እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ማቅረብ ይችላል። የአገልጋይ ፍላጎት፣ አመለካከት፣ ዓላማና ግንኙነት የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከላዊ ያደረገ መሆን አለበት። እንዲህ ሲሆን ራሱንና ሌሎችን ሊጠቅም በሚችል ጎዳና ይሄዳል። እነዚህ መልካም ባሕርያት በአንድ ጊዜ ከሕይወት ጋር ተዋሕደው የማይጠፉ ነገሮች ባለመሆናቸው ዘወትር እንክብካቤ ሊሰጣቸውና በጥንቃቄ ተከትትለው ሊያድጉና ሊጠበቁ ይገባቸዋል።

---

## ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔርን መስሎ መኖርን እንዴት ትረዳዋለህ?
2. በምታገለግልበት ቤተክርስቲያን ሰዎች በምን በምን ምሳሌ እንደሆንክላቸው ይመሰክራሉ?
3. ከመሪዎች፣ ከሌሎች አገልጋዮች እንዲሁም ከምዕመናን ጋር ያለህ ግንኙነት ምን ይመስላል? ለግንኙነትህ እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች ምንድናቸው? እንዴትስ ሊታስወግዳቸው ትችላለህ?
4. አገልጋይ ለገንዘብ ያለው ቅርበትና ርቀት (የገንዘብ ፍቅር መኖሩና አለመኖሩ) በምን ይለካል?
5. በአገልግሎትህ በጣም የምፈትንህ ነገር ምንድነው? እንዴትስ እየተከላከልክ ትገኛለህ?

## የአገልጋይ ተግዳሮቶችን ማወቅና በጸጋው መጋፈጥ

አንድ አገልጋይ የተጠራበትን ተልዕኮ ከግብ እንዳያደርስ ማለትም በአገልግሎቱ ስኬትን እንዳያገኝ ሊያደርጉ የሚችሉ የተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ተግዳሮቶች አሉ። አገልጋይ ከውጭም ሆነ ከሕይወቱ የሚመጡበትን ተግዳሮቶች ለይቶ በማወቅ የማያሸንፍበትንም ስልት መንደፍ ያስፈልገዋል።

በአንዳንድ ምዕመናን አመለካከት አገልጋይ ከችግር ነጻ የሆነ ሕይወት የሚኖርና ተግዳሮት ወይም ፈተና የማይገጥመው ሰው ሆኖ ይታሰባል። ይህ ትክክለኛ አመለካከት አይደለም። አገልጋይ እንደ ማንኛውም ሰው ወይም አማኝ የራሱ የሆነ ችግር ያለው ሰው ነው። እንዲያውም የአገልጋይ ችግርና ተግዳሮት አንድን አማኝ ከሚያጋጥመው ይልቃል። ምክንያቱም ኃላፊነት እየበዛ ሲሄድ በአገልጋይ ላይ የሚኖረው ጫና ከፍተኛ ነው።

አገልጋይ ምንም ያህል የእግዚአብሔር ኃይል የሚገለጥበት ቢሆንም ሰው መሆኑ መረሳት የለበትም። ሰው ከሆነ ደግሞ ብርቱና ደካማ ጎን አለው። ፍጹም አይደለም። አገልጋይ ሰው መሆኑ ሲረሳ እንደ እግዚአብሔር በመቁጠር ማምለክን ወይም የማይጠቅም ከሆነ እንደ ዕቃ በመቁጠር መጣልን ያስከትላል።

አገልጋይ እንደ ማንኛውም ሰው:-

- የተሻረ አዳማዊ ባህርይ አለው። ስለዚህ አንዳንድ ቀን የኃጢአት ባህርይ ብቅ ትላለች።
- ደካማና ጠንካራ ጎን አለው
- በራሱ ማድረግ የሚችለው ነገር እንዳለው ሁሉ ያለእግዚአብሔር ጸጋ ደግሞ ማድረግ የማይችላቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ሆኖም የተፈጥሮ ችሎታና ብቃትንም የሰጠው እግዚአብሔር መሆኑ መረሳት የለበትም።
- በእግዚአብሔር መርሕ የእግዚአብሔርን ሥራ ይሠራል።

አገልጋይ እንደ ሰው አማኝ መሆኑን ሲዘነጋ በራሱ ሕይወትና አገልግሎት ችግር ይፈጠራል። ምናልባት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት አገልጋይ ስለሆነ ከአማኝ በላይ እንደሆነ ሊያስብና ተራው አማኝ የሚያደርጋቸውን መንፈሳዊ ልምምዶች ሊንቅ ይችላል። ይህ ብዙ ምዕራፍ የማያስኬድ የውድቀት እርምጃ ነው። በዚህ ፈተና ላለመውደቅ አገልጋይ ሰው እንደሆነ ማወቅና ለሚያገለግላቸውም ምዕመናን ማሳወቅ ይኖርበታል። ራሱን ከሌሎች በላይ አድርጎ ካሳየ ምናልባት ሲሳሳት ሰዎች ከመጠን በላይ ሊከንኑት ይችላሉ። እንዲሁም በእርሱ ሊሰናከሉበትና ተስፋ ሊቆርጡ ይችላሉ። ምክንያቱም እርሱ እንደ ፍጹም ሰው ስለሚታይ የእርሱ ውድቀት ሌሎችን ክፉኛ ይጎዳል።

በአገልግሎት ውስጥ ከሚገጥሙ ተግዳሮቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም:-

### ለራሱና ለቤተሰቡ ጊዜ ማጣት

አገልጋይ እንደ ባለትዳርና ወላጅ በሚለው ርዕስ ሥር አገልጋይ በአገልግሎትና በቤተሰብ መካከል የሚወጠር ሰው እንደሆነ ተመልክተናል። አገልጋይ ራሱ የእግዚአብሔር ነገር መቅደም አለበት በማለት እንዲሁም ቤተክርስቲያን አገልጋይ ቅድሚያን ለአገልግሎቱ እንዲሰጥ ስለምታደርግ የወንጌል አገልጋይ መልካም ቤተሰብ ሲኖረው አይታይም። ለእግዚአብሔር አገልግሎት ብዙ ጊዜ መስጠት መልካም ሆኖ እያለ አገልጋይ በአገልግሎት በሚወጠርበት ወቅት የእርሱን ቤተሰብ ዞር ብሎ የሚያይ ከቤተክርስቲያን መጥፋቱ ሌለው ተግዳሮት ነው። አገልጋይ በወንጌል አገልግሎት ሲጠመድ የቤተሰቡን ሁኔታ የሚያይ አካል ቢኖር ችግሩን ለመቅረፍ ይረዳ ነበር። ሆኖም የአገልጋይን አገልግሎት እንጂ ለእርሱና ለቤተሰቡ ሊደረግ የሚገባውን እንክብካቤ የሚመለከት ሰው እምብዛም አይገኝም። አገልጋይን እንደ ማንኛውም ተቀጣሪ ሠራተኛ በማየት ሥራውን በተሳካ ሁኔታ መሥራትና ቤተሰቡንም በተገቢው መንገድ መምራት ኃላፊነቱ እንደሆነ ይታሰባል። ይህ አሳብ በአንድ በኩል ትክክል ነው። ነገር ግን አገልጋይ የሚያገለግለው በቀን ስምንት ሰዓት ብቻ እንዳልሆነ ማወቁ ተገቢ ነው። አገልጋይ ከሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ለአገልግሎት ተፈልጎ «ከሥራ ሰዓት ውጭ መምጣት አልችልም» ወይም «ከልጆቼ ጋር ነኝና አልመጣም» ማለት የሚችልበት ሁኔታ ያለ አይመስለኝም። እንዲህስ ማለት ይጠበቅበታል ወይ? የሚለው ደግሞ ሌላ ጥያቄ ይሆናል።

ከዚህ አንጻር አገልጋይ ቅድሚያ ለማን መስጠት እንዳለበት በሚገባ ሊያውቅ ይገባል። በአገልጋይም ሆነ በማንኛውም አማኝ ሕይወት ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ነው። ይህ እግዚአብሔርን ከማምለክና ከማገልገል አኳያ ነው። ይህ መልካም የሚሆነው ሌላውን የሕይወት ገጽታ በማይጎዳ ሁኔታ ሲከናወን ነው። እግዚአብሔርን በማገልገል ብዙ ጊዜ በመስጠት ቤተሰብ ከፈረሰ እግዚአብሔር አይከብርበትም። ስለዚህ በቤተሰብና በአገልግሎት መካከል ሚዛንን መጠበቅ ተገቢ ነው። አንዱ ሌላውን ማፍረስ የለበትም። የአገልግሎት ዘላቂ ስኬት የሚገኘው በሁለቱ መካከል ሚዛኑን በጠበቀ አገልግሎት ውስጥ ነው። አስፈላጊ ሆኖ አገልጋይ ቤተሰቡን ትቶ ለአገልግሎት በሚሮጥበት ጊዜ ደግሞ ቤተክርስቲያን የአገልጋይን ቤተሰብ መንከባከብ ይገባታል።

### የአገልግሎት አለመሳካት

አገልጋይ መሆን ልዩ ጸጋን ይጠይቃል። አገልጋይ በአገልግሎቱ ፍሬያማ ለመሆን አማኝ ከሚያከመው በላይ መድከም እና የእግዚአብሔርን መለኮታዊ እገዛ ማግኘት አለበት። አገልጋይ ከእርሱ የሚጠበቀበትን ማንኛውንም ጥረት ካደረገ ስኬት ያገኛል የሚል አመለካከት ቢኖርም የስኬት መለኪያ ምን መሆን እንዳለበት ግን ሁሉንም የሚያስማማ መመዘኛ ላይኖር ይችላል። በስኬት መመዘኛ ላይ ሁሉም ቢስማማበትም የሁሉም ጸጋና ስጦታ የተለያየ በመሆኑ ሁሉም በአንድ ዓይነት መሥፈርት ሊዳኝ አይገባም ማለት ይቻላል። አንድ አገልጋይ አልተሳካለትም የሚባለው ምን ሲሆን ነው? ይህ ከቦታ ቦታ ሊለያይ ይችላል። ስኬት የለውም ተብሎ ከአገልግሎት የሚሰናበትን አገልጋይ ብንመለከት ስለክርስቶስ መስክሮ

አዳዲስ ነፍሳትን ወደ ቤተክርስቲያን የማያመጣ፣ ምዕመናንን በማስተማር ማሳደግ የማይችል፣ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ተስማምቶ በሰላም ማገልገል የማይችል፣ ከአገልግሎት ይልቅ የራሱን ጥቅማ ጥቅሞችን የሚያሳደድ እና የመሳሰሉት የሚታዩበት ሰው ነው።

አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ ጥረትም እያደረገ ቤተክርስቲያን ከምትጠብቀው አኳያ ስኬት ላያገኝ ይችላል። አንዳንድ አገልጋዮች የወንጌላዊነት ስጦታ ኖሮአቸው አንድ ወንጌል ያልደረሰበት ቦታ ሄደው ወንጌልን ይሰብካሉ። በሁሉም አኳያ የሚገባቸውን ነገሮች አድርገው ለዓመታት እዚያ ቦታ ወንጌል ሰብከው ጥቂት ሰዎችን ብቻ ወደ ጌታ ሊያመጡ ይችላሉ። እነርሱ የከፈሉት ዋጋና የቆዩበት ጊዜ ቤተክርስቲያን በእነርሱ ሥምሪት ላይ ካወጣችው ወጪዎች አንጻር ሲታይ የእነዚህ አገልጋዮች አገልግሎት ስኬታማ ነው ማለት ይቻላል? አንዳንዶች ደግሞ የነቢይነት ስጦታ ተሰጥቶአቸው ትክክለኛውን የእግዚአብሔር መልዕክት ለሕዝብ ሲናገሩ ተቀባይነት ሊያጡ እና ባስተላለፉት መልዕክትም ዋጋ ሊከፍሉ ይችላሉ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጠቀሰው ነቢዩ ኤርምያስ መልዕክት ከማምጣት አልፎ በዘመኑ ሰዎች ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር ሲመለሱ አላየም። የዚህ ነቢይ አገልግሎት ስኬታማ ነበር ማለት ይቻላል? ይህ ሁኔታ የአገልግሎት ስኬት የሚለካው በተጨባጭ በተሠሩ ሥራዎች ብቻ የማይሆንበት ሁኔታ መኖሩን ያሳያል። አገልጋይ እግዚአብሔር በሕይወቱ ለማከናወን ለፈለገው ነገር ራሱን በመስጠት እርሱ አድርግ ያለውን ነገር ሁሉ በማድረግ ካሳለፈ አገልግሎቱ ስኬታማ ነው ማለት ይቻላል። በምንም ይሁን በምን የአገልግሎት ስኬት ጣሪያው የጠራውን ጌታ ፈቃድ ሙሉ በሙሉ መፈጸም ነው። ስለዚህ አገልጋይ አገልግሎቱን ሲመዝን ሚዛናዊ መሥፈርት ሊኖረው እና የጌታን አሳብ መፈጸሙንና አለመፈጸሙን ማየት እንጂ ምን ሠራሁ? ምን ቀረ? በሚል ብቻ ላይ ትኩረት ማድረግ የለበትም።

## ከመሪዎች ጋር አለመስማማት

አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ ከቤተክርስቲያን መሪዎች ማለትም የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪ ከሆኑት ከሽማግሌዎች ጋር ስምምነት ላይኖረው ይችላል። መቼም ግጭት ወይም አለመስማማት የአንድ ወገን ብቻ ችግር ነው ማለት አይቻልም። አገልጋይ ሁልጊዜ መንፈሳዊ ነው ማለት እንደማይቻል ሁሉ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎችም ሁሉ ጌታን ለማገልገል ራሳቸውን የሰጡ ናቸው ማለት አይቻልም።

በአብዛኛው አገልጋይ መስክሮ ወደ ጌታ ሰዎችን ያመጣል። ከዚያም በመንፈሳዊ ሕይወታቸውን ያሳድጋል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ እነዚያ አገልጋዩ መስክሮ አምጥቶ የድነት ትምህርት አስተምሮአቸው ያሳደጋቸው ሰዎች የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ይሆናሉ። የአገልጋዩ መንፈሳዊ ልጆች የነበሩ ሰዎች አሁን የመንፈሳዊ አባታቸው አስተዳዳሪዎች ሆኑ ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ አንዳንድ አገልጋዮች በጣም ይከፋቸዋል። በመንፈሳዊ ልጆቻቸው መመራትን አይፈልጉም። አዕምሮአቸው እነርሱን እንደ ቤተክርስቲያን መሪዎች ለመቀበል ይከብዳቸዋል።

እንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሲፈጠር ችግር የሚፈጥረው አገልጋዩ ብቻም ሳይሆን ሽማግሌዎችም ጭምር ናቸው። አገልጋዩን እንደ መንፈሳዊ አባታቸው ከማክበር እና አብረው ከማገልገል ይልቅ አገልጋዩን እንደ ተራ ሠራተኛ በመቁጠር "ብትፈልግ አገልግል ያለበለዚያ እናባርርሃለን" በማለት የማይገባቸውን ነገር ይናገራሉ። በሳምንት አንድ ቀን ተሰብስበው ውሳኔ በማስተላለፍ ሙሉጊዜውን ሰጥቶ ከሚያገለግለው አገልጋይ ይልቅ የቤተክርስቲያን ጉዳይ እንደሚገዳቸው ይናገራሉ። የቤተክርስቲያን ጠበቃም እንደሆኑ ራሳቸውን ይቆጥራሉ።

አገልጋይም ቢሆን የእርሱ መንፈሳዊ ልጆች አድገው ለቁም ነገር በመብቃታቸው ደስ ሊሰኝበት ይገባዋል እንጂ «እንዴት ትናንት መጥተው ሊመሩኝ ይችላሉ?» በማለት ማኩረፍ አይጠበቅበትም:: ጌታ አገልግሎት ሰዎች በመስማማትና በመደጋገፍ የሚሠሩት እንጂ የእሽቅድምድም ሥራ አይደለም:: መሪና ተመሪ የተባለው ለአሠራር እንዲያመች እንጂ በአገልግሎት ውስጥ አንዱ ከሌላው ይበልጣል ወይም አንዱ አዛዥ ሌላው ታዛዥ ነው ማለት አይደለም:: በአገልጋዮችና በቤተክርስቲያን መሪዎች መካከል የትብብር መንፈስ ሊዳብር ይገባል:: እያንዳንዱ በግሉ የሚፈልገው ነገር ካልኖረ በስተቀር በጌታ አገልግሎት ውስጥ ሰዎችን የሚያጋጭ ነገር አይኖርም:: ከአሠራር አንጻር ግን መሪ መሆን የሚችሉ በመጀመሪያ በሌሎች ሥር ሆኖ በታዛዥነት ማገልገልን የተለማመዱ ሰዎች ሊሆኑ ይገባል::

## የትኩረት ዒላማ መሆን

አገልጋይን የሚመለከቱ ሰዎች ብዙዎች ናቸው። በዓይነቁረኛ የሚከታተሉ ሰዎች አሉ። አንዳንዶች አገልጋይ ምንም ስህተት እንኳ ሳይፈጥር የፈጠራ ወሬ እያስወሩበት አገልግሎቱን ለማበላሸት ይፈልጋሉ። አገልጋይ ስህተት ከፈጸመ ወዲያውኑ ሁሉም ሰው ይሰማል። ምዕመን ኃጢአት ቢፈጽም ከቁምነገርም አይገባም። ነገር ግን አገልጋይ ትንሽ የተባለውንም ሲፈጽም እጅግ ከፋ ፍርድ ከቤተክርስቲያን ይጠብቃል። ስለዚህ አገልጋይ በሁሉም ሰዎች ፊት እንዴት መመላለስ እንዳለበት በጥንቃቄ ሊያጤነው ይገባል።

አገልጋይ የሰዎች ዒላማ ብቻም ሳይሆን የሰይጣንም የትኩረት ዒላማ ነው። ሰይጣን በቀላልና በከባድ፣ በግልጽና በስውር መንገድ አገልጋይን በኃጢአት ለመጣል ያለ የሌለ ጥበቡንና ኃይሉን ይጠቀማል። ምክንያቱም አገልጋይን ከጣለ የእርሱን ተከታዮች ለመጣል ሰፊ ዕድል ያገኛል። አንዳንዶች አገልጋይ በኃጢአት ሲወድቅ ሰምተው ብቻ ጌታን ይተዋሉ። ሌሎች ደግሞ ይሰናከላሉ፤ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ይደክማሉ። በዚህ ሁሉ ሰይጣን ያተርፋል። ስለዚህ በአገልጋይ ላይ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ይፈትነዋል።

ስለዚህ አገልጋይ የሰዎችና የጠላት የትኩረት ዒላማ መሆኑን በመገንዘብ አካሄዱን በማስተዋል ማድረግ ይኖርበታል:: ከሰዎች በሚያገኘው ሂስ ራሱን እያየና እያረመ ከትናንት ዛሬ ከዛሬ ደግሞ ነገ እየተሻለ የሚሄድ ሰው መሆን አለበት:: እንዲህ ሲሆን በሰዎች ፊት ሞገስን ያገኛል:: ጠላትም ለመክሰስና ለመኮነን ዕድሉ ይጠብበታል:: ሰይጣን የሚዘረጋውን ስውር

ወጥመድ ለማምለጥ ደግሞ በእግዚአብሔር ላይ የሚደገፍ ሕይወት አስፈላጊ ነው::

### የጸሎት ሕይወት መቀነስ

ጸሎት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ፍሬያማነት ከፍተኛ ድርሻ አለው:: የወንጌል አገልጋይ በትጋት የሚጸልይ እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ለእርሱና ለአገልግሎቱ እንዲጸልዩ የሚጠይቅ ሊሆን ይገባል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ጥሩ የጸሎት ሕይወት ነበረው፣ ሌሎች ሰዎችም ለአገልግሎት ስኬቱ እንዲጸልዩለት ይጠይቃቸው ነበር:: በአሁኑ ወቅት ሲታይ አንዳንድ አገልጋዮች የጸሎት ሕይወታቸው እየተዳከመ ይገኛል:: ለዚህም በዋነኛነት የሚጠቀሰው ምክንያት የሥራ ጫና መብዛት ነው:: ጸሎት ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ ኃይል የምንቀበልበት በመሆኑ በዚህ መድከማችን በአገልግሎታችን ስኬት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው:: ያለጸሎት አገልግሎታችን ቀስ በቀስ ሰዎችን የመለወጥ ኃይል እያጣ ይሄዳል:: ስለዚህ አገልጋይ ምንም አገልግሎት ቢበዛበትም በየዕለቱ የተወሰነ ሰዓት እንዲሁም በሳምንት የተወሰነ ቀን መድቦ ከእግዚአብሔር ጋር በግሉ የሚሆንበት ጊዜ ማዘጋጀት አማራጭ የለውም:: በግል ከእግዚአብሔር ጋር የምናሳልፈው ጊዜ የአገልግሎታችን ስኬት መሠረት ነው::

### ለእግዚአብሔር ቃል ዝቅተኛ ሥፍራ መስጠት

የወንጌል አገልጋዮች መልዕክት የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ነው:: ይህ ወቅት የመጨረሻው ዘመን በመሆኑ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ሰዎች ለጆሮዎቻቸው የሚጥማቸውን ነገር መስማት እንደሚፈልጉ ሁሉም የሚያውቀው ጉዳይ ነው:: ስለዚህ ጉዳይ ሐዋርያው ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሰዎች «ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለሆነ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ:: እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ» (2ጢሞ.4:3-4) በማለት ይናገራል:: ከምኞታቸው አንጻር መስማት የሚፈልጉትን ትምህርት ለመስማት ራሳቸውን ላዘጋጁ ምዕመናን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል መስበክ ወይም ማስተማር በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ሊያሳጣ ይችላል::

በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ አገልጋዮች የጌታን ቃል እንዳለ ከማስተማር ይልቅ ከምዕመናን ምኞት ጋር እየተነዱ እነርሱ የሚፈልጉትን መልዕክት እያሰሙአቸው ይገኛሉ:: እውነተኛውን የእግዚአብሔር ቃል ጊዜ እንዳለፈበት አሮጌ መጽሐፍ በመተው «በቅባት» ስም አዳዲስ መልዕክት ለሕዝቡ እያመጡ የቤተክርስቲያን ታዳሚዎችን እያጽናኑ ናቸው:: አገልጋይ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል ብሎ ብቻ ከመድረክ ከወረደ ሁለተኛ ወደዚያ ሥፍራ አይጋበዝም:: ምክንያቱም ሰዎች መስማት የሚፈልጉት ቃሉ እንዲህ ይላል የሚለውን ሳይሆን «የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይልሃል ወይም ይልሻል» የሚለውን መልዕክት ነው:: ሕዝቡን ለማስደሰትና የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመባል እግዚአብሔር መልዕክት ሳይሰጣቸው ሕዝቡን የሥነልቦና ስብከት የሚሰብኩና የምኞት መሳካት የፈጠራ ትንቢት በእግዚአብሔር ስም የሚናገሩ አገልጋዮች በብዛት

አፍርተናል:: ደሃው ለማግኘት ሀብት ያለው ደግሞ ለንብረቱ ዋስትና ለማግኘት ንግርትን («እንዲህ ይለሃል» የሚለውን ትንቢት) ይፈልጋሉ:: አንዳንድ አገልጋዮችም ሰዎችን በእግዚአብሔር ቃል አቅንቶ ከመመለስ ይልቅ በዚህ በተከፈተው አጋጣሚ በመጠቀም ንግድ እየሠሩ ይገኛሉ::

ቃሉን ችላ በማለት የሕዝብ ምኞት መጋቢ የሆኑ አገልጋዮች የእግዚአብሔርን ቃል ለማወቅ ከማጥናት ይልቅ የሕዝቡን ልብ ደስ ሊያሰኙና ሊያዝናኑ የሚችል ተራ ወሬ ይለቅማሉ:: ብዙ ያልተቀደሱ ስነጽሑፎችንም ያነባሉ:: ለስብከት ወይም ለትምህርት ሲቆሙም ሰዎችን የሚያስቁ ነገሮችን ወይም ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ፈጠራ በማውራት ሰዎችን እያስደነቁ በልብ ውስጥ ጠብ ብሎ መንፈሳዊ ሕይወትን የሚለውጥ ቃል ሳይናገሩ ከመድረክ ይወርዳሉ:: ምክንያቱም ራሳቸው ቃሉን አያጠኑትም፣ ማጥናትም አይፈልጉም:: የራሳቸውን ልምምድ ወይም ፈጠራዎችንና ተረቶችን ሲያወሩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ በእግዚአብሔር ስም በሚናገሩት መልዕክታቸው ያሳርጋሉ:: ሐሰት ቢናገሩም ማንም «ለምን እንዲህ ተናገርክ?» ብሎ ለመጠየቅ የሚደፍር መሪ የለም:: ይህ ለቤተክርስቲያንም ሆነ እውነተኛውን የጌታን ቃል ለማገልገል ትልቅ ተግዳሮት ነው:: ቤተክርስቲያን እውነተኛውን ቃል በስደት ሁሉ ውስጥ ይዛ እስከ ዛሬ ደርሳለች:: አሁን ግን የመጣው ተግዳሮት ከውስጥዋ የወጣ በመሆኑና መልዕክቱ ለጆሮ ስለሚጥም መቃወም አልቻለችም ወይም ስትቃወም ድምጽዋ አልተሰማም:: ለእግዚአብሔር ቃል ክብርን የማይሰጥ አገልግሎት ሁሉ በጌታ ፊት ከንቱ ነው:: ስለዚህ የአገልግሎታችን መልዕክትና ዳኛ ቃሉ እንዲሆን ራሳችንን መስጠት አለብን::

## በትሕትና የመታዘዝ መንፈስ መዳከም

ከዚህ በፊት አገልጋይ የክርስቶስ ሎሌ እንደሆነ ተመልክተናል:: የሎሌ ሕይወት ደግሞ በመታዘዝ የተሞላ ነው:: አገልጋይ ለክርስቶስና ለአካሉ መታዘዝ ይጠበቅበታል:: የአገልጋይ መለያው መታዘዙ ነው:: በአሁኑ ወቅት አንዳንድ አገልጋዮች የመታዘዝ ልብ የላቸውም:: ከመታዘዝ ይልቅ አዛዥ መሆንን ይመኛሉ:: አገልጋዮች እንደ ቃሉ ለክርስቶስና ለቤተክርስቲያን በመታዘዝ በሕይወታቸው ምሳሌነት ለምዕመናን ስለመታዘዝ ማስተማር ሲገባቸው ራሳቸው ባለመታዘዝ መከሰሳቸው በጣም ያሳዝናል:: አንዳንድ አገልጋዮች እንደ ቃሉ የሆነ መታዘዝ ከልባቸው ጠፍቶ ከመሪዎች ጋር ሲጋጩ፣ ቤተክርስቲያንን ሲገነጥሉና የራሳቸውን ቤተእምነት ሲከፍቱ ማየት የተመለደ እየሆነ ነው:: አገልጋዮች ምንም ቢሆን ለእግዚአብሔርና ለቤተክርስቲያን በመታዘዝ ትርፍ እንጂ ጉዳት እንደሌለ ማወቅ ይገባናል:: በትሕትና መታዘዝ ለጊዜው ሽንፈት ቢመስልም ወደ አገልግሎት ስኬት የሚያመራ ጎዳና ነው::

እንግዲህ ከአውዳችን አንጻር እነዚህንና የመሳሰሉትን ነጥቦች እንደ አገልግሎት ተግዳሮቶች ማስቀመጥ ይቻላል:: አገልጋይ እንደ ቃሉ በመኖርና በማገልገል በእግዚአብሔር ጸጋ እነዚህን እያሸነፈ የጠራውን ጌታ ሊያገለግል ይገባዋል:: አንድ አገልጋይ እነዚህን ተግዳሮቶች በማሸነፍና የጌታን አሳብ በማገልገል ቢያልፍ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያገኛል? እግዚአብሔር እርሱን በታማኝነት ላገለገሉ አገልጋዮቹ ምን ዓይነት ብድራት ይሰጣል? እግዚአብሔር ይህን ብድራት መቼ ነው የሚሰጠው? የሚቀጥለው ምዕራፍ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል::

## ጥያቄዎች

1. በአገልግሎት ላይ የገጠሙህ ተግዳሮቶች ምንድናቸው? እንዴት አስተናገድካቸው?
2. በእግዚአብሔርን የተጠራን ሰው ለምን ተግዳሮት ይገጥማል?
3. አገልጋይ በየጊዜው የሚገጥሙትን ተግዳሮቶች ለማሸነፍ ምን መሠረታዊ መመሪያዎችን መከተል አለበት ትላለህ?
4. ጌታ ኢየሱስ በአገልግሎት የምገጥሙንን ተግዳሮቶች እንዴት ማሸነፍ እንደምንችል ያስተማረን መንገድ አለን? ካለ ምንድነው?

## 14
## የአገልጋይን ብድራት ትኩር ብሎ መመልከት

የእግዚአብሔር ጥሪ ዘወትር ሁለት ነገሮችን ይይዛል። አንዱ ለጥሪው ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ዋጋ መክፈል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከጥሪው መሳካት ጋር የሚመጣው በረከት ተካፋይ መሆን ነው። እነዚህ ሁለቱ ነገሮች አይነጣጠሉም። እንኳን ለእግዚአብሔር ወንጌል አገልግሎት ተጠርቶ ይቅርና እግዚአብሔርን ለመከተል የወሰኑ ሰዎች እንኳ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠታቸው ዋጋ ይከፍላሉ። ጌታ ኢየሱስ እርሱን ሊከተሉት የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ እያንዳንዱ ራሱን በመካድና መስቀሉን በመሸከም እንዲከተለው መናገሩ እርሱን አምኖ በቃሉ መኖር ዋጋ እንደሚያስከፍል ማመልከቱ ነበር (ሉቃ9:23)።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት በሚጠራበት ጊዜ አስቀድሞ ለበረከት ማጨቱ አይደለም። እግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት በሚጠራበት ጊዜ በዚህ ዓለም የተመቻቸና የተደላደለ ኑሮ እንዲኖሩ ሳይሆን ዋጋ በመክፈል የእርሱን መንግሥት እንዲያስፋፉ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲጠራ ሰዎችን ከምቾት ቀጠናቸው ያወጣቸዋል። ሰዎች ተመችቶናል ብለው ተዝናንተው ከሚኖሩበት ኑሮ ላይ ነው የሚጠራቸው።

በእግዚአብሔር የተጠራ ሰው ለጥሪው ብሎ የሚተወው ነገር ይኖራል። አንድ ሰው የሚሠራው ሥራ ስኬታማ እንዲሆን አስቀድሞ ሥራው የሚያስከፍለውን ዋጋ በሚገባ መተመን አለበት። እግዚአብሔርን ለማገልገል ከመውጣት አስቀድሞ አንድ ሰው አገልግሎቱ የሚያስከፍለውን ዋጋ መተመን እንዳለበት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አስተምሯል (ሉቃ14:25-33)።

ለአገልግሎት ለመውጣት ዋጋ መተመን ማለት አገልግሎቱ ሊያስከፍል የሚችለውን መገመትና ማወቅ ማለት ነው። ለምሳሌ አገልጋይ በመሆን ብቻ ከዚህ ዓለም ማግኘት የሚችላቸውን ነገሮች ሳያገኝ መቅረትን በማወቅ ራስን መስጠት ነው። ሰዎች በራሳቸው ሊሆን ያለውን ነገር በተቻላቸው መጠን አውቀው ሲወስኑ እግዚአብሔር ደግሞ የሚበቃቸውን ጸጋ ይሰጣቸዋል።

የወንጌል አገልግሎት ዋጋ እንደሚያስከፍል የገባው ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈስ ልጁ ለሆነውና በወንጌል አገልግሎት ገና ጀማሪ ለሆነው ለጢሞቴዎስ "እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ አብረኸኝ መከራ ተቀበል" (2ጢሞ2:3) በማለት ጥሪ ያቀርብለታል። የወንጌል አገልግሎት መከራ ያለበት አገልግሎት ነው። ስለዚህ ዋጋ መተመንን ግድ ይላል።

ይህ ዋጋን መተመን የሚለው አሳብ ሰዎች ለአገልግሎት ከመውጣታቸው በፊት ለአገልግሎት ያነሳሳቸውን የልባቸውን ዓላማ በሚገባ እንዲፈትሹ ዕድል ይሰጣቸዋል። ሰዎች አገልጋይ የሚሆኑት እግዚአብሔር ጠርቶአቸው ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ስውር ዓላማዎች ነው። ስለዚህ በተመቻቸ ሁኔታ ውስጥ እንጂ ዋጋ በሚያስከፍል አውድ ውስጥ ሰዎች ሳይጠሩ ወደ አገልግሎት አይገቡም።

ኤልሳዕ ከሐብታም ቤተሰብ የነበረና ራሱም ሐብታም የሆነ ሰው ነበር። ኤልሳዕ የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣለት በአሥራ ሁለት ጥማድ በሬ ያርስ ነበር። እግዚአብሔር ሲጠራው ግን ሐብቱን ሁሉ ትቶ ወጣ (1ነገ19፡19-21)። በምድራዊ ሚዛን ኤልሳዕ ከሐብታምነት ወደ ምስኪን ደሃነት ደረጃ ወረደ። የሚገርመው ኤልሳዕ ይህን ሁሉ ሐብቱን ትቶ በመጀመሪያ ማገልገል የጀመረው የእግዚአብሔርን ነቢይ ነበር እንጂ የነቢይነት ሹመት እንኳ አልተሰጠውም። በዓለም የእሴት መመዘኛ የኤልሳዕ ጥሪ እድገት ወይም በረከት አያብልም። የእግዚአብሔር ጥሪ ሰዎችን ዋጋ የሚሰጧቸውን ነገሮቻቸውን እንዲተዉ ያደርጋቸዋል።

አንዳንድ ጊዜ ዋጋቸውን ተምነው አገልጋይ የሆኑም ሰዎች ስለብድራት ሲያሳስባቸው እንመለከታለን። ጴጥሮስ ጌታ ኢየሱስን የተከተለው ቢከተል ሊያገኝ የሚችለውን ነገር በማወቅ አልነበረም። ግን የጌታን ጥሪ ሲሰማ ያለውን ነገር ሁሉ ትቶ ተከተለው። ነገር ግን አብሮት ከቆየ በኋላ አንድ ቀን "እነሆ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን" (ማቴ19፡27) በማለት ጠየቀ።

እግዚአብሔርን ማገልገል መከራ ብቻ ሳይሆን ብድራትም አለው። አገልጋዮች በዚህ ዓለም እንዲሁም ሊመጣ ባለው ዓለም ብድራት እንደሚያገኙ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል (ሉቃ18፡29-28)። የአገልጋይን ብድራት በሁለት ከፍለን እንመለከታለን። ይኼውም ምድራዊ ብድራትና ሰማያዊ ብድራት ናቸው።

## 1. ምድራዊ ብድራት

አገልጋይ የእግዚአብሔርን ጥሪ ተቀብሎ ለአገልግሎት ቢሰማራና አገልግሎቱን በታማኝነት ቢያከናውን በዚህ ዓለም ላይ ምን ብድራት ያገኛል? እነዚህ ብድራቶችስ ምንድናቸው? የእግዚአብሔር ቃል ስለዚህ ጉዳይ የሚናገረውን እንመለከታለን።

### ሰላም

እግዚአብሔር በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተ ሰላም ይሰጣቸዋል። በዚህ በሚያስጨንቅ ዓለም ውስጥ ሆነው በሰላም ይኖራሉ። ምን ይመጣ ይሆን እያሉ አይሰጉም። የሰላማ አለቃ ልባቸውን ይጠብቃል። በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ክንድ ላይ በመታመን ተዘልለው ይኖራሉ። በውስጣቸው የጌታ ሰላም የሞላ ስለሆነ በሚሰማውና በሚሆነው ነገር አይናወጡም (ዮሐ.14፡27፣ ፊልጵ.4፡7)።

### መለኮታዊ ጥበቃ

እግዚአብሔር አገልጋዮቹ በተሠማሩበት በታ ሁሉ ከእነርሱ ጋር ይሆናል። እነርሱ በእርሱ ፈቃድ ሲሰማሩ ብቻቸውን አይደሉም። ሁሉን የሚችል የሰማይና የምድር ሁሉ ጌታ ከእነርሱ ጋር ነው። እርሱ ዘወትር ይጠብቃቸዋል። ጌታ ከሚታይና ከማይታይ ከማንኛውም ክፉ ነገር ይጠብቃቸዋል (ማቴ.28፡20፣ ዮሐ.17፡15)።

## ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸው ነገሮች

አገልጋዮች ለኑሮአቸው የሚያስፈልጓቸውን ነገሮች የሚያገኙት በተዓምር ሳይሆን ከቤተክርስቲያን ከሚከፈላቸው ቀለብ ነው፡፡ ከአስፈላጊነቱ አንጻር ስለአገልጋይ ቀለብ በስፋት ማየቱ ጠቃሚ ሊሆን ስለሚችል በጥልቀት መመልከት መልካም ይመስለኛል፡፡ በእግዚአብሔር ተጠርቶ የወንጌል አገልጋይ የሆነ ሰው ደመወዝ እየተከፈለው ማገልገሉ ተገቢ ነውን? እንዲህ ከሆነ እየተከፈሉ ወንጌልን በማገልገልና ሌላ ሥራ ሰርቶ ደመወዝ ማግኘት መካከል ምን ልዩነት አለ? ሁለቱም ሥራ አይደሉምን?

እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት ጠርቶናል ብለው በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ ሰዎች አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ለኑሮአቸው ድጋፍ የሚሆን ቀለብ ከቤተክርስቲያን ሊሰፈርላቸው እንደሚገባ የጌታ ቃል ያስተምራል፡፡ ጳውሎስ "ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል" (1ቆሮ9:14) በማለት ተናግሯል፡፡ ሐዋርያው ለወንጌል አገልግሎት ከተጠሩ በኋላ ከወንጌል ቀለብ ማግኘት መልካም እንደሆነ ቢቀበልና ቢያስተምርም ራሱ ግን ያለምንም ቀለብ ነበር ወንጌልን ሲያገለግል የነበረው፡፡ ጳውሎስ ወንጌልን እየሰበከ በትርፍ ጊዜው ድንኳን ይሰፋ ነበር፡፡ ከዚያ በሚያገኘው ገቢ ራሱንና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሰዎች ይደግፍ ነበር (የሐዋ 18:3፤ 20:34)፡፡

ጳውሎስ ከቤተክርስቲያን ደመወዝ ሳይጠብቅ ባለው ሙያ ሥራ እየሠራ ከራሱም አልፎ ሌሎችንም ይደግፍ ነበር፡፡ ጳውሎስ ይህን የድንኳን መስፋትን ሙያ የተማረው ምናልባት በወጣትነቱ ጊዜ ይሆናል፡፡ በአይሁድ ልማድ ልጆች ከማንኛውም የማህበረሰብ ክፍል ማለትም ከሐብታምም ሆነ ከድሃ ቤተሰብ የተወለዱ ሁሉ አንድ ሙያ መማር ይኖርባቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ድንኳን መስፋትን በዚያን ጊዜ ከወላጆቹ ተምሮ ይሆናል፡፡

የእጅ ሙያ በአይሁዶች ዘንድ ዋጋ ቢሰጠውም በአንዳንድ ቦታዎች በተለይም በግሪኮች ዘንድ የተናቀ ሥራ ነበር፡፡ በዚያን ዘመን የእጅ ሥራ የባሪያዎች ሥራ ተደርጎ ስለሚቆጠር የእነርሱን ሥራ የሚሠራ ሰው ይናቃል፡፡ ጳውሎስ ይህን ቢያውቅም ባለው ሙያ ተጠቅሞ ገንዘብ በማግኘት ራሱንና ሌሎች ሰዎችን በመደገፍ ወንጌልን ከማስፋፋት አልተቆጠበም፡፡ እርሱ የሚያውቀው ሥራ የተናቀ ስለሆነ አፍሮበት ሌላ ሙያ መማር አለብኝ ብሎ አላሰበም፡፡ የጳውሎስ ትኩረት ሥራ ሠርቶ ገንዘብ በማግኘት ወንጌልን ማገልገል ላይ ነበር እንጂ ሥራው በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያስገኛል ወይስ ያሳጣል በሚለው አሳብ ላይ አልነበረም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ከቤተክርስቲያን ቀለብ እየተከፈለው ማገልገል መብቱ ሆኖ እያለ ያልፈለገበት ምክንያት ምንድነው? የመጀመሪያው ጳውሎስ ምዕመናን ደክመው በመሥራት ራሳቸውን ከመደገፍ አልፈው ሌሎች ደካሞችን መርዳት እንዲችሉ ምሳሌ በመሆን ለማስተማር ነው፡፡ ምዕመናን "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ የተባረከ ነው"

የሚለውን መርሕ እንዲከተሉ ለማሳየት ራሱ እንዲህ ሆኖ መገኘት ስላለበት ነው (የሐዋ20:35)።

በዘመናችን ምዕመናን ተግተው በመሥራት ከድህነት እንዲወጡ እናስተምራለን። ስናስተምር በጣም ጎበዞች ነን፤ ነገር ግን አትለምኑ፣ ተግታችሁ ሥሩ እያልናቸው እኛ ራሳችን ግን ምዕመናን ኑሮአችንን እንዲደግፉ እንለምናለን። በቤተክርስቲያን አገልጋዮች ተርበዋልና አባካችሁ አሥራት ክፈሉ ተብሎ ማስታወቂያ ይነገራል፣ ትምህርትም ይሰጣል። ይህ በአንድ በኩል ቀጥተኛ ያልሆነ የልመና ተግባር ነው። ደፋር ምዕመን ስላልተገኘ ነው እንጂ "ለምን በትርፍ ጊዜአቸው ሠርተው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን አይደግፉም?" ብሎ ቢጠይቅ ለአገልጋዮች ከፍተኛ ተግዳሮት ይሆናል ብዬ እገምታለሁ።

ሁለተኛው ጳውሎስ በምዕመናን ላይ ጥገኛ በመሆን እነርሱን ላለማስቸገር ነው። ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልዕክት "ወንድሞች ሆይ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን" (1ተሰ2:9)። ጳውሎስ ጊዜ የለኝም ወይም በአገልግሎት ብዛት ስለደከመኝ እረፍት ያስፈልገኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ በሰዎች ላይ ሸክም መሆን አልፈለገም። ከወንጌል አገልግሎት በሚተርፈው ጊዜ ራሱን ለመቻል ሥራ ይሠራ ነበር።

ሦስተኛው ጳውሎስ ያለምንም ቁሳዊ ብድራት በመስበክ ለመመካት ነው (1ቆሮ9:15)። ጳውሎስ እርሱ የሚያገለግላቸው ሰዎች "አንተ ወንጌል የምትሰብክልን ደመወዝ ስለምንሰጥህ ነው" ብሎ እንዲናገሩት አልፈለገም። ከዚህም የተነሳ ወንጌልን በማገልገል ማግኘት የሚገባውን መብቱን መተው መረጠ። በዚህም ትምክህትን አተረፈ። ማንም ጳውሎስን ከደመወዝ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሊወቅሰው አይችልም። ይህን ማድረጉ ለእርሱ ትልቅ ድፍረት ሰጥቶታል። ወንጌልን ሲያስተምር ያለምንም መሸማቀቅ ይሰብካል። የሚያገለግላቸው ሰዎች ከወንጌል እውነት ዘንበል ሲሉ በፍቅር ይጋፈጣቸዋል።

በእኛ ዘመን አገልጋዮች እውነትን ለመናገር ድፍረት የላቸውም። የምዕመናንን ስህተት እያዩ ስህተት ሠርተሃል ተመለስ አይሉም። ወንጌልን ሲሰብኩ ሰዎች መስማት የሚፈልጉትን ነገር ይሰብካሉ። ከእግዚአብሔር ፈቃድ አገልጋይነት ወደ ሰዎች ምኞት አገልጋይነት ዘወር ብለዋል። ይህ ለምን ሆነ? ሲባል አንደኛው ምክንያት ሰዎች ቅር ብሏቸው ደመወዛቸውን እንዳይከለክሉአቸው ወይም አንዳንድ ቁሳዊ ድጋፍ ማድረጋቸውን እንዳያቋርጡባቸው ነው። ስለዚህ ሁልጊዜ ለስላሳ የሆነ ወንጌል ይሰብኩላቸዋል። በቤተክርስቲያን አንዳንድ ወሳኝ የሆኑ ጉዳዮች ሲነሱ አገልጋዮች እውነቱን እያወቁ ሳይናገሩ ወይም ለእውነት ሳይቆሙ ይቀራሉ። ለምን እውነቱን እያወቃችሁ ይህን ትወስናላችሁ? ሲባሉ "ተወኝ ልጆቼን ላሳድግበት" ይላሉ። አገልጋይ በእውነት ላይ ቆሞ የቤተክርስቲያን መሪዎችን ቢቃወም ከአገልግሎቱ ሊባረር ወይም የደመወዝ ጭማሪ ላይደረግለት ይችላል። አገልጋዮች ይህን ስለሚፈሩት ለእውነት ነገር አይቆሙም። የአገልጋዮችን ወኔ የሰለበው ከቤተክርስቲያን የሚያገኙት ደመወዝ ነው።

ከዚህ አኳያ ሲታይ አገልጋዮች የሚያገለግሉት ለደመወዝ ሳይሆን እግዚአብሔር ስለጠራቸው እንደሆነ ለማስመስከር እና ለእውነት ለመቆም ከፈለጉ ራሳቸውን በመቻል ማገልገል የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባቸዋል። ነገር ግን ቀለብ እያገኙ ማገልገል በራሱ ኃጢአት አይደለም። አገልጋይ የእግዚአብሔር መልዕክተኛ መሆኑን በመዘንጋት ትኩረቱን በቀለቡ ላይ ሲያደርግ ከእግዚአብሔር አገልጋይነት ወደ ቤተክርስቲያን ተቀጣሪ ሠራተኛነት ራሱን ዝቅ ያደርጋል። ልክ እንደ ማንኛውም ሠራተኛ ለእንጀራው ብቻ ብሎ የሚሠራ ሰው ይሆናል ማለት ነው።

ጳውሎስ ቋሚ የሆነ የሚሰፈርለት ቀለብ ባይኖረውም ከምዕመናን አስፈላጊ በሆኑ ወቅቶች እርዳታ ያገኝ ነበር (2ቆሮ11:9)።

በዚህ ዘመን በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ አገልጋዮች ከቤተክርስቲያን ደመወዝ ከሚጠብቁ በትርፍ ጊዜያቸው "ድንኳን በመስፋት" ራሳቸውን እየደገፉ ወንጌልን ቢሰብኩ ምን አለበት? መቼም እንደ አገልጋይ የሐዋርያው ጳውሎስን ያህል አገልግሎት ቢያገለግል ትንሽ አይባልም። እርሱ ድንኳን በመስፋት ራሱን እየደገፈ ይህን ያህል ወንጌልን ከሰበከ ዛሬም ያለን አገልጋዮች የእርሱን ፈለግ ብንከተል ያዋጣን ይሆን?

ይህ የጳውሎስ ተግባር ለወንጌል አገልጋዮች መልካም ምሳሌ ሊሆን ይገባል። ብዙ አገልጋዮች ወደ አገልግሎት ከመሠማራታቸው በፊት የሚያውቁት ሙያ ይኖራቸዋል። እነዚህን ሙያዎቻቸውን ከመናቅ ይልቅ በሙያዎቻቸው ሠርተው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እየደገፉ ወንጌልን ማገልገል ቢለማመዱ ከጥገኝነት ኑሮ ያወጣቸዋል።

ዛሬ በቤተክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ጠርቶአቸው የሚያገለግሉ አገልጋዮች ከቤተክርስቲያን ተገቢውን ቀለብ በማጣት ቢቸገሩና ወንጌልን ማገልገል ትተው ሌላ ሥራ መሥራት ቢጀምሩ እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር አልተጠሩም ማለት ይቻላል?

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔርን ሥራ ማለትም የክህነት አገልግሎትን የሚሠሩ ሌዋውያን የተባሉ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ሙሉ ጊዜአቸውን ለዚህ አገልግሎት የሰጡ ስለነበር ሌላ ሥራ አይሠሩም። የዕለት ሥራቸው እግዚአብሔርን ማገልገል ነበር። ሌዋውያን ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተለዩ ስለነበሩ የራሳቸው የሆነ ርስት የላቸውም። የእነርሱ ርስት እግዚአብሔር ነው። ሌዋውያን የሚኖሩት የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ቤተመቅደስ ከሚያመጣው ቁርባንና አሥራት በመብላት ነው (ዘኁ18:20፣23-24)። ይህ ሌዋውያን በእግዚአብሔር እንዲሁም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ጥገኛ መሆናቸውን ያሳያል።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተማረኩበት ከባቢሎን ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ሲፈቀድላቸው ሌዋውያን ለመመለስ ብዙም ፈቃደኞች አልነበሩም። በዚያ በምርኮ ሀገር ኑሮአቸውን በተመቻቸ ሁኔታ መስርተው ስለነበር ወደ ተገኝነት ኑሮ መመለስ ባለመፈለጋቸው ይሆናል(ዕዝ8:15)። ፈቃደኞች በመሆን ወደ ይሁዳ የተመለሱትንም ቢሆን መልካም ነገር አልገጠማቸውም። በእግዚአብሔር የተጠሩበትን አገልግሎታቸውን በሚገባ ማከናወን አልቻሉም። ሌዋውያን የተጠሩበትን

አገልግሎት ትተው ወደ ሌላ ሥራ ውስጥ ገቡ። ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ ከእግዚአብሔር ልባቸውን በመመለስ ለቤተመቅደስ የሚገባውን ስጦታ መስጠት ሲያቆሙ ካህናቱ የሚበሉት ነገር ስላጡና ኑሮአቸውን ለመደጎም ብለው ወደ ሌሎች ሥራዎች መሰማራታቸው (ነህ13:10)።

ከእነዚህ አሳቦች በመነሳት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚያገለግሉ አገልጋዮች ኑሮአቸውን የሚደግፉበት አንዳንድ ሥራዎች ቢኖራቸው ጠቃሚ ይሆናል። ከቤተክርስቲያን ደመወዝ ባያስጣቸውም የእግዚአብሔርን ሥራ መቀጠል ይችላሉ።

በአብዛኛው ቤተክርስቲያን አገልጋዮች ራሳቸውን የሚደግፉበት የራሳቸው የሆነ ሥራ እንዲሠሩ አታደፋፍርም። ምክንያቱም አገልጋዮች ሙሉጊዜያቸውን ለወንጌል አገልግሎት የሰጡ ስለሆነ በሌላ ሥራ ውስጥ መግባቱ ዓላማዩ ነው ብለው ከያዙት የወንጌል ሥራ ወደኋላ ሊመልሳቸው ይችላል በሚል ፍርሃት ነው።

*አንድ ጊዜ በገጠር ከተማ ውስጥ የሚያገለግል አንድ ወንጌላዊ ቤተክርስቲያን ከምትሰጠው ቀለብ እየቆጠበ ጥጆችን መግዛት ጀመረ። ገና ያላገባ ስለሆነ ጥጆቹ እስካገባ ድረስ ያድጉና ሳገባ ለኑሮዬ ድጋፍ ሊሆኑልኝ ይችላሉ በሚል ዕቅድ ነበር ይህን የጀመረው። ይህን ሲጀምር ቤተክርስቲያን እየሠራ ያለውን ነገር ቶሎ እንዲያቆም አስጠነቀቀችው። የእርሱ ዕቅድ በቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ዘንድ ለአገልግሎት ትኩረት እንደሌለው የሚያሳይ ሆኖ ተተረጎመ። አገልጋዩ ይህ መብቱ እንደሆነ ቢያስረዳቸውም ሊገባቸው አልቻለም። ከዚህም የተነሳ ለአገልግሎት ሸክም የለውም በሚል ምክንያት ከአገልግሎት አሰናበቱት።*

ሐዋርያው ጳውሎስ ራሱ ሌላ ሥራ እየሠራ ወንጌልን ሲሰብክ የቆየ አገልጋይ ቢሆንም በጌታ ልጁ ለሆነው ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልዕክት ውስጥ "የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም" (2ጢሞ2:9) በማለት ከወንጌል አገልግሎት ጋር ሌላ ሥራ መጀመር በጥንቃቄ ካልተደረገ በስተቀር ዓላማን ሊያስት እንደሚችል ሲነግረው እንመለከታለን።

በሀገራችን ቤተክርስቲያን በስደት ላይ በነበረችበት ወቅት የቤተክርስቲያን መሪዎች፣ አገልጋዮችና ቤተሰቦቻቸው በችግር ላይ እንዳይወድቁ በማሰብ በአንዳንድ ቦታዎች አገልጋዮች ገቢ የሚያስገኝ ሥራ እንዲጀምሩ ሁኔታዎችን አመቻችታ ነበር። አንዳንዶች ይህን ዕድል በመጠቀም ቤተክርስቲያን ቀለብ መስፈር ባልቻለችባቸው ጊዜያት ወንጌልን ሳያቋርጡ አገልግለዋል። ጥቂቶች ደግሞ ወንጌልን ማገልገል ትተው ሌላ ጊዜ ሲመኙት የነበረውን ሕልማቸውን እውን አድርገዋል። ሥራው ጥሞአቸው ከያዙት የወንጌል አገልግሎት ፈንግጧቸዋል። ስለዚህ ሚዛኑን ካልጠበቀ ገቢ የሚያስገኝ ሥራ መሥራት ከወንጌል አገልግሎት የሚያፈናቅል ፈተና ሊሆን ይችላል። ልብ እየከጀለ ከመኖር ግን ጭራሽ በሚፈልጉት ሥራ ውስጥ ገብተው ራሳቸውን በመቻል ለቤተክርስቲያን አሥራታቸውን ቢከፍሉ ይሻላል። ልቡ ለወንጌል አገልግሎት የቆረጠና እግዚአብሔር የጠራው ብቻ ጸንቶ ቢቆምና ሌሎች የወንጌል አገልግሎትን እንደ ሥራ መስክ የሚቆጥሩ ቢሄዱ መልካም ይመስለኛል።

ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች ለአገልጋዮች ቀለብ መስጠት ተገቢ እንደሆነ የሚያሳዩ ምክንያቶች ናቸው። ቁልፍ አሳብ አገልጋዮች በቤተክርስቲያን በሚሰጠው ቀለብ ላይ ጥገኛ መሆን የለባቸውም፤ ባላቸው ትርፍ ጊዜ ሌላ ሥራ መሥራትና ራሳቸውን፣ ቤተሰቦቻቸውንና ሌሎችንም እንዲሁም ቤተክርስቲያናቸውንም መደገፍ መማር አለባቸው ነው። ለአገልጋይ ቀለብ መስፈር መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ሁሉ ራስን እየደገፉ ማገልገልም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ለአገልጋዮች ቀለብ መስፈር ያለበት ማን ነው? የሚለው ጥያቄ በተለያዩ ሰዎች የተለያየ ምላሽ ሊያገኝ ይችላል። በአጠቃላይ ግን በሁለት መልክ ልንመለከታቸው እንችላለን።

የመጀመሪያው አገልጋዮች ራሳቸው ለራሳቸው የሚሰፍሩበት ሁኔታ ነው። የቤተክርስቲያናቸው የበላይ ተመልካች የሆኑ አገልጋዮች ቀለባቸውን በራሳቸው ለራሳቸው ያሰፍራሉ። ስንት ማግኘት እንዳለባቸው በራሳቸው ይወስናሉ። በቤተክርስቲያን ንብረትና ገንዘብ ላይ የሚያዙ እነርሱ ናቸው። ስለዚህ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚበቃቸውን ያህል ለመውሰድ ዕድል አላቸው። እንግዲህ ለራስ ሲቆርሱ አይሳሳም እንደሚባለው ቀለባቸውን ሲሰፍሩ ደህና አድርገው ይቀበላሉ።

አንዳንድ አገልጋዮች ይህን የቀለብ አሰፋፈር ስለሚፈልጉ የራሳቸውን ቤተክርስቲያን ለመመሥረት ትግል ያደርጋሉ። አስተዳደሩ በእጃቸው ከሆነ የሚፈልጉትን ነገር ያገኛሉ። በድምሩ ሲታይ አንዳንድ አገልጋዮች ትኩረታቸው አገልግሎት ላይ ሳይሆን በአገልግሎት ስም በሚገኘው ምድራዊ ጥቅም ላይ ነው። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ሥር ሆነው ቀለባቸው በሌሎች እንዲወሰንላቸው አይፈልጉም። ነጻ ወጥተው ራሳቸው ለራሳቸው ቀለብ የሚሰፍሩበት መድረክ ፍለጋ ከቤተክርስቲያን ይገነጠላሉ። ይህ አሠራር ለሙስና የሚያጋልጥ ቀዳዳን በስፋት ይከፍታል።

ሁለተኛው ደግሞ በሌሎች በኩል የሚሰፈርበት ሁኔታ ነው። በዚህ ሁኔታ ቀለብ የሚያገኙ አገልጋዮች ቀለብ የሚወደብላቸው ያስማራቸው የቤተክርስቲያን አካል ነው፡ ቦርድ፣ ሽማግሌዎች ወይም ዲያቆናት ሊሆኑ ይችላሉ። አገልጋዮችና ገንዘብ አይተያዩም። አገልጋዮች ገንዘብን የሚያዩት ቀለባቸውን ከሚከፍላቸው አካል ሲቀበሉ ብቻ ነው።

*ለአገልጋዩ ስንት ይከፈለው?* እንግዲህ ቀለብ መስጠት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነ ለአገልጋዮቻችን ምን ያህል መክፈል አለብን? ለአንድ አገልጋይ የሚበቃ ቀለብ በገንዘብ ቢከፈለው ስንት መሆን አለበት? የእግዚአብሔር ቃል ለአገልጋይ ቀለብ መስፈር መልካም እንደሆነ ቢናገርም ለእያንዳንዱ አገልጋይ ምን ያህል መከፈል እንዳለበት እንደዚሁም በምን መመዘኛ ቀለቡ ሊወደብ እንደሚገባ ዝርዝር ማብራሪያ አይሰጥም። ከዚህም የተነሳ ወጥ የሆነ መመዘኛ ማዘጋጀት ሁሉንም አያስማማም። ሆኖም ግን ለግንዛቤ ያህል አንዳንድ አሳቦችን እንመለከታለን።

**1. በትምህርት ደረጃ**

አንዳንድ ቤተክርስቲያናት የአገልጋዮችን የትምህርት ደረጃ ቀለባቸውን ለመወሰን እንደ ዋና መመዘኛ ይጠቀሙበታል። የትምህርት ደረጃን እንደ መመዘኛ መጠቀም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስለመሆኑ በግልጽ የተጻፈ አሳብ የለም። ትምህርትን እንደ መመዘኛ መጠቀም የወንጌል አገልግሎትን በተሳካ ሁኔታ ማገልገል የሚችሉ የተማሩ ሰዎች ናቸው ብሎ እንደ ማመን ነው። ለወንጌል አገልግሎት ስኬት ወሳኝ ሚና የሚጫወተው ትምህርት እንደሆነ ማሰብ ነው። በትምህርት ደረጃ ደመወዝ ሲሰጥ የተማሩት ካልተማሩ አገልጋዮች የተሻለ ደመወዝ ያገኛሉ፡ ይህ ማለት የእነርሱ ፍሬ ካልተማሩት ይበልጣል ማለት ነው።

በዓለም ማለትም በሌሎች ሥራዎች ሲታይ አንድ ሰው ስለሚሠራው ሥራ ትምህርት ከሌለው በሚገባ መሥራት አይችልም። ስለዚህ በትምህርት ደረጃ መቅጠርና ተገቢውን ደመወዝ መክፈል አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የሥራው ስኬታማነት የሚለካው በሠራተኛው ትምህርትና እውቀት ነው።

ቤተክርስቲያን ለትምህርት መክፈል ከጀመረች የወንጌል አገልግሎት በጥሪና በእግዚአብሔር ጸጋ መሆኑ ቀርቶ በትምህርት ሆነ ማለት፡ ይመስላል። ለወንጌል አገልግሎት ስኬታማነት ጉልህ ሚና የሚጫወተው የአገልጋዮች የትምህርት ደረጃ ነው ወይስ በእነርሱ ላይ ያለው የእግዚአብሔር ጸጋ ነው? ምናልባት መልሱ ከሁለት አንዳቸውም ሳይሆን ሁለቱም አስፈላጊ ናቸው የሚል ይሆናል።

የእግዚአብሔር ጸጋ ለአገልግሎት መሠረታዊ ቢሆንም አንድ አገልጋይ ጸጋውን እንዴት እንደሚጠቀምበት የማያውቅ ከሆነ ከሚገነባ ይልቅ የሚያፈርሰው ይበልጣል። ስለዚህ ጸጋውን እንዴት መጠቀም እንዳለበት መማር ይገባዋል። ይህን ለመማር የወሰደበት ጊዜ ደግሞ ምን ያህል የጸጋ አጠቃቀም ሁኔታ እንደተማረ ያሳያል። ጸጋ ካለው በዚያ ጸጋው ደግሞ እንዴት እንደሚጠቀምበት ከተማረ በአገልግሎቱ ፍሬያማ ይሆናል። ደመወዝ ሲከፈለው እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ መጠን ሳይሆን ጸጋውን እንዴት መጠቀም እንደሚችል በወሰደው ጊዜ መጠን ነው። ምክንያቱም ለአንድ አገልጋይ የተሰጠውን የእግዚአብሔር ጸጋ እንዴት መለካት እንችላለን?

**2. በአገልግሎት ፍሬ**

የአገልግሎት ፍሬ ለቀለብ አሰፋፈር መመዘኛ በሚሆንበት ቤተክርስቲያን በመጀመሪያ ለአገልጋዩ በተወሰነ ደረጃ ቀለብ ይሰጠውና ከዚያም ፍሬው እየታየ ጭማሪ ይደረግለታል። በአንዳንድ ቦታዎች ደግሞ አንድ አገልጋይ እግዚአብሔር ጠርቶኛል ብሎ ሲመጣ ይቀበሉና ያሰማሩታል። ከዚያ በኋላ ዞወር ብሎ የሚያየው ሰው የለም። ምን ይበላል? ምን ይጠጣል? ምን ይለብሳል? እንዴት ይኖራል? ብሎ የሚጠይቅ ሰው የለም። በዚህ ሁኔታ መከራ እየበላ ለተወሰነ ጊዜ ካሳለፈ በኋላ መሪዎች ይህ ጥሪ አለኝ ባዩ ያለውን ፍሬ ማለትም

በቤተክርስቲያን ውስጥ በእርሱ አገልግሎት የመጣውን ለውጥ መገምገም ይጀምራሉ። በእነርሱ ግምገማ ካለፈ የተወሰነ ቀለብ ይሰጡታል። ካልሆነ በፈልግ በነጻ ማገልገሉን ይቀጥላል ወይም መከራውን መጠጣት ሲሰለቸው ትቶ ይሄዳል። የአገልግሎት ፍሬ ሲባል በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ምን ምን እንደሆኑ መግለጽ ያስቸግራል።

### 3. በአገልግሎት ዘመን

ይህ መስፈርት ብዙ ዓመታት ያገለገሉ አገልጋዮች ጥቂት ዓመት ካገለገሉ አገልጋዮች በላይ ቀለብ ሊያገኙ ይገባቸዋል የሚል ነው:: በቤተክርስቲያን ውስጥ ጥርሳቸውን ነቅለው ያደጉና ዋጋ የከፈሉ ሰዎች የሚገባቸውን ቀለብ ማግኘት ተገቢ ነው:: ይህ ማለት ማለዳ ሥራ የጀመረው በቀትር እንዲሁም ከሰዓት በኃላ ከመጣው ጋር እኩል ቀለብ ማግኘት የለበትም ማለት ነው:: ቤተክርስቲያን ይህን መስፈርት እንደ ዋነኛ ነጥብ ከተቀበለች በመሰረተ አሳብ ደረጃ ጌታ ኢየሱስ ከተናገረው ምሳሌ አሳብ ጋር የሚጋጭ ይመስላል (ማቴ.20፡1-16)::

### 4. በቤተሰብ ብዛት

በአንዳንድ ቦታዎች ቤተክርስቲያን በአገልጋዩ የቤተሰብ ብዛት ላይ በመመርኮዝ ቀለብ ትሰፍራለች። በዚህ መሥፈርት መሠረት አንድ አገልጋይ ዛሬ ቢጠራና ብዙ ቤተሰብ ካለው ለረዥም ዓመታት ካገለገለ ግን ልጆች ከሌሉት አገልጋይ የበለጠ ቀለብ ያገኛል። ብዙ ቤተሰብ ያለው ቤተሰቡን ለማስተዳደር ብዙ ገንዘብ ስለሚያስፈልገው የተሻለ ቀለብ ይሰጠዋል። በዚህ መመዘኛ ውስጥ ያለእግዚአብሔር ጥሪ በስተቀር ሌሎች መስፈርቶች ቦታ የላቸውም።

### 5. እንደ አካባቢው ሁኔታ

አገልጋይ ሊከፈለው የሚገባው ቋሚ የሆነ መስፈርት የለም የሚሉ ወገኖች ደግሞ አገልጋይ እንደ አካባቢው ሁኔታ ለኑሮው የሚበቃ ቀለብ ሊሰጠው ይገባል ይላሉ። በአንድ በማዕከላዊነት በምትመራ ቤተእምነት ውስጥ ተመሳሳይ መመዘኛ (ለምሳሌ የትምህርት ደረጃ) ያላቸው አገልጋዮች የተለያየ ቦታ ስለሚያገለግሉ የተለያየ ቀለብ ይሰጣቸዋል። አንድ ተመሳሳይ የመጀመሪያ ድግሪ ያለውና በአዲስ አበባ ከተማ የሚያገለግል አገልጋይ ተመሳሳይ የትምህርት ደረጃ ኖሮት ሩቅ ቦታ ገጠር ከሚያገለግለው አገልጋይ የተሻለ ደመወዝ ያገኛል። ምክንያቱም አዲስ አበባ ከተማ የኑሮ ውድነት ስላለ አገልጋዮች በትንሽ ደመወዝ መኖር አይችሉም።

እዚህ ላይ የሥነምግባር ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ ነው። በዓለማዊ ድርጅት(በአንድ ድርጅት ለአንድ በአንድ ተመሣሣይ ሥራ) የተለያዩ የደመወዝ አከፋፈል ስኬሎች አይኖሩም። ተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች የትም ቢያገለግሉ ደመወዛቸው እኩል ነው። እንዲያውም ከከተማ ርቀው ያሉ ሠራተኞች አበል ይታሰብላቸዋል። በቤተክርስቲያን

ውስጥ ግን አንድ ሰው ከአዲስ አበባ እየራቀ በሄደ ቁጥር ደመወዙ እየቀነሰ ይሄዳል።

ለአገልጋይ ቀለቡ እንደ አካባቢው ሁኔታ ይከፈል የሚለው አሳብ የሚሠራው እያንዳንዱ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ራስ አገዝ ከሆነ ብቻ ነው። በዚህ ሁኔታ ማዕከላዊነት ስለማይኖር እያንዳንዱ አጥቢያ በፈለገበት ሁኔታ ለአገልጋዩ ቀለብ መስፈር ይችላል። በአካባቢው ሁኔታ አንድን ሰው ሊያኖር የሚችል ቀለብ ይሰጣዋል።

በአጠቃላይ አሳብ ለአገልጋይ ቀለብ መስጠት የእግዚአብሔር ቃል የሚደግፈው ተግባር ነው:: ስለዚህ አንድ አገልጋይ የተጠራበትን አገልግሎት በሚገባ እንዲያገለግል የትምህርት ደረጃውን የሚመጥን፣ ቤተሰቦቹን ማስተዳደር የሚችልበት፣ የአገልግሎት ዘመኑንና ፍሬውን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ቀለብ ሊሰጠው ይገባል:: አገልጋይ በራሱ ቀለቡን ባይወስን የተሻለ ነው:: አገልጋይ ሙሉጊዜውን እያገለገለ በትርፍ ጊዜው ሠርቶ ገቢ ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ካለ ያለጥገኝነት ለማገልገል ተመራጭነት አለው:: ከቤተክርስቲያን ቀለብ ቢኖርም ባይኖርም አገልግሎቱ ዘላቂነት ሊኖረው ይችላል::

## 2. ሰማያዊ ብድራት

እግዚአብሔር እርሱን በታማኝነት ላገለገሉ አገልጋዮች የሚገባቸውን ብድራት ይሰጣል። የሰው ዋጋው በእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ዳዊት እግዚአብሔርን *"አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጠዋለህና"* (መዝ.62:12) በማለት እግዚአብሔር ጻድቅ ዳኛና ለሁሉም የሚገባውን ብድራት እንደ ሥራው መጠንና ዓይነት እንደሚሰጥ ይናገራል። የእያንዳንዱ ሰው ሥራ እንደሚለያይ ብድራቱም የተለያየ ነው። እግዚአብሔር አንዳንዱን ብድራት በዚህ ምድር ላይ ሲሰጥ ሌሎችን ደግሞ በመንግሥተ ሰማያት ይሰጣል። ጌታ ኢየሱስ ስለስሙ መከራ ስለሚቀበሉ ሰዎች *"ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነው"* (ማቴ.5:12) በማለት ሲናገር ስለደረሰባቸው መከራ ዋጋ የሚቀበሉት በእግዚአብሔር መንግሥት እንደሆነ መግለጡ ነበር።

በሰማይ ብድራት ወይም ሽልማት የሚጠብቃቸው አገልጋዮች እነማን ናቸው? ይህ እጅግ ከባድ ጥያቄ ቢሆንም መጠየቅ ያለበትና እያንዳንዱ አገልጋይ መልሱን ከእግዚአብሔር ቃል ሊፈልግለት የሚገባ ጥያቄ መሆኑ አያከራክርም። ሁሉም አገልጋዮች ከእግዚአብሔር ዘንድ ብድራት አያገኙም። ሐዋርያው ጳውሎስ ሁሉም አገልጋይ በመባል የሚያገለግል ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ብድራት እንደማይቀበል ተናግሯል። ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች በጻፈው መልዕክቱ በ(1ቆሮ.3:10-15) ላይ ተናግሯል።

ማንም አገልጋይ እግዚአብሔርን በሚያገለግልበት ወቅት እንዴት እንደሚያገለግል በጥንቃቄ ሊያጤነው ይገባል። የአገልጋይ የአገልግሎት ጥራት የሚለካው በሰዎች ሳይሆን በእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር አገልጋዮች እንዴት እንዳገለገሉ ብቻ ሳይሆን በምን ዓላማ እንዳገለገሉም ስለሚያውቅ ትክክለኛ ግምገማ ይሰጣል። አንድ ቀን የእያንዳንዱ

አገልጋይ አገልግሎት ይገለጣል። የእያንዳንዱ አገልጋይ የአገልግሎት ጥራት የሚታወቀው አገልግሎቱ በእሳት ተፈትኖ ሲያልፍ ነው።

ሰዎች ስለአገልጋዮች አገልግሎት የተለያየ አስተያየት ሊሰጡ ይችላሉ። አንዳንዱ አስተያየት ጥሩ ሲሆን ሌላው ደግሞ መጥፎ ነው። የአገልግሎት ጥራት መለኪያው በሰዎች መወደስ ወይም መኮነን ሳይሆን በእግዚአብሔር ፊት ተፈትኖ ማለፉ ላይ ነው። በእግዚአብሔር ፊት አገልግሎታቸው ተቀባይነት የሚያገኝላቸው አገልጋዮች በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ምሪት በዚህ ዓለም የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ በማወቅ እንደ ቃሉ ያገለገሉ ናቸው። እነዚህ አገልጋዮች በሰዎች ዘንድ ዝናቸው ባይናኝም እግዚአብሔር እንደ ታማኝ ባሪያዎቹ ያውቃቸዋል። የሠሩትም ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ስለተሠራ ማለትም የሰው ሥራ ባለመሆኑ በእሳት ተፈትኖ ለማለፍ ብቃት አለው።

በራሳቸው ጥበብና ዕውቀት የእግዚአብሔርን ሥራ የሚሠሩና ለሰዎች የሚጥም ተረት በማቅረብ በሰዎች ዘንድ ዝናን ያተረፉ፣ ክርስቶስን ሳይሆን ራሳቸውን የሚሰብኩ፣ በወንጌል ስም የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድዱና የራሳቸውን የክብር ሐውልት የሚገነቡ አገልጋዮች አገልግሎታቸው በእሳት ይቃጠላል። አገልግሎታቸው በእግዚአብሔር ፊት ዋጋ አያስገኝላቸውም። ለራሳቸው የሚፈልጉትን ብድራት በዚሁ ምድር ላይ አግኝተዋል። ለእግዚአብሔር ስላልሠሩ ነገር ግን በእግዚአብሔር ስም ለራሳቸው ስለሠሩ ከእርሱ ዘንድ ምንም ብድራት አያገኙም። ይህ የሰዎች አገልግሎት በእግዚአብሔር ፊት እስኪዳኝ ድረስ የአንዱን አገልግሎት ጥሩ ነው፣ የሌላውን ደግሞ ጥሩ አይደለም ብለን እንዳንናገር ያስጠናል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዮች ለግል ጥቅማቸው ብለው የወንጌል አገልጋይ በመሆን ሚኒስትሪ ወይም ቤተክርስቲያን ሊከፍቱ ይችላሉ። ሰዎች አገልግሎታቸውን ሲያዩ ወርቅ መስሎአቸው ሊታይ ይችላል። በእግዚአብሔር ዓይን ግን ሲታይ በወርቅ የተለበደ ገለባ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ውጩን ብቻ በማየት አቤት! የእገሌ አገልግሎት ማለት መልካም አይደለም (1ቆሮ.4፡5)።

እንግዲህ አገልጋዮች አገልግሎታቸው በመጨረሻው ቀን ከንቱ እንዳይሆንባቸው ዛሬ በምን ዓላማና እንዴት እያገለገሉ እንደሆነ ራሳቸውን መፈተሽ መልካም ነው። ብዙ ደክሞ ዋጋ ቢስ ከመሆን ከተሳሳተ ዓላመና አሠራር በቶሎ መመለስ ብልህነት ነው። የእግዚአብሔር አገልጋዮች ምንም ያህል መንፈሳዊ ሥራ የሚያሠራቸው የሚመስላቸው ችሎታና ዕውቀት ቢኖራቸው የእግዚአብሔር ሥራ የሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ ኃይል መሆኑን በመረዳት በእግዚአብሔር ላይ በመደገፍ እርሱ በሚሰጠው ኃይል ማገልገል ይገባቸዋል። አገልጋዮች በመሰላቸው መንገድ በራሳቸው ችሎታ ብቻ ከሚያገለግሉት "ብዙ" አገልግሎት ይልቅ በእግዚአብሔር ላይ በመታመን የሚሠሩት ትንሽ ነገር ዋጋ አለው።

በተጨማሪም አገልጋዮች እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ለእግዚአብሔር ክብር እንጂ ለራሳቸው ስውር ዓላማ ማገልገል የለባቸውም። እግዚአብሔር በአንደበት የሚነገረውን ሳይሆን በልብ ውስጥ ያለውን ዓላማ ስለሚያውቅ የአገልጋዮች የልብ ዓላማ ከግለኝነት የነጻ

መሆን አለበት። ለእግዚአብሔር ክብርን የማይሰጥ ማንኛውም አገልግሎት ይቃጠላል። አገልጋዮች ራሳቸውን ሲያገለግሉ ቆይተው እግዚአብሔርን እንዳገለገሉ በማስመሰል ከእርሱ ብድራት መጠበቅ እግዚአብሔርን እንደ ሰዎች ለማሞኘት መሞከር ነው። ይህ ደግሞ የማያዛልቅ ጥረት ነው። እንግዲህ በእግዚአብሔር ዘንድ ለምናገለግለው አገልግሎት ብድራት ለማግኘት መንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍና ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠን ማገልገል ይገባናል።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች በዚህ ዓለም ለሚያገለግሉት አገልግሎት በሰማይ ብድራት እንደሚያገኙ ተስፋ መኖሩ ለዛሬው አገልግሎታቸው ምን ፋይዳ ይኖረዋል? በምዕራቡ የአገራችን ክፍል *ካገኙት ይልቅ ተስፋ የሚያደርጉት ነገር ይበልጣል* የሚባል አባባል አለ። ይህ ማለት በእጅ የገባ ነገር ምን ያህል እንደሆነ መተመን ይቻላል፤ ነገር ግን ተስፋ የሚደረግ ነገር በእጅ ከገባው እንደሚበልጥ ይታመናል። በአዕምሮም የሚጠበቅ ነገር መኖሩ ተስፋ ተቀባዩ አንድ ቀን ተስፋውን እንደሚያገኝ በማሰብ ወደ ተስፋው ፍጻሜ የሚያደርሰውን ተግባር ያከናውናል የሚል መልዕክት አለው።

አንድ የእግዚአብሔር አገልጋይ እግዚአብሔርን በማገልገል የሚገኘውን ብድራት በሚገባ ከተረዳ እግዚአብሔርን ማገልገል ከማንኛውም ሥራ የበለጠ ክብር ያለው መሆኑን በመረዳት በአገልግሎቱ ይጸናል። እግዚአብሔርን ማገልገል የሚያስከፍለውንም ማንኛውንም ዓይነት መስዋዕትነት ለመክፈል የቆረጠ ልብ ይኖረዋል። ሙሴ እግዚአብሔርን ለማገልገል የወሰነው እግዚአብሔርን ማገልገል የሚያስገኘውን ብድራት በሚገባ ስለተገነዘበ ነበር።

> *ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ፤ ከግብጽ ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍ፡ እጅግ የሚበልጥ ባለጠግነት እንዲሆን አስቦአልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፤ ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና* (ዕብ.11፡24-26)።

ሙሴ በግብጽ ቤተመንግሥት ቢኖር የሚያገኘውን ዋጋና ከእግዚአብሔር ሕብዝ ጋር ዕድል ፋንታውን ቢያደርግ የሚያገኘውን ብድራት በሚገባ ያወዳደረ ሰው ነው። በግብጽ ቤተመንግሥት ውስጥ ቢኖር የንጉሥ የልጅ ልጅ ይባላል፤ በዚህም ክብርና ትልቅ ማህበራዊ ደረጃን ያገኛል። የግብጽንም ባለጠግነት ለራሱ ምቾት መጠቀም ይችላል። ራሱን ለማስደሰት ማድረግ የሚፈልገውን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ ዕድል ያገኛል። ሙሴ ከእነዚህ ነገሮች ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍን መረጠ። በቤተመንግሥት ሆኖ በሰዎች ዘንድ ክብር ከማግኘት ይልቅ ስለክርስቶስ መነቀፍ ትልቅ ክብር እንደሆነ ተረዳ። በግብጽ ምድር ከሚገኘው ደስታ ይልቅ ደግሞ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን፣ በምድረ በዳ መንከራተትን መረጠ። በሙሴ እይታ በግብጽ የሚገኘው ደስታ ኃጢአትና ጊዜያዊ ነው። እርሱ ግን የመረጠው ከጊዜያዊ ደስታ ይልቅ ዘላለማዊውን ደስታ ነበር። ሙሴ እንዲህ ዓይነት

ውሳኔ እንዲወስን የረዳው እግዚአብሔርን ማገልገል ያለውን ብድራት ትኩር ብሎ መመልከቱ ነበር። ይህን ውሳኔ ከወሰነ በኋላ ሙሴ ተመልሶ የግብጽን ምድር አልተመኘም።

አገልጋዮች በመንግሥተ ሰማያት የሚጠብቃቸውን ብድራት ትኩር ብለው ማየት ከቻሉ ለዓለማዊ ነገር አይንበረከኩም። ብዙ አገልጋዮች በአገልግሎት ከሚገጥማቸው አንዳንድ ተግዳሮቶች የተነሳ ዕድል ቢያገኙ እግዚአብሔርን ማገልገል ትተው ዓለማዊ ሥራ ቢሠሩ ይመርጣሉ። ከሙሴ ሕይወት ግን ዕድሉም ቢሰጥ እግዚአብሔርን ማገልገል ከማንኛውም ዓይነት ሥራ የተሻለ ዘላቂ ብድራት እንዳለው እንማራለን። ለአገልጋዮች በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ብድራት በሚገባ ቢገባን ዓለምን ንቀን ለእግዚአብሔር ቀንና ሌሊት እንድንተጋ የሚያደርገን ነው።

እግዚአብሔርን በማገልገል ሩጫቸውን የጨረሱ አገልጋዮችም ይህ ብድራት በእርግጥ እንደሚጠብቃቸው ተስፋ በማድረግ ይናፍቃሉ። ሐዋርያው ጳውሎስ እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ሞትን በሚጠባበቅበት ወቅት ይታየው የነበረው የሞት ስቃይ ሳይሆን ከሞት ወዲያ የሚጠብቀው የጽድቅ አክሊል ነበር።

> *በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል። መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፣ ሩጫውን ጨርሻለሁ፣ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል* (2ጢሞ 4:6-8)።

ጳውሎስ ሊቀበል ያለውን ብድራት በማሰብ በተስፋ የተሞላ ነበር። ምድራዊ ሕይወቱ ለወንጌል መስዋዕት በመሆን የሚያልፍ መሆኑን ተቀብሏል። ወደ ሕይወቱ ማጠቃለያ ምዕራፍ ላይ ከመድረሱም በፊት ቢሆን ጳውሎስ ከጌታ ጋር መሆንን ይናፍቅ ነበር (ፊልጵ.1:21-23)። ጳውሎስን ሞት አያስፈራውም ነበር። ወደ ጌታ ሲሄድ የሚጠብቀው ሽልማት መሆኑን ተረድቷል።

የእግዚአብሔር አገልጋይ ጌታን እንደሚገባ በሚያገለግልበት ወቅት ሞት አያስፈራውም። ለወንጌል ዋጋ እየከፈለ ያገለግላል ምክንያቱም እርሱን የሚጠብቀው ብድራት ትልቅ እንደሆነ ያውቃል። አገልጋይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ሊያገኝ ያለው ብድራት በምድር ላይ እግዚአብሔርን ያለምንም ፍርሃት እንዲያገለግል ብርታት ይሆነዋል። ሊመጣ ያለውን ብድራት በማሰብ ለወንጌል አገልግሎት እንደ ጌታ ፈቃድ ዋጋ ይከፍላል።

እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ ለእያንዳንዱ አገልጋይ የሚገባውን ብድራት ይሰጣል። እያንዳንዱ አገልጋይ ሕይወቱን ለጌታ ምን ያህል በመስጠት እግዚአብሔር በውስጡ ሆኖ ሥራውን እንዲፈጽም እንደፈቀደ ያን ቀን ይታወቃል። ጌታ ኢየሱስ "እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ" (ራእይ 22:12) በማለት የተናገረውን በማሰብ በአገልግሎታችን እንትጋ!!

## Bibliography


Flynn, Lesie B. *19 Gifts of the Spirit: Which do you have? Are you using them?* Wheaton, IL: Victor Books, 1980.

Mosley, Ernest E. *Priorities in Ministry.* Nashville, Ten: Convention Press, 1978.

Owen, W. Stuart. *The Ministry We Need.* London, England: Grace Publications Trust, 1997.

Turnbull, Ralpha G. *A Minister's Obstacles.* Westwood, NJ: Fleming H. Revell Company, MCMXLVI.